# ሐመር

ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

ሐመር ፲፩ኛ ዓመት ቁጥር ፫ ግንቦት / ሰኔ / ሐምሌ ፲፱፻፺፰ ዓ.ም

## ለአገር ዕድገት እና ልማት የቤተ ክርስቲያን ስትራቴጂያዊ አጋርነት



ንስር ሰራሪ ንጉሠ አዕዋፍ

## የመንፈስ ዕርገት ለርእይ ሥምረት በሣልሳይ ሺሕ ዓመት

(2000 ዓ.ም)



www.eotcmk.org

# ከአንባብያን ለአንባብያን

## የክርስትና ስማችን የተጸውዖ ስማችን ቢሆንስ

የግራኝ አሕመድ ወረራ ጦስ ከኾኑት አንዱ ስመ ክርስትናችን በዓለም በምንጠራበት ስም መተካቱ ነው:: ስለ ስመ ጥምቀት /ስመ ክርስትና/ አመጣጥ፣ ምንነትና አስፈላጊነት ከዚህ ቀደም በሐመር መጽሔት «የቤተ ክርስቲያን ህን ዕወቅ ዓምድ» ላይ ጠቃሚ ትምህርት ተላልፎአል:: በስማቸው የእምነት ማንነታቸውን የምንለያቸው ወገኖች እንዳሉ ይታወቃል:: እኛስ እንደ ቆየን ሥርዐትና ትውፊት የክርስትና ስማችን የተጸውዖ ስማችን ለምን አይሆንም? የልጆቻችንንስ ስያሜ ለምን በዚህ መልክ አይሆንም?

ስሜነህ መኰንን
ደብረ ታቦር

## «መጽሔቱና ጋዜጣው ሙሉ በሙሉ ኢትዮጵያዊ ይሁኑ!!»

ሐመር - ጥር/የካቲት 1998 ዓ.ም እትም ከሰሞኑ በረከት ዓምድ ላይ «የጥምቀት በዓል አከባበር በኢትዮጵያ» በሚል ርእስ የቀረበው ጽሑፍ ከብዛቱና ታሪክ ነክ ከመኾኑ አንጻር አሰልቺ ነው:: ይሁንና መጻፍና ለታሪክ መቀመጥ ያለበት ነውና ወድጄዋለሁ:: በዚህ አጋጣሚ ከተሳትፎርቄ መቆየቴን ለመግለጽ እወዳለሁ:: ምክንያቱም እናንተ የግእዙን ቁጥር /አኀዝ/ ስለ ተጠየፋችሁት ነው:: ለመኾኑ የግእዝ ቁጥር ገጽና ዓመተ ምሕረትን ከመጻፍ አያልፍም እንዴ? ብዙዎቻችን አንባብያን ስንወተውታችሁ የነበረው መጽሔታችሁንና ጋዜጣችሁን ሙሉ በሙሉ ኢትዮጵያዊ እንድታደርጓቸው ነበር:: ፍጹም ኢትዮጵያዊነትን ከመለከት መጽሔት ተማሩ:: ለዓለም አቀፍ ግንኙነት ሲባል የስልክ፣ የመልእክት ሣጥን ቁጥርና ኢ-ሜይል ካልኾነ በስተቀር የዐረብኛው አኀዝ በመለከት መጽሔት ውስጥ ቦታ የለውም:: በጣም የሚገርመው የምትጠቅሱልን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ እንኳን በዐረብኛው አኀዝ /Arabic Numeral/ ቢሆንም በእጃችን ያለው መጽሐፍ ቅዱስ ግን በግእዝ አኀዝ የተጻፈ ነው::

ዶ/ር ዘርፉ መልአኩ
አ.አ

## «እንግሊዝኛ በዛ»

ከዚህ ቀደም በሐመር መጽሔት ልዩ ልዩ ዓምዶች ላይ በሚወጡ ጽሑፎች ውስጥ የእንግሊዘኛ ቃላት እንደሚበዙ የአንባቢ አስተያየት ተሰጥቶ ነበር:: ይሁንና ችግሩ ከመስተካከል ይልቅ እየሰፋ መምጣቱን በኅዳር/ ታኅሣሥ 1998 ዓ.ም ሐመር መጽሔት እትም በተለይም ወቅታዊ ጉዳዮችና ሐመረ ሕይወት ዓምድ ታዝበናል:: አካሄዱ የቋንቋችንን ክብር ይነካል፤ ወደድንም ጠላንም ቋንቋችን የሌላን ቋንቋ ድጋፍ አይሻም:: አሁን ለምሳሌ: - «Counselling» የሚለው ቃል አንድ ጊዜ ሳይበቃችሁ እንዲያ በተደጋጋሚ መጠቀም አስፈላጊ ነበርን? በምትኩ የግእዝ ቃል ብትጠቀሙ ትውልዱንም ቋንቋ ማስተማር ነበር:: ደግሞም እኮ መጽሔትዋ እንግሊዝኛ ቋንቋን የማይናገሩ፣ የማይሰሙና የማያነቡ አባቶቻችንና እናቶቻችንም ጭምር ናት:: እንግዲህስ ልብ አግኝታችሁ እስከታደምጡን ድረስ ከማሳሰብ አናቋርጥም:: በተረፈ የወቅታዊ ጉዳይ ዓምድ ተከታታይ ጽሑፎች ከሐዘናችንና ከትካዜያችን አውጥተው አንጀታችንን ያራሱ ናቸው:: አይዞን::

- ብሥራተ ገብርኤል - ባሕር ዳር
- ኃይለ ኢየሱስ - ዋድላ ወረዳ

## «ዘ ዳ ቪንቺ ኮድ»ን ምላሽ ልንሰጥበትና ልንቃወመው ይገባል

ሰሞኑን በመረጃ መረብ እየተሠራጨ ያለው ልብ ወለድ ጽሑፍ አሳዝኖኛል፤ አስለቅሶኛልም:: ይሁንና ዲያብሎስ ሐሰተኛ፥ የሐሰትም አባት ነውና ሐሰትን ከራሱ አንቅቶ ይናገራል:: ዮሐ.8፥44:: ዲያብሎስን በግብሩ የመሰለው ዳን ብራውን የተባለው ደራሲ *«ዘ ዳ ቪንቺ ኮድ»* በሚል ርእስ የጻፈው ልብ ወለድ መጽሐፍ በክርስትና ላይ አዲስ ወፍ ዘራሽ ትምህርት ለማምጣት የታቀደ ይመስለኛል:: ለእኛስ ግድየለም፤ የነገ ተረካቢ ልጆቻችን ግን በሚቆያቸው ታሪክ ድጡ እንዳይበዛባቸው የዲያብሎስን ሤራ ከወዲኹ ልና ሳውቃቸው ይገባል:: ስለሆነም ማኅበሩ በተለያዩ የኅትመት ውጤቶቹ ለዚህ ዓይነቱ ክሕደት ተገቢውን ምላሽ እንዲሰጥበት አሳስባለሁ::

ዮሴፍ ታምራት
ጨፋ ሮቢት


# በልደታ እንገናኝ

አዲሱ የቅዱሳት መጻሕፍት እና የንዋያተ ቅድሳት ማከፋፈያችን አዲስ አበባ ማኅደረ ስብሐት ልደታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት በቅርቡ ሥራ ይጀምራል::

በጦር ኃይሎች፣ አየር ጤና፣ ሜክሲኮ፣ መካኒሳ፣ ላፍቶ፣አብነት እና አካባቢው የምትገኙ ሁሉ በየአቅራቢያችሁ በከፈትነው ማከፋፈያ ትገለገሉ ዘንድ እንጋብዛለን::

*በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክን የሰንበት ት/ቤቶች ማ/መምሪያ*
*ማኅበረ ቅዱሳን*


**የሐመር መጽሔትና የስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ደንበኛ ይሁኑ**

| | ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ | | ሐመር መጽሔት | |
|---|---|---|---|---|
| | የ6 እትም | 12 እትም | የ6 እትም | 12 እትም |
| ለአዲስ አበባ | 12.00 | 24.00 | 25.00 | 50.00 |
| ለክፍለ ሀገር | 12.00 | 24.00 | 25.00 | 50.00 |
| አፍሪካ | 9 ዶላር | 18 ዶላር | 12 ዶላር | 24 ዶላር |
| አውሮፓና መካከለኛው ምሥራቅ | 12 ዶላር | 24 ዶላር | 15 ዶላር | 30 ዶላር |
| አሜሪካና ሩቅ ምሥራቅ | 15 ዶላር | 30 ዶላር | 18 ዶላር | 36 ዶላር |

ለማኅበረ ቅዱሳን ልማት ተቋማት የባንክ ሂሣብ ቁጥር 81164 ሥላሴ ቅርንጫፍ
Mahibere kidusan Lemate Tequamat
አድራሻዎንና የከፈሉብትን ደረሰኝ ኮፒ በመልእክት ሣጥን ቁጥር 80078 ይላኩልን
ወይም በ E-mail Mk_ distribution @ Yahoo.com

ይህ እያገባደድነው የመጣነው የ1998 ዓ.ም፣ መጪው 1999 ዓ.ም. ለእኛ ለኢትዮጵያውያን ብዙ ትርጉም ይኖራቸዋል:: ይኸውም አንድን ሙሉ ክፍለ ዘመን አጠናቀን አዲሱን ክፍለ ዘመን /2000 ዓ.ም/ ለመቀበል የምንዘጋጅበት፣ ያለፈውን ክፍለ ዘመን አዎንታዊ እና አሉታዊ ገጽታ የምናይበት፣ ለመጪው ካሁኑ የምንተልምበት እጅግ ታሪካዊ ጊዜ ላይ እንገኛለን::

የበለጸጉ ሀገራት በእጃቸው ያለውን መልካም ዕሴት ሁሉ በተገቢው ሁኔታ እየተጠቀሙበት አሁን ላሉበት የዕድገት ደረጃ ደርሰዋል:: ለኢንዱስትሪያዊ አብዮት የእንግሊዝ የእምነት ተቋማት በዘውዳዊው እና ፓርላማዊ የመንግሥት ሥሪት መሐል ዘመናዊ መንገድ የማሳየት ሚና እንደ ተጫ ወቱ ሁሉ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አሁን ልንሸጋገረው ባልነው ክፍለ ዘመን የኋላ ሒደቷን፣ የመጪውን ማኅበረሰባዊ የዕድገት ደረጃ እና ተለዋዋጩን ዓለም አቀፋዊ ሁኔታ ከግንዛቤ ውስጥ ባስገባ መልኩ በአገሪቱ የልማት ዕቅድ ቀረጻ እና ትግበራ ብሉም አዳዲስ ገንቢ ሐሳቦችን የማፍለቅ ሚናዋን መጫወቻዋ ወሳኝ ወቅት ላይ ትገኛለች:: በተለይም የመጪው ክፍለ ዘመን ፈታኝ ሁኔታዎች ተብለው የሚጠቀሱት ድህነት፣ ተስማሚና ዘላቂነት ያለው የአካባቢ ጥበቃ አለመኖር፣ሽብ ርተኝነት፣የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መስፋፋትና የመሳሰሉ ት ዐበይት መንፈሳዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚ ያዊ ችግሮች ለአገሮች ዕድገት ማነቆዎች እየኾኑ መምጣታ ቸው የተገለጠ እውነት ነው::

የእኒህ ፈርጀ ብዙ ችግሮች ጦስ ከአዳጊው ዓለም አልፎ ለበለጸጉትም እንደ ሚተርፍ ስለሚታወቅ በልማት የገፉት አገሮች ጭምር በኅብረተሰቡ ዘንድ ሰፊ መሠረት ከያዘ ተቋም (እንደ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን) ጋር በትብብር መሥራት የብዙ የልማት ሒደት ችግሮች መፍቺያ ቁልፍ እንደ ሆነ ከተገነዘቡ ቆይተዋል::

ስለሆነም አባቶች ጳጳሳት፣ አገልጋይ ካህናት፣ ምእመናን፣ መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት፣ የሲቪክ እና ሞያ ማኅበራት በቅን መንፈስ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሀገሪቱ ዋነኛ የልማት አጋር መሆኗን ከልብ በማመን፣ የነበሯትን፣ ያሏትን ዘርፈ ብዙ ዕሴቶችንና መልካም ጅምሮችን በማዳበር፣ በቀጣይም ለዕድገት እንቅፋት የሆኑ አለመግባባቶችን ሁሉ ተደማምጦ በመፍታት አዲሱን ክፍለ ዘመን በርእይ ሥምረት፣ በመንፈስ ዕርገት ለመቀበል ተቀ ናጅተው በአንድ ጊዜና በአንድ ላይ መነሣት ይኖርባቸዋል ::

/ወቅታዊ ጉዳዮች/


ዋና አዘጋጅ - ዲያቆን ዳንኤል ክብረት
ም/ ዋና አዘጋጅ - አሉላ ጥላሁን

ሪፖርተር - ዲያቆን ደረጀ ጅማ

ኮምፒዩተር ዲዞይን - ወይንሸት ወጉ
ኮምፒዩተር ጸሐፊ - ጸዳለ ሁንዴሳ
- ገነት ግርማ



E-mail: eoc-m-kidusan@ethionet.et
www.eotc-mkidusan.org
ስልክ 011-1-242753
011-1-225729
መ.ሣ.ቁ 80078
አዲስ አበባ


«ማኅበረ ቅዱሳን»

እግዚአብሔር ያከበራቸው
የነቢያት፣የሐዋርያት፣የጻድቃን፣ የሰማዕታት
በአጠቃላይ የቅዱሳን ገድል፣ትሩፋትና አማላጅነት
የሚዘከርበት በመሆኑ
ይህን ስያሜውን አግኝቷል::


ሐመር
፲፬ኛ ዓመት ቁጥር ፫
ግንቦት/ሰኔ/ሐምሌ ፲፱፻፺፰ ዓ.ም


# ይዘት


**የማኅበሩ መልእክት**
- የአበው የጽሑፍ ዘመን ይደገም......................፪

**ደብዳቤዎች**......................................................፫

**ወቅታዊ ጉዳዮች**
- ለሀገር ዕድገትና ልማት የቤተ ክርስቲያን ስትራ ቴጂያዊ አጋርነት..........................................፭
- እምነት እና እምነትን የሚያቀዘቅዙ ነገሮች..........፲

**ትምህርተ ሃይማኖት**
- ነገረ ድኅነት በመጽሐፈ ቅዳሴ..............................፲፫
- ተሠግዎተ ቃል ..................................................፲፬

**ኪነ ጥበብ**
- ደባ ተውኔት እና የፍቅረ ሥላሴ ሒስ....................፲፯
- «ዘ ዳ ቪንቺ ኮድ» በመንፈሳዊ ዐይን ሲገመገም ..................................................፳

**እናስተዋውቃችሁ**
- መካነ ሥላሴ ........................................................፳፪
- ስምያን ዘዓምድ ..................................................፳፬

**ክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ**
- ቅድስና እና ፈለገ ቅዱሳን በኢትዮጵያውያን መንፈሳዊ፣ ማኅበራዊ፣ፖለቲካዊና ምጣኔ ሀብታዊ ሕይወት ውስጥ..........................................................፳፯

**ሐመረ ሕይወት**
- ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመዋጋት ቤተ ክርስቲያን ያላት ሀብትና የሚጠበቅባት ድርሻ..............................፳፱

**ሥነ ኪን**
- ፍጥረትን ተመልከት..............................................፴፫

**እቡጊዳ - የግእዝ ቋንቋ ትምህርት**
- «ግእዝ በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች በምርጫ እንዲጠና ዕድል ይሰጠው::» ..............................................፴፬
- ካልአይ /ሁለተኛ/ አንቀጽ ......................................፴፭



በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ በማኅበረ ቅዱሳን የኅትመት ዝግጅት ማስተባበርያ ክፍል የሚዘጋጅ ትምህርታዊ መጽሔት::

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዐተ እምነትና ክርስቲያናዊ ትውፊት ጠብቆ የሚወጣ::

# የማኅበሩ መልእክት

*በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ፡፡*

# የአበው የጽሑፍ ዘመን ይደገም

ሰዎች በመንፈሳዊ፣ ማኅበራዊ፣ ሥነ ልቡናዊ ምርምር ሥራዎች ዙሪያ የተለያዩ ጽሑፎችን ጽፈው ራሳቸውን፣ ሕዝባቸውን፣ አገራቸውንና ዓለማቸውን ጠቅመዋል፡፡ ሥነ ጽሑፍ በሁሉም የዓለማችን ክፍል እየታየ ላለው ሁለንተናዊ ዕድገት ያበረከተው አስተዋፅኦ ቀላል አይደለም፡፡ በአንጻሩ በክፉዎች ክፉ ጽሑፍ ዓለማችን የደረሰባት መከራና ድቀት አይዘነጋም፡፡

ቤተ ክርስቲያንም የእግዚአብሔር ቤት ነችና መጽሐፋዊ ትምህርቷንና ሥርዐቷን፣ ክርስቲያናዊ ትውፊቷን፣ ሊቃውንቷን፣ አገልግሎቷንና ክብሯን የተመለከቱ ደገኛ ጽሑፎች ተጽፈውላታል፡፡ በታወቀ መነሻ ከ300-450 ዓ.ም ድረስ ያለው ጊዜ *«የቤተ ክርስቲያን አባቶች ወርቃማ የሥነ ጽሑፍ ዘመን»* ይባላል፡፡ ይኸውም ቅዱሳን ሊቃውንት ርትዕት ሃይማኖትን ለመግለጥ፣ አጽራረ ቤተ ክርስቲያንን ለማጋለጥና ለመገሠጽ በርካታ ጽሑፎችን ያዘጋጁበት ወቅት በመኾኑ ነው፡፡ ከዚህ በተቃራኒ በክሕደት የታወሩና በኑፋቄ የሰከሩ እኩይ ጸሐፍት ሐሰትንና ከንቱነትን በሚተፋ ብዕራቸው በቤተ ክርስቲያን ላይ ያሻቸውን ሲሉባት በእንቶ ፈንቶ የተሞሉ ጽሑፎችን በመጻጻፍ ያሳዘኗትም አልጠፉም፡፡ በጌታ *«የገሃነም ደጆች አይችሉአትም»* የተባለላት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ግን መሠረቷ የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ነውና አትነዋወጽም፡፡ ማቴ.16÷18፡፡

ይሁን እንጂ ሐቅና መንፈሳዊነት የጎደላቸው የትችትና ዘለፋ ጽሑፎች መውጣት ከኀልፈተ ዓለም በፊት ይቆማል ተብሎ ባይታሰብም ከቀድሞው በበለጠና በተደራጀ መልኩ አንሰራርቶ መቀጠሉ ብዙዎቻችንን ያሳዝነናል፡፡ አሚነ ሥላሴን የሚተቹ፣ የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት የሚክዱና ክብረ ቅዱሳንን የሚያናንቁ ጽሑፎች በዝተዋል፡፡ ሥርዐተ ቤተ ክርስቲያንን፣ ክርስቲያናዊ ትውፊትንና ክብረ ቤተ ክርስቲያንን እየተጻረሩ፣ የመንፈሳዊ አገልግሎት መዋቅሮችንና አገልግሎታቸውን እያጣጣሉ፣ መጻፍ በእውነትና በእምነት የሳቱ ሰዎች ተግባር ሆኗል፡፡

እነዚህን ጽሑፎች የሚቀፈቅፉት አሚነ ሥላሴ የሌላቸው አሕዛብና መጽሐፍ ቅዱስን እንደ ሥጋ ፈቃዳቸው የሚያጣምሙ መናፍቃን ብቻ ናቸው ብለን አንደመድምም፡፡ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሊፈጠር በሚችለው አለመግባባት ያኮረፉና ተነካን የሚሉ አገልጋዮች ለጽሑፎቻቸው ምላሽ ከሚሰጧቸው የግብር መሰሎቻቸው ጋር በመሆን ችግሩን እያበራከቱት ይገኛሉ፡፡ ዓለማውያን ጸሐፍቱም በአንባቢ ዐይን መግባት ሳልቻለ ጽሑፋቸው ማሻሻጫ ያደረጉት ይህንኑ ጉዳይ ሆኗል፡፡

ጽሑፎቹ መዳረሻ አድርገው የተጻፉበትን ዓላማ በአጽንኦት ስንመረምር የተለያዩ ምክንያቶችን አንግበው እናገኛቸዋለን፡፡ ትችትንና ዘለፋን ብቻ ዓላማና ግባቸው ያደረጉ ጽሑፎች አሉ፡፡ የሁሉ ፈጣሪና መጋቢ ከሆነው አምላክ ጀምረው በደሙ የመሠረታትን ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ከነ አስተምህሮዋ፣ ሥርዐቷና ትውፊቷ ጭምር ይተቻሉ፡፡ የቤተ ክርስቲያንን ንጹሕ አስተምህሮና ሥርዐት በዓለማዊ፣ በአሕዛባዊና በኑፋቄአዊ ጠባይዕ የመበረዝ ዓላማም አላቸው፡፡ በተለይ ምእመኑን ከርትእት ኦርቶዶክሳዊ ሃይማኖቱ በማደናገርና በማጠራጠር ወደራሳቸው አማሌቃዊ ድንኳንና መናፍቃዊ አዳራሽ ለማስኮብለል ተብለው የሚጻፉት ጽሑፎች ግን ብዙ ናቸው፡፡

በየወቅቱ ለሚወጡ ፀረ ቤተ ክርስቲያንና ፀረ ሊቃውንት ለኾኑት ጽሑፎች ምላሽ በመስጠት ረገድ ያለውን ዘገምተኛ አያያዝ የገመቱ አጽራረ ቤተ ክርስቲያንም የልብ ልብ ስላገኙ እንዳሻቸው እየፈነጩ ነው፡፡ ባፍ በመጽሐፍ ከመተንኮስ አልፈው በአንዳንድ ቦታዎች የቤተ ክርስቲያንን ይዞታና ጥንታውያኑ ሕንጻ አብያተ ክርስቲያናት ጭምር «የኛ ነበሩ» ማለት ጀምረዋል፡፡

በፈቃደ እግዚአብሔርና በአባቶቻችን ጽናት ተጠብቆ የቆየው የቤተ ክርስቲያናችን ኦርቶዶክሳዊ ትምህርት፣ ሥርዐትና ትውፊት ለመጭውም ትውልድ ያለእንከን መተላለፍ የሚችለው የሚመለከታቸው አካላት ዛሬ በሚያደርጉት የማስተማር፣ የማጽናትና የጥበቃ አገልግሎት ነው፡፡ ለችግሩ ቃላዊ ምላሽ ብቻውን በቂ አይኾንም፡፡ በቃል ከሚደረገው ትምህርትና ስብከት በላይ የጽሑፍ ሥራዎች ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ የተጣሩ የጽሑፍ ሥራዎች በተለያዩ ቦታዎች ወደሚኖሩ ምእመናን የመድረስ ሰፊ ዕድል ስላላቸው አስፈላጊውን ሁሉ መሥዋዕትነት ከፍሎ ምእመኑ የቤተ ክርስቲያኑን ንጹሕ ትምህርት፣ ሥርዐትና ትውፊት እንዲረከብ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ዛሬ ለሕዝበ ክርስቲያኑ ጠብቀን ልናስረክበው ያልቻልነውን ነገ ከየትም አምጥተን ልንሰጠው አንችልም፡፡ በዚህም ተጎጂ የሚኾነው ሁሉም ነው፡፡

ለእግዚአብሔር መንጋ የማይራሩ ጨካኝ ተኩላዎች በየቦታው ስለ ተነሡ ጥንቃቄ የተሞላበት መንጋን የመታደግ አገልግሎት ያስፈልጋል፡፡ የሐዋርያውም ማስጠንቀቂያ ይህ ነው፡፡ - *«በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቁአት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ፡፡* ከሄድሁ በኋላ *ለመንጋው የማይራሩ ጨካኞች ተኩላዎች እንዲገቡባችሁ ደቀ መዛሙርትንም ወደ ኋላቸው ይስቡ ዘንድ ጠማማ ነገርን የሚናገሩ ሰዎች በመካከላችሁ እንዲነሡ እኔ ዐውቃለሁ፡፡»* ሐዋ.ሥራ.20÷28-30፡፡

ከእግዚአብሔር ዘንድ ለተሰጠች ርትዕት ኦርቶዶክሳዊ ሃይማኖት ታማኝ የነበሩ አባቶቻችን በዘመናቸው ለተነሡ የአሕዛብና የመናፍቃን ጽሑፎች የማያዳግም ምላሽ ሰጥተው የቤተ ክርስቲያንን የውስጥና የውጪ ጠላቶች ዝም አሰኝተዋል፡፡ ከመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ጋር ፈጽመው የተዋደዱት የአበው ጽሑፎች ዛሬም ድረስ የመናፍቃንንና የአሕዛብን አንገት የሚያስደፉ ሲሆኑ የቤተ ክርስቲያንም የአስተምህሮቷ መሠረቶች ናቸው፡፡ ለምሳሌ የእስክንድርያ ፓትርያርክ የነበረው ታላቁ ቅዱስ አትናቴዎስ አርዮሳውያንን በቃልና በጽሑፍ በማሳፈር የታወቀ ከመሆኑም በላይ ለቤተ ክርስቲያን ታላቅ ሥራ ሠርቷል፡፡ የእዚናንዙ ቅዱስ ጎርጎርዮስ በዚህ ተደንቆ *«የቤተ ክርስቲያን ዓምድ»* ሲለው የቂሣርያው ቅዱስ ባስልዮስ *«ለቤተ ክርስቲያን ሕማም ከእግዚአብሔር የተሰጠ ሐኪም»* ብሎታል፡፡ በቃልና በጽሑፍ ብቻ ሳይሆን ሕይወትን ሊያስከፍል በቻለ የሰማዕትነት ጉዞ ውስጥ አልፈው የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት፣ ሥርዐትና ትውፊት ሲጠብቁ ምእመናንንም ከጨካኝ ተኩላዎች ታድገዋል፡፡ ቅዱስ እገናጤዎስ ለአናብስት ሊጣል እየተወሰደ ሳለ ለጥቂት ጊዜ ዕረፍት ባደረገባት ሰማርያ ሆኖ ክርስቲያኖችን የሚያጽናና፣ ኑፋቄን የሚቃወምና አላውያን ያካሂዱት የነበረውን ግፍ የሚያወግዝ ጽሑፍ ጽፏል፡፡ በትምህርቱ የጸኑ ክርስቲያኖችም ቤታወጀባቸው ስደት የተነሣ በዱርና በገደል እየዞሩ የእግዚአብሔርን ቤት አነጹ፡፡ በግፍ አገዳደል እየተገደሉ ሕያው ታሪክ ሠሩ፡፡ የተመቻቹ የጽሕፈት ቁሳቁሶችና ሁኔታዎች በሌሉበት ዘመን ቢኖሩም አያሌ *መጻሕፍትን በእንባቸው ባራሱት ቀለምና በደማቸው ጻፉ፡፡*

በተመሳሳይ መልኩ ዛሬም ትችትን፣ ብረዛን፣ ማደናገርን፣ ማጠራጠርንና ከኾነላቸው ደግሞ መንጠቅን ግባቸው አድርገው ለሚጻፉ ለነዚህ ጽሑፎች እስከ ዛሬ የተሰጠ ምላሽ የለም ለማለት አይቻልም፡፡ በቁጥር ከበዙት የክፉት ጽሑፎች ብዛት አንጻር ግን ወቅታዊ፣ ተገቢና የተባበሩ ምላሾች በበቂ ሁኔታ መስጠቱ ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል፡፡

በሌላ በኩል የትኛውም ሰው የመረጠውን እምነት የመከተል ሕገ መንግሥታዊ መብት በተጠበቀበት አገር ውስጥ የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት፣ ሥርዐትና ትውፊት እየተቹ መጻፍ ምንም ዓይነት መንግሥታዊ እርምጃ የማያስወስድ ከሆነ ነገሮች ከዚህ በላይ የከፉ ይሆናሉ፡፡ አሕዛብና መናፍቃን በቃልና በጽሑፍ የሚያካሂዱትን ትችት፣ ብረዛ፣ ማጠራጠርና ማስኮብለል ተከታትሎ ማስቆም ካልተቻለ የነገው ታሪክ ሌላ ይሆናል፡፡

ስለዚህ ሕግ አስፈጻሚ አካላትም ቢሆኑ በምእመናንና በቤተ ክርስቲያን ላይ ለሚነሡት የመተቸት፣ የማደናገርና የመበረዝ ዘመቻዎች ትኩረት ሰጥተው የድርጊቱን ፈጻሚዎች እርምጃ ሊወስዱባቸው ይገባል፤ እየተጣሰ ያለው ሃይማኖታዊ ብቻ ሳይሆን ሕገ መንግሥታዊ መብት ጭምር ነውና፡፡ ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን ልጆች የሆንን ሁሉ «አይመለከተንም» ሳንል ከችግሩ አኳያ ተፈላጊውን አገልግሎት በቀናነት ለመፈጸም ተባብረን መነሣት ይኖርብናል፡፡

ወስብሐት ለእግዚአብሔር



www.eotcmk.org

## የአገልግሎት እጃችሁ አይጠር

*የሐመር መጽሔትን በመከታተል የቆየኹ ቢኾንም ይህችን አስተያየት ስጽፍላችሁ ግን የመጀመሪያዬ ነው:: ባለፉት ሁለት እና ሦስት እትሞች የወጡት የሐመር መጽሔት ዝግጅቶች ቤተ ክርስቲያናችን በአገራችን ማኅበራዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ያበረከተችውንና መጫወት የምትችለውን ሚና የሚያስገነዝቡ በመኾናቸው ይበል የሚያሰኙ ናቸው፤ ቤተ ክርስቲያናችንን በወጉ የማያውቋትን ሁሉ ራሳቸውን እንዲፈትሹ የሚያነሣሣ ነው:: በሌላ በኩል የምጠሰጣችሁ አስተያየት በተለይ ከአገሩ ወጥቶ በስደት የሚኖረውን ሕዝብ ለማገልገል የአገልግሎት እጃችሁ ረዘም ይበል የሚል ነው:: በቤተ ክርስቲያናችን የሚታተሙ መጽሔቶች፣ ጋዜጦችና መጽሐፎች ለእኛ የሚደርሱበትን መንገድ አመቻቹ:: በአጠቃላይ በአገልግሎታችሁ መንፈሳዊ እርካታ የምናገኝ በመኾኑ በርቱ፤ ረድኤተ እግዚአብሔር አይለያችሁ እላለሁ::*

*ዲያቆን ብዙአየሁ በላይ*<br>
*ጅቡቲ ምሥራቀ ፀሐይ*<br>
*ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን*

## *ደባ ተውኔት ብዙ መንፈሳዊ ፋይዳ አለው!!*

በ14ኛ ዓመት ቁጥር ሁለት መጋቢት/ሚያዝያ 1998 ዓ.ም እትም ኪነ ጥበብ ዓምድ *«ደባ ተውኔት መንፈሳዊ ይዘትም ኾነ ፋይዳ ይጎድለዋል»* በሚል ርእስ በፍቅረ ሥላሴ የቀረበውን የዘገየ ሂስ አንብቤዋለሁ:: ተውኔቱንም ተመልክቼዋለሁ:: በእውነቱ ፍቅረ ሥላሴ የሰጡት አስተያየት አስገራሚና አሳዛኝ ነው፤ የብዙዎችን አስተሳሰብም ያማከለ አይደለም:: ለመኾኑ እርሳቸው መንፈሳዊ ይዘትና ፋይዳ ሲሉ የቤተ ክርስቲያንን ችግር መግለጥን አያካትት ይሆን? በበኩሌ ከተውኔቱ የወሰድኳቸው ቁም ነገሮች፦ ወደፊት በሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ውስጥ መስተካከል ያለባቸውን ጉዳዮች፣ የቤተ ክርስቲያንን የውስጥ ጠላቶች እስከ መጨረሻው ጸንቶ መቋቋምንና በፈተና አለመበገርን ናቸው:: እነኝህ ቁም ነገሮች ደግሞ በራስ ጥበብ ሳይሆን በጥበበ እግዚአብሔር ሊከናወኑ እንደ ሚገባቸው ተውኔቱ በብዙ መንገድ ያስረዳል:: ይህ የእኔ ብቻ ሳይኾን ተውኔቱን የተመለከቱት ሁሉ የሚገነዘቡት መኾኑን ፍጹም አምናለሁ:: ከዚህ አኳያ ፍቅረ ሥላሴ ሂሳቸውን ከመሰንዘራቸው በፊት የተመልካቹን ስሜትና ግንዛቤ በደንብ ሊያጤኑ ይገባ ነበር:: ይልቁንም ወደፊት በመሰል ሥራዎች ላይ የሚሰጡ ሂሶች ጥንቃቄና ማስተዋል ቢታከልባቸው ለቤተ ክርስቲያናችን ሥነ ጽሑፍ ዕድገት፣ ለተዋንያኑ ሞራል መጠበቅ ያግዛል:: ይልቁንስ ከፍቅረ ሥላሴ ሂስ ቀደም ብሎ በጥር/ የካቲት 1998 ዓ.ም እትም ላይ በዲያቆን ኤርሚያስ በዛብህ የቀረበው የደባ ቴአትር ቅኝት ብዙዎቻችንን የማረከ በመኾኑ ቴአትሩ ከአዲስ አበባ ውጭ የሚታይበት አልያም በቪድዮ ካሴት፣ በዲቪዲ ወይም በቪሲዲ ተዘጋጅቶ የሚሠራጭበት መንገድ ቢመቻች መልካም ነው እላለሁ::

ወለተ ተክለ ሃይማኖት አ.አ<br>
ኂሩተ ኢየሱስ - አ.አ<br>
ተስፋ ሚካኤል - ደብብ ኦሞ<br>
ጸጋዬ ዘውዱ - ወልዲያ

### እግዚአብሔር በማኅበሩ መልእክት በኩል ልቤን ለይቅርታ አነሣሣው

በመጋቢት/ሚያዝያ 1998ዓ.ም ሐመር መጽሔት እትም *«አንድ ነገር እንቻል - ይቅር መባባል»* በሚል ርእስ የተላለፈውን የማኅበሩን መልእክት አንብቤ በእጅጉ ተሰማኝ፤ ኅሊናዬም ወቀሰኝ:: ይኸውላችሁ በአንድ አጋጣሚ ከጓደኛዬ ጋር ተቀያይሜ ነፀር:: የማኅበሩን መልእክት ካነበብኩ በኋላ ግን ቂም በቀልን ትቼ ከባልንጀራዬ ጋር ይቅር መባባል እንዳለብኝ ለራሴ ነገርኩት:: እግዚአብሔርም ረዳኝና ግንቦት 27 ቀን 1998 ዓ.ም በመድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ከሠርክ መርሐ ግብር በኋላ ከልጅትዋ ጋር ተገናኘን:: ይቅር ተባብለን ወደ የቤታችንም ተያይዘን ገባን:: ይገርማችኋል፥ ሌሎች ጓደኞቻችን ሊያስታርቁን ብዙ ጥረዋል፤ ለፍተዋል:: እግዚአብሔር ግን በሐመር መጽሔት የማኅበሩ መልእክት በኩል ልቤን ለይቅርታ አነሣሥቶታል:: ስለ እናንተ እግዚአብሔርን አመሰግነዋለሁ:: ሐመር መጽሔት በሥጋዊ ውም ይሁን በመንፈሳዊው ሕይወት መካሪና አስተማሪ እንዲሁም የሰውን ልብ ወደ በጎው የምታቀና ናት:: እኔ በምኖርበት የቤንሻንጉል ጉምዝ ክልላዊ መንግሥት ዋና ከተማ አሶሳ በጣም ጥሩ ሥርጭት አላትና በጀመራችሁበት ግፉበት እላለሁ::

*መሠረት ግርማ እና አልማዝ ለታ/አሶሳ/*

## ይቅርታ እና ክርስትና አይነጣጠሉም

ባለፉት ተከታታይ የሐመር መጽሔት እትሞች በአገራችን ወቅታዊ ኹኔታና በቤተ ክርስቲያናችን ሚና ላይ ያቀረባችኋቸው ጽሑፎች ወቅታዊና ተገቢዎች ናቸው፤ በሁሉም ኢትዮጵያዊ ዘንድ መነበብ ይገባቸዋል ባይ ነኝ:: በምሕረት፣ ይቅር ባይነትና ዕርቅ ጉዳይ ላይ አሁንም ሰፊ ውይይት መደረግ ያለበት ይመስለኛል:: «በሽታውን የደበቀ መድኃኒት የለውም» ይባላልና ሁሉም እውነትን ከሽንገላና ከወገናዊነት ነጻ ኾኖ በመመልከት ከልብ መወያየት ይኖርበታል:: እምነታችን ፍሬ እንዳያፈራ አንቆ የያዘው፣ እንደ ምስጥ ውስጥ ውስጡን በልቶ የጨረሰው ልባችን ለይቅርታ ዝግ በመኾኑ ነው:: በባህላችን በቀልና ሤራ ይሁንታ አግኝቶ ያደረ ጉዳይ ነው:: ልጆች ሳለን እንኳ ስናድግ በቤተሰባችን ላይ የደረሰውን ጥቃት እንድንበቀል እየተመከርን ነበር:: ይባስ ብሎ በኋላ ጊዜ ደግሞ ፈሪሃ እግዚአብሔር እየጠፋ በመምጣቱ የነበረውን የበቀለኛነት ባህል ያጠናከረው ይመስለኛል:: *«ቅራኔ የሚጠፋው ተቃራኒውን በማጥፋት ነው»* በሚለው ሰይጣናዊ ትምህርት ወገኑን ለማጥፋት ያልሞከረ ማን ነው? አሁንም በየደረጃው ችግሩ ያለ በመኾኑ የተሰጠው የይቅርታ ትምህርት እንዲህ በቅርብ ዘመናት ፍሬ ያፈራል ማለት አዳጋች ነው:: እንኳን የቅርቡ የምእተ ዓመቱ ታሪክ እየተነሣ ባለበት ሁኔታ ስለ ምሕረት፣ ይቅር ባይነትና ዕርቅ ብናወራ እግዘአብሔር ይታዘበናል:: ነገር ግን ምንም ቢኾን ይቅርታና ክርስትና አይነጣጠሉምና በግልጽ ተወያይተን አገራችንንና ሃይማኖታችንን ከክፉ እንጠብቅ እላለሁ::

*ሰይፈ ሚካኤል - መቐለ*<br>
*አስመላሽ ገብረ ሕይወት-ወግዲ*<br>
*በለጠ ዓለሙ- ሆሳዕና*

## *የሚያውቋችሁን ያስታግሥላችሁ*

*በግንቦት ወር መጀመሪያ ላይ ተከብሮ በዋለው በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክን የሰንበት ት/ቤቶች ማ/መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን 15ኛ ዓመት የምሥረታ በዓል ተገኝቼ ነበር:: በመርሐ ግብሩ በታደምኩበት ወቅት ደስታም ሐዘንም ተሰምቶኛል:: የአቡነ ጎርጎርዮስ ዐጸደ ሕጻናት ተማሪዎች በንጹሕ ልቡናቸው ባቀረቡት ጣዕመ ዝማሬ ከመደሰቴ የተነሣ አልቅሻለሁ:: አምላክ መዝሙራቸውን ምንኛ በፍቅር ወደ ይቀበልላቸው ይሆን? ማኅበሩ እኒህን መሰል ሕፃናት አሠልጥኖ ለዚህ ደረጃ በማብቃቱ የነገዋ ቤተ ክርስቲያን ተስፋ ብሩህ ኾኖ ይታያል:: በሌላ በኩል ደግሞ የተሐድሶ መናፍቃን ማኅበሩን «የፖለቲካ ድርጅት ነው» እያሉ በሐሰት በመክሰስ ህልውናውንና አገልግሎቱን የሚፈታተን ውንጀላ በማቅረብ ላይ መኾናቸውን አስመልክቶ በቀረበው ሪፖርት በእጅጉ አዝኜአለሁ:: ልዑል እግዚአብሔር የአቡነ ጎርጎርዮስ ዐጸደ ሕጻናት ተማሪዎችን አሳድጎ ቤተ ክርስቲያናቸውንና አገራቸውን በቅንነት ለማገልገል ያብቃቸው እያልኩ ህልውናችሁን የሚፈታተኑትንና አገልግሎታችሁን የሚያውኩትን ደግሞ ያስታግሥላችሁ እላለሁ::*

*ንግሥት ደግፌ- አ.አ*

## ለበቁ ሰዎች ብቻ ትመስለኝ ነበር

እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የሐመር መጽሔትን ውስጣዊ ይዘት በቅጡ አንብቤ አላውቅም ነበር:: መጽሔትዋ ቃለ እግዚአብሔርን ለጠነቀቁ ሰዎች ብቻ የምትዘጋጅ ትመስለኝ ነበር:: እግዚአብሔር በፈቀደ ጊዜ ግን ውስጣዊ ይዘቷን አጣጣምኳት:: በእውነቱ በየዕለቱ በሕይወታችን ዙሪያ ከሚደቀኑብን ፈተናዎች ራሳችንን እንጠብቅ ዘንድ መካር የኾነች መመሪያችን ኾና አግኝቻታለሁ:: በ14ኛ ዓመት ቁጥር ሁለት እትምዋ:- «የቅድስና ሕይወት በወጣትነት /በብቸኝነት/» «መንፈሳዊ የምክክር አገልግሎት ለጠባይ ለውጥ» በሚሉት ርእሶች የቀረቡት ጽሑፎች በኑሮዬ እያጋጠሙኝ ላሉ ፈተናዎች ከፍተኛ ምክራዊ ትምህርቶችን ለግሠውኛል:: የእኔ ቢጤ የኾኑ ሌሎች ወጣቶችም በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ለውጥ እንዲያመጡ ያግዛሉና መሰል ወቅታዊና አገራዊ ጉዳዮችን የሚዳስሱ ጽሑፎች ተጠናክረው ቢቀጥሉ እላለሁ::

*አሰፋ ጌታነህ*

*ደቡብ ወሎ- አማራ ሳይንት*

## ደንበኝነታችን ይቀጥል አልያም ያበቃ ዘንድ...

የሐመር መጽሔት የዘወትር ደንበኛ ነኝ:: በመጽሔቱ በተዘጋጁት ጽሑፎች ሁሉ ብዙ ዕውቀት አግኝቼበታለሁ፤ እኔ ተምሬ ሌሎችን አስተምሬበታለሁ:: በውጭ ሽፋን የፊት ገጽ ላይ የምታወጧቸው የቅዱሳት መካናት ፎቶዎች የአንባብያንን ዐይነ ኅሊና ይማርኩ ነበር:: በተለያዩ ዓምዶች ላይ በሚቀርቡት ጽሑፎች ብዙዎች ከክሕደት ወደ እምነት ተመልሰውበታል፤ ያለ ማወቅን ግርዶሽ ገፈውበታል:: የምታስተዋውቋቸውን ገዳማትና አድባራት በመሳለም የበረከታቸው ተካፋይ የኾኑ አያሌ ናቸው:: እኔ በራሴ አንዱን እትም ሁለት፣ ሦስት ጊዜ መላልሼ አነበው ነበር:: ግና ምን ያደርጋል... በ14ኛ ዓመት ቁጥር ሁለት መጋቢት/ሚያዝያ 1998 ዓ.ም ያወጣችሁት እትም ግን ቀድሞ የነበረ መንፈሳዊ ይዘቱን ፈጽሞ የለቀቀ ነው:: እኛ የምንፈልገው ከሐዘናችን የሚያጽናናን እንጂ ስለ ፖለቲካውማ ጋዜጣው መጽሔቱ ገበያውን ይዞት የለም እንዴ!! እኔ ይህን እትም ከቀድሞዎቹ ጋር ለመደባለቅ እንኳ ከብዶኛል፤ እንዲያውም በመግዛቴም አዝኛለሁ:: የእትሙ የጽሑፍ ዝግጅቶች በስሕተት የቀረቡ ከኾኑ ወደ ልቡናችሁ ተመልሳችሁና ተስተካክላችሁ ደንበኝነታችንን እንድንቀጥል÷ ከድፍረትና ዓላማን ከመሳት ከኾነ ደግሞ ደንበኝነታችን ያበቃ ዘንድ ቁርጡን እንድትነግሩን እንሻለን:: እኔና ጓደኞቼ ተወያይተን ይህን ምክርና አስተያየት አቅርበንላችኋልና ተግባራዊ ምላሻችሁን እንጠብቃለን::

*/በስልክ የተሰጡ ሁለት አስተያየቶች/*

## እውነታውን እያወቃችሁ የዋሁን ምእመን ባታደናግሩ...

የመልእክቴ ዋናው ጉዳይ በሐመር መጽሔት 14ኛ ዓመት ቁጥር ሁለት መጋቢት/ሚያዝያ 1998 ዓ.ም እትም ወቅታዊ ጉዳዮች ዓምድ:- «ወቅታዊው የቤተ ክርስቲያን አገራዊ ሚና» በሚል ርእስ በአቶ ፍቅረ ሥላሴ አርአያ በቀረበው ጽሑፍ ላይ ያተኩራል:: ይህ ጽሑፍ:- «እውን ሐመር የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ሰባኪ ወይስ ሌላ ሽፍን ተግባር አላት?» የሚል ሐሳብ አጭሮብኝ አእምሮዬን ዕረፍት ነስቶታል:: ቀድሞ ነገር ጸሐፊው ጽሑፋቸው የእርሳቸውን እንጂ የአዘጋጆቹን አቋም እንደ ማያንጸባርቅ ማሳሰብ ለምን አስፈለጋቸው? «እኔ የጽሑፉ አቅራቢ ለዚህ ጭፍን ያለ ድጋፍ ተጠያቂ /ተወቃሽ/ ነኝ» ለማለት ከኾነ ከእትሙ የማኅበሩ መልእክት ይዘት መነሣት ይቻላል:: የኾነው ኾኖ የቅድሚያ ማስተባበያው አዘጋጆቹን በ«አብዮታዊ ዴሞክራሲ ዐይን» እንዳናያቸው እሳቤ እንድንወስድ ከኾነ÷ ጥሩ:: ግን የማኅበሩን መልእክት ይዘት ምን ይሉታል? መልእክቱ «ይቅር መባባል እንቻል» ይላል በርእሱ:: ለመኾኑ ከማን ጋር፣ ለምን እና በምን ዓይነት ኹኔታ ነው ይቅር የምንባባለው? የሚገርመኝ ነገር÷ በእግዚአብሔር ስም በሚታተመው መጽሔት ሥር ያለምንም ሐፍረት ምእመናንን ለማደናገር የሚደረገው ሩጫ ነው:: ... በመጨረሻም በጽሑፉ የተካተቱና መልስ መስጠት የማያስፈልጋቸው÷ የማይረቡ የሲቪክ ትምህርቶች አሉበት:: በርግጠኝነት ለጽሑፉ አቅራቢ የማስተላልፈው መልእክት እውነታውን እያወቃችሁ የዋሁን ምእመን ባታደናግሩ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ በደሙ የዋጃትን ቤተ ክርስቲያን የፖለቲከኞች ዋሻና መደበቂያ ባታደርጓት፤ እውን ለሃይማኖትና ለአገር ታስቦ የተዘጋጀ ጽሑፍ ቢኾን እንዲህ ሊቀርብ ባልተገባው ነበር እላለሁ::

*ኪሩቤል*

*ከደብረ ሳሌም*

## «ጆሮ ያለው መስማትን ይስማ»

ለሐመር መጽሔት እንግዳ አይደለሁም:: ከ1985 ዓ.ም ጀምሮ በመደበኛ ኹኔታም ባይኾን መጽሔቷን እከታተላለሁ:: እጅግ ብዙ መንፈሳዊ ትምህርት አግኝቼአለሁ:: በእናንተም ሥራ ልዑል እግዚአብሔርን አመሰግነዋለሁ:: ለ15 ዓመታት ያህል የገጠማችሁን ልዩ ልዩ ፈተና በጸሎት፣ በትዕግሥት፣ በጽናት እና በእውነት ታግሣችሁ የዘለቃችሁት እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ቢኾን ነውና በርቱ እላለሁ:: ይህችን የመጀመሪያ ደብዳቤዬን የጻፍኩላችሁ በ14ኛ ዓመት ቁጥር ሁለት መጋቢት/ሚያዝያ 1998 ዓ.ም እትም ላይ ስለ ምሕረት፣ ይቅር ባይነትና ዕርቅ ያቀረባችሁት ዝግጅት ከምንም በላይ የውስጤን ምኞትና ሐሳብ ስለ ገለጠልኝ ነው:: በማኅበሩ የተላለፈውም የሰላም ጦማር ለእኛ ለክርስቲያኖች ቀርቶ ለሌሎች ወገኖቻችንም የማንቂያ ደወል ኾኖ አግኝቼዋለሁ:: በመስቀሉ ባደረገው ቤዛነት ምሕረትን ያደረገልን፣ ዕርቅን ያወረደልን፣ ሰላምን የሰጠን መድኃኔ ዓለም ክርስቶስ እንዲህ ዓይነቱን መልእክት ነው *«ጆሮ ያለው መስማትን ይስማ» ያለው::* ወገኖቼ÷ እስኪ በአገራችንና በዓለም አቀፍ ደረጃ የተገለጠውንና በዐይናችን ፊት ያለውን መከራ እናስተውል:: «አምላክ ሆይ÷ በፊትህ የምንለምን ስለ ብዙ ምሕረትህ ነው እንጂ ስለ ጽድቃችን አይደለምና ጆሮህን አዘንብለህ ስማ፤ ዐይንህን ገልጠህ ጥፋታችንንና ስምህ የተጠራበትን ከተማ /አገራችንን/ተመልከት»/ ዳን.9÷18/ እያልን አብዝተን እንጩኽ፤ እናልቅስ፤ እንጸልይ:: የሰላም አምላክ ሰላምን እንዲሰጠን፣ ከጥፋት እንዲታደገን፤ የፈሰሰው ደም እንዲደርቅ÷ ነባር ቂም በቀል እንዲርቅ ሁላችንም ሳንዘገይ የድርሻችንን እንወጣ::

*አዲስ ቤተ ማርያም*

*ቤቴል- አ.አ*

የማኅበረ ቅዱሳንን ገጸ ድር ይጎብኙ
www.eotc-mkidusan.org

# ለአገር ዕድገት እና ልማት የቤተ ክርስቲያን ስትራቴጂያዊ አጋርነት

ዲ/ን ታኘው ወልዴ /ኤም.ኤ. በኢኮኖሚ ፖሊሲ ማኔጅመንት/
ጌታቸው በቀለ /ቢ.ኤ. በልማት ጥናት/



*ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ፕሬዝዳንት የውጭ ርዳታ ሰጭ ድርጅቶች ልኡካንን በጽ/ቤታቸው ተቀብለው ባነጋገሩበት ወቅት*

## «ቤተ ክርስቲያናችን የድኾችንና የምስኪኖችን አቅም ለማጎልበት በየአካባቢው ያሉ አብያተ ክርስቲያናት በመተባበር ለሚያደርጉት ተነሣሽነትና አስተዋፅኦ ትኩረት ትሰጣለች::»

«የእግዚአብሔር መንፈስ በእኔ ላይ ነው፡ መልካም ዜናን ለድኾች እንዳበሥር ቀብቶኛልና፡ ለታሰሩትም መፈታትን፡ ለዕውሮችም ማየትን እሰብክ ዘንድ፣ የተጠቁትንም ነጻ አወጣ ዘንድ ልኮኛል::» ሉቃ. 4፡18::

«ይህን ጥቅስ ስንመለከተው ከእያንዳንዱ ሐረግ ብዙ ነገሮችን ማውጣት እንችላለን:: የእያንዳንዱ ሐረግ ትርጉም በቅዱስ መጽሐፍ ዘመን ስለ ነበረው ሁኔታ በትክክል ይጠቁማል:: እግዚአብሔር አምላካችን ይህን ለእኛ የነገረበት ምክንያት አለው:: ይኸውም ድሆችን፡ ልባቸው የተሰበረውን፡ የተማረኩትንና የታወሩትን እንድናስብ ነው:: ዛሬ ትኩረታችንን በአፍሪካ ስናደርግ የምንረዳው የመገለልና የመዘንጋት ደረጃ ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሣ በብሔራዊም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ድህነትን ለመቀነስና የሕዝቦችን ኑሮ ለማሻሻል ምንም የተደረገ ጥረት እንደ ሌለ ነው::

አፍሪካን እየገጠመ ያለው ችግር ለአህጉሩ አመቺ የሆነ፡ በአርአያነት የሚቀመጥ /የሚጠቀስ/ ለፕሮግራሞች፡ ለፖሊሲዎችና ለስትራቴጂዎች ስልት መፈለግ ነው:: መቋጫ ያጣው የሰው ልጅ ሰቆቃ በሰው ዕድገት ላይ የመጣውን ጫና እንዲሁም ያስከተለውን የፖለቲካ ውጤት ለመገመት፡ ለማሰብ እጅግ ያስቅቃል:: ፈተናው ችግሩን ከመጣቱ ኃይል ጋር አያይዘን እንድናተኩርበት ያደርገናል:: ሕዝባችን ራሳቸውን በማንቃቃት በአካባቢያቸው ያለውን ጉልበት ለልማት ለማዋል ተስፋ በመቁረጥ ላይ ናቸው:: ምክንያቱም ራሳቸውን በእኩልነት ከሚያስቀምጡበት ደረጃ ላይ አይደሉም፡ በፖለቲካም ግንኙነት ሁኔታዎችን ለመቆጣጠር አልቻሉም:: ከዚሁም የተነሣ አብዛኞቹ ዜጎቻችን ሕይወታቸውን ለማቆየት ብቻ በመታገል ላይ ናቸው:: ስለዚህ አፍሪካ ባለችበት አጣብቂኝ በነጻ ፍላጎትና በተጽዕኖ በመታቀፍና በመገለል፡ በትምህርትና በድንቁርና እንዲሁም በመኖር ዋስትና ማግኘትና በደህንነት መካከል ባሉ ቅራኔዎች ውጥረት ውስጥ ትገኛለች::

በተጨማሪም የሰውን ደኅንነት ለመጠበቅና ተገቢውን የሰውን ልጅ ልማት ለማስገኘት አመቺ ሁኔታዎችን ለመፍጠር በሚደረግ ጥረት፡ በመመጻደቅ በትዕቢት በተሞላ ተጻራሪ የዓለም አቀፍ ዕድገት መካከል ያሉ ቅራኔዎችም በርካታዎች ናቸው::

የአፍሪካ አህጉር የገጠሙትን እነዚህን አደጋዎችና የልማት ፈተናዎች ለመቋቋም ብዙ ተነሣሽነት ዐቅዳለች:: በተለይም ቤተ ክርስቲያናችን የድሆችንና የምስኪኖችን አቅም ለማጎልበት በየአካባቢው ያሉ አብያተ ክርስቲያናት በመተባበር ለሚያደርጉት ተነሣሽነትና አስተዋፅኦ ትኩረት ትሰጣለች::

ጌታ ሆይ፡ አፍሪካን በጸጋህ አድስ፡ ጌታ ሆይ፡ በጸጋህ ኅብረተሰባችንን ለውጥ:: እግዚአብሔር ሁላችንንም ይባርክ::»

*/ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ለ9ኛው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ያስተላለፉት መልእክት/*

## «በሌላ ኀይል ሊፈታ ያልተቻለው የዓለም ችግር በሃይማኖት እየተፈታ ነው:: . . . በክርስትና ሃይማኖት ብዙ የዓለም ሁኔታ ተለውጦአል::»

«በዓለም አብያተ ክርስቲያናት በኩል የተሰጠኝ ከባድ ሐላፊነት ከዓለም አቀፍ የሰላም ሰዎች ሁሉ ጋር እንድንንቀሳቀስ ያስገድደናል:: ያለንበትም ወቅት ለብቻ የሚኬዱበት ሳይሆን ከሌሎች ጋር በመደጋገፍ የሚኬዱበት ጊዜ ነው፡ ምክንያቱም ዓለም እንደ አንድ መንደር እየተቀራረበ የመጣበት ወቅት ነውና::

በመሆኑም ልዩነት እንደ ተጠበቀ ሆኖ የአንድነት አስፈላጊነት በሁሉም ዘንድ ታምኖበታል፡ ከመለያየት አንድነትን፡ ከመራራቅም መቀራረብን ለመፍጠር የጋራ እንቅስቃሴ ያስጠፈልጋል:: በእግዚአብሔር ፈቃድ የኢትዮጵያ ፓትርያርክና የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ፕሬዝዳንት እንደ መሆኔ የዓለም አቀፍ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ አባል ስለሆንሁ በዓለማችን ላይ ስለሚታዩት ችግሮች፦ የፍትሕ መጓደል፡ የጥላቻ ስሜት፡ መናናቅና አለመተማመን፡ የዘላቂ ሰላምና መረጋጋት መታጣት፡ ኤች. አይ. ቪ/ኤድስ፡ የፆታ መግባር ጉድለትና በዘር ልዩነት ላይ የተመሠረተ ቂምና ስለሌላውም ሁሉ ከዓለም አቀፍ አካላት ጋር መወያየትና አብሮ መሥራት ይጠበቅብኛል:: ይሁን እንጂ ብቻዬን ሳይሆን ወክለው የመረጡኝና በመመረጤ ደስ ያላቸው ሁሉ ትብብራቸው ያስፈልገኛል:: ትብብሩና ድጋፉም በሃይማኖት ላይ የተመሠረተ ጸሎት ነው:: ዛሬ ሃይማኖት በችግር ፈቺነቱ ተቀባይነትን እያገኘ የመጣበት ጊዜ ነው:: በሌላ ኀይል ሊፈታ ያልተቻለው የዓለም ችግር በሃይማኖት እየተፈታ ነው:: ይህም የሃይማኖት ምንጭ እግዚአብሔር በመሆኑ ነው:: ይልቁንም በክርስትና ሃይማኖት ብዙ የዓለም ሁኔታ ተለውጦአል::

ምክንያቱም ክርስትና ከሀሜትና ግፍ ነጻ የሆነ ሃይማኖት ነው:: በክርስትና ሃይማኖት ክፉን በክፉ፡ ዐመፅን በዐመፅ መቃወም በአጽንዖት የተከለከለ ነው:: ክርስትና ሰላም ነው:: «እርሱ ሰላማችን ነው» ተብሏልና:: /ኤፌ. 2፡14/::

ስለዚህ ለሰላም መሥራት ለክርስቲያናዊ ሕይወት መለኪያ ስለሆነ ክርስቲያኖች ሁሉ ለሰላም ግንባታ ቅድሚያን ሊሰጡ ይገባል:: ክርስትና የዕርቅ ሃይማኖት ነው:: ዕርቅ በአንድነት መኖርና መሥራት፡ ስለ ጋራ መብት በአንድነት መቆም ነው:: እውነተኛ ዕርቅ የሚጸናውም እውነትን በመናገርና ራስን ለፍትሕና ለሰላም ሐላፊ በማድረግ ነው::»

*/ከብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ የ14ኛ ዓመት በዓለ ሢመት መልእክት የተወሰደ/*



www.eotcmk.org

አሁን በምንኖርበት ዓለም ባደጉትም ኾነ በማደግ ላይ ባሉት አገሮች ዘንድ ልማት የየዕለቱ ቁልፍ የመወያያ አጀንዳ ከኾነ ሰነባብቷል:: የተባበሩት መንግሥታት የምእተ ዓመቱ የልማት ግቦች የኾኑትን ስምንት ነጥቦች /የከፋ ድህነትን እና ረኀብን ማስወገድ፣ የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን ለሁሉም ማዳረስ፣ የጾታ እኩልነትን መደገፍና የሴቶችን የመወሰን መብት ማስከበር፣ የሕፃናትን ሞት መጠን መቀነስ፣ የእናቶችን ጤና አጠባበቅ ማሻሻል፣ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ፣ ወባ... ወዘተ በሽታዎችን ለማስወገድ መታገል፣ የአካባቢ ጥበቃንና ክብካቤን በቀጣይነት ማረጋገጥ፣ ዓለም አቀፍ የልማት አጋርነትን ማስፋፋት/ መመልከቱ ልማት ምን ያህል ብሔራዊ ብቻ ሳይሆን ዓለም አቀፋዊም ጥያቄ እንደ ሆነ ለመረዳት ያስችለናል:: እነኝህ የምእተ ዓመቱ የልማት ግቦች የእያንዳንዱ ሀገር የልማት እንቅስቃሴ ከሀገሩ የማደግ ፍላጎት ብቻ የመነጨ ሳይሆን በዓለም አቀፉ ኅብረተሰብ ዘንድ የሚለካበት በመሆኑ ተከታታይ ጥረትን፣ አንድነትን፣ መቀራረብንና መደጋገፍን ይጠይቃሉ:: /UN Human Development Report, 2005./

ልማት ሲታሰብ ደግሞ ከኢኮኖሚያዊ አመለ ካከት */Economic growth model/* አንጻር ብቻ መታየት እንደ ማይገባው የሚሞ ግቱ የዘርፉ ተቋማትና ጠበብት አያሌ ናቸው:: ልማት ከኢኮኖሚያዊ ዘርፍ በተጨማሪ በባህላዊ፣ ሥነ ምኅዳራዊ፣ ማኅበራዊ እና ፖለቲካዊ መስኮች ያለው አንድምታ ከፍተኛ ነው:: ይኸውም ልማት:- ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ፣ ከኋላ ቀር ወደ ተሻለና ዘመናዊ የአነዋወር ዘይቤና ደረጃ መሸጋገር ነው፤ ልማት ፖለቲካዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊ፣ ባህላዊ እና ሞራላዊ ሽግግርን */Transformative and Liberating Process/* ሁሉ ይጨምራል:: በሌላ በኩል ልማት የአንድ ወቅት ክንውን ብቻ ሳይሆን ከትውልድ ወደ ትውልድ፣ ከክፍለ ዘመን ወደ ክፍለ ዘመን የመዝለቅ ባሕርይ መላበስ እንደ ሚገባው ይነገራል:: የዚህ ዓይነቱ የልማት ሒደት ደግሞ ***«ቀጣይነት ያለው ልማት»*** */Sustainable Development/* ይባላል::

ልማት በየዘመኑ የተለያዩ ፅንሰ ሐሳቦችን ይዞ ብቅ ብሏል:: ፅንሰ ሐሳቦቹ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ፍጻሜ በኋላ ዕውቅና ያገኙ ናቸው:: የመጀመሪያው ፅንሰ ሐሳብ እ.አ.አ በ1950ዎቹና በ1960ዎቹ አካባቢ የታወቀው ***«የቀጥተኛ ዕድገት»*** */Linear Stage of Development/* ፅንሰ ሐሳብ ነው:: ፅንሰ ሐሳቡ ማንኛውም ኅብረተሰብ ለማደግ ምዕራባውያን የተከተሉትን የዕድገት ፈለግ መከተል እንዳለበት ያትታል:: ኾኖም ይህ ፅንሰ ሐሳብ አዳጊ አገሮች የሚገኙባቸው ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊ እና ማኅበራዊ ተጨባጭ ሁኔታዎች ከምዕራባውያን የተለዩ በመኾናቸው ፅንሰ ሐሳቡ በራሱ ሙሉ እንዳልኾነ ብዙዎች ይስማማሉ:: ሁለተኛው ፅንሰ ሐሳብ ***«መዋቅራዊ ለውጥ»*** */Structural adjustment/* የተባለው ፅንሰ ሐሳብ ነው:: ይህ ፅንሰ ሐሳብ:- *«ልማት ሊመጣ የሚችለው በአሠራር ሒደት የማይመቹ መዋቅሮች በአዳዲስና ተጨማሪ መዋቅሮች ተተክተው ተቋማዊ መዋቅራዊ ለውጥ ዋና ዋና በኾኑ ምጣኔ ሀብታዊ ሴክተሮች ላይ ማምጣት ሲቻል ነው»* ብሎ ያምናል::

ሦስተኛው ፅንሰ ሐሳብ ***«ዓለም አቀፋዊ ጥገኝነት»*** */International Dependency/* በመባል ይታወቃል:: ይህ ፅንሰ ሐሳብ ከፍተኛ ዕውቅናን ያገኘው እ.አ.አ በ1970ዎቹ ውስጥ ነው:: *«ይኸውም በማደግ ላይ ያሉ አገሮች ኋላ ቀርነት ዋነኛ መንሥኤ ያደጉ አገሮች ጥገኛ መኾናቸው ነው»* ብሎ ያምናል:: በሌላ በኩል *«ባደጉና ባላደጉ አገሮች መካከል ያለው ኢ- ፍትሐዊ የንግድ ግንኙነት አገሮችን ለበለጠ ድህነት ዳርጓቸዋል»* ይላል:: አራተኛውና እ.አ.አ በ1980ዎቹ ውስጥ ከፍተኛ ዝና እያገኘ፣ በምዕራባውያን የበላይነት በሚመሩት እንደ የዓለም ባንክ እና ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት /IMF/ በመሳሰሉት ታላላቅ ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅቶች ግፊት እየተ ደረገበት ያለው የ*«Neo-Classical counter»* ፅንሰ ሐሳብ ነው:: ፅንሰ ሐሳቡ *«ዕድገትን ለማምጣት መልካም አስተዳደር፣ ነጻ ገበያ፣ ምጣኔ ሀብትና የመንግሥት ጣልቃ ገብነት የተቀነሰበት /Less State Intervention/ ፖሊሲን መከተል ያሻል»* ይላል::

ከላይ የተጠቀሱት ፅንሰ ሐሳቦች እንዳሉ ኾነው ለአንድ ኅብረተሰብ ዕድገትም ኾነ ድህነት ዐበይት የሚባሉ ሁለት ምክንያቶች አሉ:: እነዚህም ምጣኔ ሀብታዊ */Economic Factors/* እና ምጣኔ ሀብታዊ ያልኾኑ / Non *Economic Factors/* በመባል ይታወቃሉ:: *ምጣኔ ሀብታዊ ሁኔታዎች* የንዋይ ክምችት /Capital Accumulation/ ፣ ቁጠባ /Saving/፣ የመዋዕለ ንዋይ /Investment/ ፣ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም፣ ክህሎት፣ ፈጠራ፣ የጉልበት አጠቃቀም / Labor Intensive or Capital Intensive/ የመሳሰሉትን ይመለከታል:: በአንጻሩ ምጣኔ ሀብታዊ ያልኾኑ በመባል የሚታወቁት:- የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ከኢኮኖሚው ዕድገት ጋር ባልተመጣጠነ መልኩ መጨመር፣ የማኅበራዊ ደኅንነት ምክንያቶች፣ ፖለቲካዊና አስተዳደራዊ ሁኔታዎች፣ የፍትሕ ሥርዐቱ ይዞታ፣ የባህላዊ ዕሴቶች አጠቃቀም እና የእምነት አስተምህሮዎች ኃይልና ዋጋ የመሳሰሉትን ያካትታል:: ***Capa. newschool.edu/het/schools /develop.htm***

እኒህ የዕድገት ፅንሰ ሐሳቦችና የድህነት መንሥኤዎች የሚጠቁሙን አንድ መሠረታዊ እውነታ አለ:: ይኸውም ድህነት የሚመጣው አልያም፣ዕድገት የሚመዘገበውና ልማት የሚመነጨው በምጣኔ ሀብታዊ ችግር ሳቢያ ብቻ ሳይሆን ምጣኔ ሀብታዊ ባልኾኑ ምክንያቶች ጭምር እንደ ሆነ ነው:: ቀደም ሲል የነበሩት የምጣኔ ሀብት ጠበብት ድህነትን ከመሠረታዊ ፍላጎቶች /ከምግብ፣ መጠለያ እና ልብስ/ እጦት ጋር ብቻ ያገናኙት ነበር:: አሁን በምንኖርበት ዘመን ግን ድህነት የመሠረታዊ ፍላጎቶች እጥረት ብቻ ሳይሆን እርስ በርሳቸው የተቆላለፉና ተነጣጥለው የማይታዩ ***የመንፈሳዊና ቁሳዊ ሀብቶች ነዳይነት*** */Chains of material and spiritual poverty/* ውጤት እንደ ሆነ የሚያምኑ አሉ:: ስለዚህም ከድህነት ወጥመድ /Poverty trap/ ሰብሮ ለመውጣትና ልማትን በቀጣይነት ለማረጋገጥ ተደጋጋሚ የልማት ዘይቤዎች ከለሳና ጥናት ማድረግ /rethinking of the development model/ የግድ ኾኗል::

በመርሐ ልማቶቹ ዘዳግም ጥናት ሃይማኖታዊ ዕሴቶችና የእምነት ተቋማት ሱታፌ እንደ ርእስና መሠረት ካልተወሰደ በቀር ልማት:- ለዝቅተኛው የማኅበረሰብ ክፍል ደኅንነትና የተመጣጠነ የገቢ ክፍፍል እንዳችም የማይፈይድ፣ ሰብአዊ ክብርና ሞራላዊ ገጽታ የሌለው፣ ከብሩህ ተስፋ ይልቅ ጨለምተኛነትን የሚያሰፍን፣ የሥርዐተ ተፈጥሮን /Ecosystem/ ሚዛን የሚያዛባና አካባቢን የሚያራቁት የካፒታሊስት ርእዮተ ዓለም ሎሌ ኾኖ እንዳይቀር ይፈራል:: ይህ ደግሞ ማኅበራዊ አለመረጋጋትንና የተፈጥሮ ከባቢ መቃወስን በመፍጠርና በማባባስ በአጠቃላይ ምርቱ ዕድገት /Gross Domestic Product/ እና በሚካበተው ገቢ ብቻ የሚመጣውን ልማት ቀጣይነት እንዳ ይኖረው በማነቀፍ አያሌ ችግሮች እንዳይፈጥር ያሰጋል:: ከዚህ አኳያ የሰውን ሁለንተና /ሥጋ፣ ነፍስና መንፈስ/ የሚገዙ መንፈሳዊና ባህላዊ ዕሴቶች የላቀ ትኩረት ሊደረግባቸው እንደሚገባ ይመከራል:: እኒህ መንፈሳዊና ባህላዊ ሀብቶች ሥርዐታዊ በሆነ መንገድ ተጠብቀው የቆዩባቸው የእምነት ተቋማት ተልእኮዎች በአዎን ታዊነት ከተወሰዱ ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን ከማስመዝገብና ቀጣይነት ያለውን፣ በመ ልካም ዕሴቶች ላይ ተመሥርቶ የበለጸገ ሐቀኛ ልማት /Real and Value- Based Development/ በማረጋገጥ በኩል ስትራቴጂያዊ አጋርነት ሊኖራቸው እንደ ሚችል ይታመናል::

⌘ ⌘ ⌘

በዚህ አነስተኛ ጽሑፍ ውስጥ የሃይማኖትንና የልማትን መስተጋብር ምንነት እና አተገባበር በዝርዝር ለመጻፍ እጅግ አስቸጋሪ ነው:: ይሁንና በአንድ በኩል እ.አ.አ በ1994 በተደረገው የሕዝብና ቤት ቆጠራ አኀዛዊ ስሌት መሠረት በከፍተኛ የምእመናን ቁጥር /ከአጠቃላዩ የሕዝብ ብዛት 50 በመቶ በላይ የሚሆነውን ወገን የያዘች/፣ ከዋና መዲናዋ እስከ እያንዳንዱ የገጠር ቀበሌና መንደር ድረስ የአገልግሎትና የአስተዳደር መዋቅር የዘረጋች፣ ከዚህም አኳያ ከፍተኛ ተደማጭነት እና የማስፈጸም ብቃት ሊኖራት የምትችለው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሚና በልማት ፖሊሲ አውጭዎች፣ በልማት ሒደቱ ተሳታፊዎች /መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች፣ በዘርፉ እንቀሳቃሾች እና በተገልጋዩ ኅብረተሰብ ጭምር/ በተገቢው መንገድ ግንዛቤ ሊያገኝ ይገባዋልና ይህን የመነሻ ጽሑፍ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኗል::

***ለምን ቤተ ክርስቲያን ለኢትዮጵያ ዕድገትና ልማት ስትራቴጂያዊ አጋር (Strategic partner) ተባለች?***

1/ ***ቤተ ክርስቲያን በማኅበረሰቡ ዘንድ ሰፊ መሠረትና ተሰሚነት ያላት በመሆኗ:-***



www.eotcmk.org

ቤተ ክርስቲያን መንግሥት ሊሠራቸው የማይችላቸውን ክፍተቶች በመሙላትና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሊንቀሳቀሱባቸው በማይችሉ ወረዳ ዎችና የገጠር ቀበሌዎች ሁሉ የመንግሥትና የሕዝብ አጋር በመኾን ትገኛለች:: በየአህጉረ ስብከቱ ነዋሪ የሆኑ ምእመናን ልጆቿ÷ የእምነቱ ተከታይ ካልሆኑቱ ነዋሪዎች ጭምር÷ ቤተ ክርስቲያን በአገሩ ልማት÷ በአካባቢ ጥበቃ እንቅስቃሴ ብታደርግ አዎንታዊ መልስንና ድጋፍን ታገኛለች፤ ከሌሎች ድርጅቶች በተሻለም ስለ እያንዳንዱ አካባቢ ሁናቴ /local relevance/ በሚገባ ለማወቅ ይቻላታል:: በእግርጥ በዚህ ረገድ ከፍተኛ የአቅም ግንባታ እንደ ሚያስፈልግ እሙን ነው:: በአጠቃላይ ግን ቤተ ክርስቲያን ሕዝቡን በምልዓት፣ በፍጥነት፣ በቀጣይነትና ውጤታማ በኾነ መልኩ ለልማት ለማንቀሳቀስ የተሻለ ዐቅም */Potential strength for speedy, effective community mobilization and influence/* ስለ አላት መንግሥትም ኾነ መንግሥታዊ ያልኾኑ የልማት አጋሮች ከእርሷ ጋር ተቀናጅተው መሥራታቸው አጥጋቢና ዘላቂ ውጤት የሚያመጣ ይሆናል::

2/ ***ቤተ ክርስቲያን የማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት ደጋፊ አለመሆኗ /nonpartisan/፦***

ቤተ ክርስቲያን አጠቃላይ ኅብረተሰብን÷ቤተሰብን÷ማኅበረሰብንና መንግሥትን እኩል ታገለግላለች፤ ለባዕለ ጸጋውና ድኻው ትምህርቷን÷ምክሯንና ተግሣጿን ትናኛለች:: በብሔርና በጐሳ መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን በሰላማዊ መንገድ በመዳኘት ታረግባለች:: የሕዝብን ሥልጣን የመንጠቅ ዝንባሌ የላትም:: ስለሆነም መንግሥትንም ሆነ ሕዝብን የመውቀስ ÷ ፍትሕ እንዳይጓደል÷ ድኻ እንዳይበደል የመከታተል ሐላፊነት በፈጣሪዋ ተሰጥቷታል:: በመሆኑም ሕዝቡ ከብኩን ሕይወት ወጥቶ፣ ከጐጂ ልምዶች ተላቅቆ ወደ ልማት እንዲሠማራና ለአገሩ ዕድገት እንዲፋጠን ለማድረግ ከልማት ኃይሎች ጋር ያለ ወገንተኝነት በጋራ መሥራት የዘወትር ተግባሯ ነው::

3. ***ቤተ ክርስቲያን መነዋወጽ የሌለባት ተቋም /Stable institution/ በመሆኗ፦***

እንደ ሚታወቀው የፖለቲካ ተቋማት ለፖለቲካ ሥልጣን ስለሚካሄደው ምርጫ አብዝተው ይተጋሉ:: የፖለቲካ መሪዎች ከመንበረ መንግሥታቸው በው ድም ይሁን ሳይወዱ የመለወጡ ስጋት፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችም የአመራር ለውጥ ቢደረግ÷የገንዘብ ድጋፉ ቢቋረጥ ወይም ቢቀንስ በሚሉና በመሳሰሉት ነገሮች አለመረጋጋት ሊገጥማቸው ይችላል:: እኒህ ሁሉ ግን ለቤተ ክርስቲያን ውስጣዊ ችግሮቿና ስጋቶቿ አይደሉም:: ለአገር ዕድገት የተሰለፉ የልማት ኃይሎች ሁሉ ተባብረው በቀናነት ሕዝብን እንዲያገለግሉ «*ማስተዋልን ስጣቸው*» በማለት ከመጸለይ በስተቀር ሌላ ሐሳብ የለባትም፤ የቤተ ክርስቲያን አመራሯ፣ ውሳኔ ሰጪ አካሏ፣ ሀብቷ በሙሉ የታወቀ ነውና::

4. ***የቤተ ክርስቲያን ሀብቷ ዘርፈ ብዙ /multidimensional/ መሆኑ፦***

ቤተ ክርስቲያን በልዩ ልዩ መስክ የሀብትና የዕውቀት ባለቤት የኾኑት ምእመናን ልጆቿ በማንኛውም እንቅስቃሴ ሁሉ በሙሉ በጎ ፈቃደኝነት በመታዘዝ የሚላኳት ታማኝ አገልጋዮቿ ናቸው:: በተጨማሪም ቤተ ክርስቲያን በሕዝቡ ዘንድ ከፍተኛ አመኔታ /ታማኝነት/ እና የላቀ ባለሟልነት አላት:: በመሆኑም በማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ሁሉ የቤተ ክርስቲያንን አቅም እንደ ምቹ ሁኔታ ወስዶ በመተባበር ቢሠራ ለዘላቂ ልማት የሕዝብን አዎንታዊ ድጋፍ በቀላሉ ማግኘት ይቻላል::

5 ***የቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ በግለሰብ እና ኅብረተሰብ አመለካከት፣ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ስለሚንጸባረቅ /moral vision and dimension/፦***

ቤተ ክርስቲያን አዳዲስ ሥራዎችን /የአሠራር ዘዴዎችን/ ለመፈልሰምና ለመተግበር አመቺ የሆነ መዋቅርና አሠራር ሊኖራት ይችላል፣ ይገባልም:: በቤተ ክርስቲያን ሥር ማኅበራት ÷ የተደራጁና የሚደራጁ የሰንበት ት/ቤቶች፣ የሰበካ ጉባኤያትና ካህናት በማኅበረሰቡ ውስጥ ያሉ በመሆናቸው ቤተ ክርስቲያን የምታወጣቸ ውንና ለማስፈጸም የምትፈልጋቸውን ተግባራት ለማከናወን፣ ራእይዋን እውን ለማድረግና በእግዚአብሔር የተሰጧትን ተልእኮዎች ለመወጣት ያስችሏታል:: በተጨማሪም ለቤተ ክርስቲያን በተለይና ለሀገራችን በአጠቃላይ የሚበጁ አስተሳሰቦችንና አዳዲስ የአሠራር ስልቶችን፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ግኝቶችን ወደ ምልዓተ ሕዝቡ ለማዝለቅ እና የተሟላ ተቀባይነት እንዲኖራቸው በማድረግ ረገድ ቤተ ክርስቲያን የመፍትሔው ቁልፍ ለመሆን አይሳናትም:: ከዚህ አንጻር የሚወጡትን ልዩ ልዩ ፖሊሲዎች፣ ዐዋጆችና የልማት እንቅስቃሴዎች ለኅብረተሰቡ ለማስተላለ ፍና ለመተግበር ከቤተ ክርስቲያን ጋር መሥራት ወሳኝነት ይኖረዋል::

⌘ ⌘ ⌘

ከተወሰኑ ዓመታት ወዲህ ቤተ ክርስቲያናችን ካለፉት ዘመናት በተሻለ መልኩ በልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን፣ በማእከል፣ በአህጉረ ስብከት፣ በወረዳ ቤተ ክህነትና በአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ደረጃ ባሏት የአገልግሎትና የአስተዳደር መዋቅሮች ሰፊ ማኅበራዊና ልማ ታዊ እንቅስቃሴዎችን በማድረግ ላይ ትገኛለች:: ይህ እንደ ተጠበቀ ሆኖ ቤተ ክርስቲያናችን ካላት ቅምጥ አቅም አንጻር ከሀገሪቱ ዕቅድ አወጣጥም ሆነ የልማት ሒደት ተሳትፎ በተገቢው መንገድ ድርሻዋ እንዲጐላ በእኛ እምነት የሚከተሉት ነጥቦች በአጋር የልማት ኃይሎች ዘንድ አሁን ካለው በተሻለ ሊተኰርባቸው የሚገቡ ሆነው እናገኛቸዋለን::

## *ሀ. መንግሥት ቤተ ክርስቲያኒቱ በልማት ዕቅድም ውስጥ ሆነ ትግበራ ላይ ላላት ስትራቴጂያዊ ሚና የተሻለ ቦታ መስጠት ይገባዋል*

መንግሥት የአገሪቱን የልማት ፖሊሲዎች በማውጣት፣ፖሊሲዎቹን የሚያስፈጽምባቸውን ስትራቴጂዎች በመንደፍ፣ የመሠረተ ልማት ተቋማትን በማስፋፋትና ሌሎች የልማት ሒደቱን የሚያቀላጥፉ የአፈጻጸም ሁኔታዎችን በማመቻቸት ቁልፍ ሚና እንደ ሚጫወት ይታወቃል:: መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣የሞያ እና ሲቪክ ማኅበራት እንዲሁም የእምነት ተቋማት ደግሞ በርእያቸውና በተልእኳቸው መሠረት ዝቅተኛውን የኅብረተሰብ ክፍል ማእከል በማድረግ የአገሪቱን የልማት ግሥጋሴ በማፋጠን ረገድ ከፍተኛ ሚና እንዳላቸው ይታመናል:: ይሁንና ከብዙ የአፍሪካ አገሮች ጋር ሲነጻጸርና ኢትዮጵያ ካላት የሕዝብ ብዛት አንጻር ሲታይ በልማት ላይ የተሠማሩ መንግሥታዊ ያልኾኑ ድርጅቶች ቁጥርና ክልላዊ ሥርጭት አነስተኛ ነው:: ስለዚህም ጎጥንና ጎሳን ሳትለይ በሁሉም የአገራችን ክፍል የምትገኘው ቤተ ክርስ ቲያናችን በሙሉ አቅሟ በልማት ጥረቱ እንድ ወትሳተፍ ኹኔታው የበለጠ ሊመቻችላት ይገባል::


ላለፉት ሠላሳ ዓመታት መንግሥት በሚያወጣው የልማት ዕቅድ ላይም ሆነ ትግበራ ላይ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ስትራቴጂያዊ ሚና ከግንዛቤ ውስጥ አለመግባቱ በአገሪቱ የልማት ሒደት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ማሳረፉ አልቀረም:: ለምሳሌ፦ በደርግ ዘመን ከተከናወኑት የልማት ተግባራት ውስጥ የመልሶ መቋቋም እና ሰፈራ መርሐ ግብር ዘመቻን ብቻ እንኳ ስንመለከት ዕቅዱ በራሱ ጥሩ የነበረ ቢሆንም ቅሉ በአፈጻጸም የታዩት ስሕተቶች ማለትም ሕዝብን በዕቅድና ትግበራ ላይ አለማሳተፉ፣ በሕዝቡ ዘንድ ተቀባይነት ያላት ቤተ ክርስቲያን አስፈላጊውን ምክር በመስጠት የዕቅዱ፣ የትግበራው እና አካል አለመሆኗ መርሐ ግብሩ የታቀደለትን ግብ እንዳይመታ ዋነኛ ምክንያት ሆኗል:: መንግሥት በሚያወጣቸው የልማት ዕቅዶችም ሆነ ትግበራዎች ላይ ኅብረተሰቡ ውስጥ ከፍተኛ ተደማጭነትና ተጽዕኖ የማሳደር ብቃት ካለው አካል ጋር አብሮ መሥራት ያስፈልገዋል:: የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከ350-1967 ዓ.ም ድረስ ብሔራዊት ሃይማኖት ሆና ኖራለች:: ሆኖም በ1967 ዓ.ም በወጣው የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ማቋቋሚያ ዐዋጅ፤ በ1979 ዓ.ም በጸደቀው የኢ.ሕ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥት በኋላም በ1987 ዓ.ም በጸደቀው የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥት፦ መንግሥት በሃይማኖት ጉዳይ ሃይማኖትም በመንግሥት ጉዳይ ጣልቃ እንደ ማይገባ ይደነግጋል:: እዚህ ላይ ምንም እንኳ መንግሥትና ሃይማኖት የውኃና የዘይት ያህል የማይወራረሱ መስለው ቢቀርቡም በነባራዊው ዓለም ግን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ስትራቴጂያዊ ሚና በተለይ

በልማቱ ሒደት ላይ እጅግ ከፍተኛ መሆኑ አሌ የማይባል ሐቅ ነው:: ስለዚህ ነው የተባበሩት መንግሥታት:- የእምነት ተቋማት በዓለም አቀፍ ሰላም እና ዕድገት ያላቸው ሚና በመጪው ዓመታት ከግንዛቤ ውስጥ መግባት እንዳለበት በጥልቅ መወያየት የጀመረው:: /UNDP, 1998/:: እንደ የዓለም ባንክና ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት ያሉት ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ደግሞ ከልዩ ልዩ የእምነት ተቋማት ጋር በመኾን በድህነት ቅንሳ፣ በምእተ ዓመቱ የልማት ግቦች፣ ከልማት ጋር በተጓዳኙ ሞራላዊና ሥነ ምግባራዊ ዕሴቶችና ድርጊቶች /ሥነ ተዋልዶና ምጣኔ ውሉድ፣ ኤች. አይ. ቪ /ኤድስ . . . ወዘተ/ ላይ ያተኮሩ የጋራ የምክክር መድረኮች /World Faith Development Dialogue/ መሥርተዋል:: [Marshall, Katherine and Marsh, Richard, (eds.) (2003), Millennium challenges for Development and Faith Institutions] [UNDP (2004), The Human Development Report, New York]. ከዚህ በመነሣት በመሠረተ ትምህርት እንቅስቃሴ፣ ኤች. አይ.ቪ/ኤድስን በመከላከልና መቆጣጠር በአካባቢ ጥበቃ፤ በመሠረተ ጤና፤ በሥራ ዕድል ፈጠራ... ወዘተ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ካላት ሰፊ የአገልግሎት ሽፋን አንጻር ያለ ብዙ ውጣ ውረድ በእያንዳንዱ ቤት በቀላሉ የመድረስ አቅም አላት::

እንደ ሚታወቀው በተለይ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ሀገሮችን ዕድገት እያቀጨጨ ያለው ችግር ምጣኔ ሀብታዊ ብቻ አይደለም፤ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊና የፍትሕ መጓደል ጭምር እንጂ:: ለረጅም ዓመታት የዘለቀው የእርስ በርስ ግጭትና አምራች የሆነው ወጣት ይማገድበት የነበረው ጦርነት፣በውጭ ብድርና ርዳታ ላይ ያለው ጥገኝነት፣ የመሠረተ ልማት አውታሮች በበቂ ሁኔታ አለመዘርጋት፣ የትምህርት፣ የጤና እና ሌሎች የማኅበራዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማት አነስተኛ መሆን፣ የወጣት ሥራ አጥ ቁጥር መጨመር፣ ከጥቂት ዓመታት ወዲህ ደግሞ በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ምክንያት አጠቃላይ ማኅበረሰቡ መጠቃቱ ተጠቃሽ ችግሮች ናቸው:: እነኝህን ሁሉ የዕድገትና ልማት ችግሮች ፈጣንና ቀጣይነት ባለው መልኩ ለመፍታት መንግሥት የቤተ ክርስቲያንን ሚና ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ያሻዋል::

### ለ. የልማት አጋር ድርጅቶች በልማቱ ዙሪያ የቤተ ክርስቲያኒቱን ከፍተኛ ሚና በተገቢው መንገድ ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል

አገር በቀልም ሆኑ ዓለም አቀፍ የልማት አጋር ድርጅቶች ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጋር ያላቸውን ተቀራርቦ የመሥራት ሒደት ስናይ በእጅጉ አነስተኛ ነው:: የዚህም ዋነኛ ምክንያቶች አጋር ድርጅቶቹ:- ቤተ ክር ስቲያኒቱ በኅብረተሰቡ ውስጥ ባላት ስር የሰደደ መሠረት እና ተደማጭነት ላይ በቂ ግንዛቤ ስለሌላቸው፣ «የቤተ ክር ስቲያኒቱ መዋቅር የሚሰጡትን ርዳታዎች በበቂ ሁኔታ ሊሸከም አይችልም» ከሚል ግምት እና «በእምነት አትመስለንም» እና «በእምነት ከሚመስሉን ድርጅቶች ጋር ኅብረት መፍጠር አለብን» ከሚል ስውር አጀንዳ የተነሣ ነው:: ይህም ሲባል ቤተ ክርስቲያኒቱ ከሀገር ውስጥም ሆነ ከውጭ አጋር ድርጅቶች ጋር ምንም ዓይነት የትብብርና የልማት ተግባራት የሏትም ለማለት ሳይሆን እንደ ስትራቴጂያዊ አጋር /Strategic Partner/ ወስዶ የመተባበሩ ሒደት ግን በጣም በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንዳለ ለማስገንዘብ ነው::



*በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን ከተሠሩት የመጠጥ ውኃ ፕሮጀክቶች አንዱ /ሰሜን ሸዋ - ሚዳ ኦሮሞ/*

### ሐ/ ሁሉም የልማት አጋሮች / Deveplopment Partners/ ቤተ ክርስቲያን ስንፍና የከፋ ኃጢአት መኾኑን እንደ ምታስተምር እና በአስተምህሮቷ ውስጥ ካለሥራ የሚኖር ተስፈኝነትን እንደ ማታ በረታታ ሊያውቁላት ይገባል::

አሁን ያለንበት ዘመን በዋነኛነት በውስጣዊ አቅማችን ላይ ተመሥርተን የዕድገትና ልማት የምንተጋበት፣ በአንድነት ለሀገር ዕድገት የምንነሣበት መሆኑን ሁሉም ያምንበታል:: የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥራ የኑሮ መሠረት መሆኑን ታስተምራለች:: የምትመራባቸው ቅዱሳት መጻሕፍትም በዓላትን በተወሰነው ሥርዐት ማክበር ብቻ ሳይሆን የሥራን ጠቃሚነት በስፋት የሚተነትኑና የሥራን ባህል የሚያዳብሩ ናቸው:: እግዚአብሔር ከስሕተት አስ ቀድሞ ለአባታችን አዳም ሐላፊነትን ሰጥ ቶት ነበር - ገነትን ያበጃት ይጠብቃትም ዘንድ:: ዘፍ.2÷15:: ከስሕተት በኋላም ሰው ከፈጣሪው ተምሮ ወደ መጣበት መሬት እስኪመለስ ድረስ ጥሮ ግሬ በወዙ እንዲበላ፣ በስንፍና ተዘልሎ እንዳይቀመጥ፣በወገኖቹ ላይ፤ ጥገኛ ሆኖ እንዳ ይከብድባቸው ይልቁንም የድካሙን ፍሬ ቢመገብ ምስጉን እንደ ሆነና መልካም እንደሚሆንለት ተነግሮታል:: ዘፍ.2÷2፤ 2÷7፤ 3÷19፤ዘጸ.20÷9፤መዝ.104÷23፤127÷2፤ መክ 9÷10፤8÷15፣ኤፌ.4÷28፤ 1ተሰ.4÷10፤2ተሰ.3÷8፤3÷10-13:: ከዚህ አኳያ ቤተ ክርስቲያን የሕዝቡን ሁለንተናዊ አንድነት በማጽናት ለኢኮኖሚው ጤናማ ዕድገት፣ ለሕዝብ ልማትና ደኅንነት መጠበቅ የበ ኩሏን ድርሻ የምትወጣ የማይተካ ሚና ያላት መሆኗን የልማት አጋሮች ሊገነ ዘቡላት ይገባል:: ሁሉም የልማት አጋሮች የቤተ ክርስቲያኒቱ አስተምህሮ፣ ሥርዐትና ትውፊት ምን ያህል ለልማት ምቹ መሆኑን በወጉ ሳይመረምሩ በስማ በለው ከመንቀፍና ከማቃለል ይልቅ በጥናት የተደገፈ መረጃ ሊኖራቸው ይገባል:: ቤተ ክርስቲያናችንም ሌሎች ወደ እርሷ መጥተው እስኪረዱ ከመጠበቅ ይልቅ ተነሣሽነቱን በራሷ በመውሰድ አጋሮቿ አቋሟንና አቅሟን እንዲያውቁ የምታደ ርገውን በጥናት የተደገፈ እንቅስቃሴ አጠናክራ መቀጠል ያስፈልጋታል::

⌘ ⌘ ⌘

በአሁኑ ወቅት የተባበሩት መንግሥታት የልማት አመልካቾች ተብለው የተቀመጡት ነገሮች:- መጻፍና ማንበብ፣ አማካይ የዕድሜ ዘመን /Life expectancy/ ፣ የተወለዱ ሕፃናት የማደግ ዕድል መሻሻል፣ ኅብረተሰቡ ለጤናና የንጹሕ መጠጥ ውኃ ያለው ቅርበት፣ የአየር ብክለትን መከላከልና የተስማሚ አካባቢን ዘላቂነት ማረጋገጥ ... ወዘተ ያጠቃልላል:: ከዚህ አኳያ ልማት የሁሉም ኅብረተሰብ አካላት ጥምር ጥረት ውጤት መሆኑን እንረዳለን:: በይበልጥም የልማት ሥራ ዝቅተኛውን የኅብረተሰብ ክፍል ያቀፈ / Pro- Poor/ መሆን ይኖርበታል:: ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ከሕዝብ ጋር በመሆን መንፈሳዊና ሥጋዊ ሕይወቱ የተስተካከለ እንዲሆን በመጣር በኩል ግንባር ቀደም ተጠቃሽ አካል ናት:: ከዝቅተኛው የኅብረተሰብ ክፍል ጋር በመሆን ከቀቢጸ ተስፋ ሸሽቶ ለነገ የተቃና ሕይወት ዛሬ ጠንክሮ ለመሥራት ይበረታታ ዘንድ ከቤተ ክርስቲያን ሌላ የቀረበ ወገን /ተቋም/ የለም:: በኢትዮጵያ ውስጥ ከ35,000 በላይ አብያተ ክርስቲያናት ሲኖሩ ኦርቶዶክሳዊው ምእመንም ከአጠቃላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከ50 በመቶ በላይ እንደ ሆነ መረጃዎች ያሳያሉ:: በአሁኑ ወቅት ቤተ ክርስቲያናችን ከግማሽ ሚልዮን በላይ ካህናት 6.5 ሚልዮን ያህል የተመዘገቡ የሰንበት ት/ቤቶች አባላት የኾኑ ወጣቶች አሏት:: /EOC-DICAC Five Year Strategic plan /2005-2009/, Addis Ababa, April 2005,P.14/. ብዙዎቹ



www.eotcmk.org

ኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት ከዋና ዋና ከተሞች በጣም የራቁ ቢሆኑም እዚያ ያለውን ሕዝብ በልማት ማሳተፍና ለአገር ዕድገት ደፋ ቀና እንዲል በንስሐ አባቶች፣ በመምህራንና በሰባክያነ ወንጌል አማካይነት በማስተማሩ ረገድ ለቤተ ክርስቲያን ቅርብ ነው:: ቤተ ክርስቲያን ከማንኛውም አካል የተሻለ አመኔታ በምእመናን ዘንድ ያላት መሆኗ፣ ምእመናን ቋንቋዋን፣ አመራሯንና ዓላማዋን ጠንቅቀው የሚያውቁ በመሆናቸው ለልማት እንዲነሡ ብትቀሰቅስ አብዛኛውን የኅብረተሰብ ክፍል የማነቃቃት አቅም አላት::

***ቤተ ክርስቲያን በስትራቴጂያዊ የልማት አጋርነት ምን ሚና ይኖራታል?***

- ቤተ ክርስቲያን ከመንግሥት ፖሊሲ አውጭ ቢሮዎች ወቅታዊ መረጃዎችን የመጠየቅ፣ መሪዎችና አማካሪዎቻቸው የሚቀርጹትን ማንኛውንም ጉዳይ የመፈተሽና በቂ ውይይት እንዲካሄድበት የማድረግና ለተግባራዊነቱም የበኩሏን ድርሻ መወጣት ይኖርባታል::
- የመልካም አስተዳደር መርሖችንና መመሪያዎችን ከማሳወቅ፣ የሥነ ዜጋ ትምህርትን ቀርጾ በየደረጃው ላለ የኅብረተሰብ ክፍል እንዲሰጥ ከማድረግ፣ ሙስናን ከማጥፋትና ግብረ ገብነትን ከማስፈን አንጻር ቤተ ክርስቲያን ድርሻ ይኖራታል::
- ቤተ ክርስቲያን የድኾች ጠበቃ ናት፤ በመሆኑም ለተበደሉትና ፍትሕ ላጡት አዘውትራ ትናገርላቸው ዘንድ ድኾች ወደ ቤተ ክርስቲያን ይጮኻሉ:: ከዚህ አንጻር ቤተ ክርስቲያን የሕዝብን ጩኸት በመስማት፣ ከመንግሥት ጋር በመነጋገር መፍትሔ የመሻት፣ ሰላምንና መረጋጋትን በማስፈን፣ ግጭትን በማስወገድ ረገድ በምንምና በማንም የማይተካ ሚናዋን መጫወት ይጠበቅባታል::
- *በማኅበራዊ አገልግሎት ተቋማት ግንባታ፣ በትምህርት ቤቶችና የጤና ኬላዎች ግንባታ ቤተ ክርስቲያን ቁልፍ ሚና ትጫወታለች:: በትምህርት ዘርፍ ከትምህርት ቤቶች ግንባታና ጥገና በተጨማሪ የትምህርት ጥራት እንዲጠበቅና የሥነ ምግባር ትምህርት እንዲካተት፣ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ገብተው የሚማሩ ተማሪዎች ቁጥር እንዲጨምር በማድረግ፣ የመማሪያ መጻሕፍት የትምህርት ጥራትን የጠበቁ እንዲሆኑ ከሚመለከተው የመንግሥት አካል ጋር መነጋገር፣ ከትምህርት ገበታ በተለያየ ችግር የሚርቁ ተማሪዎች ትምህርታቸውን የሚቀጥሉበት ሁኔታ ማመቻቸት፣ የሞያ ማሠልጠኛ ተቋማት እንዲከፈቱ ድጋፍ ማድረግ፣* ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ ት/ቤት እንዲልኩና ያለ ዕድሜ ጋብቻ እንዲቆም በንስሐ አባቶች በኩል ማስተማር... ከመደበኛ ትምህርት በተጨማሪ የጐልማሶች ትምህርት እንዲቀረጽና አሁን ያለው የጐልማሶች የመጻፍና የማንበብ ደረጃ /Adult literacy rate/ ከ41.5% (33.8 % ሴት፣ 49.2% ወንድ) ወደ 100% ለማሳደግ ቤተ ክርስቲያን ብዙ አስተዋፅኦ ማድረግ ትችላለች:: ለዚህም ተግባራዊነት ለእያንዳንዱ ጐጆ ቅርብ የሆኑት ካህናቷ እና በልዩ ልዩ የሞያ መስኮች የተሠማሩ ምእመናን ልጆቿ ዓይነተኛ መሣሪያ ሊሆኑ ይችላሉ::
- ***ቤተ ክርስቲያን የራሷ በሆኑ ሀብታቷ የማስተዳደር የባለቤትነቷ ሙሉ መብት መከበር አለበት::*** በአሁኑ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ' በባለቤትነቷ በምትታወቅበት የቱሪዝም ዘርፍ የላቀ ድርሻ አላት:: ቱሪዝም ለሀገሪቱ ዕድገት ታላቅ አስተዋፅኦ የሚያበርክት ኢንዱስትሪ ቢሆንም ዕድሉን አሟጦ በመጠቀሙ ረገድ ግን እስካሁን ያላት እንቅስቃሴ የሚፈለገውን ያህል አይደለም:: የመንግሥት የረጅም ጊዜ ራእይ፦ ኢትዮጵያን በ2020 በአፍሪካ ውስጥ ካሉ የመጀመሪያዎቹ ዐሥር የቱሪስት መናኸሪያ አገሮች ተርታ ማስገባት ነው:: ኢትዮጵያ ለቱሪስት መስብሕነት ከምትጠቀምባቸው ቦታዎች፦ ጥንታዊና ውቅር ሕንጻ አብያተ ክርስቲያናት፣ የቤተ ክርስቲያን ቅርሶችና ውብ መንፈሳዊ /ትውፊታዊ/ ባህሎቿ ተጠቃሾች ናቸው:: ስለዚህ እነዚህ ቅርሶች ተጠብቀው እንዲቆዩ የመገናኛ አውታሮች ግንባታ፣ የሚጐበኙ ቦታዎችን ታሪክ በትክክል ለቱሪስቶች አዘጋጅቶ በማቅረብ፣ የአስጐብኚዎችን ዕውቀት በማጐልበት... ወዘተ ቤተ ክርስቲያን ድርሻዋን ልትወጣና ከሚገኘውም ገቢ በአግባቡ ተጠቃሚ ልትሆን ትችላለች:: ***ቤተ ክርስቲያን በአካባቢ ጥበቃ ዘርፍ ምእመኑን ማስተማር ትችላለች::*** ቀጣይነት ያለውን ልማት ለማረጋገጥ የአካባቢ ጥበቃን በዘላቂነት እውን ማድረግ ያስጠፈልጋል:: ቤተ ክርስቲያን በአካባቢ ጥበቃና ክብካቤ ግንባር ቀደም ተዋናይት ናት:: ለዚህም ለብዙ መቶ ዓመታት የቆዩ ደኖች በገዳማቷ ዙሪያና ቅጽረ ቤተ ክርስቲያን ብቻ መገኘታቸውን ማሰብ እንኳ በቂ ነው:: አካባቢን ከመጠበቅና የአየር መዛባት ችግርን ከመከላከል አንጻርም ቤተ ክርስቲያን ጉልህ ሚና ልትጫወት ትችላለች:: እግዚአብሔር አምላክ ሰውን በአርአያውና በአምሳሉ ከፈጠረው በኋላ «ይንከባከባትና ይጠብቃት ዘንድም ሰውን በዔደን ገነት አኖረው» ይላል:: ዘፍ.2÷15:: ይህም ሰው እግዚአብሔር የሰጠውን ጸጋና ‚ ሀብት መጠበቅ÷መከባከብና በአግባቡ መጠቀም ያለበት መሆኑን ያሳያል:: ከሠላሳ ዓመታት በፊት ዛሬ ተጋልጠው የሚገኙ ተራራዎችና ኮረብቶች በዛፍና በሣር የተሸፈኑ፣ በልምላሜ የተዋቡ እንደ ነበሩ መረጃዎች ያመለክታሉ:: አሁን ግን ለሚያየው ሁሉ የሚያስደነግጥና የተለበለበ መስሎ የሚታየው ምድር ያሳዝናል::

ይህ መልክአ ምድራዊ ሁኔታ የሰው ልጅ የተሰጠውን ሀብት በአግባቡ መጠቀም ያለመቻሉን ይናገራል:: ይህን የተራቆተ አካባቢ ሙሉ በሙሉ ወደ ነበረበት ይዞታ ለመመለስ ባይቻልም እንኳ ወደ ተሻለ ሁኔታ ለማምጣት ቆርጦ ለተነሣ አስቸጋሪ አይሆንም:: በመሆኑም ቤተ ክርስቲያን የደን ሀብትን ለመጠበቅ÷ የአፈር መሸርሸርን ለመከላከልና በመልሶ ማቋቋም የተለያዩ ተግባራትን ማከናወን ይቻላታል:: ለምሳሌ፦

- ችግኝ ማፍላት
- ዛፍ መትከል
- የአፈርና ውኃ ጥበቃ ሥራዎችን ማከናወን÷
- የውኃ ማቆርንና ምንጮችን የማጐልበት ሥራ መሥራት፤

በሁለተኛው የመንግሥት የአምስት ዓመት የልማት ስትራቴጂ /PASDEP/ እንደ ተመለከተው እ.ኤ.አ በ2004/05 ንጹሕ የመጠጥ ውኃ ተጠቃሚ ያልነበረው ሕዝብ 48 ሚልዮን ያህል ነበር:: ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል የንጹሕ መጠጥ ውኃና የአነስተኛ መስኖ ልማት ተጠቃሚ እንዲሆን ከመንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርድቶች ጋር በጋራ በመሥራት ቤተ ክርስቲያን ጉልህ ሚና መጫወት ይቻላታል::

በአብዛኛው የገጠሩ ኅብረተሰብ በአካባቢው የሚገኘውን የምንጭ ውኃ ባለማጐልበትና ባለመከባከብ፣ የአካባቢንና የግል ንጽሕናን ባለመጠበቅ ከፍተኛ የጤና መታወክ ችግር ተጠቂ ሆኗል:: ይህን ችግር ለመቅረፍ ቤተ ክርስቲያን በልማት ና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን ና በሰንበት ት/ቤቶች አማካይነት፦

- ምንጮችን በማጐልበት፣
- የእጅ ውኃ ጉድጓዶች ቁፋሮና የግል ንጽሕና አጠባበቅ፣
- ጥልቅ የውኃ ጉድጓዶችን በመቆፈር፣
- የተጠቃሚዎች የጤና ሁኔታ እንዲሻሻል የአካባቢና የግል ንጽሕና አጠባበቅ ትምህርት በመስጠት፣
- ኅብረተሰቡ ገንዘቡን÷ዕውቀቱንና የአካባቢ ቁሳቁሶችን አቀናጅቶ ራሱን የማገዝና የውኃ ጉድጓዶችን በባለቤትነት የመምራት ዐቅሙን ለማጐልበት ተገቢ ሥልጠና በመስጠት እያደረገች ያለውን ጥረት አጠናክራ እንድትቀጥል መንግሥት ድጋፍ ሊቸራት ይገባል::
- ቤተ ክርስቲያናችን ከመንግሥትም ኾነ ሀገር በቀልና ዓለም አቀፍ የልማት አጋር ድርጅቶች ጋር የልማት ተግባራትን በምታከናውንበት ወቅት በአገልግሎትና በአስተዳደር መዋቅሮቿ ውስጥ ልታስተዋውቃቸውና ተግባራዊ ልታደርጋቸው ከምትችላቸው በርካታ ዘመናዊ አሠራሮች መካከል፦
- በስትራቴጂክ ኢንቨስትመንቶች /በግብርናና ፋይናንስ ተቋማት ማስፋፋት ... ወዘተ/ ላይ መሳተፍ አነስተኛ የቁጠባና ብድር ተቋማትን /Micro finance Instititions/ ቢያንስ በሀገረ ስብከት ደረጃ ማደራጀት እና ለዝቅተኛው የኅብረተሰብ ክፍል የብድር አገልግሎት መስጠትና አፈጻጸሙን መከታተል የሚሉት ይጠቀሳሉ::

/ወደ ገጽ ፴ ዞሯል/





www.eotcmk.org

# እምነት እና እምነትን የሚያቀዘቅዙ ነገሮች

/አዶስ ዘቦረና/

ኤልሻዳይ እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ሲፈጥር በውስጡ ሀብተ ሃይማኖት /የአምልኮ ዝንባሌ/ እንዲኖረው አድርጎ ነው:: ይሁን እንጂ ሰው በተፈጥሮው፡- የተሰጠውን የአምልኮ ዝንባሌ በመጠቀም በባሕርያቸው አማልክት ያልሆኑትን እንዳያመልክ የሚያገናዝብ በትን አእምሮ ግእዛን አልነፈገ ውም:: በሥነ ፍጥረት ብቻ ሳይሆን በኅሊናና በቅዱሳት መጻሕፍት በኩል መኖሩንና ሊመለክም የሚገባው እርሱ ብቻ መሆኑን ገልጾስታል:: /ሮሜ.1÷21፤ ሮሜ.2÷14፤ ዘፍ.1÷1/::

ከአዳም ጀምሮ የነበሩ አባቶቻችንም እግዚአብሔር በገለጠላቸው መንገድ ሲያመልኩት ኖረዋል:: እነርሱን ስዘለዓለም ሕይወት ያበቃቸውን እምነት ለእኛ ለልጆቻቸው አስተላልፈዋል:: እኛም ተከተልናቸው::

## እምነታችን ምን ዓይነት ነው?

- *ከእግዚአብሔር የተሰጠ እምነት፡-*

በርካታ ቁጥር ያለው የዓለማችን ሕዝብ ከሰይጣን፣ ከሰዎችና ከራሱ ልቡና አንቅቶ የተቀበላቸውን ልዩ ልዩ እምነቶች ተቀብሎ በሞት ጎዳና ሲነጉድ ማየት በጣም ያሳዝናል:: እምነት ሰውና እግዚአብሔር የሚገናኙበት እውነተኛ ድልድይ ነውና መገለጥና መስጠት ያለበት በራሱ በእግዚአብሔር ነው:: ከእግዚአብሔር ዘንድ ያልተሰጠ እምነት እምነት ሊሆን አይችልም:: የክብር ባለቤት እግዚአብሔር ምስጋና ይግባውና ዛሬ የምንከተለውን እምነት ለኛ ሰጥቶናል:: የያዕቆብ ወንድም የሆነው ሐዋርያው ይሁዳ፡- «ወዳጆች ሆይ÷ ስለ ምንካፈለው ስለ መዳናችን ልጽፍላችሁ እጅግ ተግቼ ሳለሁ ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ፈጽሞ *ስለ ተሰጠ ሃይማኖት* እንድትጋደሉ እየመከርኋችሁ እጽፍላችሁ ዘንድ ግድ ሆነብኝ::» ያለው ለዚህ ነው:: ይሁዳ.ቁጥር 3::

*ቅዱስ እምነት፡-* የምናመልከው አምላክ ቅዱስ ነው:: የሰጠንም እምነት የተቀደሰ እምነት ነው:: በሰዎች ሥጋዊና ደማዊ ሐሳብ ላይ የተመሠረቱ፣ በሰይጣንም የተንኮል ማኅ ላይ የበቀሉ የብዙ ብዙ እምነቶች በዓለም ውስጥ አሉ:: ከቅዱሱ እግዚአብሔር የተሰጠን እምነት ግን ርኩሰትና ከንቱነት ያልተደባለቀበት ልዩ እምነት ነው:: «እናንተ ግን ወዳጆች ሆይ÷ ከሁሉ ይልቅ *በተቀደሰ ሃይማኖታችሁ* ራሳችሁን ለማነጽ እየተጋችሁ ....» የሚለውን የመጽሐፍ ቃል ስንገነዘብ በተቀደሰ ሃይማኖታችን እናድጋለን:: ይሁዳ.ቁጥር 20::

*የተፈተነ እምነት፡-* አንገታችንን ቀና አድርገን የምንሔድበት ኦርቶዶክሳዊ እምነታችን በብዙ ፈተናዎች ውስጥ አልፎ እስከ ዛሬ መድረሱን ስናስላስል በእሳት የተፈተነ ወርቅ ሃይማኖት እንዳለን እንገነዘባለን:: ዛሬም እምነታችንን በከበበ ፈተና ውስጥ ቆመን ይሆናል፤ ጥንቱንም ይህን በመሰለውና ከዚህ በከፋው የፈተና እሳት ውስጥ አልፎ ነውና የመጣው አንደነቅ:: ይልቅ የተፈተነ እምነት ያለን የእግዚአብሔር ልጆች በመሆናችን ደስ ይበለን፤ «ነገር ግን በእሳት ምንም ቢፈተን ከሚጠፋው ወርቅ ይልቅ አብልጦ የሚከብር *የተፈተነ እምነታችሁ* ኢየሱስ ክርስቶስ ሲገለጥ ለምስጋናና ለክብር ለውዳሴም ይገኝ ዘንድ አሁን ለጥቂት ጊዜ ቢያስፈልግ በልዩ ልዩ ፈተና አዝናችኋል::» 1ጴጥ.1÷7::

- *የከበረ እምነት፡-* ዘለዓለም በክብር የሚኖር ልዑል እግዚአብሔር የሰጠን እምነት በክ ብር የተንቆጠቆጠ ነው:: ወልድ ዋሕድ በምትል በዚህች እምነት የምንኖር ሁሉ ክብር ያለን ነን:: በዚህ ምድር ብቻ ሳይሆን በኋለኛውም ዘመን የክብር አክሊል የሚደፋላቸው እግዚአብሔር ያከብረ ውን የክብር ሃይማኖት ገንዘብ ያደረጉ ናቸው:: ለሃይማኖታቸው ሲሉ ለተሰደ ዱት መጻተኛ ክርስቲያኖች የተጻፈው የቅዱስ ጴጥሮስ መልእክት የእምነታችንን ክቡርነት ይነግረናል፤ «በአምላካችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጽድቅ ካገኘነው ጋር የተካከለ የክብር እምነትን ላገኙ::» 2ጴጥ.1÷1::
- *አንዲት እምነት፡-* ሦስት ገጽ፣ ሦስት መልክ፣ ሦስት አካል በአንድ ባሕርይ በአንድ ህላዌ ያለው እግዚአብሔር በየዘመኑ የተለያየ እምነት አልሰጠንም:: መዝሙረኛው፡- «አንተስ አንተ ክመ፤ አንተ ግን ያው አንተ ነህ» (መዝ.101÷27) እንዳለ እግዚአብሔር ትላንት፣ ዛሬና ነገ ያው እርሱ ነውና የገለጠልን እምነት አንዲት ናት:: በየትኛውም ዘመን የሚነሣ ትውልድ በአንዲቷ ሃይማኖት ላይ ሊጨምር ሊቀንስ አልተፈቀደለትም፤ የገዛ ፈቃዱን ተከትሎ የሚነጐደው በዛ እንጂ:: እምነታችን አንዲት ከመሆኗ የተነሣ የሌሎቹን ዘወር ብለን የማናይ ስንሆን አንድ እግዚአብሔር የሚመለክባትን ርትዕት እምነትን ያልተከተሉትንና የተውትን ባሰብን ቁጥር ሐዘን ይሰማናል:: «አንድ ሃይማኖት» የሚለው የቅዱስ ጳውሎስ ስብከትና «አንድ ጊዜ ፈጽሞ ስለ ተሰጠ» የሚለው የይሁዳ መልእክት ይህን በተረዳ ነገር ያጎላልናል:: ኤፌ.4÷5፤ ይሁዳ.ቁጥር 3::

## እምነት ለምን ተሰጠን?

- *የእግዚአብሔር ልጆች እንድንሆን፡-* ልዑል እግዚአብሔር አባታችን ሲሆን እኛ ደግሞ የእርሱ ልጆች ነን:: ልጅነታችን የተገኘው ግን የእርሱን አባትነት አምነን ከመቀበላችን የተነሣ ነው:: ስለሆነም እምነትን የሰጠን በእምነት በኩል የእርሱ ልጆች እንድንሆን ስለ ወደደ ነው:: መጽሐፍ፡- «*በእምነት በኩል* ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁ::» እንዲል:: ገላ.3÷26::

*የመንፈስ አንድነት እንዲኖረን፡-* አንድነት ይኑረን ሲባል የቋንቋ ችንን፣ የባህላችንን፣ የሥራችንንና የዝንባሌያችንን የከበረ ልዩነት ጨፍልቀን አንድ እናድርግ ማለት አይደለም፤ ይህ እየመሰላቸው የታለሉ የዋህን አሉና:: በክርስትናው ዓለም አንድነት ማለት የመንፈስ አንድነት ማለት ነው:: እግዚአብሔርን በአንድነቱና በሦስትነቱ ያመን ሁሉ በእምነታችን በኩል በመንፈስ አንድ ሆንናልና የዘር፣ የቋንቋ የቦታና የዕውቀት ልዩነታችን አይለያየንም:: የሥጋ ሥራ ከሆነው መለያየት ይልቅ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ የሆነውን አንድነት የሚወድ ጌታ እግዚአብሔርም መለያየታችንን አይሻምና የመንፈስ አንድነታችን የሚቋጠርበትን የእምነት ማተብ ሰጠን::

- *ከኃጢአታችን ፡እንድንነጻ፡-* እግዚአብሔርን አለማመን ራሱ ኃጢአት ነው:: ያመነውም ብንሆን በራሳችን ድካም፣ በዓለም ፈተናና በሰይጣን ተንኮል ተታለን በኃጢአት እንወድቅ ይሆናል:: ወደ ሕይወታችን የገባው ኃጢአትም ሆነ አለማመናችን እንዳቆሸሸን ይኖር ዘንድ ግን የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም:: እርሱ መንጻታችንን ይፈልጋል:: የሚያነጻን እግዚአብሔር እንደ ሆነና በመናዘዛችንም ከኃጢአታችን እንደ ምንነጻ ካመን ከየትኛውም ኃጢአት መንጻታችን እውነት ነው:: ስለ እኛ መንጻት ዘወትር የሚገደው አባታችን እግዚአብሔርም እምነትን ከኃጢአት እንነጻበት ዘንድ ሰጠን፤ «ልብንም የሚያውቅ አምላክ ለእኛ ደግሞ እንደ ሰጠን መንፈስ ቅዱስን በመስጠት መሰከረላቸው፤ *ልባቸውንም በእምነት* ሲያነጻ በእኛና በእነርሱ መካከል አለየም::» ተብሎ እንደ ተጻፈ:: የሐዋ.ሥ.15÷9::

*ራሳችንን እንድንከላከልበት፡-* የትኛውም ምድራዊ ኑሮ በትግል የተሞላ ነው:: በክርስቲያኖችና በሠራዊተ አጋንንት መካከል የሚካሄደው ፍልሚያ ግን እስከ ዕለተ ሞት ድረስ የማያቋርጥ በመሆኑ የተለየ ያደርገዋል:: ዲያብሎስ የሚወረውራቸውን ነበልባላማ ፍላጻዎች ማን በሥጋ መሣሪያ ሊቋቋማቸው ይችላል? ከእምነት ውጪ ማንም ሊመ



www.eotcmk.org

ክታቸው አይችልም:: አምላካችን ግን በፍላጻዎቹ ተነድፈን እንዳንመረዝ እምነትን የመሰለ ጋሻ ሰጠን:: የእምነትን ጋሻ በእምነት የምናነሣ ሁሉ የዲያብሎስ ፍላጻ አያገኘንም:: «የሚንበለበሉትን የክፉውን ፍላጻዎች ሁሉ ልታጠፉ የምትችሉበትን *የእምነትን ጋሻ አንሡ*» መባላችን እምነት መከላከያ ጋሻችን መሆኑን ያጠይቃል:: ኤፌ.6÷16::

- *ድል እንድናደርግበት፡-* ፍልሚያ በመከላከል ላይ ብቻ የተወሰነ አይደለም:: ከተበረታ ድልም የፍልሚያ ፍሬ ነው:: እንደዚሁ ሁሉ እምነታችንም የሰይጣንን ነበልባላማ ፍላጻዎች የምንከላከልበት ጋሻ *ብቻ አይደለም::* ከዚህ ይልቅ ሰይጣንና ዓለማዊ መሻቶቻችንን ድል የምንነሣበት መንፈሳዊ ጉልበትና ጥበብ እንዲሁም ቆራጥነት ነው::

የምናመልከው አምላክ ዘወትር ድል አድራጊ ነውና ከእርሱ በመገለጥ፣ በአፍ፣ በመጣፍ የተቀበልነውን እምነት በእውነትና በተግባር ከተጠቀምንበት ብዙዎችን ያታለለችውንና በወጥመዷ ያሰረቻቸውን ዓለም ድል እንነሳታለን፤ «ዓለምንም የሚያሸንፈው እምነታችን ነው::» ተብሎአልና:: 1ዮሐ.5÷4::

- *ተስፋችንን አስረግጠን የማናየውን እንድናይበት፡-* እምነት ባይኖር ኖሮ ተስፋ ጉልበትና ረጅም ዕድሜ አይኖረውም ነበር:: ተስፋችን እንደ ሚፈጸም እርግጠኞች በመሆን ቆመን የምንጠብቀው በማመናችን ነው:: ሙሉ በኩለሄ ሳለ ለሥጋዊ ዐይናችን የረቀቀብንን አምላክ ያየነውም በእምነት ነው:: በአጠቃላይ በተስፋ ተሞልተን እንድንኖር መንፈሳዊ የሆኑ አካላትን እንድናይና ይኖረን ዘንድ የምንመኘውን ምድራዊ ነገር እንደ ተደረገልን አድርገን በመቁጠር እንድንጸና እምነት ተሰጠን:: ይህን አስመልክቶ ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ፡- «እምነትም ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያስረግጥ፣ የማናየውንም ነገር የሚያስረዳ ነው::» ብሏል:: ዕብ.11÷1::

- *እንድንጸድቅ፡-* የትኛውም ምእመን ያለ ሥራ መጽደቅ የማይችለውን ያህል ማንኛውም በጎ አድራጊ ያለእምነት መጽደቅ አይችልም:: እምነት የተሰጠን የሚታመነውን እግዚአብሔር አምነን በጎ ሥራ ከመሥራት ጋር እንጸድቅ ዘንድ ነው:: «አብርሃም በእግዚአብሔር አመነ፤ ጽድቅ ሆኖ ተቆጠረለት» ተብሎ የተጻፈውን አምላካዊ ቃል ባነበብን ጊዜ እምነት የጽድቅ መገኛ መሆኑን እንገነዘባለን:: ሮሜ.4÷3::

## አለማመንና ችግሮቹ

*እግዚአብሔርን ማስደሰት አለመቻል፡* - እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት የፈለገ ሰው ሁሉ መጀመሪያ እግዚአብሔርን ማመን ይኖርበታል:: አምነነውም በኃጢአትና በበደል የምናሳዝነው አለን:: ይሁን እንጂ በኃጢአት ወድቀን ከምናሳዝነው ሐዘን በበለጠ እርሱን ባለማመናችን የተነሣ የሚያዝነው ሐዘን ይበልጣል:: ያመነ ሰው እግዚአብሔርን በንስሐ ተለማምጦ ይታረቀዋል:: ያላመነው ግን እግዚአብሔርን ፈጽሞ አላወቀውምና ኃጢአትን እንደ እህል ከመብላቱም በላይ በእግዚአብሔር ላይ አፉን እያላቀቀ ዘወትር ሲያሳዝነው ይኖራል:: እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አለመቻልም ልማዱ ይሆናል:: ምክንያቱም በእግዚአብሔር አላመነምና፤ «ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም» የተባለው ለዚህ ነው:: ዕብ.11÷6::

- *ፍርሃት፡-* አዳምና ሔዋን ዕፀ በለስን ከበሉበት ቅጽበት ጀምሮ ፍርሃት ወደ ሰዎች ሕይወት ሰተት ብሎ ገብቷል:: ዘፍጥ.3÷8-11:: ይህም እግዚአብሔርን ካለማመንና ከመተው በኋላ የመጣ ችግር ነው:: እግዚአብሔርን የሚያምኑ ሰዎች ፈጽሞ ፍርሃት የማይሰማቸው ናቸው ማለት ግን አይቻልም፤ አምነው ሳለ የፈሩ ብዙ አሉና:: ይሁን እንጂ ፍርሃታቸውን በእ ምነትና በረድኤተ እግዚአብሔር ድል ሲነሱት ታይተዋል:: እምነት የሌላቸው ሰዎች ፍርሃት ግን አሰቃቂና ማንንም እንዳያምኑ እስከ ማድረግ የሚያደርስ ነው:: ሰውን ፈርቶ የቁስ አካልና የእን ስሳት ወዳጅ መሆን፣ ከመጠን ባለፈ ስጋት መታነቅና መሠቃየት ከማያምኑ ሰዎች ዘንድ የማይጠፉ እውነታዎች ናቸው::

*ሞት፡-* ማመንም ሆነ አለማመን የሰዎች ምርጫ ነው:: ይሁን እንጂ ያመኑ መሸለማቸው ያላመኑም ዘለዓለማዊ ፍርድ መቀበላቸው የግድ ነው:: የምርጫ ነጻነታቸውን ተጠቅመው እግዚአብሔርን በእምነት የማያመልኩ ሁሉ አስፈሪ ቅጣት ይጠብቃቸዋል:: ያም ቅጣት ይግባኝ የሌለበት ፍርድ /ዘለዓለማዊ የነፍስ ሞት/ ነው:: «ያላመነ ይፈረድበታል» የሚለው ቃል እንዴት ያስፈራ!! ማር.16÷16::

## የእምነት ዐይነቶች

ሰዎች የእግዚአብሔርን ህልውና በእምነት ተቀብለው በአንድ የሃይማኖት ጥላ ሥር እየኖሩ የቆሙበት የእምነት እርከን ግን የተለያየ ነው::

- *ሥር የሌለው እምነት :-* ይህን መሰል እምነት ያላቸው ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል በደስታ ይሰማሉ:: በራሳቸውም ሆነ በሃይማኖታቸው ላይ መከራ ሲመጣ ግን ከመካድ አይመለሱም:: ማእምረ ኵሉ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለነዚህ ሰዎች ይህን ብሏል፡- «በአለት ላይም ያሉት ሲሰሙ ቃሉን በደስታ የሚቀበሉ ናቸው፤ እነርሱም ለጊዜው ብቻ ያምናሉ እንጂ በፈተና ጊዜ የሚክዱ ሥር የሌላቸው ናቸው::» ሉቃ.8÷13::
- *ትንሽ እምነት፡-* እነዚህ ደግሞ እምነት ቢኖራቸውም የእምነታቸው መጠን ትንሽ የሆነባቸው ሰዎች ናቸው:: በጨረቃ እየተነሣበት በእሳትና በውኃ ውስጥ ይጥለው የነበረውን ጋኔን ማውጣት ያቃታቸው ደቀ መዛሙርት በአንድ ወቅት ስለ እምነታችሁ ማነስ ነው» ተብለው መገሠጻቸው ለዚህ ነው:: ማቴ.17÷20::

አሁንም በተለያየ ድካም ውስጥ ያለንና ነገሮችን በሙሉ እምነት መፈጸም ያቃተን ወገኖች በውስጣችን ያለውን የእምነት መጠን ማነስ እንመልከት::

- *ጎደሎ እምነት፡-* መድኃኔ ዓለም ክርስቶስ የገሊላን ባሕር ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ሆኖ በታንኳ ሲሻገር ማዕበል ተነሥቶ ታላቅ መናወጥ አስከትሎ ነበር:: ሐዋርያት የሁሉ ጌታ ከእነርሱ ጋር ሳለ በመፍራታቸው፡- «እናንተ እምነት የጎደላችሁ» በመባል ተገሥጸዋል:: ማቴ.8÷26:: ይህ የሚያሳየው በልባችን ውስጥ የሞላው እምነት በሥጋ ድካም ከቃለ እግዚአብሔር እጦትና ከዓለማዊ ተጽዕኖዎች የተነሣ ከምልዓቱ የሚጎድልበት ጊዜ እንዳለ ነው:: የስንቶቻችን የእምነት ጽዋ ጎድሎ እንደ ሚንቦጫቦጭ የሚያውቀው ግን አምላካችን ብቻ ነው:: እኛም «እምነት በምልዓት አለን» ብለን እየታበይን ይሆናል::
- *የሚያድግ እምነት፡-* እኛ ከበረታን በሕይወታችን ውስጥ ያለው ትንሽ የእምነት ችግኝ በሒደት ያድጋል:: ይህ በተለይ በሐዲስ ምእመናንና በእምነት ደክመው ዳግም ባንሠራሩቱ ምእመናን ሕይወት ውስጥ በሰፊው ያለ የእምነት ዐይነት ነው:: ቅዱስ ጳውሎስ በቆሮንቶስ ከተማ ይኖሩ የነበሩትን ግሪካውያን ክርስቲያኖች እምነታቸው በሒደት እያደገ እንደ ሚሄድ ሲነግራቸው፡- «በሌሎች ድካም ያለ ልክ አንመካም ነገር ግን *እምነታችሁ ሲያድግ* ከእናንተ ወዲያ ባለው አገር እስክንሰብክ ሥራችንን እየጨመርን በክፍላችን በእናንተ ዘንድ እንድንከብር ተስፋ እናደርጋለን» ብሏቸዋል:: 2ቆሮ.10÷16:: በልባችን ውስጥ ያለው እምነት ትንሽ መሆንና መጉደል ተስፋ የሚያስቆርጠን ሰዎች እንዳንኖር ያሻል፤ ዛሬ አንሶና ጎድሎ የተቸገርንበት እምነት አንድ ቀን ሊያድግ ይችላል::
- *ታላቅ እምነት፡-* ታላቅ እምነት ያላቸው ሰዎች እግዚአብሔር በሕይወታቸው ውስጥ የትኛውንም ዓይነት ነገር ሊሠራላቸው እንደ ሚችል ያምናሉ:: ከዚህ ጋር በትሕትና የተሞሉ ስለሆኑ በእግዚአብሔር ፊት ሲናገሩና ሲቆሙ በተሰበረ ልብ ነው:: መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡- «እውነት እላችኋለሁ ÷ በእስራኤል እንኳ እንዲህ ያለ ትልቅ እምነት አላገኘሁም» ሲል ያደነቀው መቶ አለቃ ከእነዚህ መካከል አንዱ ነው:: ማቴ.8÷10::
- *ብርቱ እምነት፡-* ብርቱ እምነት ያላቸው ሰዎች እግዚአብሔር የሰጣቸውን ተስ ፋ እስከ መጨረሻው በትዕግሥት ይጠብቃሉ፤ በየትኛውም መከራ ውስጥ ቢያልፉ እንኳን ለእምነታቸው ያላቸው ታማኝነት ጽኑዕ ነው:: በእምነቱ ዘወትር የሚደነቀው አብርሃም እግዚአብሔርን የሚያምን አባት ብቻ አልነበረም፤ በእምነቱ የበረታ ጻድቅም ጭምር ስለ ሆነ እንጂ:: ቅዱስ ጳውሎስ፡- አብርሃም አባታችን በእምነቱ ብርቱ እንደ ነበር



www.eotcmk.org

ሲገልጽ፡- «የመቶ ዓመትም ሽማግሌ ስለሆነ እንደምውት የሆነውን የራሱን ሥጋና የሣራ ማኅፀን ምውት መሆኑን በእምነቱ ሳይደክም ተከተለ፤ ለእግዚ አብሔርም ክብር እየሰጠ የሰጠውንም ተስፋ ደግሞ ሊፈጽም እንዲችል አጥብቆ እየተረዳ *በእምነት በረታ፡፡»* ብሏል፡፡ ሮሜ. 4÷19-21፡፡

• ***የሞተ እምነት፡-*** እምነት ሕያው ነው፡፡ ምውት የሚያሰኘው በአማኙ ልብ ውስጥ ከተሰጠው ቦታና በሥራ ከመ ገለጡ ላይ ነው፡፡ የሞተ እምነት ያላ ቸው ሰዎች እናምናለን ብለው ስለ እምነታቸውና ከማመናቸው የተነሣ ከእ ነሱ ስለሚጠበቀው ነገር ብዙ ያውቃሉ፤ ያወራሉ፤ ያስተምራሉ፤ ተግባር ላይ ግን የሉበትም፡፡ በአጭሩ እምነታቸውን ለመተግበር መንፈሳዊ ወኔ ያጡና መልካም ሥራ ለመሥራት የሚያስችላቸው መንፈሳዊ ጉልበታቸው የሞተባቸው ናቸው፡፡ ያዕ.2÷18-26፡፡

***የአጋንንት እምነት፡-*** አጋንንት የእግዚ አብሔርን ህልውናና አምላክነት ያምናሉ፤ ስሙ ሲጠራም ይንቀጠቀጣሉ፡፡ «አለጊዜያችን አታጥፋን» ሲሉም ይማፀናሉ፡፡ ነገር ግን ልዑል እግዚአብሔ ርን ፈቃዱን የሚፈጸሙትን ዘወትር ከመዋጋትና ከመቃወም ወደ ኋላ አይሉም፡፡ የእግዚአብሔርን ልጆች /ክርስቲያኖችን/ ኃጢአት ለማሠራትና ለማስካድ ሁሌ ይተጋሉ፡፡ በመጨረሻው ቀን በዘለዓለም እሳት እንደ ሚቀጡ ቢያውቁም እንኳን «ማረን» ከማለት ይልቅ «ጊዜያችን ሳይደርስ አታጥፋን» ከማለት ውጭ የጸጸትና የንስሐ ዝንባሌ አይታይባቸውም፡፡ ይኸም ምሕረት አልባና አልመለስ ባይነታቸውን በግልጥ ያሳያል፡፡ ማቴ.8÷28-34፡፡ ከሰዎች መካከል ይህን የመሰለ እምነት ያዘሉ አይታጡም፡፡ ልዑለ ባሕርይ ጌታ እግዚ አብሔርን መጽረፍና በእርሱ ላይ መዘበት ሥልጣኔና ዕውቀት መስሏቸው ብዙዎች የአጋንንትን ሥራ ከመሥራት አልታቀቡም፡፡

## እምነትን ያቀዘቀዙ ነገሮች በዘመነ ነቢያት

• ***ስደት፡-*** እግዚአብሔርን በማምለክ ከሰው ዘር ሁሉ ቀዳሚ ታሪክ ያላቸው እስራ ኤላውያን በረኀብና በምርኮ የተነሣ ወደ አሕዛብ አገር ይሰደዱ ነበር፡፡ በተሰደዱበት አገር የሚያዩት የጣዖት አምልኮ እምነታቸውን እያቀዘቀዘባቸው ለበርካታ ጊዜ ስተዋል፡፡ ወደውም ሆነ ተገደው የተከተሉት ክፉ ልማድ ግን ጎዳቸው እንጂ አልጠቀማቸውም፡፡ ዘጸ.32÷1-35፤ ኤር.19÷3፡፡

• ***በእምነት ከማይመስሏቸው ጋር የፈጸሙት ጋብቻ፡-*** በተለያዩ ምክንያቶች ወደ አሕዛብ አገር የፈለሱ አንዳንድ እስራኤላውያን እግዚአብሔርን ከማያምኑ የአሕዛብ ሴቶች ጋር ጋብቻ መመሥረታቸው ለእምነታቸው መቀዝቀዝ ሌላው ምክንያት ሆኗል፡፡ በዚህ መሰሉ ጋብቻ የተጣላለፉት እስራ ኤላውያን በእምነት ከመቀዝቀዛቸው በተጨማሪ ለወገኖቻቸውና ለአገራቸው የነበራቸው እምነት ዝሎባቸዋል፡፡ ይህም የገዛ ወገኖቻቸውን እስከ መውጋትና ተለይቶ እስከ መቀመጥ አብቅቷቸዋል፡፡ ተረፈ ኤር.11÷26-34፤ዮሐ.4÷1-51፡፡

• ***ቅኝ አገዛዝ፡-*** በቅኝ አገዛዝ ቀንበር ሥር መውደቅ ለባህል መበረዝና ለሃይማኖት መዳከም ይዳርጋል፡፡ በዘመነ ብሉይ የነበሩ እስራኤላውያን በተለያዩ ቅኝ ገገርዎች መዳፍ ሥር የወደቁበት ጊዜ ለእምነታቸው ደንታ ቢስ የሆኑ እስራ ኤላውያን ያቆጠቆጡበት ወቅት ሆኗል፡፡ ዛሬ በቅኝ አገዛዝ ሥር ያለፉትን አገሮች ሕዝብ የባህል፣ የሥነ ምግባርና የሃይማኖት ችግር ስናይ የቅኝ አገዛዝን አስከፊ አሻራ /ጠባሳ/ እንረዳለን፡፡

## እምነትን ያቀዘቀዙ ነገሮች በዘመነ ሐዋርያት

• ***አይሁድ፡-*** አይሁድ «ከሮማውያን ቅኝ አገዛዝ ነጻ ያወጣናል» ብለው ተስፋ ያደርጉት ከነበረው ጦረኛ ንጉሥ በተለየ መንገድ የመጣውን እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስን ከሰቀሉ በኋላ የክርስትና ጉዞ የሚገታ መስሏቸው ነበር፡፡ የክርስትና መሠረት ግን የክርስቶስ ደም ነውና በኃይልና በጽናት ቀጠለ፡፡ በዚያን ጊዜ ክርስቲያኖችን ማግለል፣ መተቸትና ማሳደድ የአይሁድ ተግባር ሆኗል፡፡ ይህም ሁኔታ እምነታቸውን ያቀዘቀዘባቸው ክርስቲያኖች ከጸኑት ጋር ሲነጻጸሩ ጥቂት ቢሆኑም ግን ነበሩ፡፡

• ***የእርስ በርስ ጥል፡-*** ከይሁዳነት ወደ ክርስትና በተመለሱትና ከአሕዛባዊነት ወደ ክርስትና በተለወጡት ክርስቲያኖች መካከል የነበረው የእርስ በርስ ጥል ቁጥራቸው ይህ ነው ሊባሉ በማይችሉ ክርስቲያኖች እምነት ላይ ቀዝቃዛ ውኃ ቸለሰበታል፡፡ አይሁድ ጥምቀት ያለ ግዝረት ወንጌልም ያለ ኦሪት ማለታቸው ከቀን በኋላ ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር ለተመለሱት አሕዛብ የማይዋጥ ነገር ነበር፡፡ ካልተገዘሩትና ሁሉን ከሚበሉ /ሁሉ በአፌ/ የአሕዛብ ክርስቲያኖች ጋር በአንድ ገበታ መታደምና በምኩራብ መሰባሰብም ለአይሁድ ክርስቲያኖች የማይታሰብ ነበር፡፡ ክርስትና የተራራቁትን የሚያቀራርብ እምነት ነውና በክርስትና ሕግ መሠረት መሄድ ግድ ሆነ፡፡ ኤፌ.2÷13-19፡፡ የክርስትናን መሠረታዊ አስተምህሮ የተከተሉት በዚህ ምክንያት ከተፈጠረው ችግር ሲተርፉ ከክርስትና መሠረታዊ አስተምህሮ ይልቅ ለአይሁድ ወግና ለአሕዛባዊ ገልበጥባጣነት ራሳቸውን የገበሩ ሁሉ እምነታቸው ቀዝቅዞባቸው፣ ከእውነተኛዪቱ መንገድ ፈቀቅ እያሉ በየጥሻው ወድቀው ቀሩ፡፡

• ***በሮም ቄሣሮች የተጀመረው መከራ፡-*** የሮም ቀደምት ቄሣሮች የክርስትናን ሃይማኖት አጥብቀው ይጠሉ ነበር፡፡ እንደ እነርሱ ስጋት ክርስትና «የሮማውያንን አገዛዝ ለመገርሰስ በፍልስጥኤም ምድር የተቋቋመ ሃይማኖት ለበስ የፖለቲካ ድርጅት» ነበር፡፡ በዘመኑ በሮም ምድር የተከሠተው ረኀብና በሽታም የሮማውያን አማልክት በክርስቲያኖች ላይ ከመቆጣቸው የተነሣ የመጣ መአት ተደርጎ ይወሰድ ነበር፡፡ በተለይ ክርስትና ከእግዚአብሔር አምልኮ በስተቀር የሮም ቄሣሮችን የመመለክ ዐዋጅ ስለሚቃወም ቄሣሮቹ በቁጣ ነደዋል፡፡ በነዚህና በሌሎች ምክንያቶች የተነሣ በክርስቲያኖች ላይ መከራ ታውጇል፤ ሀብታቸው ተወር ሷል፡፡ የትኛውንም የመብት ጥያቄ ተነፍገው ነበር፡፡ ከሁሉም በላይ በሰይፍ እየታረዱ፣ ለተራቡትም አናብስት እየተጣሉ የሮምን ሕዝብ በሞታቸው እንዲያዝናኑ የተወሰነው ውሳኔ ግን መራራ ነበር፡፡ ቅዱስ ጴጥሮስንና ቅዱስ ጳውሎስን የመሳሰሉ በአዕማደ ሐዋርያት በሰማዕትነት ያለፉት በዚህ ወቅት ነበር፡፡ ጽኑአን የሆኑት በሰይፍ ስለትና ለአናብስት በመጣል ሰማዕት ሲሆኑ ከመከራው የተነሣ እምነታቸው የቀዘቀዘባቸው ግን ከክርስትና ፈቀቅ ብለዋል፡፡

## እምነትን ያቀዘቀዙ ነገሮች በዘመነ ሊቃውንት

• ***ፍልስፍና፡-*** በዚህ ዘመን የግሪክ ፍልስፍና (Hellenism) በከፍተኛ ሁኔታ የተንሰራፋበት ጊዜ ነበር፡፡ በሃይማኖት ትምህርት ውስጥ የፍልስፍና ብጣሪያቸውን ይዘው የገቡ አንዳንድ ሰዎች ለክርስትና እምነት የማይመቹ ሆነዋል፡፡ ፍልስፍናን ከሃይማኖት ይልቅ ከፍ አድርጎ ማየትም ሌላው ችግር ነበር፡፡ በዚህ የተነሣ መፍቀሬ ፍልስፍናዎች ጠፍተዋል፡፡ የነሱን ፍልስፍና በመስማትና በመከተልም ብዙዎች በእምነት ሲቀዘቅዙ የክሕደት አዘቅት ውስጥ የገቡም ነበሩበት፡፡

• ***ኑፋቄ፡-*** ዛሬ በምድር ላይ እንደ አሸን ለፈላው ልዩ ልዩ እምነት ነቆቹ /አዘቅቶቹ/ በዚያ ዘመን የነበሩ መናፍቃን ናቸው፡፡ ከእውነተኛው አምልኮ ያፈነገጠው አስተምህሮታቸውና ጥርጥራቸው የራሳቸውን የልቡና ጽዋ በኑፋቄ አተላ በመሙላት ሳያበቃ የሌሎችን እውነተኛ የእምነት ጉልበት አቀዝቅዟል፡

እንግዲህ ቀደም ብለን የእምነትን ምንነት፣ዓይነትና ደረጃ በዝርዝር ተመልክተናል፤ በዘመነ አበው፣ በዘመነ ነቢያትና በዘመነ ሊቃውንት እምነትን ያቀዘቅዙ ስለነበሩ ነገሮችም በመጠኑ ለማብራራት ሞክረናል፡፡ በቀጣዩ እትማችን ደግሞ በዘመናችን እምነትን ስለሚያዳክሙ ነገሮችና ስለ አስከፊ ውጤታቸው እንዲሁም እምነታችንን ማጠንከር ስለምንች ልባቸው መንገዶች እንመለከታለን፡፡

ይቆየን፡፡

ወስብሐት ለእግዚአብሔር



www.eotcmk.org

# ነገረ ድኅነት በመጽሐፈ ቅዳሴ

**ባለፈው እትማችን በመጽሐፈ ቅዳሴ የተገለጸውን የነገረ ድኅነት ትንታኔ የቅዳሴው ኪዳን መዳረሻ ላይ ማሳረፋችን ይታወሳል። በጸሎተ ኪዳን ውስጥ የሚገኘውን የነገረ ድኅነት ምሥጢር «ስባቱ ኪዳናት» በተሰኘው ርእሳችን ስለሚቀርብ በዚህ ዝግጅታችን ማውሳት አላስፈለገንም። ስለዚህ ጸሎተ ኪዳን እንዳለቀ ካህኑ ጌታችን በወንጌል ያስተማረውን የዘወትር ጸሎት «አቡነ ዘበሰማያት»ን ያዙና ከሕዝቡ ጋር ይጸልያሉ። /ማቴ.6÷9-15/። ከዚህ በመቀጠል ያለውን የትምህርቱን ክፍል በየተራው እንመለከታለን። መልካም ንባብ።**

/መምህር ተስፋ እንዳለ/

### ከቅዳሴው የኪዳን ጸሎት በኋላ

ካህናቱና ሕዝቡ በኅብረት «አባታችን ሆይ» ብለው ይጸልያሉ። በመቀጠልም፡- «አ ሥሉስ ቅዱስ መሐረነ ...፤ ልዩ ሦስት የምትሆን አቤቱ÷ እዘንልን፤ ራራልን፤ ይቅርም በለን» እያሉ ሥሉስ ብለው የሥላሴን ሦስትነት÷ ቅዱስ ብለው የሥላሴን አንድነት በዝማሬ ይመሰክራሉ። ይህም በአንድነትና በሦስትነት ሲመለክ ሲወደስ የኖረውና የሚኖረው አምላክ የሰውን ልጅ ለማዳን ይቅርም ለማለት ያለው አንድ ፈቃድ መሆኑን ያሳያል።

«በእርሱ ፈቃድ በአባቱ ፈቃድ በመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ መጥቶ አዳነን» እንዲል በፈቃድ አንድ ሆኖ የሰውን ልጅ ላዳነና አሁንም ለሚያድን ጌታ የአንድነት ምስጋና ይገባልና።

### የውዳሴ ሰላምታ

ቅድስተ ቅዱሳን ድንግል ማርያም «ምክንያተ ድኂን» ናትና፡- «በነቢያት ትንቢት የተነገረልሽ፣ በመላእክት ተልእኮ የምሥራች ቃልን የሰማሽ፣ ምስጋናም የቀረበልሽ፣ በንጽሕና በድንግልና ጸጋን የተመላሽ የልዑል እናት ልዕልት ሆይ÷ ደስ ይበልሽ» እያለ ካህኑ ምስጋና ያቀርባል። ሉቃ.1÷28።

«እግዚአብሔር ከሥጋሽ ሥጋ ከነፍስሽ ነፍስ ነስቶ ባንቺ ይዋሐድ÷ ተዋሕዶም ዓለምን ያድን ዘንድ አንድያ ልጁን ሰጥቶአልና ካንቺ ጋር ነው።» እያሉ ሕዝቡ ነገረ ድኅነትን በምስጋና ቃል ይናገራሉ። ዮሐ.3÷16፤ 1÷29።

«ከተመረጡት ጋር ቃል ኪዳንን ያደረገና የሚያደርግ ተወዳጅ ልጅሽን የተናገረውን የማያስቀር ነውና በተሰጠሽ የማይለወጥ ቃል ኪዳን ለምኝልን» እያለ ካህኑ ሲማፀን ሕዝቡም፡- «ሁሉን በሥልጣኑ የሚያደርግ፣ በቃሉ ፈውስን፣ በደሙ የኃጢአት ስርየትን የሚሰጥ እርሱ ነው» ይላሉ። ኢሳ. 14÷24፤ 1ኛ ዮሐ.1÷7።

### ጸሎተ ወንጌል

ወንጌል የእግዚአብሔር ልጅ የዲያብሎስን ሥራ ያፈርስ ዘንድ ሰው እንደ ሆነ፣ ዲያብሎስም ድል እንደ ተመታ፤ ከክብር ተራቁቶ በበደል ወድቆ የነበረው የሰው ልጅ በአምላኩ ልዩ የማዳን ሥራ እንደ ከበረ ይናገራል። ዮሐ.1÷12 ና 29፤ ሉቃ.2 ÷10-11። ስለዚህ ወንጌል ከመነበቡ አስቀድሞ ካህኑ፡- «አቤቱ÷ አምላካችን እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፡- ቅዱሳን የሚሆኑ ደቀ መዛሙርትህንና ንጹሐን ሐዋ ርያትን እንዲህ ያልሃቸው፡- እናንተ የምታዩትን ያዩ ዘንድ ብዙ ነቢያት ጻድቃን ወደዱ አላዩም፤ እናንተ ዛሬ የምትሰሙትንም ይሰሙ ዘንድ ወደዱ አልሰሙም፤ የእናንተ ያዩ ዐይኖቻችሁና የሰሙ ጆሮዎቻችሁ ግን የተመሰገኑ ናቸው» እያለ ይጸልያል።

ከባሕርይ አባቱ ከአብ ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በአንድ ሥልጣን ይህን ዓለም የፈጠረና የፈጠረውንም ዓለም ማኅለፍ የሚቻለው ወልድ በዘመኑ ፍጻሜ ዓለምን ለማዳን ሰው መሆኑ እግዚአብሔርነቱን አላሳጣውምና፡- «አምላካችን እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ» በማለት ካህኑ ጸሎትን ሲጀምር ይሰማል። ፊልጵ.2÷5-9።

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን እግዚአብሔርነት /የባሕርይ አምላክነት/ ማወቅና ማመን ለአንድ ሰው ድኅነት አስፈላጊ ከሆኑት ምሥጢራት ውስጥ የመጀመሪያው ነው። ካህኑም በጸሎቱ መጀመሪያ ላይ በዜማ /በንባብ/ ይህን የሚያውጀው ንኡስ ክርስቲያኖች በእምነታቸው እንዲያድጉ፣ ተጠራጣሪዎች ደግሞ መንፈሳቸው ከጥርጥር እንዲላቀቅና እንዲድኑ ያመኑትም በአንድ ልብ እንዲጸኑ ነው።

ጌታችንም በዘመነ ሥጋዌው ባቀረበው ጸሎትና ትምህርት፡- «እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንህ አንተን የላክኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘለ ዓለም ሕይወት ናት።» ብሏል። ዮሐ.17÷3።

ጌታችን ቅዱሳን ሐዋርያትን፡- በተዋሕዶ ተገልጦ የምታዩትን ሥግው ቃል የሚያዩ ዐይኖቻችሁ /የልቡና ችሁ ዐይኖች/ ምስጉኖች ናቸው። በቃል ሰብአዊ ሲያስተምር ሰምታችሁታልና ጆሮዎቻችሁ /የልቡናችሁ ጆሮች/ ንዑዳን ናቸው። እናንተ አሁን በተዋሕዶ ሆኖ የምታዩትን «ቀዳማዊ ቃል» ለማየት ብዙ ነቢያት ሽተው ነበር፤ ግን አላዩም፤ አረፍተ ዘመን ገቶአቸዋልና።

ብዙ ጻድቃንም /እነ አብርሃም፣ ይሥሐቅ፣ ያዕቆብ... / ፈልገው ነበር፤ ግን አልቻሉም፤ የሞትን ድንበር መሻገር አልተቻላቸውምና። ትምህርቴን የሰሙ ጆሮዎቻችሁ ተአምራቴን ያዩ ዐይኖቻችሁ ንዑዳን ክቡራን ናቸው ያላቸውን እያሳሰበ፡- «እኛንም የወንጌልን ቃል እንድንሰማ፣ ሰምተንም የሚያበቃንን ሥራ እንድንሠራ አድርገን፤ በቅዱሳን ጸሎት በካህናት ልመና እርዳን።» ይላል። ሉቃ.10÷23።

ሰው ካልሰማ አያውቅም፤ አያምንም፤ ካላመነም አይሠራም። ለድኅነት የሚያበቃውን ሥራ ካልሠራም አይድንም። ለድኅነት የሚያበቃውን ሥራ ለመሥራት ወንጌልን በእምነት መስማት አለበት። «እምነት ከመስማት ነው። መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው።» ተብሏል። ሮሜ.10÷17።

/ወደ ገጽ ፲፮ ዞሯል/



ሠራዒው ዲያቆን በጸሎተ ቅዳሴው የሥርዐተ ቅዳሴ ክፍል መልእክተ ጳውሎስን ሲያነብ



www.eotcmk.org

# ተሠግዎተ ቃል

/20ኛው የእስክንድርያ ፓትርያርክ ሐዋርያዊ ቅዱስ አትናቴዎስ እንደ ጻፈው/

/ዲ/ን ያረጋል አበጋዝ/

## የዚህ ጽሑፍ ዓላማ እግዚአብሔር በቃሉ ይህን ዓለም መፍጠሩን፣ የቃለ እግዚአብሔርን ሥጋ መሆንና ዓለምን ማዳኑን ማየት ነው::

የቃልን ሥጋ መሆንና የመለኮት መገለጥን÷ ሃይማኖታችንን እንገንዘብ፤ እና ስተውል:: /1ጢሞ.3÷16/:: ይህም አይሁድ የሚያቃልሉት ግሪኮች የሚያፌዙበትና የሚሥቁበት÷ እኛ ግን የምናመልከው ነው፤ ቃል የተዋረደ የመሰለ ያህል እኛ የበለጠ ይህን እንዳደረገልን ዐውቀን እናመስግነው:: በአሕዛብ ዘንድ በተፌዘበት መጠን ለአምላክነቱ መመስከር ይገባናልና:: ለሰው የማይቻል የመሰለውን ነገር /ሰው መሆንን/ ፈጽሞ አልና÷ «ሰው ብቻ ነው» ብለው የሚቀልዱትን ሰነፎች በመስቀሉ /በተዋርዶ በሞተበት/ የጣዖታትን ሐሰት በመግለጽ እና በስውር ያሉ መናፍስትን አምላክነቱን እንዲያውቁ በማድረግ አሳፍሮአቸዋልና:: ሥጋ የሌለው ቃል እኛን ከመውደዱ የተነሣ ሥጋን ተዋሐደ፤ ዓለሙን በፈጠረበት በቃሉ እግዚአብሔር ዓለሙን ሊያድነው መውደዱ ተገቢ ነውና::

✠ ✠ ✠

ኢፒኩሪያንስ እንደ ሚሉት እያንዳንዱ ነገር በራሱ ከተገኘና ያለ ዓላማ አንድነት የተገኘ ከሆነ እያንዳንዱ ነገር አንድ ዓይነትና ተመሳሳይ ኾኖ እንዲሁ በራሱ መጥፋቱአል ማለት ነው:: እንዲህ ከሆነ ከሰውነት /አካል/ አንድነት የተነሣ ሁሉም ነገር ፀሐይ ወይም ጨረቃ ወይም መሬት... ወዘተ መሆን ነበረበት ወይም ከሰው ደግሞ ሁሉም አካሉ እጅ ወይም እግር ወይም ዐይን ... መሆን ነበረበት:: ነገር ግን የተለያዩ ሥነ ፍጥረታት ቅንጅት የሚያሳየው በራሳቸው መምጣታቸውን ሳይሆን አስገኝ ያላቸው መሆኑን ነው:: አስገኛቸውም የሁሉም መገኛ እግዚአብሔር ነው::

ፕላቶና መሰሎቹ ደግሞ «ቀድሞ ከነበረና መጀመሪያ ከሌለው ነገር /Pre-existing matter/ ዓለምን ፈጠረ» ይላሉ:: እግዚአብሔር የፍጥረታት መገኛ ካልሆነና የነበረ ነገርን ብቻ ተጠቅሞ ከፈጠረ ጥንቱ ነገሩ ባይኖር ምንም ማድረግ የማይችል ደካማ መሆኑ ነው /አናፂ ያለ እንጨት ምንም ማድረግ እንደ ማይችል ኹሉ/፤ እንዲህ ከሆነ እግዚአብሔር እንደ መካኒክ እንጂ ፈጣሪ አይባልም::

*እውነተኛው እምነት÷ ፍጥረት የእግዚአብሔር ሥራ መሆኑን ማመን ነው::*

ፍጥረት በድንገት ሳይሆን አስቀድሞ በታሰበ ሁኔታ፣ ከነበረ ነገር ሳይሆን እምኀበ አልቦ / እግዚአብሔር ደካማ አይደለምና/ በቃሉ ዓለምን ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቶ ፈጠረ:: ዘፍ.1÷1፤ ዕብ.11÷3::

ሰውን ግን መፍጠር ብቻ ሳይሆን /ግእዛን የሌላቸውን ሌሎች ፍጥረታትን እንደ ፈጠረው ሳይሆን/ በአርአያውና በአምሳሉ አስተዋይና አሳቢ አድርጎ በቅድስናና በንጽሕና ይኖር ዘንድ ፈጠረው::

የሰው ፈቃድ ወደ ቀኝም ወደ ግራም ሊዋልል እንደ ሚችል ዐውቆ በሕግና በቦታ እንዲጠበቅ /ሕግ በመስጠት÷ ቦታ በመወሰን/ አደረገው::

ዘፍ.2÷16፡- «መልካምንና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ፤ ከእርሱ በበላችሁ ቀን ሞትን ትሞታላችሁ» አለ:: ይህም ሞቶ መጥፋትና እንዳልተፈጠሩ መሆን ሳይሆን በሞት ጥላ ውስጥ ለዘላለም መኖር ነው::

✠ ✠ ✠

*ሰው ለመሆኑ ምክንያቶቹ እኛ ሰዎች ነን፤ ስለ እኛ ድኅነት ሲል ሰው ሆኖ ለመገለጥና ለመወለድ በፍቅሩ ወዶአልና::*

እግዚአብሔር ሰውን ፈጥሮ በሕያውነት እንዲኖር ቢፈልግም ሰው ግን ፈጣሪውን በመተው በማስጠንቀቂያ የነገረውን ሞት በራሱ ላይ በማምጣቱ እንደ ተፈጠረው መኖር አልቻለም:: ሞት ገዛው፤ መፍረስ መበስበስ ተከተለው፤ ከምንም ነገር እንደ ተፈጠረና በቃሉ ሕይወትን እንዳገኘ÷ የሰጠውን ሕጉን በተላለፈ ጊዜ ኃጢአቱ ወደ ጥንት ሁኔታው ማለትም ወደ መፍረስና መበስበስ መለሰው::

ሰው ካለመኖር ወደ መኖር በቃል ከተፈጠረ በኋላ የተሰጠውን ሕግ ሲያፈርስ ሊፈርስና ሊሞት ይገባዋልና::

«ሕጉን መጠበቅ የሕይወት መሠረት ነው» /ጥበብ.6÷18/ እንዳለ ሕጉን ቢጠብቅ ለዘለዓለም በኖረ ነበር፤ «እኔ ግን አማልክት ናችሁ÷ ሁላችሁም የልዑል ልጆች ናችሁ አልሁ» እንደ ተባለ:: መዝ.81÷6፤ ሮሜ.5÷14::

ስለዚህ እግዚአብሔር እኛን ከምንም መፍጠር ብቻ ሳይሆን በቸርነቱ ከእርሱ ጋር ተነጻጻሪ የሆነ ሕይወትን ሰጠን:: ሰዎች ግን በስንፍናቸውና ምክረ ሰይጣንን ባለመቀበል አለመሞት ሲችሉ በማጥፋታቸው ሞትን አመጡ:: ጥበብ.2÷23::

ሰው ካጠፋ በኋላ መሞት ጀመረ፤ ጥፋት ነገሠበት:: ከዚህ በኋላ ሰው በጥፋት ላይ ጥፋትን እየጨመረ ሄደ:: ኃጢአት የማይጠግብ ሆኖ በግልም በማኅበርም ንቅስ ጥቅስ አድርጎ ኃጢአትን ሠራ:: ሮሜ.1÷26::

ስለዚህ በእግዚአብሔር አርአያ የተፈጠረው ሰው ሞት ነግሦበት፣ መፍረስ መበስበስ ሠልጥኖበት ሞት ሕጋዊ ግዛቱ አደረገው፤ ምክንያቱም ሕጉ ሊሻርና ሳይፈጸም አይቻልምና:: /ዘፍ.2÷17/::

እግዚአብሔር «በበላህ ቀን ትሞታለህ» ያለው ሕግ አለና አዳም ካጠፋ በኋላ ባይሞት የእግዚአብሔር ቃል ታበለ ማለት ነው፤ ሰው ሕጉን አፍርሶ ትእዛዙን ጥሶ ሳለ ባይሞት እውነተኛ አይኾንምና ይህ ተገቢ አይደለም:: እንዲሁም ደግሞ በቃሉ ተፈጥሮ የጸጋው ተሳታፊ ኾኖ ከተፈጠረ በኋላ ወደ ጥፋትና መበስበስ ሄዶ ያለ መሥዋዕት ተወገዶለት ወደ መኖር መመለስ ተገቢና ምክንያታዊ አይሆንም:: የፈጠረው ፍጥረት በዲያብሎስ ምክር ምክንያት መጥፋቱ ከእግዚአብሔር ቸርነት ጋር አይስማማምና÷ የእርሱ የእጅ ሥራ በራሱ በሰው ስንፍናም ሆነ በዲያብሎስ ተንኰል ይጠፋ ዘንድ ተገቢ አልነበረም::

እንዲህ ዐዋቂ የሆነው ፍጥረት ሲጠፋ እግዚአብሔር በቸርነቱ ምን ማድረግ ነበረበት? የተፈረደበት የሞት ፍርድ እንዲገዛውና እንዲጠፋ መተው፤ እንዲህ ከሆነ የመፍጠሩ ጥቅም የት ላይ ነው? ነገር ግን አንዴ ከፈጠረ በኋላ በእርሱ በፈጣሪው ፊት ፍጥረቱ ሲጠፋ ማየት ምክንያታዊ አይደለም:: ስለዚህ ሰውን ለሞትና ለጥፋት እንደ ተሰጠ መተው ከእግዚአብሔር ቸርነትና ደግነት ጋር የማይሄድ ነው::

✠ ✠ ✠

በሌላ በኩል ደግሞ /ፍጡሩን መተው የማይታሰብ መሆኑ እንደ ተጠበቀ ሆኖ/ የእግዚአብሔር ሕግና ፈታሒነት መጠበቅ አለበት:: ሞትን በተመለከተ የተናገረውና የሠራው ሕግ መጠበቅና እውነት መሆን አለበት:: እኛን ለማዳንና ከሞት ለማውጣት ሲል ሐሰተኛ መሆን የለበትም:: ስለዚህ ምን ማድረግ ነበረበት?

*ሰው ንስሐ እንዲገባ ማድረግ /በንስሐ ማዳን/*

በስሕተት መዋቲ እንደ ሆነ በንስሐ ሕይወቱን መመለስ? ነገር ግን ንስሐ፡-

የእግዚአብሔርን ርቱዕ ፍርድ



www.eotcmk.org

አያስጠብቅም፤ ሰው ትሞታለህ ተብሎ ተፈርዶበት እያለ በምንም ምክንያት ይሁን ያን ሞት ካልሞተ ፍርዱ የት ላይ ተፈጸመ? ንስሐ ከኃጢአት ያነጻል እንጂ ሕጉን በማፍረስ ያጡትን ሕያውነት ወደ ባሕርይው አይመልስም:: የተሠራው ኃጢአት ትንሽ ጥፋት ቢሆንና የመሞት የመጥፋት ጉዳይ ባይሆን ኖሮ ንስሐ ሊበቃ ይችል ነበር:: ነገር ግን መተላለፍ ከተደረገ ጀምሮ ሰው በተፈጥሮው ባለ ሞትና መበስበስ መጠቃት ጀምሮአል፤ የተሰጠው ጸጋ ተነስቶታል:: ስለዚህ ይህን ጸጋ ለመመለስና ወደ ባሕርይ የገባ ሞትን ለማስወጣት ምን ያስፈልግ ነበር? የእግዚአብሔር ቃል ሰውን መጀመሪያ ከምንም እንደፈጠረው የሚሞተውን ወደማይ ሞት ሕያውነት ማምጣት እና የእግዚአብሔርን ርቱዕ ሕግ በጠበቀ መልኩ በአንድ ጊዜ መፈጸም፤ ሁለቱም የእርሱ ነውና:: የአብ ቃል እንደ መሆኑና የሁሉ አስገኝ እንደ መሆኑ እርሱ ብቻ ነው ሁሉንም እንደገና ሊያድስና ስለ ሰው ሁሉ መከራ መቀበልና ስለ ሁሉም የሰው ጉዳይ ከራሱና ከአባቱ አስታራቂ ሊሆን የሚችለው::

✠ ✠ ✠

ስለዚህ ምክንያት የማይሞተውና የማይለወጠው መለኮታዊ ቃል ወደ እኛ መጣ፤ /የሐዋ.17÷7/፤ ከአባቱ ሳይለይ ወረደ÷ በትሕትና ፍቅሩን ሊገልጽ ሊጐበኘን መጣ::

- የሰው ዘር በጥፋት ላይ መሆኑን÷ ሞት መንገሡን ሕጉም በሰው ላይ ሳይፈጸም ቢቀር ምክንያታዊና ተገቢ አይደለምና ሰውም በየጊዜው በደልን እየጨመረ መሄዱን እንዲሁም ሰው ሁሉ በሞት ጥላ ሥር መሆኑን ዐይቶ ራራልን÷ ይቅር አለን÷ ወደ እኛ መቶ ራሱን አዋረደ÷ ሞት ለዘላለም ሰውን ከገዛው የሰው ፍጥረት እንዳይጠፋ የእጁ ሥራ በከንቱ እንዳይቀር የእኛን ሥጋ ተዋሐደ:: መገለጥ ብቻ ሳይሆን ባሕርያችንን ተዋሐደ:: መገለጥ ብቻ ቢፈልግ መለኮታዊ መገለጡን በሌላ አስደናቂ ሁኔታ መፈጸም ይችል ነበርና:: በድንግል ማኅፀን አደረ፤ በዚህም ራሱን ገለጠ:: ከእኛ በተዋሐደው ባሕርያችን /ሁሉም በሞት ጥላ ሥር ነበርና/ ራሱን ስለ ሁላችን ለሞት ሰጠ፤ ለአባቱም መሥዋዕት አድርጎ አቀረበ:: በዚህም:-

ሀ/ ስለ ሁሉም በመሞቱ በሰው ላይ ሞትን ያመጣው ሕግ ተፈጽሞ ያበቃ÷ ይወገድ ዘንድ /የሞት ያለ ኃይሉ ሁሉ በጌታችን ሰውነት ላይ ባረፈ ጊዜ ተፈጽሞአልና ከዚያ በኋላ የርሱን ወገኖች የሚይዝበትና የሚገዛበት መሠረትና ኃይል የውምና/፤

ለ/ ሰው ሁሉ ወደ መፍረስ መበስበስ ወርዶአልና ሰውን ሁሉ ወደ ኣለመበስበስና ሕያውነት ለመመለስ÷ በትንሣኤው ኃይል ሞትንና የሞትን ኃይል ፈጽሞ ይነቅለውና ያጠፋው ዘንድ፤

✠ ✠ ✠

በመሞት ካልሆነ በቀር የሰው ሞት ሊወገድ እንደ ማይችል የእግዚአብሔር ቃል ባየ ጊዜ እርሱ በባሕርይው የማይሞት ስለሆነ ስለ ሁሉም መሞት ይችል ዘንድ የሚሞት የእኛን ባሕርይ ተዋሐደ፤ የእኛም ባሕርይ ከተዋሐደው ቃል የተነሣ የማይሞት ይሆን ዘንድ÷ መፍረስና መበስበስም በትንሣኤ ይጠፋ ዘንደ:-

- የነሳውን ሥጋ ከበደል ንጹሕ የኾነ መሥዋዕት አድርጎ በማቅረብና ለሞት በመስጠት ሞትን ከወገኖቹ አስወገደ::

- የሞትን ዕዳ ሞትን በመክፈል አስወገደልን::

- ሞትና ጥፋት ከእኛ ጋር ከተዋሐደው ቃል የተነሣ እኛን ሊገዛና ሊይዝ አልተቻለውም::

- የሁሉ ጌታና መድኃኒት መጥቶ ሞትን ድል ባያደርገው ኖሮ የሰው ዘር ጠፊ ነበር::

✠ ✠ ✠

ይህ ታላቅ የማዳን ሥራ ለእግዚአብሔር ቸርነት የተገባ ነው:: አንድ ቤት ወይም ከተማ ከነዋሪዎቹ ስንፍና የተነሣ በሽፍታ ቢጠቃ ሽፍታውን ተበቅሎ ወደ ራሱ ይዞታ ይመልሰዋል፤ እግዚአብሔር ደግሞ በበለጠ ሁኔታ ሰው ሲጠፋ ሲያይ ራሱን ለሞት አሳልፎ በመስጠት ሞትን ካስወገደ በኋላ የሰውን አለማወቅና ስንፍና በትምህርቱ አስተካከለ፤ ለሰው ተሰጥቶት የነበረውን ሁሉ በኃይሉና በሥልጣኑ መለሰ::

«አንዱ ስለ ሁሉ ሞተ፤ እንግዲያስ ሁሉ ሞቱ፣ በሕይወትም ያሉት ስለ እነርሱ ለሞተውና ለተነሣው እንጂ ወደ ፊት ለራሳቸው እንዳይኖሩ ስለ ሁሉ ሞተ::» 2ቆሮ.5÷14-15::

«ወይደልዎ ለውእቱ ዘበእዴሁ ኵሎ ወዘእምኔሁ ኵሎ ወብዙኃነ ውሉደ አብአ ውስተ ስብሐት መልአከ ሕይወቶሙ ከመ ይፈጽም በሕማማት፤ ብዙ ልጆችን ወደ ክብር ሲያመጣ የመዳናቸውን ራስ በመከራ ይፈጽም ዘንድ ከእርሱ የተነሣ ሁሉ በእርሱም ሁሉ ለሆነ ለእርሱ ተገብቶበታልና::» ዕብ.2÷10::

ይህም ማለት ሰውን ከወደቀበት ለማንሣትና ወደ ሕይወት ለማምጣት በመጀመሪያም ከፈጠረው ከእግዚአብሔር ቃል በቀር በሌላ ተገቢ አይደለም /እንደ ቃል ለዚህ ተገቢ የለም/ ማለት ነው::

እርሱ እንደ ተዋሐደው ሥጋ ያለ ለሆኑ ሥጋውያን ሰዎች ሁሉ ቤዛ ይሆን ዘንድ:- «ልጆቹ በሥጋና በደም እንደ ሚካፈሉ እርሱም እንዲሁ ተካፈለ፤ በሞቱ በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን ይሽረው ዘንድ ይኸውም ዲያብሎስ ነው፤ በሕይወታቸው ዘመን ስለ ሞት ፍርሃት በባርነት ይታሰሩ የነበሩትን ሁሉ ነጻ ያወጣ ዘንድ::» ዕብ.2÷14 እና 15::

የራሱን ሰውነት በመሠዋት በእኛ ላይ የነበረውን ሕግ /ትሞታለህ የሚለውን/ አስወገደልን:: እንዲሁም በሰጠን ተስፋ ትንሣኤ አዲስ ሕይወት ጀመረልን:: ሞት በሰው /በአዳም/ በኩል መጥቶ በሰው ላይ እንደ ነገሠ በዚሁ ምክንያት /መንገድ/ ሰው በሆነ የእግዚአብሔር ቃል ሞት ተወገደ፤ ትንሣኤ ሕይወት ተገኘ፤ ቅዱስ ጳውሎስ:- «ሞት በሰው በኩል ስለ መጣ ትንሣኤ ሙታን በሰው በኩል ሆኖአልና ሁሉ በአዳም እንደ ሚሞቱ እንዲሁ ሁሉ በክርስቶስ ደግሞ ሕያዋን ይሆናሉና::» እንዳለ:: 1ቆሮ.15÷21-22::

ከአሁን በኋላ እንደ ቀድሞው ለኵነኔ አንሞትምና፤ ነገር ግን ከሞት ተነሥቶ የሁሉንም ትንሣኤ እንደ ሚጠብቅ ሰው በራሱ ጊዜ ለሚያደርገው ትንሣኤ ዘጉባኤን እንጠብቃለን:: 1ጢሞ.6÷15:: *ይህ የመጀመሪያው መድኃኒታችን ሰው የሆነበት ምክንያት ነው::*

✠ ✠ ✠

ሁለተኛው የአምላክ ሰው መሆን ምክንያት÷ በቃሉ ሰውን የፈጠረ እግዚአብሔር ሰው እርሱን ማወቅ እንዳልቻለና ከእርሱ በሕግ በአምልኮት እንደ ራቀ አይቶ እርሱን ሳያውቁ በከንቱ እንዲቀሩ ከቸርነቱ የተነሣ አልፈቀደም /አልተወንም/÷ መኖራቸው ምንም ምን ጥቅም የሌለው እንዳይሆን፤

ፍጥረት ፈጣሪውን ካላወቀ ምን ይጠቀማል? የአብን ቃል ካላወቁስ እንዴት ዐዋቂዎች ይሆናሉ? በእርሱ ተፈጥረው ሕይወታቸውን ያገኙበት ነውና÷ ምድራዊ ነገርን ብቻ ካወቀ ሰውን ከእንስሳት ምን ይለየዋል?

እግዚአብሔርስ እነርሱ እንዲያውቁት የማይፈልግ ይመስል ለምን ከጥንቱ ፈጠረው?

ይህ እንዳይሆን /ሰው ፈጣሪውን የማያውቅ እንዳይሆን/ ቸር ስለሆነ በአርአያውና በአምሳሉ ፈጠረው፤ በዚህ ጸጋ ፈጣሪውን ያስብና ያውቅ ዘንድ÷ ፈጣሪውን ዐውቆም በደስታና በቅድስና ይኖር ዘንድ::

ሰው ግን በራሱ ስንፍናና አጥፊነት የተደረገለትን ረስቶ፣ በጸጋው መጠቀምን ትቶ እግዚአብሔርን መርሳት ብቻ ሳይሆን ነፍሱን በማደንቆር የተለያየ የእጅ ሥራንና ፈጠራን ለራሱ አዘጋጀ፤ ጣዖት መሥራት ብቻ ሳይሆን÷ በፈጣሪ ፈንታ የተፈጠረውን ማምለክ ብቻ ሳይሆን ከዚህ በባሰ የእግዚአብሔርን ክብር ለዕቃውና ለድንጋዩ ለቁሳቁሱ ሁሉ ለሰው ሳይቀር ሰጠ፤ ከዚህም በባሰ ሄደ፣ አጋንንትንም እስከ ማምለክ ደረሰ::

ሰው በእብደት ላይ እብደትን ጨመረ:: በዚህም ምክንያት መተትና ጥንቆላ ተስፋፋ÷ ሰውን አሳሳተ÷ ሰውም የመወለዱንና የሕይወቱን ነገር ከከዋብትና በሰማይ ካሉ ነገሮች ጋር አያይዞ ከሚታየው ያለፈ ነገር ሊያስብ አልቻለም::

በአጭሩ ሁሉም ነገር በክሕደትና በሥርዐት አልበኝነት የተመላ ነበር:: እግዚአብሔር ብቻ ነበር ያልታወቀው÷ ራሱን በመግቦቱና በፍጥረቱ ሁል ጊዜ ቢገልጥም እርሱን ሁሉም ረሳው::

በእግዚአብሔር አርአያና አምሳል የመፈጠር ጸጋ በራሱ ሰው እግዚአብሔርን እንዲያውቀው ያስችለው ነበር:: ቢሆንም እግዚአብሔር የሰውን



www.eotcmk.org

ግዴለሽነትና ድካም በማየት ሥነ ፍጥረትን *አዘጋጀ*፤ ሮሜ.1÷19-20:: ሰው በራሱ በተሰጠው ጸጋ ማወቅ ባይችል በሥነ ፍጥረት ፈጣሪውን ሳያውቅ እንዳይቀር ዕድል ሰጠ፤ አሁንም በግዴለሽነቱ ሰው ቀስ በቀስ እየወረደ ወደ ተዋርዶ ስለ ሄደ ለዚሁም ድካም ሕግ በመሥራት፣ ነቢያትን በመላክ ሌላ ዕድል ሰጠ፤ ሰው ከድካሙ የተነሣ የራሱን ኅሊና አዘጋጅቶ ፈጣሪውን ማወቅ ቢያቅተው ከቅርቡና አብረውት ካሉ ሰዎች ይማርና ያውቅ ዘንድ÷ ሰዎች ከሰዎች ብዙ ነገርን በቀጥታ መማር ይችላሉና:: ወደ ሰማይ ተመልክቶ የሥነ ፍጥረትን ስምምነትና ሥርዐት ተረድቶ ፈጣሪውንና ገዥውን ማወቅ ይችሉ ነበር:: ይኽም ባይሆን በነቢያትና በሕግ ማወቅ ይችል ነበር:: ሕግን በማወቅ ከኃጢአት ሁሉ ለመራቅና የቅድስና ሕይወትን ለመኖር ይችል ነበር::

የእግዚአብሔር ቸርነትና መልካምነት እንዲህ ብዙ ሲሆን ሰው ግን በጊዜያዊ ተድላ ደስታ በመሸነፍና በአጋንንት ምትሀት በመታለል ራሱን ወደ እውነት መምራት አልቻለም:: አእምሮ ያለውና የሚያስብ መሆኑ እስኪ ያጠራጥር ድረስ ራሱን በከፋ ኃጢአትና ክፋት ውስጥ እየጨመረ ሄደ::

✠ ✠ ✠

ሰው በአጋንንታዊ ምትሀትና በራሱ አረመኔ ሥራ እግዚአብሔርን ማወቅ ተስኖት በጨለማ እያለ እግዚአብሔር ምን ያድርግ? ዝም ብሎ ሰዎች በአጋንንት ሲታለሉና ሲጠፉ ማየት? እንዲህ ከሆን የሰው በአርአያው መፈጠር ከጥንቱ ምን ፋይዳ ነበረው? ምን ጥቅም አለው? ከጥንቱ እንደ እንስሳት ቢፈጠር ይሻለው ነበር፤ ዐዋቂ ሆኖ ተፈጥሮ እንደ እንስሳት አላዋቂ ከሚሆን፣ እግዚአብሔርን ማወቅ መጀመሪያ ተሰጥቶት በኋላ ሳይመለስለት ከሚነሳው ጥንቱን ባይሰጠው በተሻለ ነበር::

በእርሱ የተፈጠረ ሰው ፈጣሪዬ ሌላ ነው ብሎ እያሰበ ካላወቀውና ካላመለከው እግዚአብሔርስ ምን ይጠቀማል? በምን ይመሰገናል? እግዚአብሐር ሰውን ለራሱ ሳይሆን *ለሌላ አገልጋይነት የሠራውና* የፈጠረው አድርጎ ያሳያልና፤ ምድራዊ ንጉሥ እንኳ በግዛት የያዘውን ቦታ ለሌላ አሳልፎ አይሰጥም:: እንዲሁ በእርሱ አርአያ የተፈጠረ ሰው ሊጠፋ አይገባምና የሌላ አገልጋይ ሆኖ የፈጠረውን ሳያውቅ ሊቀር አይገባምና::

ስለዚህ ሰው ፈጣሪውን *እንደገና እንዲያውቅ ለማድረግ ምን መደረግ አለበት?* የእግዚአብሔር የባሕርይ ልጅ በሆነ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ ካልሆነ በቀር ይህ እንዴት ሊፈጸም ይችል ነበር? በሰው ሊሆን አይችልም፤ በመላእክትም አይሆንም:: ስለዚህ የእግዚአብሔር ቃል ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ሥጋን ተዋሕዶ አደሰው:: እግዚአብሔር ሰውን በሐዲስ ተፈጥሮ ያድሰው ዘንድ መጣ::

መዋቲ ሰውነትን ሲዋሐድ ሞት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ይወገድ ዘንድ፣ ሰው ይታደስ ዘንድ ይህንንም ከእግዚአብሔር አርአያ /ቃል/ በቀር ለሌላ የተገባና የሚሆን አልነበረም:: ዕብ.1÷2-3፤ ቆላ.1÷15::

በእንጨት ላይ የተሠራ ምስል ሲቆሸሽና ሲያረጅ ባለቤቱ እንደሚያድሰው÷ ሥዕሉ ያለበትን እንጨቱን በመጣል ሳይሆን ከውጭ መጥቶ ሥዕሉን ያበላሸውን በማስወገድ ወደ ጥንት ሁኔታውና ይዞታው ለመመለስ እንደሚጥር ሁሉ የእግዚአብሔር ቃል በእርሱ አርአያ የተፈጠረ ሰውን ኃጢአቱን በማስተስረይ ሊያድሰውና የጠፋውን ሊፈልግና ሊያድን መጥቶአልና::» እንዳለ:: ሉቃ.19÷10::

ነገር ግን ዓለሙን ሁሉ ጣዖትና ኃጢአት ሞልቶት ባለበት ሁኔታ እና የእግዚአብሔር ዕውቀት ተሰውሮ ባለበት ሁኔታ ዓለሙን ስለ እግዚአብሔር ማስተማርና ማሳወቅ የማን ድርሻ ነው?

የሰው ነውን? ከፀሐይ በታች ያለውን ሁሉ ማዳረስ ለሰው አይቻለውም፤ ይህን ሁሉ የመድረስ አካላዊ ብቃትም ሆነ የርኩሳን መናፍስትን ማታለልና ፈተና መቋቋም አይችልም:: ሁሉም ከአጋንንት ምትሃታዊ ሥራና ከጣዖታት መብዛት የተነሣ በነፍሱ ተቅበዝብዞና ተምታትቶበት ባለበት ሁኔታ የሰውን ነፍስና አእምሮ ማሳመንና ማሸነፍ እንዴት ይችል ነበር? ሰው ነፍስንና ኅሊናን የማያይ ስለሆነ የማያየውን እንዴት አድርጎ ሊለውጥ ይችላል?

ስለዚህ ይህን ሥራ ማን ያደርገው ዘንድ ይችላል? የእግዚአብሔር ቃል ነፍስንና ኅሊናን የሚያይ፣ ለሁሉም ፍጥረት ኃይልና ሕይወትን የሚሰጥ፣ በእነርሱም አባቱን እንዲያውቁት የሚያደርግ እርሱ ብቻ ነው ይህን ሊያደርግ የሚችለው::

ይኽን እንዴት ይፈጽመው? እንደ ቀድሞ በፍጥረቱ ህልዎቱን ማሳወቅ፤ ሆኖም ግን ይህ አስተማማኝ መንገድ አይደለም፤ እንዲያውም በተቃራኒው ሰዎች የፍጥረትን ፈጣሪ ለማወቅ ወደ ላይ ከማየት ይልቅ ወደ ታች ወደ ፍጡራን በማየት ፍጥረታትን ወደ ማምለክ ደርሰዋልና::

ስለዚህ ሰውን ለማዳንና ለመጥቀም ሰው ሆኖ መጣ:: ከዚህ በፊት አምላክነቱንና ገዢነቱን ያላወቀ አሁን ሰው ሆኖ በሚሠራው ሥራ እርሱን /ቃልን/ እና አባቱን ያውቅ ዘንድ ሰው ሆኖ ከሰው ጋር ተመላለሰ::

# ነገረ ድኅነት ...

/ከገጽ ፲፫ የዞረ/

ሰምቶም እንደ አጋንንት አምኖ ብቻ ዝም ቢል እምነቱ ዋጋ አይኖረውም፤ በሥራ አልተተረጐመምና:: «ቃሉን የምታደርጉ ሁኑ» የተባለውም ለዚህ ነው:: ያዕ.1÷22:: ስለሆነም በአስተውሎት ለመስማትም ሆነ አምነው የተቀበሉትን ቃል በተግባር ለመግለጥ እንዲሁም ድኅነትን ፍጹም ለማድረግ የቅዱሳን ረድኤትና የአማላጅነታቸው በረከት በእጅጉ ያስፈልጋል:: ቅዱስ ዳዊት:- «ዋጋዬን እስክትሰጠኝ ድረስ ጻድቃን እኔን ይጠብቃሉ» ማለቱ ለዚህ ነው:: መዝ.14÷7::

ዲያቆኑ:- «የወንጌልን ቃል ለመስማት ሰምተንም ለመሥራት አብቃን ብላችሁ ጸልዩ» ሲል «ጣዕመ መንግሥተ ሰማያትን ምረረ ገሃነመ እሳትን የሚያሳውቀውን የወንጌልን ቃል እንድንሰማ አድርገን፤ አብቃን» ብለው ሕዝቡ ይጸልያሉ::

ቃሉን ሰምቶ የማያደርገው ሊድን አይችልምና የምንሰማውን ቅዱስ ቃል በሕይወት ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ የእግዚአብሔር ፈቃድና ርዳታ የግድ አስፈላጊ ነው:: «ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉም::» እንዲል:: በመቀጠልም ካህኑ:- «የታመመውን ፈውስልን፤ የሞቱትን ማርልን- በመልካም የዕረፍት ሥፍራ አሳርፍልን ብለን ስለምንሻው ነገር አንተን በምንለምንበት ወደ አንተ በምንጸልይበት ጊዜ አትርሱን ያሉንን ዳግመኛ አስብ:: አቤቱ ፈጣሪያችን እግዚአብሔር÷ ከእኛ አስቀድመው የሞቱትን ዕረፍተ ነፍስ ሰጥተህ አሳርፋቸው:: ሕይወታችን አንተ ነህና፣ አለኝታችንም ተስፋችንም አንተ ነህ:: ብንታመም የምትፈውሰን፣ ብንሞትም የምታስነሣን አንተ ነህና ምስጋና እናቀርብልሃለን::» በማለት ይጸልያል::

### *ቅድመ ወንጌል ምስባክ*

ዲያቆኑ ለዕለቱ በዓል የሚመች ምሥጢር ያለውን መዝሙር ከዳዊት አውጣጥቶ ይሰብካል:: መዝሙረ ዳዊት ለወንጌል ምስባክ መሆኑ ስለሚከተሉት ምክንያቶች ነው::

ሀ- ቅዱስ ዳዊት በተሰጠው ሀብተ ዝማሬና ሀብተ ትንቢት የሥላሴን አንድነትና ሦስትነት አምልቶ አስፍቶ ስለ ተናገረ ነው:: «ሣህሉ ለእግዚአብሔር መልዓ ምድረ ወበቃለ እግዚአብሔር ጸንዐ ሰማያት ወእምእስትንፋሰ አፉሁ ኵሉ ኀይሎሙ፤ የእግዚአብሔር ቸርነት ምድርን መላች ብሎ አብን፣ በእግዚአብሔር ቃል ሰማዮች ጸኑ ብሎ ወልድን፣ ሠራዊታቸውም ሁሉ በአፉ እስትንፋስ ብሎ መንፈስ ቅዱስን» ያመለክታል:: መዝ.32÷5::

-ወንጌልም:- «ስታጠምቁ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ብላችሁ

- አገልግሎትን መስጠትና አፈጻጸሙን መከታተል የሚሉት ሊጠቀሱ ይችላሉ::

/ወደ ገጽ ፴፱ ዞሯል/



www.eotcmk.org



# ደባ ተውኔት እና የፍቅረ ሥላሴ ሒስ

ዲ.ን ኤርሚያስ በዛብህ
/ቢ.ኤ በቴአትር ጥበብ/

በኪነ ጥበብ ሥራ እስከ አሁን ያልተቀየረ አንድ እውነታ አለ። ለአንድ ኪነ ጥበባዊ ውጤት ብዙ ሰው የተቀራረበ ምልከታ ይኖረው ይሆናል። አንድምታዊ ትርጓሜን ግን እንደ የራሱ አስተያየት እና ፍላጐት ነው የሚተነትነው። በመሆኑም ይህ እውነት በደባ ተውኔት ሒሶች ላይ ተንጸባርቆ አየን። በርግጥ በአንድ ሥራ ላይ ችግሮችን ነቅሶ መወያየት ሥራው እንዲያድግ ትልቅ አስተዋፅኦ እንደሚያበርክት እሙን ነው። ሆኖም አስተያየቱ ግልጽ በሆነ መንገድ ካልቀረበ ወይም ችግር ናቸው የተባሉ ነገሮች አማናዊ ችግር ካልሆኑና መፍትሔ ካልተጠቆመላቸው አስተያየቱ የበጎ ካፊያ ከመሆን አይዘልም።

ስለሆነም በሐመር መጽሔት መጋቢት /ሚያዝያ ፲፱፻፺፰ ዓ.ም እትም *«ደባ ተውኔት መንፈሳዊ ይዘትም ኾነ ፋይዳ ይጎድለዋል»* በሚል ርእስ ፍቅረ ሥላሴ የተባሉ አስተያየት ሰጪ ያቀረቡት ሒስ ይህን የማስገንዘቢያ ጽሑፍ እንድጽፍ መግፍኤ /Motive/ ሆነኝ። ስለዚህ አስተያየት ሰጪው ያቀረቧቸው መከራከሪያ ሐሳቦች ከላይ እንዳነሣነው ቴአትሩን ሲመለከቱ ያልተጤነ አተያያቸው የፈጠረባቸው ሥዕሎች ናቸው ብዬ በቅንነት በማየት ለርሳቸውም ይሁን ቴአትሩን በአካል ላልታደሙት ወገኖች የተብራራ እና የተስተካከለ ግንዛቤ እንዲኖራቸው በማሰብ ይህቺን ጽሑፍ ለመጻፍ ተነሣሁ። በተጓዳኝም ጽሑፉ ስለምናብራራቸው ጉዳዮች ሲያወሳ እግረ መንገዱንም ስለ ቤተ ክርስቲያን የተውኔት ጥበብ ስልት ንድፈ ሐሳባዊ ግንዛቤያችንን ያዳብርልናል።

ፍቅረ ሥላሴ ባነሧቸው ነጥቦች ላይ በቀጥታ ዝርዝር አስተያየት ከመስጠቴ በፊት ጠቅለል ያለ ግንዛቤ ሊያገኙባቸው በሚገቡ አንዳንድ ጉዳዮች ላይ መንደርደሪያ መስጠት አስፈላጊ ኾኖ አግኝቼዋለሁ።

## ተውኔቱ የቀረበበትን ዘውግ እና ፈለግ መመልከት

አንድ ሐያሲ አንድን የኪነ ጥበብ ሥራ ሊሔስ ሲነሣ ተውኔቱ የተጻፈበትን ዘውግ /Genere/ :-መሪር /Tragedy/ ነውን? ኢመሪር /Comedy/ ነውን? ድንቃይ /Trageo-Comedy/ ነውን? ወይስ ወዘተ ... ብሎ መጠየቅ አለበት። እንዲሁም የትኛውን ፈለግ ተከትሎ የቀረበ ነውን? በእውነታዊ /Realistic/ ነውን? ተፈጥሮአዊ /Naturalistic/ ነውን? ተአምራዊ /Miracluous/ ነውን? ምሥጢራዊ /Mysterious/ ነውን? ተራኪ /Brechtiain epic/ ነውን? ብሎ መመዘን አለበት። በእውነታዊ ፈለግ የቀረበውን በተአምራዊ ላሒስህ ቢሉት መኪናን በአየር ላይ ብረር፤ የዘይትን መጭመቂያ ጤፍና በቆሎ ሰልቅ እንደ ማለት ነው። ስለዚህ አንድ የኪነ ጥበብ ሥራ ምን ጊዜም መታየት ያለበት ከቀረበበት ዘውግ እና ፈለግ አንጻር ነው።

## የሥነ ጽሑፍን ሞያ እና የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት ማስተባበር

*«ደራሲ ከብዙ ነገሮች ላይ ጥቂት ነገርን ይመለከታል፤ ሐያሲ ደግሞ ከጥቂት ነገር ላይ ብዙ ነገሮችን ይመለከታል»* ይባላል። ይህቺ ዓለም የብዙ ጉዳዮች፣ የበርካታ እውነታዎች መስተናገጃ መድረክ ናት። ከእነዚህ ለመጻፍ ቀርቶ ለመናገር፣ ለመናገርም ቀርቶ በሰው ኅሊና ታስበው ከማያልቁ እውነታዎች መካከል ደራሲው እግዚአብሔር እንዲኖር፣ እንዲያውቅ፣ እንዲያይ፣ እንዲያስብ... የፈቀደለትን ብቻ ጨልፎ ... ቆንጽሎ ይጽፋል። ሐያሲ ደግሞ ይህን የሕይወት ጭማቂ፣ የእውነት ፍንጣቂ፣ የኑሮ ብልጭታ በአጉሊ መነጽር ያየዋል። የሐያሲ መስፈሪያው ብዙ ነው። በተለይ መንፈሳዊ ጽሑፍን የሚመረምር ሐያሲ ሞያዊ የሆነውን የሥነ ጽሑፍ ሥርዐት አገባብና ትምህርተ ቤተ ክርስቲያን ምን ይላል የሚሉትን ነጥቦች አብሮ አስተባብሮ ጽሑፉን መመዘን ይኖርበታል።

ይህን ለማድረግ÷ በተለይ ቴአትርን ለማሔስ÷ ጽሑፉን ደጋግሞ ሠልሶ ማንበብ፤ ትዕይንቱ በመድረክ ላይ ሲቀርብ አፍ ተልብ ሆኖ የመጀመሪያውንና የኋለኛውን ትዕይንቶች አናጽሮ መመልከት የግድ ነው። አለበለዚያ ያልሆነውን ሆኖአል፣ የተባለውን አልተባለም ያስብላል። ይህ ደግሞ «ሂስ» ወይም «ትችት» ተብሎ የቀረበ ጽሑፍን ዋጋ መናኛ ያደርገዋል፤ አስተማሪም አይኾንም።

## ለሒሱ አስረጂ ጥቅሶችንና አሳማኝ ማብራሪያዎችን መስጠት

አንድ ሐያሲ ሒስ ሲሰጥ ለሚያነሧቸው የድምዳሜ ሐሳቦች አስረጂ ጥቅሶችን፣ አሳማኝ ማብራሪያዎችን ማቅረብ አለበት። አለበለዚያ እንዲያው ዝናም እንደ ማይሰጥ ነገር ግን በሕዋ ላይ እንደ ሚንከራተት ደመና መሆን ነው። ወይ የቋጠረውን ዝናም አውርዶ መሬትን አላረካት፣ ወይ አንድያውን ቀርቶ ሰው በዝናም የመደብደብ ስጋት ሳያድርበት ወደ ሥራው አልተሠማራ፤ እንዲያው ተንከራቶ የሚያንከራትት ይሆናል።

ስለሆነም ከተወሰነ ዝግ ድምዳሜ ላይ ከመድረስ በፊት ያንን ድምዳሜ የሚያሳድጉ የሚያጎላምሱ ... በቂ መከራከሪያዎችን በቂ ማብራሪያዎችን መስጠት አለባቸው። አንድ ጽሑፍ:- «የቤተ ክርስቲያንን ሥርዐት አፍርሶአል፣ ትምህርተ ቀኖናዋን አልጠነቀቀም፤ መንፈሳዊ ስንቅና ዘር በውስጡ የለውም» ሲባል ምን ማለት ነው? ወይም እኒህ ሁሉ አሉት ሲባልስ ምን ማለት ነው? የሚሉቱ መብራራት ያሻቸዋል።

## መልእክቱን ከቅዱሳት መጻሕፍት አንጻር መመዘን

የመንፈሳዊ ተውኔት መነሻ ሐሳብ ከብዙ አቅጣጫ የሚመነጭ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ፣ የገድላቱ፣ የድርሳናቱ፣ ታሪኮች በሙሉ በተውኔት ሊቀርቡ ይችላሉ። ሆኖም የቅዱሳት መጻሕፍቱን የአስተምህሮ መርሕ ሳይለቅ በአሁኑ ጊዜ ያለውን ችግር ለማሳየት እና መፍትሔ ለማመላከት ወይም ለማፈላለግ መንፈሳዊ ተውኔት ሲቀርብ ከገድል፣ ከድርሳን፣ ከተአምር ወይም ከመጽሐፍ ቅዱስ ሙሉ በሙሉ ተገልብጦ የተወሰደ ታሪክ ካልሆነ መንፈሳዊ አይደለም አይባልም። ዋናው ቁም ነገር እነዚህ ቅዱሳት መጻሕፍት ከሚያስተላልፉት ትምህርት አለማፈንገጡ ነው።

የፍቅረ ሥላሴ ሒስ ከርእሱ ጀምሮ «ደባ ተውኔት በይዘቱ ትንሽ መንፈሳዊ ጠባይ የነካካው ተውኔት ነው እንጂ መንፈሳዊ አይደለም፤ ከውስጡም ምንም የሚገኝ መንፈሳዊ ስንቅና ዘር የለውም» የሚለውን ሐሳብ ለማስረገጥ ይጣጣራል። ለዚህም አስተያየት ሰጪው ከተውኔቱ ውስጥ ሁለት አላባውያን /Elements/ እና የተውኔቱን ርእስ ወስደው ለመከራከር ጥረት አድርገዋል።

በመሠረቱ ተውኔት ከአምስት የማያንሱ አላባዎች /Elements/ አሉት። ይዘቱንና ቅርጹን መገመገም የሚቻለው እነዚህን አላባዎች አንሥቶ ከቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ እና ከተውኔት ንድፈ ሐሳብ ሥርዐት ጋር በማናጸር ነው።

የፍቅረ ሥላሴ ሒስ ርእስ በደባ ተውኔት ውስጥ ሊታዩ የሚችሉትን አላባዎች በሙሉ ጠቅልሎ ተሸክሞአል። ጽሑፉ ግን ርእሱ የተሸከመውን ሐሳብ ማስረዳት አልቻለም። ስለሆነም አስተያየት ሰጪው ሊሉት የፈለጉትን በትክክል መግለጽ አልቻሉም፤ አልያም ማለት የፈለጉትን አላወቁትም ያሰኛል።

እንዴት ቢሉ የአንድ ተውኔት መንፈሳዊ ይዘትና ፋይዳ የሚለካው በእነዚህ በሦስቱ ነገሮች /በርእስ፣ በታሪክ እና በመልእክት/ ብቻ አይደለም። የገጸ ባሕርያት አሣሣል፣ የመቼት አቀራረብ፣ የተውኔት ቋንቋ፣ የተውኔት ሜራ ሁሉ መፈተሽ አለባቸው። እንዲያው እንዲህ ብዙ ዘርፍ እና ቅርንጫፍ ያለውን ዛፍ ሁለትና ሦስት ዛላ ገንጥለው ሲያበቁ «ዛፉ ደረቅ ነው» ማለት





www.eotcmk.org

አይቻልም፡፡ ለእኔ ሲገባኝ፡- «ደባ ተውኔት መንፈሳዊ ይዘትም ሆነ ፋይዳ ይጎድለዋል» ማለት የተውኔቱ አላባዎች /Elements/ ሙሉ በሙሉ ሥጋዊ እና በዓለማዊ ፍልስፍና የተሞሉ ናቸው ማለት ነው፡፡

መቼቱ /የነሚክያስ ቤት/፣ ገጸ ባሕርያቱ /ሚክያስ፣ አባ፣ ሠናይ፣ ታሪኳ፣ ቃለ ተውኔቱ፣ የተውኔቱ ሤራ /Plot/ በሙሉ ቀቤተ ክርስቲያንን ድምፅ አይጮኹም፣ አያስተጋቡም ማለት ነው፡፡ ይህ እንዳልሆነ ግን አስተያየት ሰጪው ራሳቸው ባነሧቸው ማሳያዎች ላይ በመንደርደር ማስረዳት ይቻላል፡፡

## የተውኔቱ ርእስ

የተውኔት ርእስ ሳቢ፣ ግልጽ እና ተገቢ መሆን አለበት፡፡ «ደባ» የሚለውን ርእስ ከነዚህ ሦስት መስፈርቶች አንጻር እንየው፡፡ አንድ ሰው «ደባ» የሚለውን ርእስ ሲያይ ከጀርባ የሚያስባቸው በርካታ ጉዳዮች አሉ፡፡ የሚጣሉ ኃይላት እንዳሉ ያመላክታል፡፡ ሤራ የተጠመደበትና አንዳች ተንኮል የሚያራምድ አካላት እንዳሉ ያስገነዝባል፡፡ ስለዚህ የእነዚህን ኃይላት ፍልሚያና ውጤ ት ለማየት የሚያጓጓ ይሆናል፡፡ ጉጉት መፍጠር መቻሉ ሳቢነቱን ያረጋግጣል፡፡

ግልጽነትን በተመለከተ ቃሉ የሚያሻማ ነገር የለውም፤ ግልጽና ግልጽ ነው፡፡ በተለይ በመንፈሳዊ ሕይወት ውስጥ ለሚኖር እና የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ትምህርት ለተማረ የሰይጣን ተንኮል... የሰይጣን ሽምቅ ውጊያ... ስለሚገባው በርእሱ ምክንያት የመደናገር ሁኔታ ያጋጥመዋል ማለት አይቻልም፡፡

የአስተያየት ሰጪው ጥያቄ ተገቢነት ላይ ያነጣጠረ ነው፡፡ አስተያየት ሰጪው ርእሱ፡- *«ቤተ ክርስቲያን እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ የማትናወጥ መሆኗን፣ መድኃኔ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረውን የሚያስረግጥ»* መሆን እንደ ነበረበት ገልጸው ማቴ.16÷18ን ጠቅሰዋል፡፡

በርግጥ ጸሐፊው ርእሱን ለመሰየም ያዩበት አቅጣጫ አንድ አማራጭ መንገድ ቢሆንም የተውኔቱ ደራሲ የመረጠው አንጻርም ተጠቅልሎ የሚኮነን አይደለም፡፡ እርሳቸው የጠቀሱት ጥቅስም ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን የገሃነም ደጆች ተዋግተው እንደ ማያሸንፏት እንጂ እንደ ማይፈታተኗት፣ እንደ ማያነዋውጿት አይገልጽም፡፡ መርከቢቱ አትሰበርም እንጂ ንውጽውጽታማ አይቀርም፤ መርከቢቱ አትሠጥምም እንጂ ሞገድማ አይቀርም፡፡

ስለዚህ ተውኔቱ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተሸሽጉ አለሁ አለሁ እያለ እንደ ቅንቅን÷ እንደ ነቀዝ ውስጥ ውስጧን የሚበላትን ተባይ ተንኮል ለማጋለጥ የተደረሰ በመሆኑና ርእሱም የተውኔቱን ማእከላዊ ሐሳብ የሚፈነጥቅ ስለሆነ ተገቢ ርእስ ነው፡፡ አይ የለም÷ ተገቢ አይደለም ያሉበትን ምክንያት ተጠየቃዊ በሆነ መንገድ ቢያብራሩት ኖሮ አስተያየታቸው የግል አቋም /ምርጫ/ ብቻ አይሆንም ነበር፡፡ ቀደም ብለን እንዳነሣነው ደግሞ በኪነ ጥበብ ሥራ የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ እስካልተቃወመ ድረስ በቂ ምክንያት ሳያቀርቡ እንዲህ መሆን ነበረበት ማለት ጽሑፉን ሒስ ጸሐፊውንም ሐያሲ አያሰኝም፡፡



*ግርማ - አባ - ሚክያስ በደባ ተውኔት*

## የተውኔቱ ይዘትና ቅርጽ

ፍቅረ ሥላሴ በሁለቱም ቀጣይ ንኡሳን ርእሶቻቸው፡- «የተውኔቱ ታሪክ» እና «የተውኔቱ መልእክት» በሚሉት ንኡሳን ርእሶች ሥር ከታሪክ እና ከመልእክት ውጭ ያሉ ሌሎች የተውኔት አላባውያንን /Elements/ እያጫፈሩ በማንሣት ለማሔስ ሞክረዋል፡፡ ስለሆነም ለአቀራረብ እንዲመች ከጽሑፉ ውስጥ እያንዳንዱን አላባ በመልቀም በፈርጅ በፈርጁ አድርገን እናያለን፡፡

**መቼት፡-** ተውኔቱ የተፈጸመበትን ቦታና ጊዜ የሚያመላክት ቃል ነው፡፡ በተውኔቱ ውስጥ አጠቃላይ መቼቱ የተውኔቱ ታሪክ የተፈጸመበትን ሀገረ ስብከት፣ ወረዳና አጥቢያ አይጠቅስም፡፡ ይህ መገለጽ እንደ ነበረበት አስተያየት ሰጪው ተናግረዋል፡፡ እኔ ደግሞ በተውኔቱ ውስጥ የተንጸባረቀው የቅርስ ዘረፋ በይፋ ታውቆ ሕጋዊ እርምጃ የተወሰደበት ቦታ ካልሆነ በቀር መገለጽ የለበትም ባይ ነኝ፡፡ ለምን? አንድ ቅርስ ያለበትን ገዳም ወይም ደብር ወስደን መድረክ ላይ ብናቀርብ ለቅርስ ዘረፋ የሚሮጡ ሰዎችን መንገድ መሪ ወይም አስደንባሪ መሆናችን ነው፡፡ በሌላ በኩል ውስን ቦታ ተጠቅሶ አለመቅረቡ ተመልካች ሁሉ የየራሱን አጥቢያ እንዲፈትሽ ነጻነት ይሰጠዋል፡፡ ምልከታው በአንዲት አጥቢያ ላይ የተወሰነ አይሆንም፡፡ በአሁኑ ጊዜ ጠላት የበረታባት፣ ባገኘው አጋጣሚና ቦታ ሁሉ ጥፍሩን የሚሰድበት ስለሆነ ሁሉም ገዳማትና አድባራት በያሉበት ትኩረት ያሻቸዋል ነው ነገሩ፡፡ ይህ በመሆኑ ደግሞ ችግሩ እንዲጎላ ያደርገዋል እንጂ አያድበሰብሰውም፡፡ ለምን? ተመልካች ችግሩ ስለ ተከሠተበት ቦታና አጥቢያ ሳይሆን ስለ ችግሩ ጠለቅ ብሎ እንዲያስብ ይመራዋል፡፡

**ገጸ ባሕርያት፡-** በተውኔቱ ውስጥ ያሉት ባለታሪኮች ናቸው፡፡ አስተያየት ሰጪው በተውኔቱ ውስጥ ያሉትን አቀንቃኝ /Protagonist/ እና ፀረ አቀንቃኝ /Antagonist/ ባለ ታሪኮች ከዘረዘሩ በኋላ በሚና ክፍፍል እና በኃይል ሚዛን በቤተ ክርስቲያን ላይ በጠላትነት የተነሣው ፀረ-አቀንቃኙ ታምሩ ገንኖ እንደ ታየ÷ ለተናገራቸውም የድፍረት ቃላት ማንም የቤተ ክርስቲያን ወገን የሆነ ባለታሪክ በድፍረት መልስ ሊሰጠው አልቻለም ይሉናል፡፡

በርግጥ እንደ ተባለው ታምሩ የሰይጣን ፈረስ ነውና እጅግ ደፋር ነው፡፡ ለአንደበቱ ልክ ለጽርፈቱ ወሰን የለውም፡፡ ይኼ ደግሞ የበመፀኞች ጠባያቸው ነው፡፡ ኔሮን ቄሣር እንዲህ ነበር፡፡ ሄሮድስም ይኸው ነበር፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ታምሩ የተሣለበት ባሕርይ የሚጠይቀው እንዲህ መሆንን ነው፡፡ ከዚህም ባሻገር በአሁኑ ሰዓት እንዲህ ዓይነት እኩይ ዓላማ ይዘው የሚንቀሳቀሱ ሰዎች እያደረሱት ያለው ችግር ምን ያህል ከፍተኛ ደረጃ ላይ እንደ ደረሰ የሚያሳይ እውነት ነው፡፡

እናም ሚክያስና ግብረ አበሮቹ እንደ ታምሩ እየተንቀገገቀገፉ ሳይሆን የሚገባውን መንፈሳዊ መልስ ሰጥተውታል፡፡ ለአብነትም ያህል ሠናይ በመጀመሪያው ትዕይንት ላይ፤ ታሪኳም እንዲሁ በሦስተኛው ትዕይንት ላይ ታምሩ የያዘው ተግባር ሰይጣናዊ እንደ ሆነ ነግረውታል፡፡ ይህም ንግግር ታምሩን ወደ ሽንፈት ጉድጓድ አንደርድሮታል፡፡

ከዚያ ውጪ የሚክያስ ጸሎት ቀቢጸ ተስፋ የዋጠው፣ የጽናት አቅም የሌለው ተብሏል፡፡ አንድ መዘንጋት የሌለበት ነገር አለ፡፡ ሚክያስ ፈተና በዝቶበት የሚያስጋው ሰው ነው፡፡ «ፈተናውን እንዴት አለፈው÷ እንዴት አሸነፈው÷ ነው እንጂ በፈተና መጨነቅ የለበትም» ማለት ተገቢ አይደለም፡፡ የጸለየው ከመዝሙረ ዳዊት ነው - አባቶቻችን የቀቢጸ ተስፋ ማዕበል ሲያማታቸው ጸልየው የሚድኑበትን ጸሎት፡፡

በሚክያስና በታምሩ መካከል ያለው ውድድር በመንፈሳዊ እና በሥጋዊ ኃይላት መካከል እንደ መሆኑ ሁለቱም የየራሳቸውን ትምክህት ይዘው መቅረብ ነው ያለባቸው እንጂ ታምሩ እሳት ስለ መዘዘ ማሸነፊያው የሚንቀለቀል ችቦ ላይሆን ይችላል፡፡ በቀላሉ ቀስ ብሎ በውኃ ማጥፋት ይቻላል፡፡ ይህም ደግሞ በጥበበ እግዚአብሔር ሲሆን ታይቷል -በተውኔቱ ውስጥ፡፡

ሌላው ጉዳይ «ሚክያስ ታምሩን



www.eotcmk.org

በምን ምክንያት እንደ ጠረጠረው አይታወቅም» የሚለው ነጥብ ነው:: ይኼ ጉዳይ በግልጽ በተውኔቱ ውስጥ ተንጸባርቆአል:: የሠናይ መረጃ ማጠናከሪያ እንጂ ሚክያስ ለስብከተ ወንጌል ሌላ ቦታ እንደ ሄደ በቂ አሳማኝ ማስረጃ አግኝቶ መመለሱን ለግርማም ለአባም ነግሮአቸዋል:: ስለዚህ ተውኔቱን በትኩረት ካለማጤን የተሰነዘረ አስተያየት ነው::

ከዚህም ባሻገር ፍቅረ ሥላሴ ሚክያስን ከታምሩ ጋር ለብቻው የሚታገል ምስኪን አድርገው ፈርጀውታል:: ነገር ግን ተውኔቱ ውስጥ የታሪኳ ማፈንገጥና የሠናይ መልካም ሐሳብ ከሁሉም በላይ ደግሞ ሚክያስ ለብቻው የሆነ በመሰለው ጊዜ የእግዚአብሔርን ርዳታ፤ የድንግልን ምልጃ መማፀን አላቆመም:: እግዚአብሔርን ከያዘ ደግሞ ከማንም በለይ ለብቻው አይደለም::

ታምሩ በሰበካ ጉባኤ ምክትል ሰብሳቢነት መመረጡ ለዓላማው መሳካት ምን ያህል ፋይዳ ይኖረዋል? የሚለውን ጥያቄ በተመለከተ ግን የታምሩ ባሕርይ ያላቸውን ሰዎችና በቀበሌና በወረዳ ያሉ ብዙ የገጠር አብያተ ክርስቲያናትን ማሰብ በቂ ይመስለኛል:: እውነታውን የሚያውቅ ይህን ጥያቄ አይጠይቅም:: ያለውን እውነት ደግሞ በሰፊው ለማብራራት ይህ ዓምድ አይበቃውም:: ራሱን ችሎ ሊጻፍበት የሚገባ ነው:: ነገር ግን እንደ ማሳያ ታምሩ የተጫወተውን ሚና ማየት በቂ ነው::

ቋንቋ:- የተውኔት ቋንቋ ግልጽ÷ቃለ ምልልሱ አጫጭር መሆን አለበት:: ሆኖም እንደ ትዕይንቱ ዐውድ ለተለየ ጠቀሜታ ሊረዝም ይችላል:: በአጠቃላይ የደባን ቃለ ተውኔት ስንመለከት አጫጭር ሆኖ እናገኘዋለን::

ነገር ግን ሚክያስ በተጨነቀ ጊዜ አምላኩ እግዚአብሔርን ሲማፀን፤ በአንጻሩም ታምሩ ምሥጢሩ ተነቅቶበት በጭንቀት ውስጥ ሆኖ ሲወራጭ፣ ከዘገየ እና ከታሪኳ ጋር ሲነጋገር፣ ሲያወራ ረጃጅም ቃለ ተውኔቶች ተጠቅመዋል:: ይኸን ደግሞ ተዋንያኑ በትወና ትክክለኛ ስሜቱን ለክተው ስለ ተናገሩት በተውኔቱ ላይ የፈጠረው አሉታዊ ጫና የለም:: ይልቁንስ በሚክያስ ጭንቀት ተመልካቹ አብሮ እንዲጨነቅ፣ በታምሩም ሩጫ ተመልካቹ ተናድዶ የችግሩን ምሬት እንዲቀምሰው ያደርገዋል:: ከዚያ ውጪ ረጃጅም ሆነው የተውኔቱን ጉዞ የሚጐትቱት ቃለ ተውኔቶች እንዲያው ለምሳሌ ቢነሡ ጥሩ ነበር::

ሤራ:- የተውኔቱን ታሪክ እና በታሪኩ መካከል የተፈጠሩትን ግጭቶች በምክንያትና ውጤት ተጠየቅ የምንተልምበት ነው:: በደባ ተውኔት ውስጥ አውራው ሤራ በቅርስ ዘረፋ ምክንያት የተፈጠረው ትግል ነው:: ይህ ሆኖ ሳለ «የቅርስ ዘረፋ በተውኔቱ በተነሣው መልኩ በቁንጽል የሚታይ ነገር አይደለም» ይሉናል-ፍቅረ ሥላሴ:: በርግጥ የተለያየ አተያይ ሊኖር ይችላል:: ይህ የተለያየ አቀራረብ መኖሩ ግን ተውኔቱ ጉዳዩን ያቀረበበትን ሁኔታ የሚቃወም አይሆንም:: የለም÷ ይኼ ትክክል አይደለም ከተባለም ትክክለኛው የቱ እንደ ሆነ መግለጽ ያባት ነበር:: በመሠረቱ የአንድ ድርሰት መጠነ ርእይ የሚወሰነው በደራሲው ነው:: ዋናው ነገር ደራሲው የመረጠውን መጠነ ርእይ አጥጋቢ በሆነ መልኩ የመግለጹ ጉዳይ ነው::

ተውኔቱ በታሪኩ ተጻራሪ ኃይላት መካከል ያለውን የጥቅም ግጭት በትክክል አሳይቶአል:: አንዱ ቡድን:- «ቅርስ ዘርፌ እከብራለሁ» የሚል ሲሆን ሌላው ደግሞ «የቤተ ክርስቲያን ቅርስ አይዘረፍም፤ በሯ-ቅጥሯ አይደፈርም» ባይ ነው:: የተውኔቱ ርእስም ይሁን ሌሎቹ አላባውያን እንዲሁም አጫፋሪ ታሪኮች ይህንኑ ዐቢይ ግጭት እያጫፈሩ እና እያጎላመሱ ነው በተውኔቱ ውስጥ የፈሰሱት:: ተነሥቶ ያልተመለሰ ጥያቄ በተውኔቱ ውስጥ ካለ ጠቅሶ ማስረዳት ያስፈልጋል::

ተውኔቱ «የችግሩን ምንጭ አይጠይቅም» የሚል አስተያየትም ተሰንዝሯል:: ተውኔቱ ግን መጠየቅ ብቻ ሳይሆን መልስም ሰጥቷል:: የችግሩ ምንጭ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ይዛ ያቆየቻቸው የእውነተኛነት መገለጫ የሆኑ ቅርሶቿ እና ንዋያተ ቅድሳቷ እንዲጠፉ የሚፈልጉ ወገኖች መነሣታቸው፣ በቀጥታና በተዘዋዋሪ ወደ ቅጥሯ አንገታቸውን መስበቃቸው፤ እጃቸውንና እግራቸውን መስደዳቸው ነው:: በአንጻሩም ውጤቱ ታምሩን የመሳሰሉ ምንደኞች መፈጠራቸው ችግሩን ከምንጩ እየቀዱ ገፈቱን ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመቸለስ መሞከራቸው መሆኑ በግልጽ ተንጸባርቆአል::

ጭብጥ:- በተውኔቱ ሊተላለፍ የተፈለገው ዐቢይ መልእክት ማለት ነው:: ፍቅረ ሥላሴ በአስተያየታቸው: - «የተውኔቱ ጭብጥ የቀረበበት አንጻር የእግዚአብሔር ቸርነት ዕለት ዕለት ከቤተ ክርስቲያን እንደ ማይለይ በማያሻማ አገላለጽ አላቀረበም» ሲሉ ይወቅሳሉ:: እዚህ ጋር ሁለት ነገሮችን መመልከት ያሻል::

አንደኛ:- ተውኔት እንደ ዐውደ ጥናት ወይም ቀጥተኛ ስብከት የሚያነሣውን ጭብጠ ሐሳብ እንደ መፈክር በቀጥታ ላይናገር ይችላል:: ከመናገር ይልቅ በተግባር ያሳያል:: ይህ በተለይ ተውኔቱ በእውነታዊ ፈለግ /Realistic/ የቀረበ እንደ ሆነ ነው:: ከዚያ ውጪ ተውኔቱ የቀረበው በተራኪ /Brechtian epic/ ፈለግ ከሆነ አስተያየት ሰጪው የተናገሩት ትክክል ሊሆን ይችላል:: ደባ ተውኔት ግን የቀረበው በእውነታዊ ፈለግ ነው::

ሁለተኛ:- «በጊዜያችን በቤተ ክርስቲያን ላይ የተሰለፉ የጠላት ኃይሎች ቤተ ክርስቲያንን እንደ ማያሰኙት መገለጽ ነበረበት» የሚል ሐሳብ አላቸው:: መስጋትማ አይቀርም፤ መፍራትማ አይቀርም:: ይህ ስጋትና ፍርሃት ቤተ ክርስቲያን ትጠፋለች በሚል አይደለም ነገር ግን የእውነት መመናመን ያስፈራል፤ የቅርሶች መዘረፍ ያሰጋል፤ የቤተ ክርስቲያን በደካማ ሰዎች መደፈር ያስፈራል፤ ንዋያተ ቅድሳት እየተዘረፉ በየፖሊስ ጣቢያው ከሐሺሽ እና ልዩ ልዩ መጥፎ ነገሮች ጋር በኤግዚቢትነት መያዛቸው ያስፈራል... ብዙ የሚያሰጋ ነገር አለ:: ነገር ግን በነዚህ ሁሉ ማዕበሎች ቤተ ክርስቲያን የማትሸነፍ መሆኑንና በተውኔቱ ፍጻሜ ላይ የእግዚአብሔር እጅ ሲራዳት በተግባር አይተናል::

ምናልባት ከዚሁ ጋር ተያይዞ - «በተውኔቱ ፍጻሜ ላይ ታምሩ ፍጹም ሲሸነፍ አልታየም» የሚል አስተያየት ይነሣል:: እዚህ ጋር መገንዘብ ያለብን ትግሉ በታምሩ ተሸናፊነት እንደ ተደመደመ ነው:: ያሰበው - የተናገረው - ያደረገው ሁሉ አልተሳካለትም፤ ከሽፎበታል:: ሆኖም ከተሸነፈ በኋላም ተስፋ ሳይቆርጥ ከታሪኩ ፍጻሜ በኋላ በሚክያስ ላይ ሸጉጥ ሲደግንበት እናያለን:: ይህም ጌታ እንደ ተናገረው የዘመኑ ፍጻሜ ሲቀርብ ፈተናው እየጨመረ እንደ ሚመጣ የሚያመለክት ነው:: በፈተናው መካከል ግን ምእመናን መጋደል አለባቸው:: አንዱን ፈተና ድል ሲያደርጉ ለሌላው መዘጋጀት አለባቸው ነው ቁም ነገሩ::

ሌላው ተውኔቱ ችግሩን ለማቃለል ምእመናን ምን ያድርጉ የሚለውን የሚመልስበት ክፍል እንደሌለው ቀርቧል:: የዚህኛውም ጥያቄ በተግባር ተመልሷል:: የሚክያስ እና ግብረ አበሮቹ ሕይወት ለዚህ ዐቢይ ጥያቄ መልስ ነው:: ከዚህ አልፎ ጉዳዩ እንደ ስብከት ወይም እንደ መፈክር መነገር ነበረበት ለማለት ከሆነ ይህ እንዲሆን የተውኔቱ አቀራረብ ተራኪ /Brechtian epic/ ፈለግን የተከተለ መሆን ነበረበት:: ነገር ግን ተውኔቱ በቀረበበት በእውነታዊ /Realistic/ ፈለግ አንጻር ካየነው «ሁሉም በያለበት ቤተ ክርስቲያኑን ከመናፍቃንና ከአስመሳይ ተንኮለኞች ነቅቶ ይጠብቅ» የሚለውን ሐሳብ በተውኔቱ ሁለመና አስተላልፎአል::

ቴክኒክ:- ተውኔቱ በመድረክ ላይ የሚቀርብበት ቅንብራዊና ቅንጅታዊ ሥልት ነው:: አስተያየት ሰጪው አሁንም:- «ቴክኒካዊ ብቃቱ የተሻለ ቢሆንም አንዳንድ አቀራረቦቹ ዓለማዊ መድረክ አስመስለውታል» ይላሉ:: ዓለማዊ ሲሉ ምን ማለታቸው ነው? ቤተ ክርስቲያናዊነቱን ያጐደለው መብራቱ ነው? የድምፅ ግብአቱ ነው? የተዋንያኑ አተዋወን ነው? አልባሳቱ ናቸው? ቁሳቁሱ ነው? የመድረክ ገጹ ነው? ይህን ለማለት ምንም አስረጂ ጭላንጭል ምክንያት አልቀረበም::

በአጠቃላይ ፍቅረ ሥላሴ በማጠቃለያ አንቀጻቸው እንዳሉት:- «መንፈሳዊ ሥራ በመንፈሳዊ ጥበብ መታነጽ አለበት፤ ጸሎት መደረግ አለበት:: ተውኔቱን የሠሩት አገልጋዮች በሚችሉት እና በሚገባቸው መጠን አድርገዋጠል:: ምክር እና አስተያየት መቀበል ያስፈልጋቸዋል::» ብለዋል:: ደባ ተውኔት ለሁለት ዓመት እየተመከረበት እና በአስተያየቶች እየበለጸገ መድረክ ላይ የወጣ ተውኔት ነው:: በተለይም ደግሞ ምክርና አስተያየትን በመቀበልና ተቀባይነት ባላቸው ሐሳቦች ተውኔቱን የማዳበሩ ሒደት የማኅበሩ ኤዲቶሪያል ቦርድ ሥራዬ ብሎ የተጋበት ዓይነተኛ ተግባሩ ነበር ለማለት ይቻላል::

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

የማኅበረ ቅዱሳንን ገጸ ድር ይጎብኙ
www.eotc-mkidusan.org



www.eotcmk.org

# «የዳ ቪንቺ ኮድ» ልቦለድ መጽሐፍ በመንፈሳዊ ዐይን ሲገመገም

/ፍሬምናጦስ/



ዳን ብራውን የተባለው ደራሲ «የዳ ቪንቺ ኮድ» በሚል ርእስ የጻፈው ልቦለድ መጽሐፍ በአቤል ሰይፉና ተስፋሁን ምትኩ ወደ አማርኛ ተተርጉሞ ቀርቧል:: የመጽሐፉ ይዘት የምእመናንን ኅሊና ጎድቷል፤ ብዙ ጥያቄዎችም አሥነስቷል:: በመሆኑም የመጽሐፉን ይዘት፣ የተጻፈበትን ዓላማና ፋይዳውን በመገምገም ይህችን ለውይይት መነሻ ልትኾን የምትችል የማስገንዘቢያ ጽሑፍ ለማቅረብ ወደድኹ::

የዳ ቪንቺ ኮድ መጽሐፍ የብዙ አንባቢያን ትኩረትን የሳበ በመሆኑ ለደራሲውም ሆነ ለተርጓሚዎቹ ከፍተኛ ንዋይ አስገኝቷል:: በክርስትና ስም የሚጠሩ የተለያዩ እምነት ድርጅቶች ዐዋቆችም የመጽሐፉን መሠረታዊ ሕጸጾች እየነቀሱ፥ በየኅትመት ውጤቶቻቸው ለእምነት ተከታዮቻቸው በመግለጽ አያሌ የማስተባበል ተግባራትን አከናውነዋል፤ ለተቃውሞም ቀስቅሰዋል::

የመጽሐፉ ታሪክ መሠረት: - አውሮፓ ውስጥ በዐሥረኛው ምእተ ዓመት የተቋቋመ «የጽዮን ጽላት ጽዋ» የሚባል የምሥጢር ማኅበር /ቡድን/ የነበረ ሲሆን የዚህ ማኅበር አባላት ለዘመናት የያዙትን ምሥጢር በኅቡዕ መልእክት በምልክት ሲያስተላልፉ ኖረዋል :: ይህ «የወንድማማቾች ማኅበር» በማእዘን ድንጋይ የሚመራ ካርታ ያለውና የ«እንስት ጣዖቶችን» የማምለክ ባህል ያለው ነው:: «ዳ ቪንቺ የተባለው እውቅ ሠዓሊ የዚህ ቡድን አባል የነበረ በመሆኑ በሥዕሎቹ ምሥጢራዊ መልእክቶችን አስተላልፏል» በሚለው ጉዳይ ላይ ያተኩራል::

የመጽሐፉ ደራሲ ዳን ብራውን የግኖስቲኮችን ትምህርት መሠረት በማድረግ አዲስ ልቦለድ ታሪክ አቅርቦአል:: የዳ ቪንቺ ኮድ መጽሐፍ:- «የካቶሊ ክ እምነት ይህን ኅቡዕ ቡድን ስትከታተልና ስታጠፋ ኖራለች» ይላል:: በመጽሐፉ ማርያም መግደላዊት ማእከላዊ ተምሳሌት የያዘች ሲሆን የተለያዩ አፈ ታሪኮችን መሠረት በማድረግ በተለይ «የእንስት አምልኮ» በሚለው ጉዳይ ላይ በማተኮር የጥንት ቤተ ክርስቲያንን ታሪክ በማፋለስ ያቀርባል:: እንደ መጽሐፉ አገላለጽ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የማርያም መግደላዊት ሚና እንዲቀነስ የተደረገው ከአራተኛው ምእተ ዓመት በኋላ ሲሆን ይህም የተደረገው የካቶሊክ እምነትን አስተምህሮ ስለሚቃረን ነው:: በዚህ መሠረት «ቤተ ክርስቲያን እውነታውን ለመደበቅ ከፍተኛ እልቂት ፈጽማለች» የሚል ሐሰተኛ ክስ ያቀረበ ሲሆን «የግኖስቲኮችን አምልኮ ለማቆየት የምሥጢር ቡድኑ አባላት «እውነቱን» በጥበብ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፍ አድርገዋል::» ይላል:: የመጽሐፉ የታሪክ ትልም /ሤራ/ በዚህ ተውኔት ላይ የሚያጠነጥን ነው::

መጽሐፉ በ«ምሥጢራዊ ታሪክ»፣ በሃይማኖታዊ ሤራና በወንጀል ጉዳይ ላይ የተዋቀረ በመሆኑ የብዙ አንባቢዎችን ቀልብ ስቧል:: አንዳንዶችም ልቦለድ መሆኑን ዘንግተው አማናዊ አድርገው እስከ መቀበል ደርሰዋል:: ደራሲው የተለያዩ «ምሥጢራዊ» የሚመስሉ ታሪኮችን በማገጣጠም የራሱን ልቦለድ የጻፈ ሲሆን በተለይ ትውፊታዊ ታሪኮችን በማዛባቱ፣ ኾነ ብሎ በማጋነኑ ብዙዎችን ለማሞኘት ችሏል:: «የጽዮን ጽላት ጽዋ ማኅበር» «ፕራዮሪ ኦፍ ዚዮን» - «የጽዮን ተራራ ማኅበር» በሚል የተቋቋመው ገዳም አባላትን ታሪክ መሠረት ያደረገ ነው:: ዳን ብራውን «ቴምፕላርስ» የተባሉትን ሚስዮኖች የማርያም መግደላዊትን ምሥጢር ጠባቂዎች አድርጎ አቅርቧል:: ይሁን እንጂ ይህ እውነተኛ ታሪክ አይደለም:: የደራሲው ዓላማ የአንባብያንን ትኩረት የሚስብ ልቦለድ ታሪክ መጻፍ በመሆኑ እውነታውን በማዛባት ማቅረቡ ብዙዎችን አሳዝኖአል፤ አስቆጥቶአል::

የታሪኩ መዋቅር በልቦለድ ትረካ የተመሠረተ ነው:: መጽሐፉን ስናነብ ጥንታዊ ምስሎችን፣ ምልክቶችንና ሥዕሎችን በመመርመር በተለይ በምልክቶች መካከል ያለውን የተወሳሰበ ዝምድና በማጥናት ከፍተኛ ዝና ያተረፈው ፕሮፌሰር ላንግደን የተባለ አሜሪካዊ ምሁር «የተምሳሌታዊ ምልክቶች ኃይል» በሚል ርእስ ፓሪስ ውስጥ ትምህርታዊ ንግግር አድርጎ እንደ ጨረሰ በግድያ ወንጀል ጉዳይ በፈረንሳይ ፖሊስ ለጥያቄ እንደ ሚፈለግ በታሪኩ ውስጥ እንመለከታለን:: የፈረንሳይ ፖሊስ አዛዥ በዙ ፋቼ ፕሮፌሰር ላንግደን ወንጀሉ በተፈጸመበት ቦታ እንዲገኝ ካደረገ በኋላ የሟቹን የምሥጢር መልእክት እንዲፈታ ይጠይቀዋል:: በመካከሉ ሶፊ ኖቩ ጣልቃ ትገባና ሕይወቱ አደጋ ላይ እንደ ሆነ ነግራው እንዲያመልጥ ታደርጋለች:: በመጽሐፉ እንደ ተገለጸው «የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን» ክፍል የሆነው ኦፐስ ዴይ ማኅበር መሪ የእግዚአብሔር ጠላቶች ናቸው የሚላቸው የወንድማማች ማኅበሩን አባላት ምሥጢር ለማግኘት በሕይወት የሚገኙትን በማሳደድ «የማእዘን ድንጋዩን» ይፈልጋል:: የኦፐስ ዴይ ሊቀ ጳጳስ ዐማኑኤል አሪንጋሮሳ የካቶሊክ እምነት እሴቶች እንዲጠበቁና አባላቱ የፈጣሪያቸውን መልእክት ለማድረስ ሲላስ የተባለው መነኩሴ ምሥጢሩን እንዲቀበልና አባላቱን እንዲገድል ይልኩታል:: ይህ ዘመናዊ ልቦለድ በነዚህ ባለታሪኮች ዙሪያ የሚውጠነጠን ነው::

በመጽሐፉ የሚነሡት ጭብጦች የብዙዎችን ትኩረት የሚስቡ ዓይነት ናቸው:: ምክንያቱም በጉዳዩ ላይ በቂ ዕውቀት ለሌለው ሰው እውነት የሚመስሉ ልቦለድ ታሪኮችን በመያዛቸው ነው:: መጽሐፉ የሚያተኩርባቸው ጉዳዮች ምሥጢራዊ ስለሚመስሉና አንዳንዴም በግልጽ ውይይት የተደረገባቸው ባለመሆናቸው የዋህ የሆኑ ምእመናንን እምነት በመሸርሸር ለጥርጥርና ለክሕደት የሚያጋልጡ ናቸው:: በመሆኑም ቤተ ክርስቲያን በመሠረታዊ ጉዳዮች ላይ ትምህርት ልትሰጥ ይገባል:: ለአብነት ያህል ከሚጠቀሱት ውስጥ ስለ ሐዲስ ኪዳን በተለይም ስለ ወንጌል ያቀረባቸውን ነጥቦች መመርመሩ መልካም ነው:: ዳን ብራውን:- *«መጽሐፍ ቅዱስ የሰው አእምሮ ውጤ ት ነው፤ የእግዚአብሔር ሥራ አይደለም:: አሁን መጽሐፍ ቅዱስ ተብሎ የምናውቀው መጽሐፍ ጣዖት አምላኪ በነበረው የሮማ ንጉሥ ታላቁ ቆስጠንጢኖስ የተሰበሰበ ነው:: ሐዲስ ኪዳን የሐሰት ምስክርነት ነው:: ሐዲስ ኪዳን በሬ ወለድ ዓይነት ታሪኮችን የያዘ ነው»* በማለት መሬት የለቀቀ የኑፋቄና የክሕደት ትምህርቱን ይነዛል:: የዳ ቪንቺ ኮድ መጽሐፍ ዝነኛ መሆን በቀላሉ ሊታይ አይገባውም:: ምክንያቱም የየዋህ ክርስቲያኖችን እምነት የመበረዝ ኃይሉ ቀላል አይደለም:: መጽሐፉ ምሁራዊ ትንታኔን የያዘ ሳይሆን ጥቂት እውነት የሚመስሉ ታሪኮችን ከፈጠራና ሐሰት ጋር በመደባለቅ የተዘጋጀ ልቦለድ እንደ መሆኑ መጠን በተራው አንባቢ ዘንድ የሚያስከትለው መደናገር ቀላል አይኾንም:: የተደባለቁ ታሪኮችን በመለየት እውነታውን ለማወቅ እንድንችል ለአብነት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መመልከቱ ተገቢ ነው::

በመጀመሪያ መጽሐፍ ቅዱስ መቼና እንዴት ተጻፈ? የሚለውን ጉዳይ በሚመለከት ዳን ብራውን:- *«መጽሐፍ ቅዱስ በዘመነ ቆስጠንጢኖስ ተከልሶ ተጽፏል:: ይህም በኒቅያ ጉባኤ በእምነት ልዩነት እንዳይኖርና የሮማን የግዛት አንድነት ለማጠናከር የተደረገና የኢየሱስ ክርስቶስ አምላካዊ ባሕርይ እንዲጎላ ለማድረግ የተፈጸመ ነው::»* በሚል ያቀረበው አዲስ መላምት ከቤተ



www.eotcmk.org

ክርስቲያን ታሪክ አንጻር የሚጋጭና ፍጹም ሐሰት ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ መሪነት የተጻፈ መሆኑን ቤተ ክርስቲያን ታስተምረናለች፡፡ 2ጴጥ.1÷16፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ በመጀመሪያዎቹ ክፍለ ዘመናት በተሠሩ የሐዋርያትና የሐዋርያውያን አበው ሊቃውንት ሲኖዶሳት አሁን ባለው ቅርጹ የተዘጋጀ መሆኑን ታሪክ ያስተምረናል ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ በታላቁ ቆስጠንጢኖስ እንደ ገና አልተጻፈም ፡፡ ንጉሡ የመጽሐፍ ቅዱስ ይዘቱንም ሆነ ቅርጹን በመወሰን ረገድ ምንም ሚና አልነበረውም፡፡ እንደ ሚታወቀው የኒቂያ ጉባኤ ዓላማ በአርዮስ የኑፋቄ ባህል ምክንያት የተፈጠረውን ችግር ለመፍታት ነው፡፡ የዳን ብራውን መጽሐፍ የክርስትና ሃይማኖትን መሠረታዊ ታሪክ በማዛባት የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት በቆስጠንጢኖስ ዘመን እንደ ተጻፉ ይናገራል፡፡ እዚህ ላይ መገንዘብ ያለብን ጉዳይ ደራሲው ግኖስቲኮች የሚባሉት መናፍቃን በቆስጠንጢኖስ ዘመን በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የራሳቸውን ባህል አሥርገው እያስገቡ በመቀስጥ ከአራቱ ወንጌሎች ተጨማሪ ሌሎች የሚባሉት «ወንጌሎች» በቤተ ክርስቲያን የማይታ ወቁና ተቀባይነት የሌላቸው ሲሆኑ ግኖ ስቲኮች የሚያራምዱት እምነት መሠረት ሆነው እንዳገለገሉ ይታመናል፡፡ በተለያዩ ዘመናት የተለያዩ የኑፋቄ ትምህርቶችና ፍልስፍናዎች እንደ ተነሡ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በሚገባ ያስጠ ረዳናል፡፡ ግኖስቲኮች የሚባሉትን ሰብአ ፈጠራዎች በሚመለከት በብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ የተጻፈው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ መጽሐፍ ግኖስቲኮች «መዳን በዕውቀት እንጂ በእ ምነት አይደለም» እንደ ሚሉ ይገልጻል፡፡ /1978 ዓ.ም÷ ገጽ 55/፡፡ ይህም የትምህ ርታቸው መሠረት ልብ ወለድ ፍልስፍና መኾኑን ያመለክታል፡፡ *ግኖስቲኮች በመ ሠረቱ ክርስትናን ከተቀበሉ በኋላ የምሥራቃውያን የመተትና የጥንቆላ ልማድ* ከእምነት ጋር ለመቀላቀል በመሞከራቸው ለቤተ ክርስቲያን የውስጥ ሕመም ኾነውባት ነበር፡፡

የዳ ቪንቺ ኮድ መጽሐፍ በሊ ኦናርዶ ዳ ቪንቺ «የመጨረሻው ራት» በተባለው ሥዕል «ከጌታ አጠገብ የተቀመጠ ችው ማርያም መግደላዊት ናት» የሚል መላምት ቀርቧል፡፡ በምሴተ ኀሙስ ሥዕል *ሰንዝሯል፡፡ የዳን ብራውን መጽሐፍ፡ - «ሥዕሉ የሠዓሊውን የግል እምነት የሚያንጸባርቅ ነው» የሚል መልእክት አለው፡፡* በርግጥ የዳ ቪንቺ ሥዕል የራሱ የሆነ ሕጸጽ አለው፡፡ *በኛ በኩል ግን* ዋናው ነጥብ በወንጌል እንደ ተጻፈውም ሆነ በሥዕሉ ላይ እንደ ተመለከተው ከኢየሱስ አጠገብ የተቀመጠው ፍቍረ እግዚእ /የጌታ ወዳጅ/ የተባለው ቅዱስ ዮሐንስ መሆኑን ነው፡፡ ይህ ደግሞ በሌላ መነጽር ሲታይ የእምነት ጉዳይ በመሆኑ በማያምን ሰው አይመረመርም፡፡

ደራሲው ዳን ብራውን መጽሐፉን የጻፈው እውነተኛ ታሪክን መሠረት አድርጎ እንደ ሆነ በመግለጹ እንዲሁም በመግቢያው በልብ ወለዱ ውስጥ የተጠቀሱት ጉዳዮች ትክክለኛ ናቸው በማለቱ ብዙዎችን ለማወናበድ ችሏል፡፡ ለክርስቲያኖች ሁሉ የዚህ መጽሐፍ ጉዳይ አሳሳቢ ሆኗል፡፡ ምክንያቱም መ ጽሐፉ «በቀደምት አባቶቻችን ስለ ክርስትና የተነገረን ሁሉ ውሸት ነው» የሚል ድምዳሜን ይዟል፡፡ አቀራረቡ በማር የተለወሰ /የተቀባ/ በመኾኑ ውስጡ ያለው መርዝ በቀላሉ አይታ ይም፡፡ የዋህ የሆኑ ሁሉ በማር መሰል አቀራረቡ ተዘናግተው መርዙን እንዲ በሉ የቀረበ እንደ መሆኑ መጠን እም ነት እንዲናጋ የሚያደርግ መጽሐፍ ነው፡፡ ታሪኩ ልቦለድ ነው ቢባልም የክር ስትናን እምነት መሠረታዊ ትምህ ርቶችንና እምነቶችን የሚያፋልስና እው ነታውን ለማድበስበስ የተደረገ ነው፡፡ ይህ መጽሐፍ ዳን ብራውንና ሌሎቹ ***«የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ» /New age movement/*** አባላት የራሳቸውን አስተ ምህሮና ፍልስፍና በተለያዩ መንገዶች በማስተላለፍ ለማሥረጽ የክርስትና ሃይ ማኖትና እምነት እንዲጠፉ የሚያደ ርጉት ዘመቻ አካል ነው ለማለት ይቻላል፡፡

**በምዕራቡ ዓለም እውነታና ልቦለድ ታሪክ በሚቀላቀልበት በዚህ ዘመን የእምነት ነገር የተናቀ በመሆኑ ማንም ተነሥቶ የሌሎችን እምነት እያንኳሰሰ ቢጽፍ የሚጠየቅበት ሥርዐት ስለሌለ የእምነትን ኀይል ለማዳከምና ለማቀዝቀዝ ትልቅ በር ከፍቷል፡፡**

የሐሰት ወንጌሎችንና መልእክታትን በቅዱሳን ሐዋርያት ስም በመጻፍ የጀመሩትን የማደናገር ሥራ ለማስቀም የተወሰዱትን ርምጃዎች እውነቱን ለማዛባት የተጠቀመበት መሆኑን ነው፡፡

የመጽሐፉ ዋና ዋና ጭብጦች ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደ ተሞከረው በጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክነትና የመጽሐ ፍ ቅዱስ «እውነተኛነት»ን በሚመለከት በሚነሡ ነጥቦች ላይ ያተኩሩ በመሆ ናቸው ነጥቦቹን በተመለከተ ግል ጽ የሆኑ መልሶችን መስጠት፣ ተቃ ውሞን ማሰማት ያስፈልጋል፡፡ በመጀ መሪያ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት በወንጌል ቃል የተመሰከረው ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ሳይወለድ ከሁለት መቶ ዓመታት በፊት እንደ ሆነ ከታሪክ ምስክሮች መረዳት ይቻላል፡፡

የዳ ቪንቺ ኮድ ላይ የተጠ ቀሱት ጉዳዮች ከእውነት የራቁና የደራ ሲው ግላዊ አመለካከት የተንጸባረ ቀባቸው ናቸው፡፡ ለምሳሌ ዳን ብራውን በመጽሐፉ የሚጠቅሳቸው በፊልጶስ እና በመግደላዊት ማርያም ተጽፈዋል

በተለይም ሊኦናርዶ ዳ ቪንቺ በሣለው «የመጨረሻው ራት» ሥዕል ከጌታችን ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ አጠገብ /ሕጽን/ የተቀመጠው ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ እንደ ኾነ የሃይማኖት ሰዎችም ሆኑ የሥነ ጥበብ ምሁራን ያረጋግጣሉ፡፡ ከሁሉም ይልቅ ግን የሚከተለው የቅዱስ ወንጌል ቃለ ኃይል እውነቱን ያስረግጥልናል፡- «ጴጥሮስም ዞሮ ብሎ ኢየሱስ ይወደው የነበረውን ደቀ መዝሙር ሲ ከተለው አየ፤ እርሱም ደግሞ በእራት ጊዜ በደረቱ ተጠግቶ፡- ጌታ ሆይ÷ አሳልፎ የሚሰጥህ ማን ነው? ያለው ነበረ፡፡» /1ዮሐ.21÷20/፡፡ በመጽሐፉ በሊኦናርዶ ዳ ቪንቺ «***የመጨረሻው ራት***» /ምሴተ ኀሙስ/ ተብሎ በተሰየመው ሥዕል ከመድ ኃኔ ዓለም በቀኝ በኩል የተቀመጠችው ማርያም መግደላዊት እንደ ሆነች የተገለ ጸው ለምንድን ነው? የሚል ጥያቄ ስናነሣ በግኖስቲኮች አስተምህሮ የቀረበውን ሐሰ ተኛ ታሪክ ለማጉላት መሆኑን እንረዳለን፡፡ በሥዕሉ ላይ ከኢየሱስ አጠገብ የተቀመጠ ው ፍቍረ እግዚእ /የጌታ ወዳጅ/ ቅዱስ ዮሐንስ መሆኑን በሁሉም ዘንድ ሊታወቅና ሊታመን ይገባል፡፡ ዳን ብራውን፡- *«ይህ ሥዕል ዳ ቪንቺ በኀቡዕ መልእክት ለማስ ተላለፍ ያዘጋጀው ነው» ያሚል መላምት*

እንደ ኒውስ ዊክ÷ ሜይ 26 ቀን 2006 እ.አ.አ እትም ሐተታ በዳን ብራውን መጽሐፍ ውስጥ ማርያም መግደላዊት አዲስ ሚና ተሰጥቷታል፡፡ ይኸውም የምሥጢር ልጅ የመውለዷ ጉዳይ እና ከኢየሩሳሌም መሰደዷን፣ የወለደችው ልጅ በሒደት ከፈረንሳይ የነገሥታት ትውልድ ጋር መጋባቱን፣ የልጅ ልጇቿ እነ ሊዮናርዶ ዳ ቪንቺ፣ አይዛክ ኒውተን ዓይነት የሳይንስና የሥነ ጥበብ ሊቃውንትን የሚያካትት ሲሆን የዚህ ቤተሰብ ሐረግ አሁን ድረስ በአውሮፓ እንደ ሚገኝ ገልጿል፡፡ ይህ ልቦለዳዊ ታሪክ በክርስትና እምነት የሚኖሩትን ሁሉ የሚፈትን ነው፡፡ ክብር ይግባውና ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ወልደ አምላክ ነው ብለን ለምናምን ሁሉ የዚህ ዓይነት ኑፋቄ ማንበብ ሆነ መስማት ባለንበት ዘመን ያለው መንፈሳዊ ፈተና ምን ያህል ውስብስብ፣ረቂቅና ከባድ እንደ ሆነ ያመላክተናል፡፡ በተለይ በምዕራቡ ዓለም እውነታና ልቦለድ ታሪክ በሚቀላቀልበት በዚህ ዘመን የእምነት ነገር የተናቀ በመሆኑ ማንም ተነሥቶ

*/ወደ ገጽ ፳፮ ዞሯል/*



**www.eotcmk.org**

# መካነ ሥላሴ

* አሳምረው ደሴ /በቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን የአርኬዎሎጂ ቡድን መሪ/
* ኃይሉ ዘለቀ /የታሪክ ዘመን አርኪዎሎጂ ኤክስፐርት/



የመካነ ሥላሴ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን /በ1968 ዓ.ም/



የመካነ ሥላሴ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን /አሁን/

## መግቢያ

የመካነ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን በአማራ ክልላዊ መንግሥት በደቡብ ወሎ ዞን ወረዒሉ ወረዳ የምትገኝ ናት፡፡ ከአዲስ አበባ 476 ኪሎ ሜትር እንዲሁም ከደሴ ከተማ 76 ኪሎ ሜትር ወረዒሉ ለመድረስ 15 ኪሎ ሜትር ሲቀረው ሰኞ ገበያ ተብላ ከምትጠራ አንዲት ትንሽ ከተማ በስተምዕራብ በኩል አራት ኪሎ ሜትር ርቃ ትገኛለች፡፡ በጂ.ፒ.ኤስ መለኪያም በ$10^0$ $44^1$ $57^{11}$ የኬክሮስ መስመርና በ$39^0$ $24^1$ $97^{11}$ ምሥራቅ የኬንትሮስ መስመር ላይ ዐርፋለች፡፡

## 2. የመካነ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ከታሪክ ጸሐፊዎች እይታ አኳያ

የታሪክ መዛግብትም ሆኑ አፈ ታሪኮች እንደ ሚስማሙበት ከሆነ ጥንታዊቷ የመካነ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችው ከዛሬ 485 ዓመታት በፊት በ1513 ዓ.ም ነበር፡፡ የቤተ ክርስቲያኗ የሕንፃ መሠረት የተጣለው በዐፄ ናዖድ ዘመነ መንግሥት /1489-1500 ዓ.ም/ ሲሆን፣ አስገንብተው ያስጨረሱት ልጃቸው ዐፄ ልብነ ድንግል /1500-1533/ ናቸው፡፡ በቤተ ክርስቲያኗ የምረቃ በዓል ላይ በ1513 ዓ.ም በሥፍራው በመገኘት ስለ ቤተ ክርስቲያኗ ያየውንና የሰማውን በመጻፍ ለትውልድ እንዲተላለፍ በማድረግ ግንባር ቀደሙ ፖርቱጋላዊው ፍራንሲስኮ አልቫሬዝ ነው፡፡ አልቫሬዝ ስለ ጥንታዊው ቤተ ክርስቲያን ሥነ ሕንፃዊ ጥበብ ያሰፈረው ሐተታ ከታሪካዊ መረጃነቱ በተጨማሪ ለአርኬዎሎጂና አርክቴክቸር ጥናትና ምርምር ጥሩ መነሻ ሊሆን የሚችል ነው፡፡ አልቫሬዝ ስለ ቤተ ክርስቲያኗ ሥነ ሕንፃዊ አወቃቀር እንዲህ ሲል ጽፏል፡- «ግድግዳዎቹ በጥርብ ድንጋይ ተሠርተው በሐረግ አጊጠዋል፤ ...... የዋናው በር መዝጊያ በወርቅና በብር ተለብጿል፡፡ በወርቁ ልባድ ውስጥ አንዳንድ የከበሩ ድንጋዮች ...... አሉ፡፡ ጣሪያዎቹ በስድስት ምሰሶዎች ላይ ዐርፈዋል፡፡ የውጭ ታዛውን 61 ረጃጅም ምሰሶዎች ደግፈውታል፡፡ ...... በሠገነቱ ዙሪያ እያንዳንዳቸው ከ16 ቅጽ ወርቀ ዘቦ ጨርቅ የተሠሩ 16 ተከፋች መጋረጃዎች አሉት.......፡፡»

በአሕመድ ኢብን ኢብራሂም አልጋዚ /ግራኝ አሕመድ/ የሚመራው የሙስሊሞች ሠራዊት የዐፄ ልብነ ድንግልን ጦር ድል አድርጎ የያኔዋን ዋስል፣ የዛሬዋን ወረዒሉ በመቆጣጠር የመካነ ሥላሴን ቤተ ክርስቲያን ከማጥፋቱ ቀደም ብሎ /ከ1524 ዓ.ም በፊት/ የቤተ ክርስቲያኗን ገጽታ በብዕሩ የከተበው የግራኝ አሕመድ ታሪክ ጸሐፊ ዓረብ ፋቂህ እንዲህ ሲል ገልጿታል፡ - «በዚህ በቤተ አምሐራ በሐበሻ ምሳሌ የሌላት አንዲት ቤተ ክርስቲያን አለች፡፡ እርሷን የሠራት የወናግ ሰገድ /ልብነ ድንግል/ አባት ንጉሥ ናዖድ ነው፡፡ የእርሷ ሥራና ጌጥ 13 ዓመት ፈጀበትና ሳይጨርሳት ስለ ሞተ ልጁ ወናግ ሰገድ ከአባቱ አስበልጦ 25 ዓመት ሙሉ አሠርቶ አስጨረሳት፡፡ ሁለመናዋ በወርቅ የተለበደ ስለሆነ እንደ እሳት ታንጸባርቃለች፤ በውስጧ ያለው ጻሕል፣ ሰንና ብርት የወርቅና የብር ነው፡፡ ስፏቷ መቶ ክንድ ቁመቷ ግን ከመቶ ኀምሳ ክንድ ይበልጣል፡፡ ሁለመናዋ በጌጠኛ እንጨትና ድንጋይ በወርቅና በከበረ ድንጋይ የተለበደ ነው፡፡ ስሟ በክርስቲያኖች ቋንቋ መካነ ሥላሴ ትባላለች፡፡ .... በዚህች ቤተ ክርስቲያን የዘርዐ ያዕቆብ የልጅ ልጅ የአድማስ ሰገድ /በእደ ማርያም/ ልጅ የናዖድ መቃብር አለ፡፡»

ያቺ በሥነ ሕንፃዊ ጥበቧና በተሠራችበት የከበሩ ድንጋዮች ወደር ያልተገኘላት የመካነ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን በኅዳር ሰባት ቀን 1524 ዓ.ም በግራኝ አሕመድ ፊታውራሪነት እንድትዘረፍና እንድትቃጠል እንደ ተደረገች ዓረብ ፋቂህ ጽፏል፡፡ ግራኝ አሕመድ ቤተ ክርስቲያኗ እንድትዘረፍና እንድትቃጠል ከማዘዙ በፊት የቤተ ክርስቲያኗን ሥነ ሕንፃ ማድነቁን ዓረብ ፋቂህ አልሸሸገም፡፡ «ይህን የመሰለ የወርቅ ሐውልት ያለበት በወርቅ የተሠራ ቤተ ክርስቲያን በሕንድ፣ በሮም /በቤዛንታይን/ ግዛት አይታችሁ ታውቃላችሁ?» ብሎ ግራኝ አሕመድ በዙሪያው ያሉትን ዓረቦች መጠየቁን የሚያትተው ዓረብ ፋቂህ፡- «ይህን የመሰለ በሮምም፣ በሕንድም አይተንም፣ አለ ሲባልም ሰምተን አናውቅም፤ በዓለምም የለም» ብለው መለሱለት ሲል ጽፏል፡፡

ሆኖም አልቫሬዝ የመካነ ሥላሴ ሕንፃ የማእዘን ድንጋዮች ትናንሽና በደረቅ ካብ የተሠሩ በመኾኑ የጣሪያው መዋቀሪያ እንጨት በግድግዳው እንደ ማያልፍ ገልጦ፣ ከቤተ ክርስቲያኗ የሚበልጡ ሕንፃዎችን በአውሮፓ ማየቱን ቢያትትም የመካነ ሥላሴ ሕንፃ ጥበብ፣ ግዙፍነትና በከበረ ድንጋይ ያጌጠች እንደ ነበረች አረጋግጧል፡፡ ይህ የሚያመለክተው የመካነ ሥላሴ ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን እንደ ላሊበላ ውቅር ሕንፃዎች፣ እንደ ዐፄ ፋሲል /ጐንደር/ ቤተ መንግሥቶች ሁሉ በወቅቱ የነበሩትን ኢትዮጵያውያንን የሕንፃ ጥበብ የሚያሳይ አሻራ ነው፡፡ የመካነ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ሕንፃ ጥበብ የላሊበላ አብያተ ክርስቲያናት በተሠሩበት ዘመንና በጐንደር የፋሲል አብያተ መንግሥታት የተሠሩበት ዘመን መካከል መገኘቱ ያ የኢትዮጵያውያን የሥነ ሕንፃ ጥበብ ቀጣይነት እንደ ነበረው ጠቋሚ ሊሆን ይችላል፡፡

ከግራኝ አሕመድ ሠራዊት ዘረፋና ቃጠሎ የተረፈው የቤተ መቅደሱ የመሠረት ግንብ፣ የቅድስቱና የቅኔ ማሕሌቱ መለያ ግንቦች በዕድሜ ጫና፣ ጥበቃና ክብካቤ በማጣት እየፈራረሱ ወደ አፈርነት እየተለወጡ ለዘመናት ቆይተዋል፡፡

## 3. የመካነ ቅርሱ አሠራርና መጠን

የመካነ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን እንደ አካባቢው አጠራር ገሀ ተብሎ





www.eotcmk.org

ከሚጠራ የኖራ ድንጋይ የተሠራ፣ ሰፊና ግዙፍ ቤተ ክርስቲያን ነው:: ይህ ቤተ ክርስቲያን አራት ጉኖቹ እኩል የሆኑ ቤተ መቅደስና ቅድስት የነበረው ሲሆን ቅኔ ማሕሌቱ ክብ ነው::

የቤተ መቅደሱ ወለል 20 ሜትር በ20 ሜትር ሆኖ የቤተ መቅደሱ መሠረት ግንብ አራቱም ጎኖች ተለክተው 26 ሜትር በ26 ሜትር ሆኖ ተገኝቷል:: ከቤተ መቅደሱ እስከ ቅድስቱ መሠረት ድረስ ያለው ርዝመት አምስት ሜትር ሲሆን ከቅድስቱ እስከ ቅኔ ማሕሌቱ ያለው ርቀት 16 ሜትር ነው:: በዚህ መሠረት ቤተ ክርስቲያኑ ከደቡብ እስከ ሰሜን 47 ሜትር እንዲሁም ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ 47 - ሜትር ያህል መሆኑ ተለክቶ ተረጋግጧል::

ከቤተ መቅደሱ ወለል እስከ መሠረቱ ያለው ጥልቀት ሁለት ሜትር ሲሆን በቤተ መቅደሱ ወለል ላይም 16 መንበሮች መኖራቸው በተካሄደው የቅርስ አድን ሥራ ወቅት ማወቅ ተችሏል:: መንበሮቹም አራት አራት ሆነው በአራቱም ጎኖች ተቀምጠዋል:: መንበሮቹ በጠፍጣፋ ገሀ ድንጋይ በመስቀል ቅርጽ የተሠሩና አራቱም የመንበሮቹ ጉኖች /አንድ ሜትር ከ10 ሣ.ሜ/ እኩል ናቸው::

በደቡብ፣ በሰሜን፣ በምዕራብና በምሥራቅ በኩል ወደ ቤተ መቅደሱ የሚያስገቡ አራት ደረጃዎች እንደ ነበሩት ታውቋል:: በሰሜንና በደቡብ በኩል ያሉት ደረጃዎች አራት ሜትር ቁመትና ሦስት ሜትር ጉኖች ያሏቸው ሲሆን በምዕራብና በምሥራቅ በኩል የነበሩት ደረጃዎች ወድመዋል::

በቤተ መቅደሱና በቅድስቱ ወለል እስከ መሠረት ግንብ ጥልቀት ባለው ሁለት ሜትር ቁመት ላይ የዘመኑን የሥነ ሕንፃ ምሕንድስናና ጥበብ የሚያንጸባርቁ የተለያዩ ጌጣጌጦች ተቀርጸው ይታያሉ:: እነዚህም ጌጣጌጦች የሐረግና የተለያዩ አበባዎች ቅርጾችን እንዲሁም የተለያዩ ምስሎችን ይዘው ይገኛሉ::

በሌላ በኩል በጥንታዊው የመካነ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ቤተ መቅደስ ወለል ላይ በዐፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት ተሠራች ተብሎ በአካባቢው ነዋሪዎች የሚነገር አንዲት አነስተኛ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ቆማ ትገኛለች:: ቤተ ክርስቲያኗ መጀመሪያ ስትሠራ በሣር የተከደነች እንደ ነበርና በኋላ ግን የሣሩ ክዳን ተነሥቶ ቆርቆሮ መልበሷን ግድግዳዋ ግን ሳይነካ ቀድሞ በነበረበት ሁኔታ ላይ እንዳለ ነዋሪዎቹ ያስረዳሉ:: የቤተ ክርስቲያኗ ግድግዳ ከድንጋይ የተሠራ ሆኖ ከእነዚህ የግድግዳ ድንጋዮችም የተወሰኑት የጥንቱ የመካነ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ፍራሽ እንደ ሆኑ ለማወቅ ተችሏል:: ይህች ቤተ ክርስቲያን እስከ አሁን ድረስ አገልግሎት በመስጠት ላይ እንደ ምትገኝ በግልጽ ታውቋል::

4. መካነ ቅርሱ አሁን ያለበት ሁኔታ

የመካነ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ዕድሜ ጠገብ እንደ መሆኑ መጠን ዝናምና ፀሐይ እየተፈራረቁ እያበላሹት ይገኛሉ:: ከፍታ በሌለው የድንጋይ ካብ የታጠረና ጠንካራ በርም ስለሌለው ልጆችና ከብቶች በቀላሉ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ግቢ በመግባት በቅርሱ ላይ ጉዳት ሊያደርሱ እንደ ሚችሉ መረዳት አያዳግትም:: በጥንታዊቷ የመካነ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ቤተ መቅደስ ወለል ላይ በዐፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት ተሠራች ተብሎ የሚነገርላት ቤተ ክርስቲያን በአሁኑ ጊዜ አገልግሎት እየሰጠች ነው:: ስለሆነም ተገልጋዩ ወገን ጥንታቂ በጐደለው ሁኔታ በየጊዜው በቤተ መቅደሱ ወለል ላይ በመውጣትና በመውረድ ሊጐዳው እንደ ሚችል መገንዘብ ተችሏል::

ጥንታዊው የመካነ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ተሠርቶ ባለቀ በዐሥራ አንድ ዓመቱ በግራኝ አሕመድ ወረራ ጊዜ እንደ ተቃጠለ የታሪክ መዛግብት ያስረዳሉ:: ከዚህ ሌላ የአካባቢው ነዋሪዎች በተለያዩ ጊዜያት ከቤተ ክርስቲያኑ ላይ ንጣፍ ድንጋዮችን በማንሣት ለቤት መሥሪያ፣ ለአጥርና ለመቃብር መዘጊያ አገልግሎት ያውሉት ስለነበረ አሁን ቅርሱ በጣም ተጐድቶ ይገኛል:: ይኸውም የመቅደሱ፣ የቅድስቱና የቅኔ ማሕሌቱ ግድግዳዎች ወድመዋል:: ለምልክት የተረፈው የመቅደሱ ግድግዳ ብቻ ነው:: የዘመኑን ሥነ ጥበብ የሚያመላክቱ ብዙ ጌጣጌጥ የተሣለባቸው ጠፍጣፋና ባለአራት ማእዘን የገሀ ድንጋዮች ከነበሩበት ቦታ ተነሥተዋል፣ ተሰባብረ ዋልም:: ከግንዛቤ ጉድለት የተነሣና የቅርስን ምንነ ትና ጥቅም ባለማወቅ አንዳንድ ያካባቢው ነዋሪዎች በሰሜን፣ በደቡብና በምዕራብ በኩል የቤተ መቅደሱን መሠረት በመቆፈር በመሬት ውስጥ ተቀብረው የነበሩ የአርኬዎሎጂ መረጃዎችን አበላሽ ተዋል:: በደቡብና በምዕራብ በኩል ያሉት የቤተ መቅደሱ ጉኖች በከፊል ዘመው ይታያሉ:: የቤተ መቅደሱ ወለልም በመጠኑም ቢሆን ሰርጉዶ የሚታይ ሲሆን በላዩ ላይ ያሉት መንበሮች ግን ከሌሎች በተሻለ ሁኔታ ላይ ይገኛሉ::

ቤተ ክርስቲያኗ ታሪካዊነት ስላላት ከቴክኒክ አሠራሯና ጥበቧ አኳያ ትምህርት ሰጪ ናት:: ይሁንና ክብካቤና ጥበቃና የጐደለው ለመሆኑ ከቤተ ክርስቲያኗ ገጽታ ለመረዳት ችለናል::

የመካነ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን የሕንፃ ቅሪት ከ485 ዓመታት በላይ ማስቆጠሩ ቅርስን ዕድሜ ጠገብ የሚያደርገው ሲሆን፣ የሥነ ሕንፃው ምሕንድስና እና ጥበብ በዘመኑ ከነበሩት የተለየ ነው:: ጥንታዊው ቤተ ክርስቲያን ከአብ ዛኞዎቹ ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናት በተለየ መልኩ ሰፊና ግዙፍ መሆኑ ራሱ ልዩ ያደርገዋል:: ቤተ ክርስቲያኑ የተሠራበት ጥሬ ዕቃ /ገሀ ድንጋይ/ በአካባቢው በቅርብ ርቀት አለመገኘቱና በሌሎች በአካባቢው ባሉ አብያተ ክርስቲያናት ጥቅም ላይ ውሎ አለመታየቱ ቤተ ክርስቲያኑ በጥንቃቄና ታስቦበት የተሠራ መሆኑን ይጠቁማል:: ቤተ ክርስቲያኑን ለመሥራት የፈጀው ዓመት ረጅም መሆን የቤተ ክርስቲያኑን ታሪክ ልዩ ያደርገዋል:: ይህ ሁሉ ዘመን ከዚያም በኋላ ያለውን ጊዜ የሚጠቁሙ አርኬዎሎጂያዊ፣ ታሪካዊና ባህላዊ መረጃዎችን ሸሽጐ መያዙ አይቀሬ በመሆኑ፣ እነዚህን መረጃዎች የማዳን ተግባር አስፈላጊነቱ ከፍተኛ ነው::

በቅርሱና በአካባቢው የተካሄደውን የቅኝት ሥራ ውጤት መሠረት በማድረግ የጥንታዊዋን ቤተ ክርስቲያን ግቢ የማጽዳት ሥራ በማከናወን፣ የቤተ መቅደሱን መሠረተ ዙሪያና ወለሉን በማጽዳት በወለሉ ላይ የነበሩ የመስቀል ቅርጽ የነበራቸው 16 ወንበሮች በጉልህ እንዲታዩ ሆነዋል::

የሙከራ ቁፋሮ ተካሂዶ የቤተ መቅ ደሱ የመሠረት ግንብ ጥልቀት ምን ያህል እንደ ሆነ ተረጋግጧል:: የቤተ መቅደሱን፣ የቅድስቱንና የቅኔ ማሕሌቱን የግንብ መጠን በመለካት መጠነ ዙሪያቸውን፣ ስፋታቸውንና ርዝመታቸውን፣ ለማወቅ ተችሏል:: የቅኝት ስልቱን ውጤት በመንተራስ የዘመሙና ሊወድቁ ተቃርበው የነበሩ የቤተ መቅደሱ መሠረት ድንጋዮችን በደረቅ ካብ በመካብ ደግፎ በጊዜያዊነት እንዲያቆያቸው ተደርጓል:: ይህም ተግባር ቅርሱ አጠቃላይ ጥገና እስከሚካሄድለት ድረስ ጊዜያዊ ድጋፍ እንደ ሚሆነው ይታመናል::

የቅኝቱንና የአሰሳውን ስልት መሠረት በማድረግ የተጐዳውን የቤተ ክርስቲያኗን ፍርስራሽ ክፍል ደኅና ከሚባለው ለመለየት ተችሏል:: ባለማወቅ ተቆፍረው ለጥፋት ተዳርገው የሚገኙትን የቤተ መቅደሱን ክፍሎች አፈር በመመለስ ለዝናም፣ ለፀሐይ፣ ለሰውና ለእንስሳት ተጋልጠው ጉዳት እንዳይደርስባቸው ለማድረግ ተችሏል::

በጣም ጉዳት ደርሶበት ያለው ምሥራቃዊው የቤተ መቅደሱ ጉን አፈሩ በዝናም ታጥቦ /ተሸርሽሮ/ ተጨማሪ ጉዳት እንዳይደርስበት ድንጋይ የማልበስ ሥራ ተሠርቷል:: በተጨማሪም በዚሁ በምሥራቃዊው ጉን ላይ ተከማችተው የነበሩ፣ ለሕንፃው ባዕድ የሆኑ ድንጋዮች ከሥር ያለውን የመሠረት ድንጋይ ስለ ጐዱት ከቦታቸው በማስወገድ፣ ከቤተ መቅደሱ እስከ ቅድስቱ መለያ ግንብ ድረስ ታጥሮ የነበረውን የድንጋይ ካብ በማንሣት ለሰዎች መተላለፊያ እንዲሆን በማስቻል፣ ምእመናን በፍርስራሹ ላይ እንዳይረማመዱ ማድረግ ተችሏል::

ለአካባቢው ማኅበረሰብ ስለ ቅርሱ ምንነትና ጠቀሜታ እንዲሁም ክብካቤና ጥበቃ ብሎም ለወደፊት ስለሚያስገኘው ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊና ማኅበራዊ ጠቀሜታ ግንዛቤ በማስጨበጭ፣ ኅብረ ተሰቡ ጠቃሚ ትምህርት /መረጃ/ እንዲያገኝ ማድረግ ተችሏል::

ከላይ ከተጠቀሰው ጋር በተያያዘ መካነ ቅርሱን ለወደፊት የሚጠብቅና የሚከባከብ፣ ዘጠኝ አባላትን ያቀፈና ከተለያዩ የኅብረተሰቡና የመንግሥት አካላት የተወጣጣ «የመካነ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ጥበቃና ክብካቤ ኮሚቴ» ማቋቋም ተችሏል::

6. ግኝቶች

በአርኬዎሎጂ አሰሳ ሥራ የቤተ ክርስቲያኗን ቅኔ ማሕሌት መጠነ ዙሪያ ለማግኘት ተችሏል:: በዚሁ አሰሳ የተቃጠሉ ድንጋዮች፣ ከሰል፣ የተሰባበሩ ሸክላዎች፣ ቁርጥራጭ ብረቶች፣ የጥይት ቀለሀ፣ የሰው ዐፅም..... ተገኝተዋል::

በሰሜን የቤተ መቅደሱ ጉን የአርኬዎሎጂ ሙከራ ቁፋሮ ተደርጐ የቤተ መቅደሱና የቅድስቱ የመሠረት ግንብ ጥልቀት ታውቋል:: ከቤተ መቅደሱ ወለል እስከ መሠረቱ ያለው ቁመት ሁለት ሜትር መሆኑም ተረጋግጧል:: በአፈር ሥር ያለው የመሠረት ድንጋይ 50 ሣንቲ. ሜትር ጥልቀት ያለው መሆኑም ታውቋል:: በቁፋሮው የወጡት መረጃዎች ሸክላዎች፣ የተቃጠሉ ድንጋዮች፣ ከሰል፣ የሰው ወይም የእንስሳት ዐፅም ..... ናቸው::

በአጠቃላይ የመካነ ሥላሴን ቤተ ክርስቲያን ጥንታዊነት፣ ታሪኩን፣ የሕንፃውን ምሕንድስናና ጥበብ እንዲሁም አሁን የምትገኝበትን ሁኔታ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ተጠብቃ፣ ከጥፋትና ብልሽት ድና ለተገቢው ጥናትና ምርምር እንድትበቃ ብሎም ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጠቀሜታ እንድታስገኝ የሚከ ተሉትን ሐሳቦች ተግባራዊ ማድረግ ተገቢ መሆኑን እንገልጻለን::

1. በመካነ ቅርሱ አካባቢ የሚገኙ ነዋሪዎች ቅርሱን በመጠበቅ ከፍተኛ ተሳትፎ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል:: ይኸውም ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ቅጥር ግቢ ውስጥ ከብቶችና ሕፃናት እንዲሁም አንዳንድ ስለ ቅርስ ግንዛቤ የሌላቸው ሰዎች ከሌላ ቦታ እየመጡ ባለማወቅ ገብተው እንዳያበላሿቸው ነዋሪዎቹ መጠበቅ ይኖርባቸዋል::

2. የተቋቋመው የመካነ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ቅርስ ጥበቃና ክብካቤ ኮሚቴ ቅርሱም ምን ያህል እየተጠበቀ እንደ ሚገኝ በየጊዜው ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይገባዋል::

3. የመካነ ቅርሱን ቦታ ከልሎ የማስጠበቅ ሥራ በተቻለ ፍጥነት መሠራት አለበት::

4. በቤተ ክርስቲያኑ ቅጥር ግቢም ሆነ በዙሪያው ምንም ዓይነት ቁፋሮ መካሄድ የለበትም::

5. ቤተ ክርስቲያኑ በቃጠሎ የተጐዳ ስለሆነና የዕድሜ ብዛትም ስላለው በቀላሉ ሊበላሽ ስለሚችል በቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣንን አስቸኳይ ጥገና ሊያደረግለት ይገባል:: ፀሐይና ዝናምም ተፈራርቀው ከናካቴው እንዳያጠፉት መጠለያ ሊሠራለት የግድ ይላል::

6. በጥንታዊዋ የመካነ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ቤተ መቅደስ ወለል ላይ በዐፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት ተሠራች የተባለችው አነስተኛ ቤተ ክርስቲያን በአሁኑ ጊዜ አገልግሎት እየሰጠች ስለሆነ ከዚህ አገልግሎት ጋር በተያያዘ ልጆች ወደ ግቢው እየገቡ በቅርሱ ላይ በመጫወት ሲጐዱና አንዳንድ እንስሳትም ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ግቢ ውስጥ እየገቡ ከግንቡ ጋር በመታከክ ጥፋት ሲያደርሱ ተመልክተናል:: ከዚህ በተጨማሪ ብዙ ምእመናን በዕለተ እሑድና በሌሎች በዓላት ቀናት በቤተ መቅደሱ ወለል ላይ እየወጡ ስለ ሚጸልዩ የሰረጐደው ወለል በክብደትና ጥንቃቄ በጐደለው አያያዝ ሊፈርስ እንደ ሚችል እሙን ነው:: በጥንታዊው ቤተ ክርስቲያን ፍራሽ ቅርስ ላይ እየተሰጠ ያለው ሃይማኖታዊ አገልግሎት በቅርስ ላይ ተጨማሪ ጉዳት የሚያስከትል ስለሆነ መቆም አለበት:: በቦታው ላይ ሊሠራ የታቀደው አዲስ ግንባታም መካሄድ የለበትም::

7. ከተቋቋመው ኮሚቴ ጋር በመተባበርና ኅብረተሰቡን በቀጥታ በማሳተፍ የቅርስ አስተዳደርና ጥበቃ ሰነድ መዘጋጀት ይኖርበታል:: ✠

*የትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት ሥራ አስኪያጅ የኾኑት ሊቀ ካህናት ብርሃኑ ገብረ ዐማኑኤል ለዚህ ዝግጅት መሳካት ላደረጉልን አስተዋፅኦ ከፍ ያለ ምስጋናችንን እናቀርባለን::*



www.eotcmk.org

# ስምዖን ዘዓምድ

/ጌታቸው በቀለ/

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ቅዱሳንን በብቃታቸው፣ በሃይማኖት ጽናታቸው፣ በሐዋርያዊ ተልእኳቸውና በተአምር ሠሪነታቸው የቅዱስነት ደረጃ እየሰጠቻቸው በስማቸው ታቦት ቀርጻ፣ ገድላቸውን ጽፋ ታከብራቸዋለች::

ቅዱሳን በመራራ ተጋድሎና መሥዋዕትነት፣በሐዋርያዊ ተልእኮ ስብከተ ወንጌልን በማስፋፋት ተግባር ላይ የሚሠማሩት የዕለት ምግብ፣ የዓመት ልብስ አጥተው፤ ተጋድሎን እንደ አንድ መተዳደሪያ አማራጭ በመውሰድ አይደለም:: ከነገሥታት ተወልደው፣ በቤተ መንግሥት አድገው፣ የዚህን ዓለም ምቾትና ቅንጦት፣ ተድላና ደስታ ንቀው በመተው በክርስቶስ ትምህርተ ወንጌል ተመሥጠው እንደ አባቶቻቸው ሐዋርያት፣ ጻድቃንና ሰማዕታት ዘለዓለማዊውን ሕይወት በመምረጥ ወደ ፍጹም ምናኔና ገድል የገቡ ናቸው:: ከእነዚህ ቅዱሳን መካከል አንዱ ስምዖን ዘዓምድ ነው::

በአምስተኛው ምእተ ዓመት አዲስና ዓይነተኛ የቅድስና መንገድ አዕማድ ለተባሉ ቅዱሳን አባት በሆነው በስምዖን ተከፈተ:: እነዚህ ቅዱሳን ለረጅም ዓመታት፣ እግዚአብሔርን በመሻት ቀንና ሌሊት፣ በጋና ክረምት፣ ዝናምና ፀሐይ፣ ውርጭና ንዳድ እየተፈራረቀባቸው በተራራ ላይ፣ ጣራ በሌለው ቤት በጾምና በንስሐ ሕይወት አሳልፈዋል:: በዚሁ ተጋድሎአቸው ሊያልፉበት ጭንቅ የሆነውን ጠባቡን የገነት መንገድ አለፉ::

የስምዖን ታሪክ በዘመኑ ከነበሩ እና የዐይን ምስክር ከሚሆኑ ሦስት ሰዎች የተገኘ ነው:: የእንጦንስ፣ ቆዝሞስ እና በተለይ ደግሞ በዝርዝር የጻፈው ቴዎድሮት ይጠቀሳሉ:: ቴዎድሮት ታሪኩን የጻፈለት ስምዖን ከማረፉ ከ16 ዓመታት በፊት ነበር::

ቅዱስ ስምዖን የተወለደው በ389 ዓ.ም በሲሳ /Sissa/ ከተማ ነው:: ከተማዋ ከቂ ሮስ በስተ ሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ 40 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ትገኛለች:: ስምዖን የሚናገረው ቋንቋ አርመን ሲሆን በኋላ የግሪክ ቋንቋ በገዳሙ ውስጥ ተምሯል:: / History of the Christian Church, Volume III: Nicene and post- Nicene Christianity. 311 – 600 A.D./

በነሐሴ 3 ቀን የሚነበበው ስንክሳር እንደ ሚተርከው ስምዖን ዘዓምድ በተወለደ በስድስት ዓመቱ እንደ አገራቸው ልማድ በሶርያ እና በኪልቂያ ድንበር ላይ በምትገኝ ቦታ የአባቱን በጐች ይጠብቅ ነበር:: ስምዖን በአባቱ የታዘዘውን የእረኝነት ተግባሩን እየተወጣ የ13 ዓመት ብላቴና ሳለ ፍቅረ እግዚአብሔር በልቡ አድሯልና ወደ ቤተ ክርስቲያን እየሄደ ቅዱሳት መጻሕፍትን ይሰማ ነበር:: በልቡናው ዘወትር እግዚአብሔርን ያስብ ቸርነቱንም ያደንቅ ነበር:: በኋላም በቤተ ክርስቲያን ሲነበብ ይሰማው እና ይመኘው በነበረው በቅዱሳን ሕይወት ተማርኳልና ራሱን ለገዳማዊ ሕይወት አዘጋጀ::



ስምዖን ዘዓምድ

ስምዖን የእግዚአብሔር ቸርነት አነሣስቶት፣ በሰማው ቃለ እግዚብሔር ልቡናው ተሰብሮ፣ በዓለም ከመኖር ይልቅ፣ እንደ ቅዱሳን አባቶቹ በበረሐ ወድቆ እግዚአብሔርን ማገልገል የሚሻል መሆኑን ተገነዘበ::

አብርሃም ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘት ከወገኑ ከቤተሰቡ ተለይቶ እንደ ወጣ፤ በሐዲስ ኪዳንም መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ ለሠላሳ ዓመታት ያህል በበረሐ እንደ ኖረ ስምዖን ዘዓምድም ይመኘው የነበረውን የክርስትና ሕይወት በመሻት በከተማው አቅራቢያ ወደ ምትገኝ አንዲት አነስተኛ ገዳም ሄደ:: ወደ ገዳሙም በደረሰ ጊዜ ሳይበላና ሳይጠጣ ገዳማውያኑን ሊያዩት በሚችሉት በገዳሙ መግቢያ ፊት ለፊት ወደቀ:: ገዳማውያኑም እንደ አንድ ትንሽ አገልጋይ ተቀብለው ወደ ገዳሙ ያስገቡት ዘንድ ተማፀናቸው::

በመጽሐፈ መነኮሳት «ጸጋ ክብር ለማግኘት ምግባር ትሩፋትን አብዝቶ ለመሥራት የሚወድ ሰው ቢኖር አስቀድሞ ከዓለማዊ ግብር መለየት ይገባዋል» እንዳለ ቅዱስ ይሥሐቅ በዚህ ዓለም ለጊዜው ሰውነትን ደስ ከሚያሰኘው ነገር መከራ መቀበልን ነው ስምዖን የመረጠው::

ስምዖን በዚያ ገዳም በፍጹም ትሕትና ወደ ገዳሙ አበ ምኔት ቀርቦ ይመኘው የነበረውን የክርስትና ሕይወት ነግሮ ወደ ገዳሙ እንዲያስገቡት ተማፀናቸው:: አበ ምኔቱ ስምዖንን የገዳሙ አባል አድርገው ከመቀበላቸው በፊት ልጅነቱን ተመልክተው ከባድና አስቸጋሪ የሆነውን የምንኩስና ሕይወት ሊቋቋም እንደ ማይችል ቢነግሩትም ስምዖን ግን አልተቀበለውም፤ በፈቃደ እግዚአብሔር ነበርና የተጓዘው በገዳሙ እያገለገለ መነኮሰ:: ለብዙ ዘመናትም በገድል ተጠምዶ በጾም፣ በጸሎት፣ በስግደት ተወስኖ ኖረ::

ስምዖን በሳምንት አንድ ቀን በዕለተ እሑድ ብቻ ራሱን አስለመደ፤ በጾም ወቅት አርባውን ቀናት በሙሉ በመጾም ያለምግብ ይሰነብት ነበር:: ይህን መሰል ሕይወት በሞቃታማው የአየር ጠባይ እንኳን በጣም የማይታመን ነው:: ይህን መሰሉ የመንፈሳዊ ሕይወት ተጋድሎ እስከ ሞት አድርሶት ነበር:: ነገር ግን የነበረው የመንፈሳዊ ሕይወት ጥንካሬ የደረሰበትን መከራ አስቻለው:: ቴዎዶሬት ሲጐበኘው ዐቢይ ጾምን ያለምንም እህል ውኃ አሳልፎ ነበር:: በዚህም ነቢያቱን ሙሴን፣ ኤልያስንና ፈጣሪው ኢየሱስ ክርስቶስን መስሏቸዋል::

/History of the Christian Church, volume III: Nicene and post-Nicene Christianity. 311-600.A.D. /

ሌላውና ስምዖን ዘዓምድን ከሌሎች ቅዱሳን ለየት የሚያደርገው ተጋድሎ ደግሞ ሰውነቱን ቀጭንና ጥልፍልፍ ባለ ገመድ አጥብቆ ማሰሩ ነው:: ስምዖን ዘዓምድ ወገቡን የታጠቀበት ገመድ ሥጋውን /ሰውነቱንም/ ከርክሮ ቆርጦት እስከ አጥንቱ ይደርስ ነበር:: ወገቡን የታጠቀበት ገመድ ሰውነቱን ከርክሮ ስለ ቆረጠው ሰውነቱ ቆሰለ፣ ተላ፣ ከሰውነቱም የሚከረፋ ሽታ ይወጣ ነበር:: ይህም አሠቃቂ የሆነ ሕማም አድርሶበታል:: ከመሽተቱ የተነሣ በአጠገቡ ሰው አያልፍም፤ የሚጠጋውም አልነበረም:: በዚህ ክፉ ጠረን በዚያ ገዳም የሚኖሩ መነኮሳት ተጸየፉት፤ በዐይናቸው ሊያዩትም አልወደዱም:: ስንክሳሩ እንደ ሚተርከው መነኮሳቱ ወደ አበ ምኔቱ ተሰብስበው በመሄድ:- «ይህን መነኩስ ስምዖንን ከዚህ ገዳም አባርርልን፣ አንፈልገውም፤ በእርሱ የሚገኘው ጽድቅ ይቅርብን፤ ከሰውነቱ የሚወጣው ሽታ አላስቀመጠንም፤ የማታባርርልን ከሆነ ግን ገዳሙንም አንተንም ጥለን እንሰደዳለን» ብለው:: ለመኑት:: /ስንክሳር ዘወርኀ ነሐሴ/::

አበ ምኔቱ የሰማው ነገር ሁሉ አዲስ ሆነበት:: በመነኮሳቱ አባባል ተገርሞ:- «ምንድን ነው ጥፋቱ? እስቲ ችግሩን በዝርዝር አስረዱኝ? ለምን በሰው ትፈርዳላችሁ?» አላቸው:: እነርሱም «እኛ ነግረንሃል፤ በተጨማሪም ማየት ማመን ነውና አንተ ራስህ መጥተህ እይና ለችግራችን መፍትሔ ስጠን?» አሉት::

አበ ምኔቱ የመነኮሳቱን ቃል ሰምቶ ስምዖንን አስጠርቶ አንድ ጥያቄ ጠየቀው፤ ስምዖንም መጥቶ በፊታቸው ቆመ:: ከተጋድሎው የተነሣ ከሰውነቱ ደምና መግል በእግሮቹ ላይ ይፈስ ነበር:: አበ ምኔቱም ስምዖን ዘዓምድን ተመልክቶ እጅግ ተጨነቀ:: የስምዖንን ልብስ ገልጦ ሲመለከት ሰውነቱን ከርክሮ የገባውን ገመድ አይቶ አዘነ:: ስምዖንን: - «ሰውነትህ እንደዚህ እስኪቆስል ድረስ ይህን ታደርግ ዘንድ እንዴት ደፈርክ?» አለው:: ሰውነቱን ከርክሮ የገባውን ገመድ ቀስ ብሎ አወጣለት:: ቁስሉም እስከ ሚድንለት ድረስ ለኀምሳ ቀናት



www.eotcmk.org

ስቶስ ለእናቱ በጎ ነገርን ያደርግላት ዘንድ ስለርሷ ለመነ /ጸለየ/:: ያን ጊዜም እናቱ ስምዖን ዘዓምድ በሚጸልይበት ምሰሶ ሥር እንደ ተኛች /በእንቅልፍ ላይ እንዳለች/ ዐረፈች:: ከደንጊያው ምሰሶ በታችም ቀበሩዋት::

ለበጎ ነገር የማይተኛው ሰይጣን ስምዖን ዘዓምድን ለማሳት የማያደርገው ነገር አልነበረም:: ሰይጣን በስምዖን ላይ ቀንቶ እግሩን መታው፤ ከእግሩ ትል እየወደቀ በአንዲት እግሩ ለብዙ ዓመታት ኖረ:: ከዚህም በኋላ የሽፍቶች አለቃ ወደርሱ መጥቶ ንስሐ ገባ:: ጥቂት ቀኖችም ኑሮ ዐረፈ፤ በጸሎቱም የዘለዓለም ሕይወትን ወረሰ:: ወደርሱ ስለሚመጡ ብዙ ሰዎችም የውኃ ጥማት እንዳያስጨንቃቸው ወደ እግዚአብሔር ለምኖ ከድንጋይ ምሰሶው ስር ፈዋሽ ጠበል አፈለቀላቸው:: የካቲት ዘጠኝ ቀን የሚነበበው ስንክሳር እንደ ሚተርከው የስምዖን ዘዓምድን ቅድስና በመንፈስ ቅዱስ መነጽርነት የተመለከተው አባ በርሶማ የተባለ አባት ነው:: አባ በርሶማ በኤፌሶን ንስጥሮስን ለማውገዝ ከተሰባሰቡት ሊቃውንት አንዱ ነበር:: ስምዖን ዘዓምድን ሊያየው ወደደ:: ስምዖንም የአባ በርሶማን ዜና ከብዙ ሰዎች ሰምቶ ነበር:: አባ በርሶማ ወደ ስምዖን መጥቶ እርስ በርሳቸው በረከትን ተቀባበሉ:: በኋላም በሶርያ አገር እያስተማረ በፊታቸው ተአምራትን በአደረገ ጊዜ በትምህርቱ ብዙዎች አመኑ:: /ስንክሳር÷ ዘወርኀ የካቲት/:: በኋላም ወደ ሌላ ምሰሶ ተዛወረ:: በእርሱም ላይ እየተጋደለ ሠላሳ ዓመት ኖረ::

ስምዖን ዘዓምድ ብዙዎች አረማውያንንና ከሐድያንን አስተምሮ አሳምኖ ወደ ፈጣሪያቸው እግዚአብሔር መልሷቸዋል:: ቅዱስ ስምዖን በዚያ ረጅምና አድካሚ ገዞ /ተጋድሎ/ ቀናትን፣ ሳምንታትን፣ ወራትንና ዓመታትን ለሚያቃጥል ፀሐይ፣ ለሚያርስ ዝናም፣ ለሚሚጭር ጫካ /እሾህ/፣ ለሚያፏጭ ውሽንፍር ራሱን መሥዋዕት አድርጐ ገብሮ ለበርካታ ዓመታት ቆሟል:: ዕለት ዕለት በሞት ጥላ ውስጥ እያለፈ በሰማዕትነት ኖሯል:: በምድራዊ ቆይታውም ለሥጋዊ ምቾትና የነፍስ ዕረፍት ቦታ አልሰጠም:: ከዚህ ይልቅ ለሌሎች ሰዎች ለላቀ የቅድስና ሕይወት ከልቡ ተጣጣረ እንጂ፤ በሰማይ ላለው የከበረ ሽልማት እና በምድር ላይ ለማይሞት ተው ስሙ ተጋደለ:: ስምዖን ዘዓምድ በተወለደ በ69 ዓመቱ በ459 ዓ.ም ነሐሴ ሦስት ቀን በሰላም ዐርፎ ወደ ወደደው ክርስቶስ ሄደ፤ የዘላለም ሕይወትንም ወረሰ::

የአንጾኪያው ሊቀ ጳጳስ ቅዱስ አባ ስምዖን እንዳረፈ በሰማ ጊዜ ካህናትን፣ ዲያቆናትንና የአገሩን መኳንንቶች ከእርሱ ጋር ይዞ የቅዱስ አባ ስምዖን ሥጋው ወዳለበት ደረሰ:: በታላቅ ክብርም ተሸክመው እየዘመሩና እያመሰገኑ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አኖሩት:: ከሥጋውም ድንቆችና ተአምራት ታላቅ ፈውስም ተገለጡ:: የቅዱስ ስምዖን ልመናው ይደረግልን፤ በረከቱ ይደርብን:: አሜን::

# ደባ ተውኔት እና...

/ከገጽ ፳፩ የዞረ/

የሌሎችን አምልኮ እያንኳሰሰ ቢጽፍ የሚጠየቅበት ሥርዐት አለመኖሩ የእምነትን ኃይል ለማዳከምና ለማቀዝቀዝ ትልቅ በር ከፍቷል::

ባለንበት ዘመን ብዙ ደራስያን የጥንት ታሪኮችን መሠረት በማድረግ በብዙ ተመራማሪዎች ዘንድ በእርግጠኝነት ሊታወቁ ያልቻሉ ጉዳዮችን በማንሣት መጻሕፍትን የመጻፍ ዝንባሌ ያሳያሉ:: የዳ ቪንቺ ኮድ ታሪክ በሚያጠነጥንባቸው ጉዳዮች ላይ የተጻፉ ብዙ መጻሕፍት አሉ:: እነዚህ ጭብጦች የአያሌ አንባብያንን ትኩረት የሚስቡ በመሆናቸው ለደራስያኑ ከፍተኛ ንዋይ ስለሚያስገኙ ለዓለማውያኑ ያላቸው ጠቀሜታ በዚያው መጠን የሚታይ ነው::

ደራሲው የራሱን አስተሳሰብ በአንባቢው ልቡና ለማንገሥ ሐሳቡን የሚያራምዱለት ባለታሪኮች የሚያቀርቡትን መላምት የሚሞግት እንዳይኖር አድርጓል:: ለምሳሌ ቲቢንግ የተባ ለው ባለታሪክ የሚሰነዝራቸውን ሐሳቦች በምልክቶች መካከል ያለውን ዝምድና በማጥናት የታወቀው ፕሮፌሰር ላንግደን እንኳ መልሶ ሲጠይቅ አይደመጥም:: ይህ ሆን ተብሎ የተደረገ ነው:: በተለይ የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ ጠንቅቆ የማያውቀውን ክርስቲያን አመለካከት የሚያዛባ ነው:: *«ቅዱሳት መጻሕፍት በአራተኛው ምእተ ዓመት እንደ ገና ተከለሱ፤ ተጻፉ»* የሚለውን ሐሰት መቀበል አደገኛ ነው::

የዳ ቪንቺ ኮድ መጽሐፍ፡- «ቤተ ክርስቲያን ሴቶችን በማጥላላት፣ እንደ ጠንቋይ በመቁጠር በመንፈሳዊ አገልግሎት እንዳይሳተፉ አድርጋለች» ይላል:: አያይዞም *«የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በኃይል የመጠቀም ታሪክ ያላት በመሆኑ የቤተ ክርስቲያን አባላት ሃይማኖት የለሾቹን «እንስት አምላኪዎች» ለማስተማር /ለመለወጥ/* በሚል ሰበብ ለሦስት ክፍለ ዘመናት ብዙዎችን ጨፍጭፈዋል::» ይህ እምነቱን የማይቀበሉትን ለማጥፋት በቫቲካን ውሳኔ የተቋቋመ የካቶሊክ «እንኵዊዚሽን ቡድን» ያከናወነውን ተግባር «የሴት ጠንቋዎች መዶሻ» በተሰኘው መጽሐፍ ዝርዝር ታሪኩ ተጽፏል:: በዚህ ሒደት የነጻ አስተሳሰብ ባለቤት የሆኑ ሴቶች እንዲገደሉ ተደርጓል::» የሚል ክስ ያቀርባል ዳን ብራውን:: በርግጥ የጥንት ቤተ ክርስቲያን የሴቶችን ሚና በማንኳሰስ የወንዶች የበላይነት እንዲነግሥ አድርጋለች ወይ? የሚለውን ጥያቄ በሚመለከት እውነታውን ስንመለከት ቤተ ክርስቲያንን የመሠረታት መድኃኔ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ስብከቱ ቅዱሳን አንስት ተከትለውት እንደ ነበር በወንጌል ተጽፎልናል:: በቤተ ክርስቲያንም ታሪክም ብዙ ሴቶች በሰማዕትነትም በሐዋርያዊነት ከፍተኛ ሚና እንደ ተጫወቱ እንረዳለን:: የግኖስቲኮችን እምነት መሠረት አድርገው በዘመናችን ለሴቶች እኩልነት /የበላይነት/ ቆመናል የሚሉት አካላት (Feminist) የሚያስተ ምሩት ፍልስፍና:- «ማርያም መግደላዊት በጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን ከሁሉም ሐዋርያት የተለየ /የበለጠ/ ደረጃ ነበራት» ቤተ ክርስቲያናችን እንደ ምታስ ተምረው፤ የሴቶች እኩልነት በሁሉም መስክ የሚታይ ሲሆን ቤተ ክርስቲያን በጾታ የተመሠረተ የሥራ /የተልእኮ/ ክፍፍልና ድርሻ የሰጠችው ፈጣሪ ያደረገውን የድርሻ /የተል እኮ/ ክፍፍል መሠረት በማድረግ መሆ ኑን ለሁሉም ታስተምራለች:: ቤተ ክርስቲያን በምእመናን ዘንድ ለሚነሡ መሠረታዊ መንፈሳዊ ጥያቄዎች ተገቢና ወቅታዊ ምላሽ በመስጠት እውነተኛውን ትምህርት ማስተማር ይጠበቅባታል በሚለው ብዙዎች ይስማማሉ::

ይህ መጽሐፍ ክርስትናን ለመንቀፍ የወጣ ቢሆንም ይህን አጋጣሚ በመጠቀም ስለ እምነታችን እውነቱን ለማስተማር እንችላለን:: የጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት እና የመጽሐፍ ቅዱስን እውነተኛነት በሚመለከት በተለያዩ ጊዜያት የኑፋቄ ትምህርቶች መነዛታቸው እንግዳ ነገር አይደለም:: ይሁን እንጂ የቤተ ክርስቲያን ልጆች በዲያብሎስ ልዩ ልዩ ወጥመዶች እንዳንታለል መጠንቀቅ፣ የእርሱ ሐሳብ ምን እንደ ሆነ ልንስተው አይገባም:: /1ቆሮ.2÷11/:: ቤተ ክርስቲያንን የሲዖል ደጆች እንደ ማያናውጧት እናምናለንና ሃይማኖታችንን ጠንቅቀን በማወቅና ለሌሎች በማስተማር ብልቦለድ ታሪክና ለምንምና ለማንም በማይጠቅም ዘመን አመጣሽ ፍልስፍና በመመራት ልንስት አይገባም:: ስለሆነም በጊዜውም አለጊዜውም በእምነታችን ጸንተን በዚህ መጻሕፍት የተነሡትን ጉዳዮች ሐሰተኛነት በማሳየት መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ መሪነት የተጻፈልን የሃይማኖታችን መመሪያ፣ የቀናና ቤተ ክርስቲያናችን መሠረት መኾኑን ማመንና መታመን ያሻናል እላለሁ:: 2ጢሞ. 4÷1-5::

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

## አስቸኳይ የርዳታ ጥሪ

በ14ኛ ዓመት ቁጥር ሁለት መጋቢት/ሚያዝያ 1998 ዓ.ም የሐመር መጽሔት እትም በእናስተዋውቃችሁ ዓምድ:- *«አስቸኳይ የርዳታ ጥሪ ለግሮት ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን»* በሚል ርእስ የደብሯን ታሪክ ማስተዋወቃችን ይታወሳል:: ታሪኩን ያነበቡ በርካታ ሰዎች የደብሯን ችግር ለማቃለል ድጋፍ የሚሰጡ በትን መንገድ ጠይቀውናል:: በዚህም መሠረት ርዳታችሁን በተከታዩ አድራሻ መላክ የምትችሉ መኾኑን እየገለጽን ስለምታደርጉልን ድጋፍ ከፍ ያለ ምስጋናችንን እናቀርባለን::

<u>አድራሻ:-</u> የግሮት ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን
ሕንጻ ሥራና ልማት ኮሚቴ
ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ
አራት ኪሎ ቅርንጫፍ
የባንክ ሒሳብ ቁጥር:- 120031

የማኅበረ ቅዱሳንን ገጸ ድር ይጎብኙ
www.eotc-mkidusan.org



www.eotcmk.org

# ቅድስና እና ፈለገ ቅዱሳን

*በመጋቢት/ሚያዝያ 1998 ዓ.ም እትማችን የቅድስናን ሕይወት በወጣትነት ዘመን ወይም በብቸኝነት ጊዜ እንዴት ጠብቆ መኖር እንደ ሚቻል የምእመናንን የሕይወት ተሞክሮና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃዎችን በማቅረብ ማስነበባችን የሚታወስ ነው። በወጣትነት ዘመናችን የቅድስናን ሕይወት እንዳንኖር የሚገዳደሩንን ውስጣዊ መሻቶችና ውጫዊ ተጽዕኖዎች ረድኤተ እግዚአብሔርን አጋዥ በማድረግ ከተዋጋናቸው ድል ልንነሳቸው እንደ ምንችልና የምን ናፍቀውን የቅድስና ሕይወት በተጋድሎ ውስጥ ለማስጠበቅ እንደ ማይሳነን ተመልክተናል። በዚህ እትማችን ደግሞ ባለትዳሮች የቅድስና ሕይወትን ለመኖር ሲሹ የሚገጥሟቸውን ፈተናዎችና እነዚህን ፈተናዎች እንዴት ለመወጣት እንደሚችሉ በልዩ ልዩ ምእመናን ተሞክሮ መሠረትነት የሚያስቃኘውን ዝግጅት ይዘንላችሁ ቀርበናል። መልካም ንባብ።*

*/መ/ር ደረጀ ጅማ/*

## በኢትዮጵያውያን መንፈሳዊ ፣ ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ ሕይወት ውስጥ

አቶ መሐሪ ወልደ ኢየሱስ ይባላሉ። ከአዲስ አበባ 470 ኪ.ሜ ርቃ በምትገኘው የክብረ መንግሥት ከተማ ነው የሚኖሩት። በትዳር ሕይወት ውስጥ የቅድስና ኑሮን መኖር ስለ መቻሉ ሲናገሩ፡- «ትዳር በራሱ ቅድስና እና የበረከት ምንጭ ነው። በጋብቻና ከጋብቻ ውጭ የተወለደ ልጅ እኩል አይደለም። መልካም የትዳር ጓደኛ ካገኘህ የቅድስናን ሕይወት መምራት ይቻላል።» ብለዋል። ነዋሪነታቸው በሐረር ከተማ የሆኑት መምህር ፈቃዱ ግን፡- «የቅድስና ሕይወትን በትዳር ውስጥ መምራት ስለ መቻሉ ሙሉ እምነት ቢኖረኝም ባለትዳሮች ወደ ቅድስና ለመድረስ የጋብቻቸው መሠረት መስተካከል አለበት።» ይላሉ። አቶ መስፍን የተባሉ የአዲስ አበባ ነዋሪ የመ/ር ፈቃዱን ሐሳብ ይጋራሉ፤ እርሳቸው እንደ ሚሉት፡- «በመሠረቱ በትዳር ውስጥ ሆኖ የቅድስና ሕይወትን መምራት ይቻላል። ጋብቻው ግን በቅድስና መሠረት ላይ መመሥረት አለበት።»

በብቸኝነት ሕይወታቸው የቅድስናን ሕይወት የኖሩ ነቢያቱ እነ ሔኖክና እነ ኤልያስ የመኖራቸውን ያህል አባታችን ይሥሐቅና ጻድቁ ዮሴፍን የመሳሰሉ ባለትዳሮችም በቅድስና ኖረዋል። ዛሬም አሉ። የትዳር መሠረታቸውን ቅዱስ በሆነ ጋብቻ ላይ የመሠረቱት ግን ከሌሎች ይልቅ የቅድስና ጉዞአቸውን ከትዳራቸው ጅማሬ አንሥቶ የቀጠሉ ናቸው። ከቤተ ክርስቲያን ሥርዐት ውጭ በሆነ መልኩ የመሠረቱትን ጋብቻ በንስሐ አድሰውና በሥጋ ወደሙ አጽንተው የቅድስና ኑሮን መኖር የጀመሩ ቆራጥ ክርስቲያኖች የሉም ማለት አይደለም። ወደዚህ መሰሉ መለየት ያልደረሱ ግን ብዙ ናቸው።

ቀሲስ እንዳለ አሻግሬ ይባላሉ። አየር ላንድ ውስጥ «Milton Institute of Theology and Philosophy> ከተባለ ተቋም በቤተ ክርስቲያን ታሪክ፣ በቀደምት አባቶች ዜና ሕይወትና ትምህርት ላይ በሚያተኩር ጥናት ሁለተኛ ዲግሪያቸውን አግኝተዋል። በአሁኑ ወቅት በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ የዜና አበው /PATROLOGY/ መምህር ናቸው። «ቅድስና በትዳር ውስጥ ይቻላል»ን አስመልክቶ የሚከተለውን ብለዋል፡- «እግዚአብሔር አስቀድሞ ትዳርን ሲያዘጋጅ ለቅድስና መሠረት እንዲሆን አድርጎ ነው። «ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም። የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት» የሚለው የቅድስት ሥላሴ ቃል አዳም የቅድስና ሕይወትን እንዲላበስ ረዳት ያስፈልገዋል የሚለውን ጥቁምታ ይሰጣል።

በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ የነገረ መለኮት ምሁር የኾኑት ሕንዳዊው ካህን ዶ/ር ጆሲ ደግሞ፡- «ቅድስና በየትኛውም የሕይወት ጎዳና ሊንጸባረቅ ይችላል። በገዳማዊ ሕይወት ውስጥም ሆነ በጋብቻ ሕይወት ውስጥ ቅድስናን መምራት ይቻላል። ቅድስና በትዳር ሕይወት ውስጥ ይታጎላል ብዬ አላምንም።» በማለት ያስረዳሉ።

በትዳር ውስጥ የቅድስናን ሕይወት ለመምራት ግን በፈተና ውስጥ ማለፍ ግድ ነው። ፈተና የሌለበት ሕይወት የለምና። የቅድስናን ሕይወት በትዳር ውስጥ ለመምራት የማያስችሉ ምክንያቶች ገና ጋብቻው ሲመሠረት አብረው ሊኖሩ ይችላሉና መጠንቀቅ ያሻል። መ/ር ፈቃዱ ሣህሌ እንዳሉት፡- «ትዳር በይድረስ ይድረስ ሳይሆን በርጋታና ቤተ ክርስቲያን በምታዝዘው መሠረት መመሥረት አለበት። በጥቂት ጊዜ ትውውቅ ትዳር ከመሠረቱ



*በቅድስና ላይ የተመሠረተ ጋብቻ የበረከት ምንጭ ነው።*



www.eotcmk.org

በኋላ እያደር የሚያውክ ችግር ውስጥ ገብቶ የቅድስና ሕይወትን ሳለማጣት መጠንቀቅ ያሻል:: ሳይጠናኑና ሳይተዋወቁ በሚመሠረት ትዳር ውስጥ የቅድስና ሕይወትን መምራት ሳይቻል ይችላል:: ሌላው ቀርቶ በተክሊል የተመሠረተውን የቅድስና ጋብቻ የሚፈታተን ችግር ወይ ከወንዱ አለበለዚያ ከሴቷ ሊመጣ ይችላል::

የመሠረቱት የጥድፊያ ጋብቻ ሊኖሩት የሚፈልጉትን የቅድስና ሕይወት እንዳይመሩ እንቅፋት ሆኖባቸው የሚቸገሩ በርካታ ባለትዳሮች አሉ:: ከችግሩ አሳሳቢነት የተነሣ ለፍቺና ላልተፈለገ ሕይወት የተዳረጉትንም ቤቱ ይቁጠራቸው:: በማይጨው ከተማ ያገኘናት ወ/ሮ ንግሥት አኅናፍር የሰጠችን ግለ ታሪክ የዚህ ችግር አንዱ አካል ነው:: *«...በዚያን ጊዜ በከተማችን ውስጥ ወታደሮች ነበሩ:: ከእነርሱም አንዳንዶቹ እኔን ለማግባት ይጥሩ ነበር:: ስለዚህ በአንድ አባት ምክር በሥጋ ወደሙ ተወሰንኩኝ:: ይህንንም ያደረግኹት የመማር ዓላማ ስለነበረኝና ራሴን በንጽሕና ለመጠበቅ ካለኝ ፍላጎት የተነሣ ነው:: በሰንበት ት/ቤቱ ውስጥ ደግሞ ተሳትፌ ነበረኝ:: ሰንበት ት/ቤት ውስጥ አደርግ በነበረው እንቅስቃሴና ወደ ቤተ ክርስቲያን በመመላለሴ የቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያንን በመሪጌትነት ያገለግል የነበረ ጎልማሳ ዐይን ውስጥ ገባሁ:: መሪጌታውም በሥጋ ወደሙ መወሰኔን ሲያውቅ ለጋብቻ ጠየቀኝ:: እኔም ለሃይማኖቴ ፍቅር ስለነበረኝ ስለ ማንነቱ ሳላጠናና አስተሳሰቡ ይመጥነኛል፣ አይመጥነኝም ብዬ ሳልመረምር አገባሁት:: አንደኛ በዕድሜዬ ትንሽ ነበርኩ:: በከተማችንም የሚያማክረኝ ሰው ባለመኖሩ ያንን ሰው የሃይማኖት ፍቅር ገፋፍቶኝ አገባሁት:: ከተጋባን በኋላ ግን አስተሳሰባችንም ሆነ አመለካከታችን አንድ አልሆን አለ:: ሥጋ ወደሙ አስተሳስሮናል:: እኔም ከጌታ ሥጋና ደም በላይ ምንም ነገር እንደሌለ ዐውቄ ነበር ያገባሁት:: ከዚህ በኋላ እኔም መምህርት የመሆን ዕድል አግኝቼ ገጠር በመመደቤ ባለቤቴ ይጠራጠረኝ ጀመር፤ በሥጋ ወደሙ በመታተሜ ከእርሱ ውጭ የትም ልሔድ እንደ ማልችል እንኳን ሊያምን አልቻለም:: በየ40 ቀኑ እንቀበላለን፤ ግን ይጠራጠረኛል፤ ይመታኛል፤ ይጨቀጭቀኛል:: እንዲያምን ብዬ በየዓመቱ ሦስት ልጅ ወለድኩለት:: ያንን ሁሉ አድርጌ መፍትሔ አላገኘሁም:: ከዚያ በኋላ እኔም ከትዳሬ ተሰናክዬ ልጆቼን ይዤ እየኖርኩ ነው:: ይኸው በብቸኝነት ለ11 ዓመታት ተቀምጫለሁ::»*

የትዳር ጓደኛ ለማግኘት በሚደረግ ሩጫ ውስጥ ምርጫንና ጥያቄን ለተመረጠው ሰው ለመንገር መቸኮል አይገባም:: ተጠያቂዎች የኾነውም ፈቃዳችንን ለመስጠት መቸኮል የለብንም:: ከዚህ ይልቅ ለትዳር ጓደኝነት ስለ ፈለገን ሰውና እኛ ስለ ምንፈልገው ሰው ብዙ መስማት፣ ብዙ ማወቅ ያሻናል፤ «ሰው ሁሉ ለማስማት የፈጠነ ለመናገርም የዘገየ ይሁን::» እንዲል:: ያዕ.1÷19-20:: የአብርሃም ሎሌ ኢያውብር ርብቃን ለይሥሐቅ ከማጨቱ በፊት ውኃ ስትቀዳና ግመሎቹን ስታጠጣ በትክታ ተመልክቷታል፤ «ሰውየውም ትክ ብሎ ይመለከታት ነበር::» ዘፍ.24÷21:: ከዚህ በኋላ ነው ወደ ስጦታውና ወደ ጥያቄው *የገባው:: በምድራችን ላይ የቅድስና ሕይወትና መዓዛ ለሌላቸው በርካታ ጎጆዎች ባለመጠናናትና በችኩልነት የተመሠረተ ጋብቻ እንደ ምክንያት መቅረቡ ትዳር ያልመሠረቱ ሁሉ አካሄዳቸውን በጥንቃቄ እንዲያደርጉ ትምህርት ይሰጣል:: በችግሩ ውስጥ ያሉትም ከፍቺ ይልቅ ለመፍትሔው እንዲተጉ ግድ ነው::*

«ሌላም ችግር አለ» ይላሉ መ/ር ፈቃዱ፤ «ክርስትናና የቅድስና ሕይወት እስከ ጋብቻ ነው» የተባለ ይመስል ትዳር ከመሠረቱ በኋላ ከቤተ ክርስቲያንና ከአገልግሎት የሚርቁ ባለትዳሮች አሉ:: ይህ ደግሞ ከቃለ እግዚአብሔርና ከሥጋ ወደሙ የሚያርቅ አካሔድ ስለሆነ ከቅድስና ሕይወት ያርቃቸዋል:: እርስ በእርሳቸው እየተመከኛኙ የሚቀፉም አሉ:: የባለትዳሮች ሐሳብ የተከፈለ ነው:: እርሱ ለእርሷ፣ እርሷም ለእርሱና ለትዳራቸው ያስባሉ:: ሐሳባቸው ግን እግዚአብሔርንና የቅድስና ሕይወታቸውን እርግፍ አድርገው እስኪተዉ ድረስ መሄድ የለበትም:: ሐሳብን ለእግዚአብሔር ያለመስጠት፣ ችግሮችን በጸሎትና በውይይት ለመፍታት ያለመጣርና ከአገልግሎት መራቅ፣በትዳር ውስጥ ለሚመራ የቅድስና ሕይወት እንቅፋቶች ናቸው:: በተለይ ከግራኝ አሕመድ ወረራ ወዲህና በልዩ ልዩ የባዕዳን ባህል ተጽዕኖ ሳቢያ በሕገ ጋብቻ አለመጽናትና ከአንድ በላይ ሚስት ማግባት ልማድ ኾኗል::

*ማንኛውም ባለትዳር ምግበ ሥጋ እንደሚያስፈልገው ሁሉ ቃለ እግዚአብሔርን ካገኘ የቅድስና ኑሮን ለመኖር ብርታት ያገኛል:: በአጠቃላይ እምነትና በጎ ኅሊና በባለትዳሮች መካከል ካለ የቅድስናን ሕይወት ሊኖሩት ይችላሉ::*

ከአንድ በላይ ሚስት አግብቶ የቅድስና ኑሮ እንዴት ሊኖር ይቻላል? በርካታ ቁጥር ያለው ሕዝባችን ትዳርን የሚመሠርተው በግዴለሽነት ነው:: ጋብቻውን ከቤተ ክርስቲያን ውጭ ማድረጉ ለዚህ ማስረጃ ይሆናል:: በእንተያይ የሚጋቡ አሉ:: እናትና አባትም ባለው ባህላዊ ተጽዕኖ ሥር ከመውደቃቸው የተነሣ ድርጊቱን ሲኮንኑ አይታዩም::

«ቅድስናን በትዳር ውስጥ መኖር ቢቻልም ሚስትህ እናትና አባትህን እንዳትጠይቅና እንዳትረዳ የምትከለክልህ ከሆነና አንተም እንደ ቃሏ ብታደርግ እናትና አባትን በመርዳት የሚገኘውን የቅድስና ሀብት ታጣለህ:: «ለቤተ ክርስቲያን እንርዳ» ሲባል «አይሆንም» በማለት ባሏን ወይም ሚስቱን የሚቃወም ሰው በምጽዋት ከሚገኘው ቅድስና ይለያል:: ጓደኛህ እቤት ሲመጣ ፊቷን የምታጠቁር ሚስት ወይም ጓደኛዋ እቤት ስትመጣ ፊቱን የሚያጠቁር ባል ባለበት ጎጆ ውስጥ በእንግዳ ተቀባይነት የሚገኘው ቅድስና አይታሰብም:: እንቍረብ ሲባል «እንቆይ» የሚል ባል ወይም የምትል ሚስት በተጣመሩበት ጋብቻ ውስጥ የቅድስናን መዓዛ ሕይወት እየተራቡ መኖር የማይቀር ዕዳ ነው:: ሴቷ ለምን እምቢ እንደ ምትል አይገባኝም:: እርግጥ አንዳንዶች ጨሌና ባዕድ አምልኮ ጓዳቸው ካለ ከቍርባን ይሸሻሉ:: አንዳንድ ወንዶችም ከሚስቶቻቸው ውጪ ወደ ሌላ ስለሚሄዱ ሚስታቸው «እንቍረብ» ስትላቸው «ገና ነኝ» በሚል ምክንያት ይዘገያሉ:: ምክንያታቸው ሌላም ሊሆን ይችላል:: ሁለት ሚስት ያለው ግን «የቷን ልያዝና ልቍረብ፤ የቷንስ ልተው» በሚል ሐሳብ ስለ ሚጨነቅ ኀሊናው እንደ ከሰሰው ይኖራል:: ከሁሉም የሚገርመኝ ሁለት ሚስት ላላቸው ሰዎች የንስሐ አባት የሚሆኑ አባቶች ናቸው:: «ምነው?» ሲባሉ «የተለመደ ነው» ይላሉ:: ክፉ ልምድና ክርስትና ምን አገናኛቸው? በአጭሩ ከላይ የጠቀስኳቸው ምክንያቶች ባለትዳሮች የተቀደሰ ሕይወት እንዳይመሩ ያግዷቸዋል::» የሚሉት ደግሞ አቶ መሐሪ ናቸው::

አሕዛባዊ ባሕል ለርስት መንግሥተ ሰማያት በተመረጠ የእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ሠልጥኖ ሲታይ ያሳዝናል:: ሐዋርያው፡- «ለእያንዳንዱ ለራሱ ሚስት ትኑረው፤ ለእያንዳንዱ ደግሞ ለራስዋ ባል ይኑራት» አለ እንጂ መች ሚስቶችና ባሎች ይኑራችሁ አለ:: 1ቆሮ.7÷2:: በዚህ መሰሉ ሕይወት ተጠላልፈው ያሉ ባለትዳሮችን ካህናተ እግዚአብሔር፡- «የአሕዛብን ፈቃድ ያደረጋችሁበት ያለፈው ዘመን ይበቃል» ሊሏቸው ይገባል:: 1ጴጥ.4÷3:: ከመምከርና የቅድስና ሕይወት ይኖሩ ዘንድ መንገዱን ከማሳየት ውጭ ከእነርሱ የሚገኘውን ጥቅም እንደ በግ ጠጉር በመሸለት *በዝምታ ማለፍ ጴጥሮሳዊነት አይደለም::* ለመንጋው የማይራሩ ጨካኝ እረኞችን የሚጠብቃቸው ቅጣት እንደዚህ ባለ ግብር የሚጸኑትን ካህናት አያልፋቸውም:: የሐረር ከተማ ነዋሪ የሆነው

/ወደ ገጽ ፴፩ ዞሯል/



www.eotcmk.org



*ይህ ዓምድ በሥርጭቱ ፍጥነትና በጥቃቱ ስፋት አሳሳቢ ደረጃ ላይ የደረሰውን ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በመከላከልና በመቆጣጠር ረገድ ማኅበረ ቅዱሳን ከአክሽን ኤይድ ኢትዮጵያ ጋር በመተባበር የጀመረው ሰፊ ሥራ አካል ነው:: ማኅበራችን ይህን ሥራ ሲጀምር ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት እና የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ፕሬዝዳንት ባገኘው መልካም ፈቃድና መመሪያ መሠረት ነው:: አጠቃላይ የሥራ ሒደቱም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ መምሪያ ክትትል ይደረግበታል::*

# ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመዋጋት ቤተ ክርስቲያን ያላት ሀብትና የሚጠበቅባት ድርሻ

*ኀይለ ኢየሱስ አዳሙ*
*/ከማኅበረ ቅዱሳን የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ቦርድ/*

ዓለምን እያስጨነቋት ካሉት ችግሮች መካከል አንዱና ዋነኛው የኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ ጉዳይ ነው:: የዓለም የሳይንስ ጠበብት ለበሽታው የክትባት መድኃኒት ሊያገኙለት አልቻሉም:: ስለሆነም ዋነኛው የመከላከያ መንገድ ቫይረሱ ወደ ሰውነት ከመግባቱ በፊት ባለበት መግታትና መከላከል ነው:: የቫይረሱን ሥርጭት ለመግታትም በሽታው የሚያስከትለው ችግር ዘርፈ ብዙ በመሆኑ ዘርፈ ብዙ ምላሽ ያስፈልገዋል:: ይሁንና የመከላከልና የመቆጣጠር ሒደቱ በምልዓተ ሕዝቡ ቀጣይ ተሳትፎ የታገዘ ባለመሆኑ አመርቂ ውጤት ሊያስመዘግብ አልቻለም:: የቫይረሱ /የበሽታው/ ሥርጭትም እስከ ዛሬ ድረስ በአስጊ ሁኔታ ላይ መገኘቱን ዘገባዎች ያመለክታሉ:: ለምሳሌ ያህል የተባበሩት መንግሥታት የኤድስ ፕሮግራም /UNAIDS/ እ.አ.አ በ2006 ያወጣው ዘገባ ይህንኑ ያረጋግጣል::

*ዘገባው በዓለም ላይ እ.አ.አ እስከ 2005 38.6 ሚሊዮን የሚገመት ሕዝብ ከቫይረሱ ጋር እንደ ሚኖር ይተነትናል:: በዚሁ ዓመትም አዲስ ከቫይረሱ ጋር አብሮ የሚኖረው ሰው ቁጥሩ ወደ 4.1 ሚሊዮን እንደ ሚሆን ተገምቷል:: በተጨማሪም 2.8 ሚሊዮን የሚሆን ሕዝብ በኤድስ ሕመም ምክንያት ሕይወቱን ኣጥቷል:: ይኸው ዘገባ እንደ ሚያመለክተው ከሰሐራ በታች የሚገኙ አዳጊ ሀገሮች በበሽታው ክፉኛ እየተጐዱና ለዕድገታቸውም ከፍተኛ እንቅፋት እንደ ሆነባቸው ያስረዳል:: በተለይም ደግሞ በአገራችን ኢትዮጵያ የቫይረሱ ሥርጭት በቶሎ ካልተገታ የሚያስከትለው ሰብአዊ ጥፋት በቀላሉ የሚገመት አይኾንም:: በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ ቫይረሱ በላቦራቶሪ ከተከማቸ የደም ናሙና በ1976 ዓ.ም በተደረገው ጥናት መኖሩ የተረጋገጠ ሲሆን በ1978 ዓ.ም ደግሞ የመጀመሪያዎቹ ሁለት ግለሰቦች በኤች.አይ.ቪ አማካይነት የኤድስ ሕመምተኞች መኾናቸውን የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር አረጋግጧል::*

**የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከልና መቆጣጠር እንቅስቃሴ የዐቅም ግንባታ ከአጠቃላዩ የቤተ ክርስቲያን ዐቅም ግንባታ ስትራቴጂ ጋር መጣጣምና በተለይም ከሰው ኃይል ልማት፣ የአደረጃጀትና የአሠራር ዘይቤ ጋር መገናዘብ ይኖርበታል::**

ከ1981 ዓ.ም ጀምሮ በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ዙሪያ ቅኝት የማድረግ እንቅስቃሴ እንደ ተጀመረ የ1996 ዓ.ም የጤና ጥበቃ ሪፖርት ያስረዳል:: ችግሩ የተወሳሰበ በመሆኑ የቫይረሱን ሥርጭትና የበሽታውን መስፋፋት ለመግታት ሁሉም በቅንጅትም ይሁን በተናጠል ተግቶ መሥራት ይገባዋል፤ ጉዳዩ በቀጥታም ኾነ በተዘዋዋሪ የማይመለከተው ማንም የለምና::

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም ከማንም በበለጠ ተግታ መሥራትና ውጤት ማሳየት ይጠበቅባታል:: ቤተ ክርስቲያኒቱ በሚከተሉት ነጥቦች ምክንያት የአንበሳው ድርሻ ይኖራታል:-

## 1ኛ. *ከ45 ሚልዮን ያላነሱ የምእመናን ብዛት ያላት መሆኑ:-*

ሕዝብ የሀገር ሀብት ነው:: ኢትዮጵያ 75 ሚልዮን ያህል የሕዝብ ብዛት ያላት ሀገር ናት:: ከዚህ ውስጥ ደግሞ ከግማሽ በላይ የሚሆነው /60 በመቶው/ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመን ነው:: ይህን ያህል ሕዝብ በየቤቱ፣ በአጥቢያ፣ በወረዳ፣ በአህጉረ ስብከትና በማእከል ደረጃ በሚገኙ የብዙኀን መገናኛ መድረኮች የክርስትናዋ እምነትና ሥርዐት በጠበቀ መልኩ አስተምሮ በተግባር ራሱን የጠበቀ እንዲሆን በማድረግ በኢትዮጵያ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ሥርጭትን መግታት ይቻላል:: ይህ አንድ ትልቅ ዕድል ነው::

## 2ኛ. *ቤተ ክርስቲያኒቱ ከ500,000 በላይ አበው ካህናት ያሏት መሆኑ:-*

አበው ካህናት በንስሐ ልጆቻቸው አማካይነት በግለሰብና በቤተሰብ ደረጃ በማስተማር፣ በመምከር ... ወዘተ ለውጥ ማምጣት ይችላሉ::

የቤተ ክርስቲያኒቱን ትምህርት በየደረጃው የተማረ ይህን ያህል የሰው ኃይል በቀላሉ ስለ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በማነጋገርና በማንቃት ከላይ የተጠቀሰውን ሕዝብ መለወጥ ይቻላል:: ከቤተ ክርስቲያኒቱ ውጭ ለኾኑትም አርአያ ለመሆን ያስችላል:: እኒህ አባቶች በሕዝቡ ዘንድ ባላቸው ከፍተኛ ተደማጭነት ትምህርቱን በቶሎ ያሠራጫሉ፤ ተፈላጊውንም ለውጥ ያመጣሉ::

ቤተ ክርስቲያን ምእመናኗን ብቻ ሳይሆን መላውን ሕዝብ:- ዘር፣ ቋንቋ፣ ወንድ፣ ሴት፣ ሀብታም ድኻ ሳት ለይ መርዳት፣ መከባከብ ክርስቲያናዊ ተግባር መሆኑን በማመን ይህንኑ ስታ ደርግ ቆይታለች:: በመሆኑም የ«ደጉ ሣምራዊ»ን አርአያነት በመከተል አበው ካህናትና በየደረጃው ያሉ አገልጋዮቿ በችግሩ ዙሪያ ሰብአዊ ተግባርን ለሁሉ ሊፈጸሙ ይገባል::

## 3ኛ. *ከ6.5 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ወጣቶች በሰንበት ት/ቤቶች መታቀፋቸው*

ወጣቱ የኅብረተሰብ ክፍል ለቫይረሱ ተጋላጭ ከሆኑት አካላት መካከል ዋነኛው ነው:: ወጣቱን ደግሞ በሥነ ምግባር ኮትኩቶ በሥርዐተ ቤተ ክርስቲያን ታንጾ እንዲያድግ ማድረግ ለበሽታው ሥርጭት መገታት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይኖረዋል:: በአቻ ለአቻ ትምህርት በእኒህ ወጣቶች አማካይነት ለውጥ ማምጣት ይቻላል::



www.eotcmk.org

## 4ኛ. *የቤተ ክርስቲያናችን አገልጋዮችና ምእመናን ቋሚ የመገናኛ ጊዜ ያላቸው መሆኑ፡-*

ከላይ የተጠቀሱት በሙሉ በየ አጥቢያቸው በየጊዜው የመገናኘቱ÷ የመወያየቱ ዕድሉ አላቸው:: በዚህም አዳዲስም ሆኑ የቆዩ ጠቃሚ መረጃዎችን በአጭር ጊዜና ያለምንም ወጪ ማስተላለፍ ይቻላል::

ከላይ የተጠቀሱት እና ሌሎችም ሁኔታዎች ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ቤተ ክርስቲያኒቱ ያላትን ዕድል ከሁሉም የበለጠ ያደርገዋል:: ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ እና ተያይዘው የሚመጡት ችግሮች በሙሉ አፋጣኝ ምላሽ ያስፈልጋቸዋል:: ከዚያ አኳያ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለሚከተሉት ጉዳዮች ትኩረት መስጠት ይገባታል::

## ሀ. *ዐቅም ግንባታ/ማጐልበት፡-*

ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመዋጋት በቤተ ክርስቲያናችን የልማት፣ የአስተዳደርና የአገልግሎት መዋቅሮች ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ነው:: ከዚህ አኳያ ዐቅምን መገንባት ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ዋና ስልት መሆን ይገባዋል:: ዐቅም ግንባታው ከምእመኑ ጀምሮ ጉዳዩ በቀጥታም ኾነ በተዘዋዋሪ እስከ ሚመለከታቸው አካላት ድረስ መሆን ይገባዋል:: የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከልና መቆጣጠር እንቅስቃሴ የዐቅም ግንባታ ከአጠቃላዩ የቤተ ክርስቲያን ዐቅም ግንባታ ስትራቴጂ ጋር መጣጣምና በተለይም ከሰው ኃይል ልማት፣ የአደረጃጀትና የአሠራር ዘይቤ ጋር መገናዘብ ይኖርበታል:: ይህን በዕቅድ አዘገጃጀትና በሥራ አፈጻጸም በማካተትና በማስተሳሰር፣ በአመራር፣ በሀብት አጠቃቀም፣ በክትትልና ግምገማ ሁሉ መፍትሔ እንዲፈልግ ዐቅም ያለው ኃይል ይሻል:: ዐቅም ግንባታው በተለይ ለዚህ አፋጣኝ ምላሽ ሊሰጠው ይገባል:: ስለሆነም የዘርፉን አቅም በመገንባት የወረርሽኙን ሥርጭትና የሚያስከትለውን ጫና ለመቀነስ፣ ለመከላከል፣ የድጋፍና ክብካቤ አገልግሎቶችን ለማቅረብ ቤተ ክርስቲያናችን ብቁ፣ ጠንክረው በመሥራት ላይ የሚገኙ ሰዎቿን ዐቅም መገንባት ያስፈልጋታል::

ምእመናንም ተሳትፎአቸውን ማሳደግና ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን የመከላከልና ክብካቤ ጥረት በባለቤትነት እንዲያከናውኑት ያስፈልጋል:: እስከ አሁን ድረስ ኤች. አይ.ቪ/ኤድስን የመከላከልና የመቆጣጠር ፕሮግራሞች የታለመላቸውን ውጤት ሳያስገኙ የቀሩት ምእመኑ የችግሩ ባለቤትና መፍትሔም እንዲሆን ዐቅሙ ባለመገንባቱ ዕድሉም ባለመሰጠቱ ነው:: ስለኾነም ምእመኑ በየ አጥቢያው ችግሮቹን ለይቶ እንዲያውቅ ከችግሮቹ ተነሥቶ ራሱ ዕቅድ እንዲያወጣና እንዲፈጽም፣ ጐጅ ልማዶችንና ገደቦችን እንዲተው ዐቅሙን ማሳደግ ያስፈልገዋል:: ይህ ደግሞ ለቤተ ክርስቲያኒቱ በቀላል ወጪ ብዙ ሥራዎችን መሥራት ነውና ከባድ አይደለም::

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በየደረጃው የሚገኙ ሐላፊዎችን፣ አስተዳዳሪዎችን፣ ሰባክያነ ወንጌልን... ወዘተ ዐቅም ማሳደግ ቤተ ክርስቲያኒቱ ለተለመችው ዕቅድ ተፈጻሚነት ትልቅ ድጋፍ ይኖረዋል:: በየሰንበት ት/ቤቶች ያሉ ወጣቶች ንም በባለቤትነትና በተጠያቂነት መልኩ ዐቅማቸውን መገንባት ለትጋቱ ጥሩ መፍትሔ ነው:: በተናጠል የሚ ደረግ ሩጫ ለጊዜው እንጂ ዘለቄታ ስለ ማይኖረው በየአካባቢው የሚገኙትን የቤተ ክርስቲያናችንን የአገልግሎትና የአስተዳደር መዋቅሮች ማስተባበርና ማቀናጀት ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ የሚያደርሰውን ዘርፈ ብዙ ቀውስ ለመከላከልና ለመቆጣጠር አመቺ መንገዶች ናቸው::

## ለ. *ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን የመከላከል እንቅስቃሴ ከቤተ ክርስቲያኒቱ አገልግሎት ጋር ማካተትና መምራት፡-*

የፀረ-ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ዘመቻ ማኅበረሰቡ በራሱ ተነሣሽነት እንዲያካሂደው አበው የመሪነቱን ሚና በቁርጠኝነት ሊወስዱ ይገባል:: የአመራሩም ሒደት ከላይኛው አኪያ ጀምሮ እስከ ታች ድረስ ከመንፈሳዊው ትምህርትና አገልግሎት ጋር እንደ ዋና ሥራ ተደርጐ ሊወሰድ ይገባዋል:: ይህም በቤተ ክርስቲያኒቱ የሚገኙ አገልጋዮችና ተገልጋዮች ሁሉ የዕለት ተዕለት ሥራቸው አድርገው እንዲወስዱት አመራሩን ባልተማከለ ዘዴ ወደ ታች ማውረድ ለዘመቻው መቃናት አንዱ መንገድ ነው::

እስከ አሁን እንደ ታየው በኩለንታዊነት የማካተቱ /Mainstreaming/ ጥረት በብዙ የመንግሥትና የግል ዘርፎች እንዲካተት /ተግባራዊ እንዲሆን/ ሲደረግና የሥራ ቦታ መመሪያ ሲዘጋጅ ይስተዋላል:: ይሁን እንጂ በብዙዎች ዘንድ እንደ ዋና ተግባር ተደርጎ አልተወሰደም:: የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም ካሏት ምእመናን ብዛትና አደረጃጀት አንጻር ቀዳሚውን ሚና ልትጫወት ይገባል:: ይህ እስካልሆነ ድረስ ግን የበሽታው መስፋፋት እየጨመረ መሄዱን ይቀጥላል:: ስለዚህ የቤተ ክርስቲያናችን የአገልግሎትና የአስተዳደር መዋቅሮች ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በእንቅ ስቃሴያቸው ሁሉ የማካተቱን ሥራ እንደ ዋና ጉዳይ ማየቱን አጠናክረው መቀጠል ይኖርባቸዋል::

## ሐ. *የታቀደውን ሥራ በጊዜው መፈጸም፡-*

ብዙውን ጊዜ ዕቅዶች በጣም ያማሩ ሆነው በጊዜው ወደ ተግባር ባለመቀየራቸው ካለፉ በኋላ ሲስተጓጐሉ እናስተውላለን:: ዕቅዱ ላለመፈጸሙ ብዙ አሳማኝ ምክንያቶች ሊቀርቡለት ይችላል:: ነገር ግን የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጉዳይ በምክንያት ብቻ ሊታለፍ የማይገባው በመሆኑ የሰው ኃይልን፣ ገንዘብን፣ ቦታንና የመሳሰሉትን ግብአቶች ሁሉ ግምት ውስጥ ያስገባ ዕቅድ ውጤቱ ያማረ እንደ ሚሆን አያጠራጥርም:: ቤተ ክርስቲያን ካላት የሰው ኃይል አንጻር ብዙ ብዙ ነገር መሥራት ይቻላታል:: በተለይም ደግሞ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የታቀደው የአምስት ዓመቱን መሪ ዕቅድ ወደ ተግባር ለመለወጥ እየተደረገ ያለውን ጥረት ማጠናከርና መምራት ያስፈልጋል:: ይህ ከሆነ የተጻፈው በተግባር ሊታይ ይችላል:: ይሁንና መሪ ዕቅዱን ተግባራዊ ለማድረግ የየአህጉረ ስብ ከቱ ሐላፊዎች፣ ሊቃነ ጳጳሳት፣ የሰንበት ት/ቤት አባላት ... ወዘተ ዋና የሥራው አስፈጻሚና ፈጻሚ መሆናቸው ይታወቃል:: ይሁን እንጂ ማኅበረሰቡ የየአካባቢውን ችግር አንጥሮ በማውጣት ማቀድ ይገባዋል:: ለዚህም የሞያ ድጋፍ እንዲያገኙ ማድረግ፣ ዕቅዳቸውም በአም ስት ዓመቱ የመከላከልና መቆጣጠር መሪ ዕቅድ ማዕቀፍ ውስጥ መሆኑን ማረጋገጥ የግድ ነው::

## መ. *ማስተባበርና የግንኙነት መረብ መዘርጋት፡-*

በጋራ የማቀድ፣ የመፈጸም፣ የክትትልና ግምገማ መረብ በመዘርጋት ማስተባበር ጥሩ ውጤት እንዲታይ ያደርጋል:: ፕሮግራሞች ሳይደራረቡ በመተጋገዝ መተግበር የሀብት መባከንን ከመቀነሱም ሌላ ድግግሞሽን፣ መሰልቸትን ያስወግዳል:: በአንድ አካባቢ የተገኙ ጥሩ የሥራ ልምዶችን ለሌላው በማስተላለፍ መጠቀም ይገባል:: ይህም የመረጃ ልውውጥን ያዳብራል:: ዘርፈ በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ያለው የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ መምሪያ በኩል የሚደረገው ጥረት ብቻውን አመርቂ ውጤት ሊያመጣ ስለማይችል ሌሎች ተባባሪ አካላትን ለምሳሌ:- ከመንግሥታዊ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤቶች ጋር መተባበርና የጋራ አካሄድን መፍጠር ሐላፊነትንና ግዴታን ለመወጣት ያስችላል:: የመረጃ ሥርዐቱም ቢሆን የተጠናከረ ባለመሆኑ አንድን ጉዳይ መደጋገም ይታያል:: ስለዚህ ውጤታማ የማስተባበር ሥራን በማስፋትና የግንኙነት መረብን በመዘርጋት ተቋማዊ አደረጃጀቶችን በመገምገምና በማጠናከር ተልእኮን ማሳካት ይገባል::

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር ይቆየን::*



www.eotcmk.org

ከገጽ ፳፰ የዞረ



መ/ር ጥበቡ ግርማ ደግሞ ትዳር የመሠረቱ ሰዎች የበለጠውን ሐሳባቸውንና ኢኮኖሚያቸውን ለራሳቸው ቤት ማድረጋቸው «በቤተሰቦቻቸው ዘንድ ገሸሽ እስከ መደረግ ያደርሳቸዋል» ይላል:: «ብቻህን በነበርክ ጊዜ የበለጠ ለቤተሰብህ ታደርግ ይሆናል:: አሁን ግን ከትዳር ጓደኛህ ጋር ስለምትሆንና ነገሮችን በምክክር ስለ ምታደርግ ለቤተሰብህ የበፊቱን ያህል ለመፈጸም ትቸገር ይሆናል:: ወላጆችህ በትዳር ዙሪያ ያላቸው አመለካከት ያልበሰለ ከሆነ ፍቅራቸው ሊቀዘቅዝ ይችላል:: ይህን ሁሉ የምታደርገው «ሚስቱ» ናት በማለት በሚስትህ ላይ ሊነሣሱ ይችላሉ:: በዚህ ጊዜ በእርሷና በአንተ ቤተሰብ መካከል ወይም በአንተና በእርሷ ቤተሰብ መካከልም ፍቅርና ሰላም ይጠፋል:: ሰላምና ፍቅር በሌለበት ትዳር ውስጥ ደግሞ የተቀደሰ ኑሮ ለመኖር አዳጋች ነው::»

ሰዎች በዘመናት ታሪክ ውስጥ በውል ያልተረዱት ነገር ቢኖር ወንድና ሴት በጋብቻ ከተጣመሩ በኋላ ፍጹም አንድ መሆናቸውን ነው:: እግዚአብሔር ለጋብቻ ከሰጠው ፈቃድና ኃይል መካከል እናትና አባትን ትቶ የትዳር ጓደኛን መከተል አንደኛው ነው:: ወላጆች የወላጆቻቸውን ቤት ከለቀቁ በኋላ ዛሬ ልጆቻቸው እንደ ሆኑት መሆናቸውን ይዘነጋሉ:: ነገሩ ሁሉም ሰው የእኔ ብቻ ያለውን ነገርም ሆነ ሰው÷ ሌላ ሰው ሲወስድበት ሙሉ ደስታ አይሰማውም:: ትዳር ግን «ሰው እናትና አባቱና ይተዋል፤ ከሚስቱም ጋር ይተባበራል፤ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ» የሚል ኪዳን ተሰጥቶታል:: ለኪዳኑ መታዘዝ ግድ ነው:: ይህም ሲባል ወላጆችን እርግፍ አድርጎ መተው ተገቢ አይደለም:: በተቻለ መጠን መር ዳትና መጎብኘት ግድ ይላል:: ምክንያቱም ቅድስና በዚህም ይበዛልና:: «ትዳር ከመሠረትኩ በኋላ የምን ቤተሰብ» የሚሉ ግን ከኀሊናና ከማኅበረሰቡ ወቀሳ አያመልጡም:: የሚያስፈራው ደግሞ «ስለ ቤተሰቦቹ የማያስብ ማንም ቢሆን ሃይማኖትን የካደ ከማያምንም ሰው ይልቅ የሚከፋ» መኾኑ ነው:: 1ጢሞ.5÷8::

አቶ መስፍን መንግሥቱ የተባሉ የአዲስ አበባ ነዋሪ በበኩላቸው:- «ራስ ወዳድነት በትዳር ውስጥ ካለ የቅድስና ሕይወትን መምራት አይቻልም:: ሰው ራስ ወዳድ ሲሆን አይደለም ከሌላ ሰው ጋር ከራሱም ጋር በሰላም መኖር አይችልም:: ባለትዳሮች እምነትና በጎ ኅሊና ከሌላቸው መተማመንና አንደኛው ያደረገውን ነገር በበጎ ጎኑ ማየት አይችሉም:: የዚህን ጊዜ ትዳር ስለ ሚበጠበጥ ለቅድስና ሕይወት የሚ ደረገው ሩጫ ይገታል:: ኑሮአቸው በሙሉ በመካሰስና በጭቅጭቅ ስለ ሚሞላ የቅድስናን ሕይወት ይርቁታል::» ይላሉ::

አቶ ሶምሶን ደግሞ «ትዳር በሙሉ ነጻነት የሚፈጸመውን መንፈሳዊ አገልግሎት በተወሰነ ደረጃ ሊጋፋ ይችላል» ሲሉ ስጋታቸውን ይገልጻሉ:: «ከቤተሰብ ጋር በምትኖርበት ጊዜ ጠ

# ሐሳብን ለእግዚአብሔር ያለመስጠት፣ ችግሮችን በጸሎትና በውይይት ለመፍታት ያለ መጣርና ከአገልግሎት መራቅ፣በትዳር ውስጥ ለሚመራ የቅድስና ሕይወት እንቅፋቶች ናቸው::

ዋት ተነሥተህ ወደ ኪዳንም ሆነ ወደ ሌላ አገልግሎት መሔድ ትችላለህ:: እነዚህ ነገሮች ግን በትዳር ሕይወት ውስጥ በተወሰነ ደረጃ ይገደባሉ:: ይህም ቤትህንና ትዳርህን ስለ ምታስብ ነው:: ሐሳብህን የግድ ከትዳር ጓደኛህ ጋር ስለ ምትካፈል ብቻህን መጓዝ አትችልም:: በክርስትና የበረታች ሚስት ካገኘህ ግን ከነበረው የበለጠም ልታተጋህ ትችላለች::»

የብቸኝነትም ሆነ የጋብቻ ሕይወት በራሳቸው ክፋት የሌለባቸው ችግሮች አሏቸው:: ዋናው ነገር በሁለቱም የሕይወት ጎዳናዎች ላይ ሲጓዙ አቅምና ሁኔታ በፈቀደው መጠን ለቅድስና መታገል ነው:: ስለ እግዚአብሔር ባሰብን ቁጥር ልባችንን በግርምት የሚሞላ አንድ እውነት አለ:: የትኛውም ሰው ለቅድስና ሲተጋ የሚጠበቅበት ነገር እንደ ተሰጠው ጸጋ መጠን የቻለውን ያህል መጋደል ነው:: ሌላው በእግዚአብሔር ቸርነትና ረድኤት የሚሞላ ይሆናል::

ቄስ (ዶ/ር) ጆሲ ያዕቆብም ቢሆኑ በትዳር ውስጥ የሚደረግ የቅድስና ኑሮ ትግል ከብቸኝነት ሕይወት ይልቅ የከበደ እንደ ሆነ ያምናሉ:: *«There are a lot of possibilities for friction and quarrel of many things like between husband and wife or children and parent. So it is difficult in married life to express holiness, but it is a duty of people who are leading a married life.* ቅድስናን በጋብቻ ሕይወት ውስጥ ጠብቆ መኖር በሌላ የሕይወት ጎዳና ውስጥ ቅድስናን ከመጠበቅ ይልቅ የከበደ ይመስለኛል:: ምክንያቱም ባለትዳሮች የምንጠመድባቸው ብዙ ሥራዎች /ሐላፊነቶች/ ይኖራሉ:: ሌላው ነገር ደግሞ በጋብቻ ሕይወት ውስጥ ለግጭትና ለንትርክ የሚዳርጉ ብዙ ሁኔታዎች ይኖራሉ:: ለምሳሌ:- በባልና በሚስት ወይም በልጆችና በቤተሰብ መካከል ሊሆን ይችላል:: የቅድስና ሕይወትን መምራት በጋብቻ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ተግባር ቢሆንም ከባድነቱ ግን አያጠያይቅም:: እርግጥም ከብቸኛው የሳሌም ንጉሥንና ካህን መልከ ጸዴቅ ይልቅ አብርሃምና ሣራ በተለያዩ ችግሮች ውስጥ አልፈዋል:: እርስ በእርሳቸውም ሆነ ከሌሎች ጋር ተጋጭተው ነበር:: ይሁን እንጂ በዚህ ሁሉ መሐል አልፈው በቅድስናና በፍጹም እምነት የተሸለመ ኑሮ ኖረዋል::» ዘፍ.14÷18-24፤ ዘፍ.21÷10-11:: ፈተናዎች የሰው ልጅ መፍትሔ ፈላጊ ብቻ ሳይሆን የተለያዩ መንገዶችን የሚቀይስ ፍጡር መሆኑን መስክረዋል:: ባለትዳሮች የቅድስናን ሕይወት እየመሩ ይኖሩ ዘንድ ምን ማድረግ አለባቸው?

አቶ መስፍን መንግሥቱ ይህን ብለዋል:: «ሚስቴ ለእኔ ታማኝ እንድትሆንልኝ የምፈልገውን ያህል እኔም ለሚስቴ ታማኝ መኾን ይኖርብኛል:: ያን ጊዜ የቅድስና ሕይወት በመተማመናችን ላይ ይደረጀል:: ሚስቴ ለኔ እንድ ታደርግልኝ የምፈልገውን ለእርሷም በማድረግ ደስታ አገኛለሁ፤ ለሰዎች ከምናደርጋቸው መልካም ነገሮች ደስታን በቀዳሚነት የምናገኘው ራሳችን ነንና:: እኔ ታማኝ ከሆንኩ ሚስቴ አትታመንም የሚል ፍራቻ የለኝም:: እኔ ለእግዚአብሔር ሳልመች ስቀር ሚስቴ በኔ ላይ በደል እንድትፈጽም እየጋበዝኳት ነው:: መልካም የሆነችውን ሚስቴን ለብልሹ ድርጊት ልገፋፋት ወይም ምክንያት ልኾናት የምችለው እኔ ነኝ:: እርስዋም በፊንታዋ እንዲሁ:: በመሆኑም በመተማመንና በመልካምነት ከጸኑ የቅድስና ሕይወትን ሊኖሩ ይችላሉ:: አንድ ሰው ከጾም፣ ከጸሎት፣ ከስግደት ካልተለየና ለክርስትና ሕይወቱ ከሚመቹ ባልንጀሮች ጋር ከዋለ ለሕይወቱ እንደ መሥዋዕት ዕጣን በጎ የምግባር መዓዛ ይኖረዋል:: ቅድስናውም ከዕለት ወደ ዕለት ይደምቃል:: የትኛውም ባለትዳር ምግበ ሥጋ እንደ ሚያስፈልገው ሁሉ ቃለ እግዚአብሔርን ካገኘ የቅድስና ኑሮን ለመኖር ብርታት ያገኛል:: በአጠቃላይ እምነትና በጎ ኅሊና በባለትዳሮች መካከል ካለ የቅድስናን ሕይወት ሊኖሩት ይችላሉ::»

ሁለት ጥንዶች በመጠባበቅ ላይ ሆን በመተማመን ላይ የተመሠረተ ፍቅርና ትዳር ካላቸው እግዚአብሔር በእነርሱ ስለ ሚደሰት የቅድስናው ተካፋይ ያደርጋቸዋል:: መተማመናቸው ለቅናት፣ ለጥልና ለመተማማት በር ስለ ማይከፍት ጎጇቸው በተድላ ደስታ የተሞላ ይሆንላቸዋል:: አምላካቸው እግዚአብሔርም በቅድስና ካባ ይሸልማቸዋል፤ ሰላምን ያጎናጽፋቸዋል:: እርስ በእርስ የማይተመማኑ ባለትዳሮች እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት ስለ ማይችሉ ዘውትር የቅድስና ጽዋቸው የጎደለ ነው:: «እግዚአብሔርን ያለ እምነት ደስ ማሰኘት አይቻልም» ተብሎ መጻፉ ስለዚህ ነው:: ዕብ.11÷6::

አንዳንድ ጊዜ ውጤቱ «ለትዳራችን መልካም ይሆናል» ተብሎ የተጀመረ ነገርም መጨረሻው ላይሠምር ይችላል:: በዚህም ጊዜ ቢሆን በበጎ ዐይን ማየት እንጂ «እኔን ሊጎዳ»፤ «እኔን ልትጎዳ»፤ «ትዳራችንን ሊያደፈርስ»... የሚሉ ክፉ ሐሳቦችን በኅሊና እያመላለሱ መኖር አያስፈልግም:: ይህ የኅሊና ክፉ ዕንስ በአንድ አጋጣሚ በአንደበት ይወለድና ምንም የማያውቀውን የትዳር ጓደኛ ልብ ሊያጠቁር ይችላል:: ነገሮችን በበጎ መልኩ የሚያዩ ጥንዶች ግን ልባቸው ስለ ማይጠቋቆር፣ ስለ ሚተማመኑና ስለ ሚዋደዱ ልዑል እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ይሆናል:: ቅዱስ እግዚአብሔር ባለበት ሕይወት ደግሞ ቅድስና አለ:: ስለዚህ ባለትዳሮች «በጎ ኅሊናን ገንዘብ ሊያደርጉ ይገባል:: በጎ ኅሊና ይኑራ





www.eotcmk.org

ችሁ::» ተብሏልና:: 1ጴጥ.3÷16::

«ከስሕተት በኋላ ብዙ መለያየቶች ወደ ሰዎች ሕይወት ገብተዋል» በማለት የሚጀምሩት ደግሞ ቀሲስ እንዳለ አሻግሬ ናቸው:: በገለጻቸው ይቀጥላሉ:- «ይህን ከአዳምና ከሔዋን ውድቀት ጀምሮ ማየት እንችላለን:: በመጀመሪያ ሔዋን ስትፈጠርለት ይህች አጥንት ከአጥንቴ፣ ሥጋዋም ከሥጋዬ ነው:: ከወንድ ተገኝታለችና ሴት ትባል እያለ የደስታ ቅኔን ተቀኝቷል:: ኃጢአትን ከሠራ በኋላ ግን እንኳን ሊያመሰግናት እርሷን አሳልፎ ለመስጠት ነበር የሞከረው:: ይህን ዐይነቱ መካሰስ አልፎ አልፎ በትዳር ጓደኞች መካከል ሊከሠት ይችላል፡ መቀባበል÷ መቻቻል ግን ይህን ችግር ይቀርፉል:: መቀባበል÷ መቻቻል የሚያስፈልገው ከትዳር ጓደኛ ሊወረወሩ ከሚችሉ አንዳንድ ሸካራ ቃላት ብቻ አይደለም:: በድርጊትም የሳተውን የትዳር ጓደኛ ችሎ ማሳለፍ ኋላ በትዕግሥት የሚተርፈውን የቅድስና ዋጋ ለማግኘት ይጠቅማል::»

«ከእናንተ እያንዳንዱ የአንዱን ሸክም ይሸከም::» /ገላ.6÷2/ ይላል እግዚአብሔር:: ዘወትር የትዳር ጓደኛቸውን ጉድለት በመቻል የሚሸከሙ ባለትዳሮች ስለ ትዕግሥታቸው ሰማያዊ ደመወዝ ያገኛሉ:: በትዕግሥት የተሸከሙት የትዳር አጋራቸውም አንድ ቀን ይስተካከላል፤ የናፈቁትን የቅድስና ሕይወትም መኖር ይጀምራሉ::

ፈቃዱ ሣህሌ ደግሞ በትዳር ውስጥ ለሚኖር የቅድስና ሕይወት መሠረቱ ጅማሬው እንደ ሆነ ሲናገሩ:- «አስቀድመው በመጠናናት ቆይተው በሥርዐተ ቤተ ክርስቲያን የሚጋቡ ባልና ሚስት የተቀደሰ ሕይወት ሊኖሩ ይችላሉ:: ግን አይፈተኑም ማለት አይደለም:: ቢፈተኑም ይችሉታል::» ብለዋል:: አስከትለውም:- «በትዳር ውስጥ የሚፈጠሩትን ችግሮች በግልጽነትና በውይይት መፍታት አለባቸው:: ከሁለቱ ውይይት የሚያልፍ ነገር የለም:: ቢያልፍ እንኳን ለንስሐ አባት መንገር ይገባል:: ግን አልፎ አልፎ ካልሆነ በስተቀር ይህ ልማድ በምእመኑ ዘንድ የለም:: በእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን አንድ ተሞክሮ እንዳለ ሰምቻለሁ:: የተጣሉ ባልና ሚስት ዘጠና በመቶ የሚሆነውን ችግራቸውን ራሳቸው ናቸው በውይይት የሚፈቱት:: ዘጠኝ በመቶ ደግሞ በንስሐ አባታቸው አማካይነት እልባት ይሰጠዋል:: አንድ በመቶ ብቻ በሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ይፈታል:: በአጠቃላይ 100% የሚሆነው ችግራቸው በቤተ ክርስቲያን እንደ ሚፈታ ልብ ማለት ያሻል:: ስለዚህ ባለትዳሮች ችግሮች እንዳይፈጠሩ ቅድመ ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው:: ችግሮቹ ቢፈጠሩም በውይይት፣ በንስሐ አባትና በሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ እንደ ክብደት መጠናቸው ቢፈቱ መልካም ነው:: በዚህ ጊዜ ነው ባለትዳሮች የቅድስናን ሕይወት ሊመሩ የሚችሉት:: በዓለም ችሎቺ የሚዳኝ ትዳር የቅድስና መፍለቂያ ሊሆን አይችልም:: ቤተ ክርስቲያን በትዳር ጉዳይ ላይ ለመፍረድ ሙሉ ሥልጣኑና ብቃቱ አላት:: ዳኑ ከቤተ ክርስቲያን ውጪ የተመሠረተ ጋብቻ የቤተ ክርስቲያን ዳኝነት አይሻ ይሆናል:: በቤተ ክርስቲያን ጋብቻቸውን የፈጸሙትም ችግር ሲገጥማቸው መች መጡ? ተጠናንተው ጋብቻቸውን የሚመሠርቱና ችግራቸውን በመንፈሳዊ መንገድ ለመፍታት የወሰኑ ባለትዳሮች ከተገኙ የቅድስና ሕይወት በኑሮአቸው የማይታይበት ምክንያት የለም::» ብለዋል::

ይህን መሰሉ ልምድ በቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ዘንድ ተለምዶ ስለነበር ቅዱስ ጳውሎስ በዚህ መልኩ ገሥጿቸዋል:: «የትዳር ጉዳይ ይቅርና በመላእክት እንኳ እንድንፈርድ አታውቁምን? እንግዲህ ስለ ትዳር ጉዳይ የፍርድ ቤት ቢያስፈልጋችሁ በቤተ ክርስቲያን የተናቁትን ሰዎች ፈራጆች አድርጋችሁ ታስቀምጣላችሁን? አሳፍራችሁ ዘንድ ይህን እላለሁ፤ እንደዚህ ነውን? በወንድሞች መካከል ሽማግሌ ሊሆን የሚችል አንድ አስተዋይ ሰው በእናንተ ዘንድ አይገኝምን?» 1ቆሮ.6÷3:: ይህ ተግሣጽ ዛሬም ባሉ ባለትዳሮችና ሌሎች ክርስቲያኖች ላይ ሕያው ነው::

ጋብቻ ክቡርና ታላቅ ምስጢር ነው:: በትዳር ሕይወታቸው ችግር የተፈጠረባቸው ባልና ሚስት ገመናቸውን ለዓለም ለመግለጣቸውም ሆነ ቤተ ክርስቲያን ችግራቸውን እንድትፈታላቸው ወደ ቤተ ክርስቲያን ላለመምጣታቸው በዋቢነት የሚቀርቡ ብዙ ምክንያቶች አሉ:: በየትኛውም የስሕተት ድርጊት ውስጥ የመጀመሪያው ምክንያት አለማወቅ ነው:: የትዳርን ክቡርነት አለማወቅና እግዚአብሔር የመፍትሔ ባለቤት መኾኑን አለመረዳት ባለትዳሮች ችግሮቻቸውን ለቤተ ክርስቲያን እንዳይነግሩ አድርጓቸዋል:: በዚህም ብዙዎች እየተጎዱ ነው:: ለዚህ ነው አምላካችን በነቢዩ ሆሴዕ አድሮ «ሕዝቤ ዕውቀት ከማጣቱ የተነሣ ጠፍቶአል::» ያለው:: ሆሴ.4÷6::

አንዳንዶቹ ደግሞ ሕገ ቤተ ክርስቲያንና ሥርዐቷን ስለ ሚደፋፈሩ ወደ ቤተ ክርስቲያን መጥተው መዳኘት አይሹም:: ካልወለደቻቸው ዓለም ይልቅ የወለደቻቸው እናት ቤተ ክርስቲያን ብትዳኛቸው ይሻላቸው ነበር:: እነርሱ ግን በድፍረታቸው ትተዋታል:: «ከእናንተ አንዱ ከባልንጀራው ጋር ሙግት ቢኖረው በቅዱሳን ፊት በመፋረድ ፋንታ በዐመፀኞች ፊት ሊፋረድ ይደፍራልን?» ተብሎ እንደ ተጻፈ:: 1ቆሮ.6÷1 ቅዱስ እግዚአብሔር ደፋሮችንና ኩሩዎችን ስለ ሚጠየፍ ቅድስናንና ሰላምን እንደ ተራቡ ይኖራሉ::

ሌላው ችግር ደግሞ የባለትዳሮችን ሥነ ልቡናዊ ችግር ለመረዳት ነው:: እርግጥ ገና ሳይነገራቸው የልጆቻቸውን ችግር የሚረዱ አንዳንድ አባቶች አሉ:: መንፈሳዊ የሆነውን የምክክር ዘዴ በመጠቀም የንስሐ ልጆቻቸውን ቁስል በመንፈሳዊው የመፍትሔ ዘይት የሚጠግኑ ብዙ አባቶች አሉ:: ቁጥራቸው ግን ጥቂት ነው:: የባለትዳሮችን ችግር መረዳት ያልቻሉ አባቶች መኖር ደግሞ ብዙ ባለትዳሮች ከአባቶቻቸው ጋር ልብ ለልብ ሳይሆን አፍ ለአፍ ብቻ የሚግባቡ አድርጓቸዋል:: በዚህ የተነሣ ብዙዎቹ የትዳር ችግራቸውን ወደ አባቶቻቸው ላያቀርቡ ችለዋል:: ስለሆነም በመንጋው ላይ የተሾሙ እረኞች ዘመኑን ሊዋጁና በትዳር ዓለም ያለውን ክርስቲያን ማኅበራዊ፣ ሥነ ልቡናዊና መንፈሳዊ ችግር በጥልቀት ሊያውቁ ይገባል:: አለበለዚያ አሁን ካላቸው ርቀት በበለጠ ከሕዝቡ ሊርቁ ይችላሉ:: በዚያው መጠን የባለትዳሮች ሕይወት ከቅድስና ይርቃል:: በመሆኑም ክርስቲያን ባለትዳሮች ቤተ ክርስቲያን ችግሮቻቸውን ለመፍታት ያላትን ጥበብ፣ ዕውቀትና ሥልጣን በመሠረቱ ሊያውቁ ይገባል:: መንጋውን እንዲያሠማሩና እንዲከባከቡ ልዑል እግዚአብሔር የሾማቸው ካህናትም ወደ ባለትዳሮች የውስጥ ችግር ገብተው የችግሩን ጠባይ፣ በሚገባ ተረድተው መፍትሔ ሊሰጡ ይገባል:: ለዚህ ደግሞ ከዘመኑና ከትውልዱ ቀድሞ ማሰብ ያስፈልጋል:: ከትውልዱ ኋላ ሆኖ ትውልዱን መቆጣጠር አይቻልም፤ መልካሙ እረኛ በጎቹን ከፊት ከፊት እየሄደ አይደል የሚመራው:: ዮሐ.10÷4:: አባግዐ ምእመናንን ለመጠበቅና ለማሠማራት በእረኞች አለቃ የተሾሙ ካህናት ሁሉ ፍለጋውን ይከተሉ:: ያን ጊዜ ባለትዳሮች በቅድስና ካባ የተንቆጠቆጡ የዓለም ፈርጦች ይሆናሉ:: ባለ ትዳርና የአንድ ልጅ አባት የሆኑት ቄስ /ዶ/ር/ ጆሲ ያዕቆብ በጋብቻ ሕይወት ያሉ ሰዎች የተቀደሰ ኑሮ መኖር የሚችሉት የሚከተሉትን ፈጽመው ሲገኙ ነው ብለዋል:: *«In married life each member of family has his own responsibility to keep the solidarity of the family. And which will lead the family to the holiness. So we have to keep the law, ultimate commandment of God –love. We should exercise it in family. So the family bond should be a bond of love when it be comes a bond of selftess or a love which intended by God. Then holiness will be there.* *በጋብቻ ሕይወት ውስጥ ያለ እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል የቤተሰቡን አንድነት የመጠበቅ ሐላፊነት አለበት:: ይህም ቤተሰቡን ወደ ቅድስና ይመራል:: ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን ስለ ጋብቻ ያወጣችውን ሕግ መጠበቅ አለብን:: የትእዛዛት ፍጻሜ የተባለውን የእግዚአብሔርን ሕግ /ፍቅርን/ መጠበቅ መንፈሳዊ ግዴታችን ነው:: ፍቅርን በቤተሰብ ውስጥ መተግበር ይገባናል:: ስለሆነም የቤተሰብ ጥምረት የፍቅር ጥምረት መሆን አለበት:: የቤተሰብ ጥምረት ከራስ ወዳድነት ከነጻና እግዚአብሔር በፈቀደው ፍቅር ከታሰረ ቅድስና በዚያ ይኖራል::»*

በትዳር ውስጥ ያለውን የቅድስና ሕይወት አስመልክቶ መምህር ሐዲስ ባካፈሉን ተሞክሮ ዝግጅታችን እንቋጭ:- «እኔ ባለትዳር ነኝ፤ ባለቤቴም ጥሩ ሴት ናት፤ ቤተ ክርስቲያንን ትወዳለች፣ እኔም ቤተ ክርስቲያኔን እወዳለሁ:: ወደ ቤተ ክርስቲያን ስንሔድ ደግሞ አብረን ነው የምንሔደው:: ከእርሷ ጋር ተጣልቼ አላውቅም:: እርሷም በእኔ እኔም በእርሷ አንበሳጭም:: እርስ በእርሳችን ተጽናንተን እንኖራለን:: እርሷም ሆነች እኔ ወደ ክፋት አንሔድም:: ችግር ቢፈጠር እንኳን ተቻችለን ወደ እግዚአብሔር እናመለክታለን:: ክፉም ሲገጥምን ሁሉን በትዕግሥት እናሳልፋለን:: ልጆቻችንንም በሃይማኖት አንጸን አሳድገናል:: የአቅማችንን ሰጥተን የአምላካችንን ቅዱስ ሥጋ ክቡር ደም በመቀበል እንኖራለን::»

ይቆየን::

ወስብሐት ለእግዚአብሔር






www.eotcmk.org

# ፍጥረትን ተመልከት ቀመረ እግዚአብሔር ቀመረ ውበት

/ምሥጢረ ናግራን/

የፍጥረታት መገኛዎች የኾኑት አራቱ ባሕርያት፡- እሳት፣ውኃ፣ነፋስ፣መሬት ናቸው። እኒህ ባሕርያት በየጠባያቸው የማይስማሙ ተጣዮች ናቸው። እሳቱ ውኃውን ያፈላዋል፤ ውኃው እሳቱን ያጠፋዋል፤ ንፋሱ መሬቱን /ትቢያውን/ ይዘራዋል፤ መሬቱ ንፋሱን ይገታዋል። በአንጻሩ ደግሞ የአራቱ ባሕርያት የየጠባያቸው ሥራ እዚያው ሳለ እርስ በርስ ይስማማሉ፤ «ወአስተሰናአዎሙ በበይናቲሆሙ እንዘ ዘዚአሁ ግእዘ ጠባኢሆሙ» እንዳለ ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ። እሳቱ፡- በሙቀቱ /ውዕየት/ ከንፋስ፣ በብሩህነቱ ከውኃ፣በደረቅነቱ /ይብስት/ ከመሬታዊ ባሕርይ ጋር ይያያዛል፤ ይዋሐዳል፤ ይስማማል። ውኃው፡- በብሩህነቱ ከእሳት፣ በርጥበቱ ከመሬት፣ በቅዝቃዜው /ቊሪት/ ከንፋሳዊ ባሕርይ ጋር ይያያዛል፤ ይዋሐዳል፤ ይስማማል። ንፋሱ፡- በሙቀቱ ከእሳት፣ በቅዝቃዜው ከውኃ፣ በፅሉምነቱ ከመሬታዊ ባሕርይ ጋር ይያያዛል፤ ይዋሐዳል፤ ይስማማል። መሬቱ፡- በደረቅነቱ /ይብሰት/ ከእሳት፣በርጡብነቱ ከውኃ፣ በፅሉምነቱ ከንፋሳዊ ባሕርይ ጋር ይያያዛል፤ ይስማማል፤ ይዋሐዳል። አራቱ ባሕርያት በእግዚአብሔር ጥበብ እንዲህ በየጠባያቸው ተስማምተው በየወገኑ ያስገኙት ፍጥረት፡- *ሥነ ፍጥረት* ይባላል። እንዲያው በጥቅሉ እግዚአብሔር ፍጥረትን በየወገኑ ያስገኘበት ቀመሩ ይኸ ነው፤ ውበቱም የባሕርያቱ በህልውና መስማማትና መገናዘብ ነው። *«ነገርን ሁሉ በጊዜው ውብ አድርጎ ሠራው፡፡»* እንዳለ። መክ.3÷11። ሥነ ፍጥረት ማለት ቅሉ የፍጥረት መበጀት፣ የበጀ ፍጥረት፤ የፍጥረት መስማማት፤ የተስማማ /ስምም/ ፍጥረት ማለት ነው። ፍጥረተ እግዚአብሔር ሁሉ በተለይም ከሰው መገኘት በኋላ እጅግ ውብ እንደ ኾነ ቅዱስ መጽሐፍ ይነግረናል። «እነሆ እግዚአብሔር ያደረገውን ሁሉ አየ፤ እነሆ እጅግ መልካም ነበረ። ማታም ሆነ ጥዋትም ሆነ÷ ስድስተኛ ቀን።» እንዳለ። ዘፍጥ.1÷31። ከሌሎቹ ይልቅ በክብሩ ገኖ በእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ የተፈጠረው ሰው ራሱንና አካባቢውን የመመርመር፣ የማወቅ፣ የመረዳት፣ የመግዛት ጸጋና ችሎታ አለው። ይህን መሠረት በማድረግ የሥነ ሕንጻ በካር ባለሞያ የሆኑት *«ምሥጢረ ናግራን»* ዓለም ዛሬ የደረሰበት የሳይንስና ቴክኖሎጂ ምጥቀትና ርቀት መሠረቱ፡- «እግዚአብሔር የፈጠረውን ፍጥረት በጥልቀት ወደ ውስጥ /ወደ መካከሉ/ እና በግዝፈት ወደ ላይ መመርመሩ ነው» ይሉናል። ለሳይንስና ቴክኖሎጂው መነሻ የኾኑና ሊኾኑ የሚችሉ፤ በመንፈሳዊ አስተምህሮና በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የተካበቱ ሀብቶችንም እየገላለጡ ያሞቁናል፤ በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና ያወጉናል፤ ያትቱልናል፤ ይሞግቱናል፤ ለበለጠ ኀሠሣም ያነቃቁናል። እነሆ እኛም የጥበብ አፍቃሪያን በ*«ምሥጢረ ናግራን»* ሐተታ ጠልቀው ገብተው ዋኝተው ይወጡበት ዘንድ ይህን ዓምድ ከፈትን - *ሥነ ኪን*። *«ኪን»* የሚለው የግእዙ ቃል በጥበብ እድና በተግባረ እድ የፈጠራ ተግባር መራቀቅንና መጠበብን ያመለክታል። በሌላ አነጋገር *ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ* የሚለውን ቃል ይተረጉማል። *«ሐተታ ምሥጢረ ናግራን»* ላልተወሰነ ጊዜ በሥነ ኪን ዓምድ ይቀጥላል...




*ከውኃ ቅንጣቶች ተፈጥሯዊ ቅርጾች ጥቂቶቹ*

እግዚአብሔር ከምንም ነገር /እም ኀበ አልቦ/ ይህን ዓለም እንደ ፈጠረ የፍጥረት ልደት ታሪክ ይነግረናል። «በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ።» /ዘፍጥ.1÷1/ እንዲል። በዚህ ላይ ተመሥርተን ፍጥረትን ስንመረምር ሁሉ በሥርዐት እንደ ተፈጠረና ሁሉንም በጊዜው ውብ አድርጎ እንደ ሠራው ያሳየናል። ከምንም ነገር ቅርጽ አስይዞ እያንዳንዱን ነገር እንዳስገኘው እንረዳለን። ሥነ ፍጥረት በኀልዮ /በሐሳብ/፣ በነቢብ /በቃል/፣ በገቢር /በሥራ/ እንደ ተከናወነ መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳናል። ሁሉም በተቀመጠለት ሥርዐት ማለትም ወፎች ከጠፈር በታች ከምድር በላይ ይብረሩ እንደ ተባሉ፣ ፀሐይ በቀን፣ ጨረቃ በሌሊት እንዲሠለጥኑ፣ ብርሃንና ጨለማን እንዲለዩ እንዳደረጋቸው ጥንቱንም ሆነ አሁን እስከ ጊዜው ድረስ እንዳለ ይቀጥላል። ሁሉም ከሥርዐቱ አላፈገፈገም። በመጨረሻም እግዚአብሔር ሰውን ከአራቱ ባሕርያተ ሥጋና ከሦስቱ ግብራተ ነፍስ አስማምቶ በመልኩና በምሳሌው አክብሮና አግንኖ ፈጠረው። ከምድር አፈር የተበጀው ሕያው ሰው እስትንፋሰ እግዚአብሔር ያለበት፣ ከሌላው ተለይቶ አካባቢውን የማወቅ፣ የመረዳት፣ የመመርመር፣ የመግዛት ችሎታ ኖሮት ተፈጠረ። ዘፍጥ.2÷7።

እግዚአብሔር ቅርጽ ሰጥቶ የፈጠራቸውን ፍጥረታቱን በምናስተ ውልበት ጊዜ በትልቁ ሁለት ነገሮች አሉ- *ቅርጽ /Form/* እና *ሞገድ /Wave/*። ቅርጽና ሞገድ ፍጥረተ ዓለምን ለመረዳት የሚያገለግሉን ናቸው። በተጨማሪም የዓለም *መለኪያ* /the yardstick of the world/ ናቸው። ሁሉም ነገር ቅርጽ አለው፤ ሁሉም ነገር በውስጡ እየገባን ስንሄድ ሞገድ አለው። «ምድርን ተመልከታት፣ ትነግርህማለች» በማለት መጽሐፍ ቅዱስ ፍጥረታትን እንድናስተውልና የሚጠቅመንን እንድንይዝ ይመክረናል። የእግዚአብሔርን ፍጥረት በጥልቀት መመርመሩ፣ የሰው ልጅ የሚጠቀምበትን ድብቅ የሆነ ዕውቀት እያወጣ ለሁሉም በሚጠቅምበት መንገድ በማሰናዳቱ ዓለም አሁን ከደረሰበት የቴክኖሎጂ ምጥቀት ሊያደርሰው ችሏል። ይህም ለሰው ልጅ ምቾት አስተዋፅኦ እያደረገ፣ የዕለት ምግብ የዕለት ልብስ እየሆነ፣ ዕውቀት በዕውቀት ላይ እየተደመረ ካለንበት ደርሰናል፤ ወደፊትም እንቀጥላለን። ይህ ጥበብ ያላቸው ሰዎች መሠረታቸው ሌላ ሳይሆን እግዚአብሔር የፈጠረውን ፍጥረት በጥልቀት ወደ ውስጥና በግዝፈት ወደ ላይ መመርመራቸው ነው።

ከግዙፉ ዓለም እስከ እያንዳንዷ ነቁጣ /ጥቃቅን ኤሌክትሮን/ ድረስ ቅርጽ የሌለው ወይም በቅርጽ የማይገለጽ ነገር የለም። ይህ ቅርጽ ደግሞ ርዝመት፣ ጥልቀት፣ ስፋት ወይም ወርድ አለው። ከእነዚህ የአንዱ መቀየር በሌላው ላይ የሚያመጣው ለውጥ ወይም ተጽዕኖ ባለመኖሩ *ገጽታ /Dimension/* ይባላል። ይህ ዓይነት ገጽታ ያላቸውን በርካታ ነገሮችን እናያለን፤ እንዳስሳለን። ስለዚህ ማንኛውም ቅርጽ በእነዚህ ይለካል፤ ይወሰናል። ፍጥረታት በቅርጻቸው የተለያዩ ቢሆኑም በእኽዚህ ይለካሉ። በዚሁ ፈጥሮ አስቀምጧቸዋል። ስለዚህ በዚህና በቀጣይ ጽሑፎች የቅርጽን ምንነት



*የውኃውን ተፈጥሯዊ ቅንጣቶችና የመጾር መስቀሉን አንዳንድ ቅርጾች ያነጻጽሩ?*

በመገንዘብ እንዴት እንደ ምንጠቀምባቸው፣ አካባቢያችንን ለመመልከት እንደ ሚረዳንና እንደ ምንጠቀምበት ለመማማር እንሞክራለን። በተጨማሪም በእጃችን ከምንዳስሰው ቅርጽ በተጨማሪ በዐይናችን ከማየታችን ጋር የተያያዘ ሞገድ አለ። በዚህ ሞገድ አማካይነት እናያለን፤ እንሰማለን። የማየት የመስማት ሂደት በውስጣችን በቅርጽ አማካይነት በሥርዐቱ ተቀናብረው በተቀመጡት ቅርጾች አማካይነት ተንትነን እንጠቀምበታለን። ስለዚህ ሁሉም ነገር ከማየታችን፣ ከመስማታችንና ከመዳሰሳችን ወይም ከስሜት ሕዋሳታችን ጋር ይያያዛል።

ሰው ክቡር ፍጥረት ነውና የሚሠራበትንና የሚቀመጥበትን ቦታ ዔደን ገነትን ሰጠው። በዚህም ቦታ መያዙን እንመለከታለን። «እግዚአብሔር አምላክም ÷ በአዳም ከባድ እንቅልፍን ጣለበት ÷ አንቀላፋም፤ ከጎኑም አንዲት አጥንትን ወስዶ ሥፍራውን በሥጋ ዘጋው።» /ዘፍ.2÷21/ የሚለውን ስንመለከት የዘመኑን የሰመመን ሳይንስ /አንስቴዥያ/ እና የቀዶ ጥገና ሕክምና ጥበብ እናስታውሳለን። ሌላው አዳም በገነት ውስጥ ካለው የዛፍ






www.eotcmk.org

ፍሬ ሁሉ እንደ ሚበላ ነገር ግን «በመካከሉ» ካለው የዛፍ ፍሬ እንዳይበላ ታዝዞ ነበር:: /ዘፍ.3÷2/:: ሁሉንም ፍሬ የምንበላው ሥጋውን እንጂ የውስጡን /የመካከሉን/ ፍሬ አንበላም:: ለምሳሌ፡- ብርቱካን ጣፋጭ ሆኖ ሳለ ፍሬውን ብንበላው መራራ ነው:: የሁሉም ፍሬ ሥጋው ሲበላ የመካከሉ ግን ተመልምሎ ይጣላል:: በተመሳሳይ የምድር መካከሉን፣ የሰማይ መካከሉን፣ የፍጥረት መካከሉን አጉልቶ በሚያሳይ መነጽር ወይም በኤሌክትሮን ማይክሮስኮፕ ወይም ጥቃቅን ፍጥረታትን ተንቀሳቃሽ ምስል በሚቀርጽ ሌዘር ማይክሮስኮፕ ቢጠና ጥልቀቱን ማየት መንካት አልተቻለም:: አንዱ ጥልቅ ሲገኝ ሌላውን ጥልቅ እያሳየ የማይደረስበት አዘቅት ሆኗል:: ዕውቀት በየዘርፉ እየበረከተ የአንዱ መጨረሻ የሌላውን መጀመሪያ እየገለጸ ይሄዳል:: የዚህ ዕውቀት መገኘት ሰውን ከሰው እያበላለጠ፣ አንዱን ገዢ ሌላውን ተገዢ እያደረገ ጊዜው ይነጉዳል::

እናታችን ሔዋን በገነት መካከል ያለችዋን የዛፍ ፍሬ፡- «ለመብላት የምታስጎመጅ፣ ለዐይን ያማረች፣ ለጥበብም መልካም ሆና እንዳየቻት» ቅዱስ መጽሐፍ ያስረዳናል:: ዘፍ.3÷6-9:: በገነት መካከል ያለች፣ ለመብላት የምታስጎመጅ፣ ለዐይን ያማረች ለጥበብም መልካም የሆነች ዛፍ ምንድን ናት? «ሞት ያለባት ኃጢአት ናት» ይባል ይሆናል:: ይልቅስ ባሕርያችንና አካባቢያችንን እንመርምር:: ሳይንስ በጥበብ የተራቀቀ፣ ወደ ውስጥ በጥልቀት ተመልክቶ ሰው የሚጠፋበትንም የሚጠቀምበትንም ግኝት አገኘ፤ የዛሬው ኒውትሮን ቦንብ፣ ሀይ ድሮጅን ቦንብ «በእያንዳንዱ ፍጥረት መካከል» የተገኙ አይደሉምን? ሐሳባችን ከምንጠቀምበት ፍጥረት ጋር ያለው ግንኙነት ምን ያህል እንደ ሆነ ወደ ውስጥ እንድንመለከት ነው:: የሰው ልጅ ወደ ጥልቁ መርምሮ ዕውቀት አግኝቶ የተጠቀመበት በመልካም ጐኑ ለራሱ አሳልፎ ለሰውም ጠቅሞ ሲያሳልፍ÷ በመጥፎ ጐኑ ደግሞ ራሱን ሳይቀር ሲያጠፋበት ይገኛል:: ስለዚህ ቅርጾችንና የሞገዶችን አካሄድ ማየትና መመርመር የአሁኑ ሥልጣኔ መነሻና ትኩረት እንደ ሆነ እንገነዘባለን::

ቅርጾች ከነጥብ ጀምረው ወደ መስመር÷ ከመስመር ወደ ገጽ /Shape/ ከገጽ ወደ ቅርጽ /Form/ እየተያያዙ አንዱ ለሁሉም ሁሉም ከአንዱ ጋራ በተለየ ቀመር እየተያያዙ አንድነታቸውን እንድናይና በውበታቸው እንድንደመም ያደርገናል:: ቅርጽ ስንል፡- ርዝመት፣ ጥልቀትና ወርድ ያለው ቅርጽ ሲሆን ይህ ደግሞ ከሦስት ጐን ከሚሠራው ቴትራ ሃይድሮን ቅርጽ ጀምሮ እስከ አሎሎ ቅርጽ ይደርሳል:: ከሦስት ጐን ባለ አራት ቅርጽ ጀምሮ እስከ አሎሎ /ኳስ መሰል/ ቅርጽ ባለው ሂደት ውስጥ በርካታ ቅርጾችን እናገኛለን:: እነዚህ መሠረታዊ ቅርጾች በጥንቱ ዓለም በርካታ ምርምር የተደረገባቸው÷ ለአሁኑ የሰው ልጅ ሥልጣኔ መሠረት የተጣለባቸው ናቸው::

ፕላቶ የተባለው የግሪክ ፈላስፋ «አምስት መሠረታዊ ቅርጾች አሉ» ይለናል:: ባለ አራት ገጽ ,ሦስት ጐን፣ /tetrahedron/ ባለ አራት ገጽ ስድስት ጐን /Cube/፣




*የማንኛውም ፍጥረት መሠረታዊ ቅርጾች /ፕላቶናዊ ጠጣር ቅርጾች/*

ባለ ዐሥራ ሁለት ገጽ አምስት ጐን እና ባለ ሃያ ገጽ ስድስት ጐን፣ ባለ ሦስት ሃያ ጐን ቅርጾች ከዚያም አሎሎ ቅርጽ ወይም ኳስ /Sphere/ ናቸው::

እነዚህ ቅርጾች በሁሉም ፍጥረት ይገኛሉ:: እነዚህ ቅርጾች የሚሰጡትን ጥቅም በመረዳት በማጣመር፣ በማያያዝ፣ በመበሳሳት ቅርጾች የሚሰጡትን ጥቅም እናገኛለን:: ከቅርጾች በተጨማሪ በውስጣቸው ያለው የተሠሩበት ንጥረ ነገር ስብጥርና አቀማመጥ የነዚሁን ቅርጾች መልክ ይዞ ይገኛል:: የአንዱ ነገር ጥንካሬና ድክመቱ የሚታወቀው በነዚህ ቅርጾች አቀማመጥ እንደ ሆነ እንረዳለን:: በየትምህርቱ ዓይነት ስለ ቅርጽ ጥናት /Morphology/ የማይካሄድበት የትምህርት ዘርፍ የለም፤ ጥቅምና ይዘቱ ይለያይ እንጂ:: እግዚአብሔር ለኖኅ ከማየ አይኅ ይጠለልበት ዘንድ መርከብ እንዲሠራ ቀመር እንደ ሰጠው በመጽሐፍ ቅዱስ እናስተውላለን:: ጻድቁ ኖኅ በእግዚአብሔር ትእዛዝ ርዝመቱ ሦስት መቶ ክንድ፣ ወርዱ ኀምሳ ክንድ፣ ከፍታው ሠላሳ ክንድ የሆነ በማለት እንዲሠራ መታዘዙ ቅርጽ እንዲሠራ ማዘዙ ነው:: ዘፍ.6÷13-22:: የሰሎሞን ቤተ መቅደስ በእግዚአብሔር ትእዛዝ ርዝመቱ 60 ክንድ /ሠላሳ ሜትር/፣ ወርዱ 20 ክንድ /ዐሥር ሜትር/፣ ቁመቱ ሠላሳ ክንድ /15 ሜትር/ ያለው ቅርጽ እንዲሠራ አዝዞታል:: ነገሥ ቀዳ.6÷2:: በተጨማሪም ቅድስተ ቅዱሳኑ የኩብ ቅርጽ እንዲኖረው በማለት ርዝመቱ፣ ስፋቱና ቁመቱ 20 ክንድ /ዐሥር ሜትር/ እንዲሆን አዝዞታል:: ጠቢቡ ንጉሥ ሰሎሞን የራሱን ቤት ሲሠራ ርዝመቱ መቶ ክንድ /50 ሜትር/፣ ስፋቱ ኀምሳ ክንድ /25 ሜትር/፣ ቁመቱ ሠላሳ ክንድ /15 ሜትር/ በማድረግ ቅርጽን እንዲሠራ እንዳዘዘው እንረዳለን::

ስለ ቅርጾችና አለካክ የሚያጠና የትምህርት ዓይነት ጂኦሜትሪ ይባላል:: ጂኦሜትሪ በጥንታውያን ግብጻውያን፣ ባቢሎናውያን ፣ግሪካውያን መዛግብት ላይ ሰፍሮ የሚገኝ ነው:: ትምህርቱ ምሥጢር የሞላበት በመሆኑ በአንድ ጊዜ ላይረዳን ይችላል:: ቅርጽን በመመርመር ለሰው ልጅ ጥቅም የሚውሉ በርካታ ነገሮች ሲሠሩ /ሲፈለሰፉ/ እናያለን:: የተፈጥሮን ውስጥ ምሥጢር፣ የእግዚአብሔርን ረቂቅ ጥበብ እንረዳበታለን::

ከራሳችን ጀምረን በዙሪያችን በግዝፈትና በርቀት ያሉትን ስንመለከት ሁሉም ቅርጽ አላቸው:: ከምንሳለመው መስቀል ጀምሮ የምንሠራበት ማናቸውም መሣሪያ፣ እኛ ራሳችን፣ የሚንቀሳቀሰውም የማይንቀሳቀሰውም ሁሉ፣ ይህ ዓለም በግዝፈቱ ሳይቀር በርካታ ቅርጾችን ያሳየናል:: ቅርጾች ከጥቅማቸው ጋር ይያያዛሉ:: የአንዱ ቅርጽ ጥቅም ከሌላው ይለ ያል:: ይሁን እንጂ በሰፊው አተያይ ቅር ጾች በሁለት ዓይነት ይከፈላሉ፤ አንደ ኛው ነጻ ቅርጽ /Free form/ ሲሆን ሌላው ደግሞ ጂኦሜትራዊ ቅርጽ /Geometric form/ ይባላሉ:: ጂኦሜትራዊ ቅርጽ በየዕለቱ ከምንሠራቸው ሥራዎች የምና ገኘው ቅርጽ ሲሆን መደበኛ ነው፤ «ነጻ ቅ ርጽ» ቅርጽ ግን በተፈጥሮ የሚገኝ ነው::


የቅርጽን ምንነትና ጥቅሙን በመጠኑም ቢሆን ካሳየን በቀጣይ እግዚአብሔር ከፈጠረው ፍጥረት የሚገኙ ቀመሮችን እንመለከታለን:: የሰው ልጅ ፍጥረትን እየተመለከተ አስመስሎ ለመሥራት ልዩ የእግዚአብሔር ስጦታ ያለው በመሆኑ ተፈጥሮን በማየት የተለያዩ ቅርጾችን ይሠራል:: ይሁን እንጂ የሚታዩንን ቅርጾች ለመሥራት የውስጥ ቀመራቸውን ማወቅን ይጠይቃል:: ቀመራቸውን አለማወቅ ለዐይን ደስ የማያሰኝ በመሆኑ የገንዘብና የጉልበት ኪሳራ ያመጣል:: ለዚህም ነው የጥንቶቹ አባቶቻችን «ሲያዩት ያላማረ ሲበሉት ያቅራል» በማለት ሁሉም በሚያ ምር መልኩ መደራጀት እንዳለበት የሚገልጹት:: ስለዚህ የምናየው ሁሉ የሚያምረን ውብ ሆኖ የተፈጠረበት ቀመሩ ምንድን ነው? ይህ ቀመር ከየት መጣ? በዚህ ቀመር የሰው ልጅ ምን ሠራበት? አሁንስ ምን እየተጠቀመበት ነው:: በእኛስ ሀገር የዚህ ቀመር በጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያን እንዴት ተይዞ÷ ተገልጾ ነበር? ለምን ተሰውሮ ቀረ? ፍጹም ቁጥር የሚባለው ምንድን ነው? በተለያዩ ጸሐፍት እንዴት ተተርጉሟል? ቅርጽና ፍጹማን ቁጥሮች ግንኙነታቸው ምንድን ነው? እንዴትስ እንጠቀምበታለን? የሚሉትን ለመመልከት እንሞክራለን:: እስከዚያው ድረስ በራሳችሁ ላይና በዙሪያችሁ ያሉ ግዑዛንና ሕያዋን ቅርጾችን በትክታ እየተመለከታችሁ እንድታሰላስሉ በማሳሰብ እሰናበታችኋለሁ::

ይቆየን::

ወስብሐት ለእግዚአብሔር



www.eotcmk.org



ፕሮፌሰር ፓውሎ ማራሲኒ

# «ግእዝ በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች በምርጫ እንዲጠና ዕድል ይሰጠው፡፡»

/ፕሮፌሰር ፓውሎ ማራሲኒ
የሴማዊ ሥነ ቃላተ ልሳን ምሁር/

## መግቢያ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለኢትዮጵያ ካበረከተቻቸው ቅርሶችና ቅርስ ንዋያተ ቅድሳት መካከል ጥንታውያን ጽሑፎች በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡ እነዚህም በድንጋይ፣ በብራና... ወዘተ ላይ የተጻፉ ጽሑፎች ናቸው፡፡ የቀደሙ አባቶቻችን በብራና የጻፏቸው ጽሑፎች በየገዳማቱና አድባራቱ፣ በየአብያተ መጻሕፍቱ ይገኛሉ፡፡

ሌሎችም በጥንቃቄ ማነስና፣ በአያያዝ ጉድለት የተነሣ እየተበላሹ ይገኛሉ፡፡በተቻለ መጠን ተጠብቀው ለትውልድ እንዲተላለፉ ለማድረግ መዛግብቱ የያዙትን ነገር በየመልካቸው ማጥናትና መቀመር ያስፈልጋል፡፡

እነዚህን ጥንታዊ የሥነ ጽሑፍ ቅርሶች የሚያጠና የጥንታውያን ጽሑፎች ጥናት /Philology/ ትምህርት ክፍል በ1997 ዓ.ም በድኅረ ምረቃ ደረጃ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መከፈቱ ይታወሳል፡፡

<Philology> የግሪክ ቃል ሲሆን የጥንታውያን ጽሑፎች ጥናት ወይም ሥነ ቃላተ ልሳን ማለት ነው፡፡ የሚያጠናውም የጥንታውያን ጽሑፎችን ትክክለኛነት፣ የፊደላትን የአጻጻፍ ስልት፣ ይዘትን፣ ቋንቋን ፣ ሥነ ጽሑፍን፣ ማኅበራዊ ሳይንስን፣ ሥነ ልቡናን፣ ታሪክን ፣ መልክአ ምድርን፣ ሥነ ሕዝብን... ወዘተ ነው፡፡

በዓለም ላይ የጥንታውያን ጽሑፎች ጥናት /ሥነ ቃላተ ልሳን/ ዕንስ ሐሳብ የተጀመረው በሮማውያንና በግሪካውያን ዘንድ በ196 ዓመት ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ገደማ ሲሆን በወቅቱ ለድራማ፣ ለቀኖች ሒስ ለመስጠት ወዘተ ይጠቀሙበት ነበር፡፡

በአራተኛው መቶ ክ/ዘመን የነበረው ይኸው ጥናት ተስፋፍቶ በመካከለኛው ዘመን ከ1800 -1950 ዓ.ም ድረስ በዓለም ላይ በስፋት ይጠቀሙበት ነበር፡፡ ጥንታውያን የጽሑፍ ቅርሶች እንዲጠበቁ በማድረግ ከትውልድ ወደ ትውልድ ለማስተላለፍ፣ በዘመናዊ መልኩ እንዲጠበቁ በማስቻል ከፍተኛ አስተዋፅኦ አበርክቷል፡፡ ምክንያቱም መዛግብቱ በውስጣቸው የሚያስደንቁ የፍልስፍና፣ የታሪክ፣ የፖለቲካ፣ የጊዜውን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ እውነታዎች የሚያሳዩ ዕንስ ሐሳቦችን የያዙ ናቸው፡፡

የኢትዮጵያ ጥንታውያን ጸሑፎች ጥናት የተጀመረው በነገደ ሴማውያን ነው፡፡ የኢትዮጵያዊው መነኮስ አባ ጎርጎርዮስ የግእዝ ደቀ መዝሙር የሆነው ጀርመናዊው ኢዮብ ሉዶልፍ / Hiob Ludolf/ «በአውሮፓ የኢትዮጵያ የግእዝ ሥነ ጽሑፍ ጥናት መሥራች» በመባል ዕውቅና ተሰጥቶታል፡፡ ቢሆንም ያለ አባ ጎርጎርዮስ የቅርብ እገዛ የሉዶልፍ ተደናቂ ሥራዎች አልተጻፉም፡፡ /Hiob Ludolf's Lexicon Aethiopico-Latinum,1661).

የሥነ ልሳን ተመራማሪው /Linguist/ አገስት ዲልማን በ1850 ዓ.ም ገደማ የግእዝ ሰዋስው አጥንቶ አዘጋጅቶ ለኅትመት አብቅቷል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በ19ኛውና በ20ኛውመቶ ክፍለ ዘመን በጣሊያን ሀገር የኢትዮጵያን ቋንቋ ለማጥናት ብዙ ምሁራን ተነሥተዋል፡፡

የሕክምናና የተፈጥሮ ሳይንስ ተመራማሪ የነበረው ሉዶልፍ በኋላ የሥነ ጽሑፍ ዝንባሌው አመዝኖ የቋንቋ ተመራማሪ በመሆን ጥልቅ የግእዝ ሰዋስው መጽሐፍ ጽፎ ለአንባብያን አበርክቷል፡፡ ይህ ጽሑፍ ዛሬ ክሪችቶል በሚባል የቋንቋ ተመራማሪ <Truly Monumental Dictionary of Geez> በሚል ርእስ ወደ እንግሊዘኛ ተተርጉሞ በብሪትሽ ሙዚየም ይገኛል፡፡

የጥንታውያን ቋንቋዎች ጥናት ፍቅር ያደረበት ሉዶልፍ ከጀርመን ወደ ጣሊያን ሲጓዝ በጣሊያን የግእዙን ኢትዮጵያዊ ምሁር አባ ጎርጎርዮስን ያገኛል፡፡ ታዋቂነትን /ተደናቂነትን/ ለማግኘትና የቋንቋ ፍቅር ጥማቱን ለመወጣት ሲል ወደ ጣሊያን የሄደበትን ዋነኛ ጉዳይ ትቶ የግእዝ ቋንቋን ለማጥናት ጉጉት አደረበት፡፡ የግእዙን ፊደል፣ ግእዝ ንባብ፣ ውርድ ንባብ፣ ቁም ንባብ ከእነ ትርጉሙ ተምሮ መጻሕፍትን እያነበበ የግእዝ ዕውቀት አድማሱን አስፍቶ ብዙ መጻሕፍትን ለመጻፍ አስችሎታል፡፡

የኢትዮጵያ ታሪክ አድናቂዎችና አጥኚዎች ለኾኑ የውጭ ዜጎች የኢትዮጵያ ታሪክ፣ የነገሥታቱ ታሪክ መጻሕፍት የተጻፉት በግእዝ ቋንቋ ስለነበር፣ የግእዝ ቋንቋም በተለየ መልኩ ቀላል ስለኾነ ለማጥናትና ለማወቅ ብዙ ጊዜ አይወስድባቸውም ነበር፡፡ ለምሳሌ፡- ሉዶልፍ ከአባ ጎርጎርዮስ ከተማረ በኋላ ለሰላምታ በሚላላኩት ደብዳቤ በግእዝ ቋንቋ ይጻጻፉ እንደ ነበር መጻሕፍቱም ምሁራኑም ይመሰክራሉ፡፡ የኢትዮጰያና ጀርመን የጠበቀ ግንኙነት የተመሠረተውም ይኸው የግእዝ ቋንቋ ጥናት ዳበረው መልካም ግንኙነት በጣለው መሠረት ምክንያት ነው፡፡ ቋንቋ ሰውን ከሰው፣ሕዝብን ከሕዝብ፣ ሀገርንም ከሀገር ያዋሕዳል፣ ያገናኛልና፡፡

ኢትዮጵያዊው አባ ጎርጎርዮስ በ1588 ዓ.ም ደቡብ ወሎ ወረዒሉ ከተማ ተወለደ፡፡ በመካነ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪና የቅኔ መምህር ሆኖ ሲያገለግል በዐፄ ሱስንዮስ ዘመን ወደ ሮም ተጉዞ በጣሊያን ሀገር ሉዶልፍን የግእዝን ቋንቋ አስተምሯል፡፡ አንጋፋው የሥነ ልሳን ሊቅ ፕሮፌሰር ባዬ ይማም እንደ ሚሉት፡- «ሉዶልፍ በአውሮፓ የኢትዮጵያ ጥናት ጀማሪ መሆኑ ቢታወቅም ሉዶልፍን ደግሞ አባ ጎርጎርዮስ ቀድሞ በማስተማሩ የኢትዮጵያ ጥናት የተጀመረው በኢትዮጵያውያን ነው፡፡» ይላሉ፡፡

አባ ጎርጎርዮስ ለሉዶልፍ ከጻፈላት ደብዳቤ መግቢያ ለአብነት የሚከተለው ይገኝበታል፡፡ «ስጣዌ ክታብ ወሰላመ እሜኔ መንፈሳዊ እም አባ ጎርጎርዮስ ዘኢትዮጵያ ለዘጥቀ ፍቁር ዶም ኢዮብ ሉዶልፍ እኁየ በክርስቶስ፡፡ ሰላም ለከ ወሰላመ መስቀሉ ወሣህሉ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ምስለ ፍሥሐ ወጥዒና የሀሉ ዘልፈ ምስሌከ እንዘ ይናዝዘከ እም ዝኩ ሐዘን ወትካዝ በእንተ ተፈልጦትከ እምኔየ፤ ከኢትዮጵያዊው አባ ጎርጎርዮስ የተላከ መንፈሳዊ የሰላምታ ደብዳቤ፣ በፍጹም ለምወድህ በክርስቶስ ወንድሜ ለሆንኸ ዶም ኢዮብ ሉዶልፍ ከእኔ ስለ ተለየህ ከዚህ ሐዘንና ትካዜ እንድትጽናና ሰላም ላንተ ይሁን፤ የመስቀሉ ሰላም፣ የጌታችን የኢየሱስ




www.eotcmk.org

*ክርስቶስ ምሕረት ዘወትር ከአንተ ጋር ይሁን። »*

*አባ ጎርጎርዮስ ሰውና ሀገሩን ወዳድ በመሆኑ የሀገሩን ጥንታዊና ብሔራዊ ቋንቋ በፍቅር ለሉዶልፍ አስተምሯል። ሉዶልፍ ከተማረ በኋላ ቋንቋውን በደረሰበት ሥፍራ ሁሉ በደስታ ያስተምር ይጽፍ ነበር።*

*ሀገራችን ኢትዮጵያ በግእዝ ሥነ ጽሑፍ የካበተ ብዙ ሀብት ያላት በመሆኗ ወደፊት በተለይም በግእዝ ቋንቋ ዙሪያ በርካታ ጥናቶችን ማድረግ ግድ ይላል። በሀገራችን ያሉት ጥንታውያን ጽሑፎች ሁለት ዓይነት መሆናቸውን በአ.አ.ዩ የፊሎሎጂ ትምህርት ክፍል ሐላፊ የኾኑት ዶክተር ሞገስ ይገዙ እንዲህ በማለት ያስረዳሉ፦ «አንደኛው፦ በግእዝ ቋንቋችን የተጻፉ ጥንታውያን ጽሑፎች ሲሆኑ ሁለተኛው ደግሞ በጥንታዊው የዐረብኛ ቋንቋ የተጻፉት ናቸው። በኢትዮጵያ ደረጃ በጥንታውያን ጽሑፎች ረገድ በአመዛኙ ሀብታችን በግእዝ ቋንቋችን የተቀረሰው የሥነ ጽሑፍ ሀብት ነው። በዚህ ቋንቋ የሀገራችን እምነት፣ ፍልስፍና፣ ታሪክ፣ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ሁኔታ... ወዘተ በሰፊው ተዘግቦ ተቀምጧል። በመሆኑም በግእዝ ቋንቋ በተጻፉ መዛግብት ላይ ጥናትና ምርምር እናደርጋለን።» /ሐመር፣ 13ኛ ዓመት ቁጥር አንድ፣ ጥር - የካቲት 1997 ዓ ም/።*

*በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የፊሎሎጂ ትምህርት ክፍል ባለፈው ዓመት የመጀመሪያውን ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ጥንታውያን ጽሑፎች ጥናት ሲምፖዚየም አካሂዷል። በጥናታዊ ጉባኤው የቋንቋ፣ የሥነ ጽሑፍ እና የሥነ ቃላተ ልሳን ምሁራን በተገኙበት በርካታ ጥናቶች ቀርበው ነበር። በያዝነው ዓመት ደግሞ ከጥር 8-10 ቀን 1998 ዓ.ም ተመሳሳይና ከውጭ ሀገርም ከሀገር ውስጥም በርካታ ምሁራን የተገኙበት ሁለተኛው ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ጥንታውያን ጽሑፎች ጥናት ሲምፖዚየም /ጥናታዊ ጉባኤ/ ተካሂዷል። በጥናታዊ ጉባኤው በጥንታውያኑ የግእዝና የዐረብኛ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፎች ላይ የተመሠረቱ ጥናታዊ ጽሑፎች ቀርበው ነበር።*

*ከእነዚህም መካከል፦*

*የመጽሐፈ ቀሌምንጦስ ግልባጮች ይዘት ጥናት- በፕሮፌሰር አሌክሳንድሮ ባውዚ /ጣሊያን/*

*የሳባና ግእዝ ቋንቋዎች የድምፅ፣ የሰዋስውና ቅርፀ ፊደላት ዝምድና ንጽጽራዊ ጥናት -በመምህር አምሳሉ ተፈራ /አ.አ.ዩ/*

*የቅድስት ፍቅርተ ክርስቶስ /እማ ምዑዝ/ ተአምራትና መልክእ ጥናት - በዶ/ር ዴኒስ ኖስቲን /ሐምቡርግ ዩኒቨርስቲ/*

*የቅዱሳት መጻሕፍት ትርጓሜ ስልቶች - በአቶ ገዛኸኝ ጌታቸው /አ.አ.ዩ/*

*የብሉይ ኪዳን ዘዳግም ቀኖና መጻሕፍትና የሐዲስ ኪዳን ሥርዐት መጻሕፍት አመጣጥ ችግሮች - በፕሮፌሰር ፓውሎ ማራሲኒ /ፍሎሬንስ - ጣሊያን/*

*የግእዝ ፊደላት /ሀ፣ ሐ፣ ኀ፤ ሰ፣ ሠ፤ አ፣ ዐ፤ ፀ፣ ጸ/ ድምፆች መዋሐድ - በሽመልስ ማዘንጊያ /አ.አ.ዩ/*

*የሚሉት ይገኙባቸዋል። የጥናቶቹን ዝርዝር ይዘት ወደፊት እንደ አስፈላጊነታቸው ለመዳሰስ እንሞክራለን። በዚህ እትማችን ግን በአውሮፓ የኢትዮጵያ ግእዝ ሥነ ጽሑፍ ጥናትን፣ የግእዝ ቋንቋንና ሌሎች ተጓዳኝ ርእሰ ጉዳዮችን በተመለከተ በጣሊያን - ፍሎረንስ ዩኒቨርስቲ የግእዝ ሥነ ጽሑፍን በሴማዊ ሥነ ቃላተ ልሳን /Semitic Philology/ና በደቡብ ዐረቢያ ቋንቋዎች ጠገግ በስፋት በማጥናት ከሚታወቁት የ63 ዓመቱ ጣሊያናዊ ምሁር ፕሮፌሰር ፓውሎ ማራሲኒ ጋር ዲ/ን ቸሬ አበበ እና ዲ/ን ደረጀ ጅማ ያደረጉትን ቆይታ እንደ ሚከተለው አጠናቅረን አቅርበንላችኋል። የ«አቡጊዳ - ግእዝ ቋንቋ ትምህርት» ዓምደኞችንና በአ.አ.ዩ የሥነ ቃላተ ልሳን ትምህርት ክፍል የመጨረሻ ዓመት የድኅረ ምረቃ ተማሪ የኾነው መምህር ደሳለኝ ቀለብ ለዝግጅታችን መሳካት ስላደረገልን ትብብር በአንባብያን ስም እናመሰግነዋለን።*

## *የኢትዮጵያ ጥናት በጣልያን*

ኢትዮጵያን ማጥናት የጀመርኩት ገና የ17 ዓመት ወጣት ሳለሁ ነው። እንግሊዝ በሚገኘው የማንቸስተር ዩኒቨርሲቲ ስማር ፕሮፌሰር ኤኔሪኮ ቼሩሊ የተባለ ሰው ግእዝን እንዳጠና ዕድልና ፈቃድ ሰጠኝ። ግእዝን በማጠናበት ወቅት በጊዜው በማንቸስተር ዩኒቨርሲቲ ያስተምር የነበረው ፖላንዳዊው ስቴፈን ስቴልሲን ለአንድ ዓመት ተኩል አማካሪዬ ነበር። የግእዝ ቋንቋ እና የኢትዮጵያ ሥነ ቃላተ ልሳን አስተማሪዬ እርሱ ነበር። የግእዝ ቋንቋ በጣም ከባድ አይደለም። ጥናቱን ራስህ ልትጀምረው ትችላለህ።

ወደ ጣልያን ከተመለስኩ በኋላ በፒዛ ዩኒቨርስቲ የዕብራይስጥን ቋንቋ ለአንድ ዓመት፣ የሴማውያንን ሥነ ቃላተ ልሳን ደግሞ ለአንድ ዓመት አስተምሬያለሁ። ከዚያ በኋላ ወደ ተወለድኩባትና እየተማርኩ ወደ አደግኹባት ፍሎረንስ ሔድኩ። በዚያም የኢትዮጵያ ቋንቋና የግእዝ ሥነ ጽሑፍ ተባባሪ ፕሮፌሰር ሆኜ ሠራሁ። ሙሉ ፕሮፌሰር ከኾንኩ በኋላ ግእዝን ለማስተማር ወደ ኔፕልስ ሔድኩ። ከአራት ዓመታት በኋላ ይህንኑ ትምህርት /ግእዝን/ ለማስተማር ወደ ፍሎረንስ መጣሁ። እዚያ በማስተምርበት ጊዜ ብዙ ጎበዝ ተማሪዎች ነበሩኝ። ለምሳሌ፦ አሌክሳንድሮ ባውዚን ብንወስድ በአሁኑ ወቅት በኔፕልስ ዩኒቨርሲቲ የግእዝ ቋንቋ ተባባሪ ፕሮፌሰር ነው። እንዲሁም በፍሎረንስ የሚኖረውና የሚያስተምረው አሌክሳንድሮ ጎሪ በኢትዮጵያ ውስጥ ስለሚገኙ ሙስሊሞች ምርጥ ባለሞያ ነው። ሌላው ደግሞ ቤሉጂ ቤዋኔሊ ሲሆን እርሱም በካናዳ ኩቤክ ዩኒቨርሲቲ መምህርና የአዋልድ መጻሕፍት /Apocrypha Literatures/ ባለሞያ ነው። ሌላው ዶ/ር ሉዚኒ ነው። በዘመነ አክሱም ጽሑፎችና በሌሎች ተዛማጅ መስኮች ባለሞያ ሲሆን በኔፕልስ ያስተምራል። እነዚህ ሁሉ ቀደም ሲል ያስተማርኳቸው ተማሪዎቼ ናቸው። በጣልያን ለሚካሄደው የኢትዮጵያ ጥናት ሕይወት የሰጡት እኒህ ምሁራን መሆናቸውን መግለጽ እፈልጋለሁ። ምክንያቱም እነዚህ ከመነሣታቸው በፊት በጣልያን የነበረው የኢትዮጵያ ጥናት እየተዳከመ ነበር። ቼሩሊም በወጣትነቴ በእንግሊዝ ሳለሁ ግእዝን እንዳጠና ጥቁምታ የሰጠኝ በዚህ ምክንያት ነው፤ ለምን ብትል በዚያ ወቅት የነበረው የኢትዮጵያ ጥናት ተዘግቶ ነበርና። ቼሩሊ ይህን ያደረገው ለኢትዮጵያ ያለው ፍቅር እጅግ ልዩ ስለነበረ ነው። ይሁን እንጂ በዚያን ወቅት የዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰር ሳይሆን አምባሳደር ነበር።

ሌላው የአዲግራት ተወላጅ የሆነውና በአሁኑ ወቅት እኛ ጋር አማርኛ የሚያስተምረውን ፕሮፌሰር ያዕቆብ በየነን ልጥቀስላችሁ። እጅግ በጣም ጥሩ ሰውና ምሁር ነው። ነገር ግን በግእዝ የተመረቀ አንድም ተማሪ የለውም። ስለዚህ ዛሬ በጣልያን ያለው የኢትዮጵያ ጥናት ዘላቂነት ያገኘው ቀደም ሲል ብዙም ስመ ጥር ባልነበረው በፍሎረንስ የኢትያጵያ ጥናት ማእከል አማካይነት ነው። ይህ ማእከል በጣልያን ላለው የኢትዮጵያ ጥናት ልዩ ጥንካሬን ሰጥቶታል።

ወጣት ሳለሁ ከፍሎረንስ ወደ ኔፕልስ እየሔድኩ አስተምር ነበር። ከፍሎረንስ ወደ ኔፕልስ ሔዶ ለማስተማር በየሳምንቱ ጉዞ ማድረግን እንደ ሚጠይቅ አስቡ። አሁንም ፕሮፌሰር ባውዚ በየሳምንቱ ከኔፕልስ ወደ ፍሎረንስ ይሔዳል። በዚያም ለአምስት ሰዓታት ያስተምራል። በኔፕልስ አምስት በፍሎረንስ አምስት ሰዓታት ማስተማር በጣም ብዙ ሲሆን ትጋትን ጭምር ይጠይቃል። ሥራው አድካሚ ነው። ይህ ሁሉ ድካም ግን በጣልያን ያለውን የኢትዮጵያ ጥናት መልሶ ለማቋቋም ነው።

ለዚህ የኢትዮጵያ ጥናት ቀጣይነት በኔፕልስ የሚያስተምረው ባውዚ እና በፍሎረንስ ደግሞ የማስተምረው እኔ ብዙ ወጣት ተማሪዎች አሉን። ምክንያቱም ግእዝን አስመልክቶ የሚደረገው ቀጣይ ታሪካዊ የሥነ ቃላተ ልሳን ጥናት በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ጥናት ነውና።



www.eotcmk.org

## «ኢትዮጵያ ምስጢራዊት አገር ነች»

በኢትዮጵያ ጥናት ወይም ሥነ ቃላተ ልሳን ላይ እንዳተኩር ፍላጎት ያሳደረብኝን ነገር በርግጠኝነት አላውቀውም፤ ሁል ጊዜ ምክንያታዊ ምርጫ ላታደርግ ትችላለህ:: ይህም የሚሆነው ቀደም ሲል ግልጽ ባልሆነ መንገድ በነገሩ ስትማረክ ነው:: ጥናቴን የጀመርኩት በሴማውያን ንጽጽራዊ ሥነ ቋንቋ ላይ ነው:: ያን ጊዜ ነው በሴማውያን ጥናት ዝነኛ ፕሮፌሰር የሆነውና በሮሌ ኮሌጅ ያስተምር የነበረው አለቃዬ:- *«ለምን ከሴማውያን ቋንቋዎች አንዱ በሆነው በግእዝ ላይ ትኩረት አታደርግም»* ሲል የመከረኝ:: ምክሩ ትክክል ነበር:: ምክንያቱም እንደ ነገርኩህ በዚያን ወቅት በኢጣሊያ ያለው የኢትዮጵያ ጥናት እየሞተ ነበር:: ስለዚህ *«ለምን ይህን ጥናት ጀምረህ እንዲያንሰራራ አታደርገውም?»* አለኝ:: ወዲያውኑ ፕሮፌሰር ኤኔሪኮ ቼሩሊ መጣ:: ዕድሉንም ሰጠኝ::

ስለዚህ በኢትዮጵያ ጥናት ወይም ሥነ ቃላተ ልሳን ላይ እንዳተኩር ያደረገኝ በሮሌ ኮሌጅ ያስተምር የነበረው ፕሮፌሰርና የቀድሞው መምህሬ ምርጫ ይመስለኛል:: በራሴም በኩል ቢሆን ኢትዮጵያን አስመልክቶ ትንሽ ፍላጎት ነበረኝ፤ ምክንያቱም ኢትዮጵያ ምስጢራዊት አገር ነችና:: በዐድዋ ጦርነት በጣሊያኖች ላይ ያገኘችው ድልና በኋላም ፋሽስቶች በእርሷ ላይ የፈጸሙት ጥቃትና ወረራ የሚታወስ ነበር:: ይህን የፋሽስቶች ወረራ ሙሉ በሙሉ የምቃወም መሆኔን ልታውቁ ይገባል:: ምክንያቱም ቀደምቶቼ የነበሩት ሪቼ እና ፋዜላ ሙሉ በሙሉ ፋሺስቶች ነበሩ:: ከእነርሱ በዚህ እለያለሁ:: እንዲሁም ሙሉ ለሙሉ ፋሺስት ነው ብዬ ለመናገር ባልደፍርም ቼሩሊ ራሱ በአንድ ወቅት በፋሺስት ፓርቲ ውስጥ ተሳትፎ አድርጓል:: ይህ መገለጽ አለበት:: በአጭሩ በሕግ፣ በሥነ ጽሑፍና በመካከለኛው ዘመን ታሪክ ላይ እንደ ሚደረጉና አዘውትረው እንደ ሚታዩ አመ ክንዮአዊ ምርጫዎች አይደለም እኔ በኢትዮጵያ ጥናት ወይም ሥነ ልሳን ላይ ለማተኮር የወሰድኩት ምርጫ::

## የግእዝ ቋንቋ ትምህርት በአውሮፓ

በአሁኑ ወቅት እዚህ እንዳሉት ብዙም ባይሆኑ ጥቂት ተማሪዎች አሉን:: እኔ 10 የሚሆኑ በፍሎረንስ፣ ሌሎች 10 ደግሞ በኔፕልስ በአጠቃላይ ኻያ የሚሆኑ የግእዝ ተማሪዎች አሉኝ::

*ማወቅ ያለባችሁ ነገር በጣሊያን በግእዝ ቋንቋ የሚሠለጥኑ ተማሪዎች በጣም ጥቂት መሆናቸውን ነው:: ልክ በጣሊያን ላቲንን የሚያጠኑ ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች ቁጥር ጥቂት እንደ ሆነ::*


በአውሮፓ ውስጥ ግእዝ በይፋ የሚሰጠባቸው ቦታዎች ፍሎረንስና ኔፕልስ ናቸው፡ ሐምቡርግም ይሰጣል:: ለንደንና ፓሪስ አስተማሪ በመጥፋቱ ተቋርጧል:: አሁን የቀሩት በጣልያንና ጀርመን ያሉ ትምህርት ቤቶች ናቸው:: ከነዚህም ይፋዊ የሆነ የግእዝ ትምህርት የሚሰጠው ጣልያን ውስጥ በሚ ገኙት ፍሎረንስና ኔፕልስ ከተሞች ነው::

## «በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ የብራና ጽሑፎች በዝርዝር ሁኔታ አልተደራጁም»

እርግጥ ስለ ኢትዮጵያ ጥንታዊ ጽሑፎች በኢትዮጵያ ውስጥ ጥናት ማካሔድ ጠቃሚ እንደ ሆነ መታመን አለበት:: እንዲሁም አንድ ሰው በኢትዮጵያ ውስጥ ሆኖ ስለ ኢትዮጵያም ሆነ ስለ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጥናት ቢያደርግ የቤተ ክርስቲያኒቱን አማናዊ ሕይወት ለማወቅ ስለ ሚረዳው ጠቀሜታው የጎላ ነው:: ይሁን እንጂ እንደዚህ ዐይነቱን ጥናት በአውሮፓም ሆነህ ልትጀምረው ትችላለህ፤ ምክንያቱም ብዙ ጥንታዊ የብራና ጽሑፎች በአውሮፓ አሏችሁና:: ዋናውን ማይክሮፊልምም ማግኘት ይቻላል:: በእርግጥ እዚያ ካሉት የበለጡ የብራና ጽሑፎች ዛሬም ድረስ በኢትዮጵያ ውስጥ ይገኛሉ:: ነገር ግን አብዛኞዎቹ እስከ አሁን ድረስ በዝርዝር ሁኔታ አልተደራጁም:: ስለዚህ እነዚህን ጥንታዊ ጽሑፎች /ሀብታት/ ልታደራጇቸው ትችላላችሁ::

በዝርዝር ሁኔታ ካለመደራጀታቸውና በተለያዩ ምክንያቶች የተነሣ እነዚህ ልዩ ልዩ ስብስቦች ብዛታቸውና ጠቀሜታቸው እስከ አሁን ድረስ አልታወቀም:: በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉትን አብዛኞዎቹን ገዳማት ስለ ምታውቋቸው የምላችሁ ነገር እንግዳ አይሆንባችሁም::

*በ «EMML» ቤተ መጻሕፍት ዝርዝር ማውጫ አለ:: ነገር ግን ከ10,000 የበለጠ አይደለም:: ይህም በኢትዮጵያ ውስጥ በእውነት ከሚገኙት ጥንታዊ የብራና ጽሑፎች ጋር ሲነጻጸር በጣም ትንሽ ነው:: ይሁን እንጂ በአውሮፓ ሆነህ የኢትዮጵያን ጥናት በመልካም ሁኔታ መጀመር ትችላለህ::*



*ኢትዮጵያን ማጥናት የጀመርኩት ገና የ17 ዓመት ወጣት ሳለሁ ነበር::*

እዚህ መምጣት ፍላጎትህ ጥልቅ እንዲሆን ይረዳሃል:: የጥናት አድማስህን ሰፋ ለማድረግና ለመሥራት ያስችልሃል:: ነገር ግን በዘርፉ አእምሮአዊና ሒሳዊ ሞያ ረገድ በአውሮፓ በጥሩ ሁኔታ ይሠራበታል:: ይሁንና በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የተለያዩ ቤተ ጉባኤያትን ዘይቤዎች፣ ይትበሃሎችንና ልዩ ልዩ አስተሳሰቦችን ማወቅ በጣም አስፈላጊ ነገር ስለሆነ ጥናቱ በኢትዮጵያ ውስጥ ቢካሔድ ተመራጭ ነው::

## «ከጥንታዊ ጽሑፎቻችሁ እየተጠቀማችሁ አይደላችሁም»

እንደ ነገርኳችሁ እዚህ ብዙ ጽሑፎች አሏችሁ:: በቀላሉ ግን ልታገኟቸው አትችሉም:: ምክንያቱም በግድ ወደ ገዳም መሔድ አለባችሁና:: ሌላም ችግር አለ:: ጽሑፎቹን በቀጥታ ለማየት ችግር አለ:: ወደ ሌላ ገዳም ለመሔድ ብትፈልግ መልካም እንቅልፍ የምታገኝበት ሁኔታ የለም:: ከገዳም ወደ ገዳም መዘዋወርም ሌላ አድካሚ ነገር ነው:: ስለዚህ አንድ ላይ እስክታሰባስቧቸው ድረስ በማይክሮ ፊልም አሰባስባችሁ ልትጠቀሙ ትችላላችሁ:: እርግጥ በጣም ውድ ነው:: ነገር ግን በጣም ይጠቅማል::

*የኢትዮጵያ ጥንታዊ ጽሑፎች በሙሉ በተለያዩ ገዳማት ይኖራሉ:: ነገር ግን ወደ ገዳማት በሔዳችሁ ቁጥር እነዚህን ጽሑፎች በማይክሮ ፊልም እያደረጋችሁ ማይክሮፊልሙን አንድ ቦታ ብታስቀምጡ ይበጃል::*

ያንጊዜ ማንኛውም አውሮፓዊ ምሁር ኢትዮጵያ ሲመጣ ሊያያቸው ይችላል:: በማይክሮ ፊልም ይዞ ወደ አገሩ መሔድ ከፈለገም ኢትዮጵያ ካለው ማይክሮ ፊልም ላይ ገልብጦ መስጠት ይቻላል:: ይህ በቫቲካን ቤተ መጻሕፍት ይሠራበታል:: ሁሉም ጥንታዊ ጽሑፎቻቸው በማይክሮ ፊልም ተዘጋጅተው የተቀመጡ ናቸው:: ለምሳሌ:- የአንድን መጽሐፍ ማይክሮ ፊልም ብትፈልግ እንደዚህ ብለህ ለቤተ መጻሕፍቱ ልትጽፍ ትችላለህ:- *«ቤተ መጻሕፍታችሁ ውስጥ የተማረኩበት /የምፈልገው/ ጥንታዊ ጽሑፍ ስላለ የእርሱን ማይክሮ ፊልም እፈልጋለሁ::»* በአንድ ወይም በሁለት ቢበዛ በሦስት ሳምንት ውስጥ የመጽሐፉን ማይክሮ ፊልም ይሰጡሃል::

በኢትዮጵያ ውስጥ ያሏችሁን በርካታ የጽሑፍ ሀብታት ማእከላዊ በሆነ ተቋም ውስጥ ማግኘት መቻል ሊሰጥ ማችለውን ጠቀሜታ ልትገምቱ ትችላላችሁ:: ለጊዜው ሰፊው ሕዝብም ሆነ እናንተ ከነዚህ ጽሑፎች እየተጠቀማችሁ አይደላችሁም:: ምክንያቱም አንድን ጥንታዊ ጽሑፍ ለማጥናት ወይም ለማግኘት ትግራይ ውስጥ ከሚገኝ ገዳም ወደ ላሊበላ ከዚያም ወደ ሌላ ቦታ መሔድ ይከብዳልና::

ይቆየን::

ወስብሐት ለእግዚአብሔር



www.eotcmk.org

የሐመር መጽሔት ዝግጅት ክፍል የግእዝ ቋንቋ ያለውን የማይተካ ዘርፈ ብዙ ሚና በማጤንና የአንባብያንን ፍላጎት መሠረት በማድረግ ይህን «አቡጊዳ - የግእዝ ቋንቋ ትምህርት» የተሰኘ ዓምድ ከ1994 ዓ.ም. ጀምሮ መክፈቱ ይታወሳል። በዓምዱ የሚቀርበው ትምህርት በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መምህራንና ተማሪዎች በሚያዝያ ወር 1997 ዓ.ም በተቋቋመው «የልሳነ ግእዝ ወዳጆች ማኅበር» የሚዘጋጅ ነው። ማኅበሩ ለግእዝ ቋንቋ ፍላጎት ያላቸውን ሁሉ በቋንቋው ማንበብ፣ መጻፍና መናገር የማስቻል፣ በቋንቋው የተጻፉትን ዕድሜ ጠገብ መጻሕፍት በመመርመር ያካበቱትን ልዩ ልዩ ሀብት ለትውልድ የማቆየት ዓላማና ግብ አንግቦ የተነሣ ነው።

*ውድ አንባብያን ባለፈው የ13ኛ ዓመት ቁጥር አምስት መስከረም/ጥቅምት 1998 ዓ.ም እትም ትምህርታችን የግስ ለውጥ ሂደትን በግስ አርእስት መሠረትነት ሕጋውያን አንቀጾች ከሓላፊ /ቀዳማይ/ ወደ ካልአይ /የአሁን እና መጻኢ/ ዘንድ፣ ትእዛዝ እና ንኡስ አንቀጽ እንዴት በዐሥሩ መራሕያን እንደ ሚረቡ ተመልክተናል። ዛሬ ደግሞ የግሶችን ሂደት በሁለተኛው ዐቢይ አንቀጽ /በካልአይ አንቀጽ/ በዝርዝር እንማራለን። ትምህርቱ ለተከታታይ ሦስት እትሞች ተቋርጦ በመቆየቱ ከፍ ያለ ይቅርታ እንጠይቃለን። ትምህርቱ የቆመበትን እትም ከዚህ እትም ክፍለ ትምህርት ጋር በማገናዘብ መማማራችንን እንድንቀጥል እናሳስባለን።*

*/መምህር ደሳለኝ ቀለብ/*

*2. ካልአይ /ሁለተኛ/ አንቀጽ፡- ይህ አንቀጽ የአሁን /Present/ እና የመጻኢ /Future/ አንቀጾችን የጊዜ ለውጥ ሂደትን ይይዛል። ለዚህም ከአማርኛ የግስ እርባታ ጋር እያገናኘን እንመለከታለን።*

## የአማርኛ የግስ እርባታ መንገድ

| ንኡስ አንቀጽ | ሓላፊ /ቀዳማይ/ | ካልአይ | ሣልሳይ | |
|---|---|---|---|---|
| 1. መብላት | በላ | ይበላል | ይብላ | ይበላ ዘንድ |
| 2. መናገር | ተናገረ | ይናገራል | ይናገር | ይናገር ዘንድ |
| 3. መዋሸት | ዋሸ | ይዋሻል | ይዋሽ | ይዋሽ ዘንድ |
| 4. መሞት | ሞተ | ይሞታል | ይሙት | ይሞት ዘንድ |
| 5. መርገጥ | ረገጠ | ይረግጣል | ይርገጥ | ይረገጥ ዘንድ |
| 6. መቀመጥ | ተቀመጠ | ይቀመጣል | ይቀመጥ | ይቀመጥ ዘንድ |
| 7. መሄድ | ሄደ | ይሄዳል | ይሂድ | ይሄድ ዘንድ |
| 8. ማስተባበር | አስተባበረ | ያስተባብራል | ያስተባብር | ያስተባብር ዘንድ |

እዚህ ላይ፡- በላ፣ ተናገረ፣ ዋሸ፣ ሞተ፣ ጠረገ፣ ተቀመጠ፣ ሄደ፣ አስተባበረ ለአማርኛው የሕጋውያን ግሶች /Regular verbs/ ቤት አርእስት ናቸው። ስለሆነም የሚከተሉት ግሶች ቤቶች እነማን እንደ ሆኑ ለመለየት እንሞክራለን።

| ሓላፊ | ቤቱ | ካልአይ | ትእዛዝ/ ዘንድ | ንኡስ አንቀጽ |
|---|---|---|---|---|
| ቀዳ | በላ | ይቀዳል | ይቅዳ/ይቀዳ ዘንድ | መቅዳት |
| ተዋረደ | ተናገረ | ይናገራል | ይናገር/ይናገር ዘንድ | መናገር |
| ዋኘ | ዋኘ | ይዋኛል | ይዋኝ/ይዋኝ ዘንድ | መዋኘት |
| ጮኸ | ሞተ | ይጮኻል | ይጩኽ/ይጮኽ ዘንድ | መጮኽ |
| ወደቀ | ረገጠ | ይወድቃል | ይውደቅ/ይወድቅ ዘንድ | መውደቅ |
| ተከደነ | ተቀመጠ | ይከድናል | ይክደን/ይከድን ዘንድ | መክደን |
| አስተናገደ | አስተባበረ | ያስተባብራል | ያስተባብር/ያስተባብር ዘንድ | ማስተባበር |

## የግእዝ ግስ እርባታ መንገድ

| ሓላፊ | ካልአይ | ትእዛዝ/ ዘንድ | ንኡስ አንቀጽ |
|---|---|---|---|
| ቆመ-ቆመ | ይቀውም-ይቆማል | ይቁም-ይቆም ዘንድ /ይቁም | ቀዊም/ቀዊሞት |
| ሤመ/ሾመ/ | ይሠይም | ይሢም | ሠዩም/ሠዩሞት |
| ቀተለ /ገደለ/ | ይቀትል | ይቅትል | ቀቲል/ቀቲሎት |
| ባረከ/ባረከ/ | ይባርክ | ይባርክ | ባርኮ/ባርኮት |
| ደንገፀ/ደነገጠ/ | ይደነግፅ | ይደንግፅ | ደንግፆ /ደንግፆት |
| ማህረከ/ማረከ/ | ይማህርክ | ይማህርክ | ማህርኮ/ማህርኮት |
| ብህለ /አለ/ | ይብህል | ይብሃል | ብሂል/ብሂሎት |
| ገብረ/ሠራ/ይገብር | ይገብር | ይግበር | ገቢር /ገቢሮት |
| ዴገነ/ተከተለ/ | ይዴግን | ይዴግን | ዴግኖ/ዴግኖት |
| ኖለወ/ጠበቀ/ | ይኖሉ | ይኖሉ | ኖልዎ/ኖልዎት |
| ቀደሰ/አመሰገነ | ይቄድስ | ይቀድስ | ቀድሶ/ቀድሶት |

### አንዳንድ የአማርኛውና የግእዙ አርእስት ሂደት ተመሳሳይነት

| ሓላፊ | ትእዛዝ | ሓላፊ | ትእዛዝ |
|---|---|---|---|
| ቆመ | ይቁም | ሞተ | ይሙት |
| ሤሜ | ይሢም | ሔደ | ይሒድ |



www.eotcmk.org

## አቡጊዳ –የግእዝ ቋንቋ ትምህርት

የሚከተሉት ግሶች እንዴት ወደ ካልአይ ይለወጣሉ:: ይህም የሚታወቀው በቤት ነው::

| ሓላፊ | ቤቱ | ካልአይ |
|---|---|---|
| ሞተ | ቆመ | ይመውት |
| ጌሠ | ሤመ | ይገይስ |
| ነጸረ | ቀደሰ | ይኔጽር |
| ተንበለ | ደንገፀ | ይተነብል |

### ካልአይን በዐሥሩ መራሕያን

1. ሰገደ-ሰገደ- ቤቱ ቀተለ

| | | |
|---|---|---|
| አነ-እሰግድ | እኔ- እሰግዳለሁ | እቀትል- እገድላለሁ |
| አንተ-ትሰግድ | አንተ- ትሰግዳለህ | ትቀትል-ትገድላለህ |
| አንቲ-ትሰግዲ | አንቺ- ትሰግጃለሽ | ትቀትሊ-ትገድሊያለሽ |
| አንትሙ- ትሰግዱ | እናንተ- ትሰግዳላችሁ | ትቀትሉ- ትገድላላችሁ |
| አንትን- ትሰግዳ | እናንተ- ትሰግዳላችሁ | ትቀትላ- ትገድላላችሁ |
| ንሕነ- ንሰግድ | እኛ- እንሰግዳለን | ንቀትል- እንገድላለን |
| ውእቱ- ይሰግድ | እርሱ - ይሰግዳል | ይቀትል- ይገድላል |
| ይእቲ- ትሰግድ | እርሷ- ትሰግዳለች | ትቀትል- ትገድላለች |
| ውእቶሙ- ይሰግዱ | እነርሱ - ይሰግዳሉ | ይቀትሉ- ይገድላሉ |
| ውእቶን- ይሰግዳ | እነርሱ - ይሰግዳሉ | ይቀትላ- ይገድላሉ |

2. ኖመ = ተኛ - ቤቱ - ቆመ

| | | |
|---|---|---|
| አነ- እነውም | - እተኛለሁ | እቀውም- እቆማለሁ |
| አንተ- ትነውም | - ትተኛለህ | ትቀውም- ትቆማለህ |
| አንቲ- ትነውሚ | - ትተኛለሽ | ትቀውሚ- ትቆሚያለሽ |
| አንትሙ- ትነውሙ | - ትተኛላችሁ | ትቀውሙ- ትቆማላችሁ |
| አንትን- ትነውማ | - ትተኛላችሁ | ትቀውማ- ትቆማላችሁ |
| ንሕነ- ንነውም | - እንተኛለን | ንቀውም- እንቆማለን |
| ውእቱ- ይነውም | - ይተኛል | ይቀውም- ይቆማል |
| ይእቲ- ትነውም | - ትተኛለች | ትቀውም- ትቆማለች |
| ውእቱሙ- ይነውሙ | - ይተኛሉ | ይቀውሙ- ይቆማሉ |
| ውእቶን- ይነውማ | - ይተኛሉ | ይቀውማ- ይቆማሉ |

3. መጽአ=መጣ ቤቱ- ገብረ /ሠራ/

| | | |
|---|---|---|
| እነ- እመጽእ- እመጣለሁ | I/will/ come | እገብር- እሠራለሁ |
| እንተ- ትመጽእ- ትመጣለህ | You/will/ come | ትገብር- ትሠራለህ |
| እንቲ- ትመጽኢ- ትመጫለሽ | You/will/ come | ትገብሪ- ትሠሪያለሽ |
| አንትሙ- ትመጽኡ- ትመጣላችሁ | You/will/ come | ትገብሩ- ትሠራላችሁ |
| አንትን- ትመጽአ- ትመጣላችሁ | You/will/ come | ትገብራ- ትሠራላችሁ |
| ንሕነ- ንመጽእ- እንመጣለን | We/will/ come | ንገብር- እንሠራለን |
| ውእቱ- ይመጽእ- ይመጣል | He/will/ come/s/ | ይገብር- ይሠራል |
| ይእቲ- ትመጽእ- ትመጣለች | She/will/ come/s/ | ትገብር- ትሠራለች |
| ውእቶሙ - ይመጽኡ -ይመጣሉ | They/will/ come | ይገብሩ- ይሠራሉ |
| ውእቶን- ይመጽአ- ይመጣሉ | They /will/ come | ይገብራ - ይሠራሉ |

4.ቀደሰ = አመሰገነ- ቤቱ - ቀደሰ

| | | |
|---|---|---|
| አነ- እቄድስ- አመሰግናለሁ | I/will/ Praise | /እቄድስ/ |
| አንተ- ትቄድስ- ታመሰግናለህ | You /will/ Praise | /ትቄድስ/ |
| አንቲ- ትቄድሲ- ታመሰግኛለሽ | You /will/ Praise | /ትቄድሲ/ |
| አንትሙ- ትቄድሱ- ታመሰግናላችሁ | You /will/ Praise | /ትቄድሱ/ |
| አንተን- ትቄድሳ- ታመሰግናላችሁ | You /will/ Praise | /ትቄድሳ/ |
| ንሕነ- ንቄድስ- እናመሰግናለን | We /will/ Praise | /ንቄድስ/ |
| ውእቱ- ይቄድስ-ያመሰግናል | He /will/ Praise | /ይቄድስ/ |
| ይእቲ- ትቄድስ- ታመሰግናለች | She /will/ Praise | /ትቄድስ/ |
| ውእቶሙ- ይቄድሱ- ያመሰግናሉ | They /will/ Praise | /ይቄድሱ/ |
| ውእቶን- ይቄድሳ- ያመሰግናሉ | They /will/ Praise | /ይቄድሳ/ |

5. ደንገፀ - ፈራ ቤቱ - ደንገፀ

አነ - እደነግፅ - እፈራለሁ

አንተ - ትደነግፅ - ትፈራለህ

አንቲ - ትደነግፂ - ትፈሪያለሽ

አንትሙ - ትደነግፁ - ትፈራላችሁ

አንትን - ትደነግፃ - ትፈራላችሁ

## ነገረ ድኅነት ...

/ከገጽ ፲፪ የዞረ/

አጥምቁ::» ትላለች:: ማቴ.28÷19-20::

- «አነ ወአብ አሐዱ ንህነ፤ እኔና አብ አንድ ነን ማለት በመለኮት፣ በህልውና፣ በእግዚአብሔርነት፣ በሥልጣን፣ በአገዛዝ አንድ ነን::» እንዳለ:: ዮሐ.10÷30::

አንድም ከአብ የሚወጣ፣ የአብና የወልድ የባሕርይ ሕይወታቸው እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም ከአብና ከወልድ ጋር እነርሱ አንድ በሚሆኑበት ነገር ሁሉ አንድ ነው:: /ዮሐ.15÷26/ በማለት ከመዝሙረ ዳዊት ጋር ትገናዘባለችና::

ለ- ዳዊት የወልድን ቀዳማዊነት፣ ሥጋ መሆኑን፣ ሕማሙንና ሞቱን፣ ትንሣኤውን ዕርገቱንና ዳግም ምጽአቱን ይናገራል:: መዝ.109÷3፤ መዝ.86÷5፤ መዝ.21÷16-19፤ መዝ.67÷19፤ መዝ.46÷5 ፤ መዝ. 49÷2:: ወንጌልም ይህን ሁሉ ትናገራለች::

ሐ. ዳዊት የነቢያትን፣ የሐዋርያትን፣ የሰማዕታትን፣ የመነኮሳትን፣ የመላእክትን ነገር ይናገራል:: ወንጌልም ይህን ሁሉ ትናገራለች::

መ. ዳዊት ጠላትን ስለ መውደድ ይናገራል፤ ወንጌልም ትናገራለች::

ሠ. ዳዊት የትሕትናን ነገር:- «አንሰ እዜ ወአኮ ሰብእ፤ እኔ ግን ትል ነኝ ሰውም አይደለሁም» እያለ ይናገራል:: መዝ.216:: ወንጌልም «ራሱን ዝቅ የሚያደርግ ከፍይላል» ትላለች:: ሉቃ.18÷14::

ረ. ዳዊት «በተነ፣ ለምስኪኖችም ሰጠ» እያለ የምጽዋትን ነገር ይናገራል:: ወንጌልም :- «ፍጹም ልትሆን ብትወድ ያለህን ሽጥ፣ ለምስኪኖችም ስጥ» ትላለች::

ሰ. ዳዊት «ከክፉ ሽሽ መልካምም አድርግ» ይላል:: ወንጌልም «ክፉውን በክፉ አትቃወም» ትላለች:: መስቀል ይዞ መስበኩ ነቢያት ለአዳም የተሰጠውን ተስፋ በጊዜአቸው ለመናገራቸው አምሳል ነው:: ምስባክ ዲያቆኑ ሁለት ጊዜ በመደጋገም ያዜመውን ያንኑ ቃል ሕዝቡ ሦስት ጊዜ በመደጋገም የሚያዜሙት በጥቅሉ አምስት ጊዜ ይሆናል:: ይህም አምስት ጊዜ መባሉ አምስት ሺህ ካምስት መቶ ዘመን ትንቢት ለመነገሩ ምሳሌ ነው:: በስድስተኛው ቄሱ ወንጌል ማለቱ በስድስተኛው ሺ ጌታ ከቅድስት ድንግል ማርያም ሰው ሆኖ ተወልዶ ወንጌልን ለማስተማሩ አምሳል ነው::

ዲያቆኑ ከአዳም እስከ ዮሐንስ መጥምቅ ያሉ ነቢያት ምሳሌ፣ ቄሱ የጌታ ምሳሌ ናቸው::

ይቆየን::

ወስብሐት ለእግዚአብሔር



www.eotcmk.org

ንሕነ - ንደነግፅ - እንፈራለን
ውእቱ - ይደነግፅ - ይፈራል
ይእቲ - ትደነግፅ - ትፈራለች
ውእቶሙ- ይደነግፁ - ይፈራሉ
ውእቶን - ይደነግፃ - ይፈራሉ

6. ሤመ ፡ ሾመ

አነ- እሠይም- እሾማለሁ
አንተ - ትሠይም - ትሾማለህ
አንቲ - ትሠይሚ - ትሾሚያለሽ
አንትሙ.- ትሠይሙ - ትሾማላችሁ
አንትን - ትሠይማ - ትሾማላችሁ
ንሕነ - ንሠይም - እንሾማለን
ውእቱ - ይሠይም - ይሾማል
ይእቲ - ትሠይም - ትሾማለች
ውእቶሙ - ይሠይሙ - ይሾማሉ
ውእቶን - ይሠይማ - ይሾማሉ

ማሳሰቢያ:- የተመለከትነው ርባታ በሕጋውያን ግሶቹ /Regular verbs/ ነው።

## ማጠቃለያ

| መጽአ = መጣ | ቅጥያዎች | የካልአይ ቅጥያዎች |
|---|---|---|
| አነ- እመጽእ- እመጣለሁ | እ-እ /የግእዝ/ | እ...ለሁ. /የአማርኛው/ |
| አንተ- ትመጽእ- ትመጣለህ | ት... እ /አናባቢ/ | ት... ለ.ህ |
| አንቲ- ትመጽኢ- ትመጫለሽ | ት... ኢ /አናባቢ/ | ት... ጫለሽ |
| አንትሙ - ትመጽኡ - ትመጣላችሁ | ት.... ኡ » | ት.... ላችሁ |
| አንትን - ትመጽኣ - ትመጣላችሁ | ት... ኣ » | » |
| ንሕነ - ንመጽእ - እንመጣለን | ን.... እ » | እን .... ለን |
| ውእቱ - ይመጽእ - ይመጣል | ይ.... እ » | ይ..... ል |
| ይእቲ - ትመጽእ - ትመጣለች | ት.... እ » | ት.... ለች |
| ውእቶሙ - ይመጽኡ - ይመጣሉ | ይ... ኡ » | ይ..... ሉ |
| ውእቶን - ይመጽኣ - ይመጣሉ | ይ.... ኣ » | » |

የቅጥያዎቹ ዝርዝር አንዳንዴ እንደ ቤቱ ይለያያል።

ምልማድ

ትእዛዝ:- የሚከተሉትን አናቀጽ እንደ ቤቱ ወደ ካልአይ በመለወጥ የሚስማማውን ምረጥ/ጪ። ለግንዛቤ ያህል የሚጠብቁትን ግሶች እንለያለን።

1. አንተ ትዜምር መዝሙረ ካለ አነ ______________ ላዕለ ዐራትየ
 ሀ. እነውም ለ. ኖምኩ ሐ. ትነውም መ. ይነውም
2. ትቀውም ማርታ ቅድመ ቤተ መቅደስ ካለ ______________ አስቴር ቅድመ አቡሃ
 ሀ. ይደነግፃ ለ. ትደነግፂ ሐ. ይደነግፁ መ. ደንገፀት ሠ. ትደነግፅ
3. ይመጽእ ዮሐንስ ኀበ ታቦር ካለ ______________ ኤልያስ ንጉሠ በላዕሌነ
 ሀ. ይሠይም ለ. ይሤም ሐ. ሤመ መ. ይሠይሙ
4. ______________ እንስት ኀበ መስቀሉ ለኢየሱስ
 ሀ. ቆማ ለ. ይቀውማ ሐ. ቆምክን መ. ሐ ወ ለ ሠ. ሁሉም
5. ቅድሜከ እግዚኦ ______________ ወንሴብሐከ
 ሀ. ንሰግድ ለ. እሰግድ ሐ. ይሰግድ መ. ይሰግዱ ሠ. ሰገድነ
6. አሜሃ ይመጽእ ክርስቶስ ካለ አሜሃ ______________ ፍሥሐ
 ሀ. ኮነ ለ. ይከውን ሐ. ይኩን መ. ንከውን
7. ወ______________ዮም በትሕትና በቅድመ ዝንቱ ምሥጢር ግሩም
 ሀ. ንቀውም ለ. እቀውም ሐ. ትቀውም መ.ሁሉም
8. ተከዘ= ተከዘ፣ አዘነ። ተከዘ የጠበቀ ግስ ነው።
 ለምንት ______________ ነፍስየ።
 ሀ. ትቴክዚ ለ. ተከዝኪ ሐ. ተከዘት መ. ተከዛ ሠ. ሁሉም
9. አምላክነሰ ኃይልነ ወጸወንነ ውእቱ በእንተዝ
 ሀ. ንፈርህ ለ. ኢንፈርህ ሐ. ፈራህነ መ. ፈራህኩ
10. ተወከል ቦቱ ወውእቱ ______________ ለከ
 ሀ. ገብረ ለ. ይገብር ሐ. ንገብር መ. ገብረ
11. ምስለ ጻድቅ ትጸድቅ ወምስለ ኅሩይ ኅሩየ ______________
 ሀ. ትከውን ለ. ኮንከ ሐ. ቸከውኒ መ. ኮንክሙ
12. ትፀንሲ ወ______________ ወልደ
 ሀ. ወለድኪ ለ. ትወልዲ ሐ. ወለደት መ. ትወልድ

ይቆየን።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

## ለአገር ዕድገት እና ልማት ...

/ከገጽ ፱ የዞረ/

ለማጠቃለል ያህል፡- ይህ እያገባደድነው የመጣነው የ1998 ዓ.ም፣ መጪው 1999 ዓ.ም. ለእኛ ለኢትዮጵያውያን ብዙ ትርጉም ይኖረዋል። ይኸውም አንድ ሙሉ ክፍለ ዘመን አጠናቀን አዲሱን ክፍለ ዘመን 2000 ዓ.ም ለመቀበል የምንዘጋጅበት፣ ያለፈውን ክፍለ ዘመንን አዎንታዊ እና አሉታዊ ገጽታ የምናይበት፣ ለመጪው ካሁኑ የምንተልምበት እጅግ ታሪካዊ ጊዜ ላይ እንገኛለን።

የበለጸጉ ሀገራት በእጃቸው ያለውን መልካም እሴት ሁሉ በተገቢው ሁኔታ እየተጠቀሙበት አሁን ላሉበት የዕድገት ደረጃ ደርሰዋል። ለኢንዱስትሪያዊ አብዮት የእንግሊዝ የእምነት ተቋማት በዘውዳዊው እና ፓርላማዊ የመንግሥት ሥሪት መሐል ዘመናዊ መንገድ የማሳየት ሚና እንደ ተጫወቱ ሁሉ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አሁን ልንሸጋገረው ባልነው ክፍለ ዘመን የኋላ ሒደቷን፣ የመጪውን ማኅበረሰባዊ የዕድገት ደረጃ እና ተለዋዋጩን ዓለም አቀፋዊ ሁኔታ ከግንዛቤ ውስጥ ባስገባ መልኩ በሀገሪቱ የልማት ዕቅድ ቀረጻ እና ትግበራ ብሎም አዳዲስ ገንቢ ሐሳቦችን የማፍለቅ ሚናዋን መጫወቻዋ ወሳኝ ወቅት ላይ ትገኛለች። በተለይም የመጪው ክፍለ ዘመን ፈታኝ ሁኔታዎች ተብለው የሚጠቀሱት ድህነት ተስማሚና ዘላቂነት ያለው የአካባቢ ጥበቃ አለመኖር፣ ሽብርተኝነት፣ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መስፋፋትና የመሳሰሉት ዐበይት መንፈሳዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ለአገሮች ዕድገት ማነቆዎች እየኾኑ መምጣታቸው የተገለጠ እውነት ነው። እኒህ ፈርጀ ብዙ ችግሮች ከአዳጊው ዓለም አልፈው ለበለጸጉትም እንደ ሚተርፉ ስለሚታወቅ በልማት የገፉት አገሮች ጭምር በኅብረተሰቡ ዘንድ ሰፊ መሠረት ከያዘ ተቋም (እንደ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን) ጋር በትብብር መሥራት የብዙ የልማት ሒደት ችግሮች መፍቺያ ቁልፍ እንደ ሆነ ከተገነዘቡ ቆይተዋል።

ስለሆነም አባቶች ጳጳሳት፣ አገልጋይ ካህናት፣ ምእመናን፣ መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት፣ የሲቪክ እና ሞያ ማኅበራት በቅን መንፈስ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሀገሪቱ ዋነኛ የልማት አጋር መሆኗን ከልብ በማመን፣ የነበሯትን፣ ያሏትን ዘርፈ ብዙ ዕሴቶችንና መልካም ጅምሮችን በማዳበር በቀጣይም ለዕድገት እንቅፋት የሆኑ አለመግባባቶችን ሁሉ ተደማምጦ በመፍታት አዲሱን ክፍለ ዘመን በርእይ ሥምረት፣ በመንፈስ ዕርገት ለመቀበል ተቀናጅተው በአንድ ጊዜና በአንድ ላይ መነሣት ይኖርባቸዋል እንላለን።

የዚህ ጽሑፍ ይዘት በተሻለ መልኩ እንዲወጣ አስፈላጊውን ሞያዊ ምክርና የጽሑፍ ምንጮች በመስጠት የተራዱንን የግብርና ኢኮኖሚክስ ባለሞያና ተመራማሪውን ዶ/ር ዕድለኛው ዋሌን፣ በኢት/ኦ/ተ/ቤ/ክን የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን የጤና እና የማኅበራዊ ጉዳዮች ከፍተኛ አማካሪ ዶ/ር መስፍን ተገኝን፣ የዕቅድ ፖሊሲ ዝግጅትና ግምገማ መምሪያ ሐላፊን አቶ አደሬ አዱኛን በእጅጉ እናመሰግናለን። በተጨማሪም የምጣኔ ሀብትና የማኅበራዊ ሳይንስ መስኮች ባለሞያዎቹን ወ/ሮ ክብነሽ መቺሳን፣ ወ/ሪት ገነት ከበደን፣ አቶ መስፍን ጥላሁንን፣ አቶ መስፍን ነጋሽን፣ መ/ር ቴዎድሮስ በየነንና መ/ር እሸቱ ጌታሁንን ከፍ ያለ ልባዊ ምስጋናችንን እናቀርብላቸዋለን። ♦



www.eotcmk.org

# «መዝሙርና የመዝሙር ግብይት»

*የተወደዳችሁ አንባብያን፥ በ14ኛው ዓመት ቁጥር ሁለት መጋቢት/ሚያዝያ 1998 ዓ.ም እትማችን ዓምደኞችን «መንገደኛው» እና ሌሎች አራት ተሳታፊዎች በወቅቱ የመዝሙር ካሴቶች ይዘትና ሽያጭ ሁኔታ ላይ በማተኮር ትዝብታቸውንና አስተያየታቸውን መሰንዘራቸው ይታወሳል:: ይህን ተከትሉም በርካታ ደብዳቤዎች ለዝግጅት ክፍላችን ደርሰዋል:: ከደብዳቤዎቹ መካከል እንደ «መንገደኛው» ሁሉ የየራሳቸውን ትዝብት በስፋት የጻፉልን አሉ:: ከቦታ ጥበት እና ከተመሳሳይነታቸው አንጻር ሁሉንም ባሉበት ኹኔታ ለማስተናገድ ባለመቻላችን ይቅርታ እየጠየቅን በሚከተለው መንገድ ጭምቅ ሐሳባቸውን ያቀረብን መኾናችንን እንገልጻለን::*

## መልካሙን አገልግሎት የሚቃወም የቤተ ክርስቲያናችን ወገን አይደለም!!

በመጋቢት/ሚያዝያ 1998 ዓ.ም ለንባብ የበቃው 14ኛ ዓመት ቁጥር ሁለት የሐመር መጽሔት እትም የጀርባ ሽፋን የውስጥ ገጽ ላይ «መንገደኛው» ኃ/ገብርኤል ዘሐና «አዲሱ የመዝሙር ገበያ» በሚል እና እነ መ/ር ብርሃኑ ይመር «ለአገልግሎት ወይስ ለቢዝነስ?» በማለት የጻፉትን ትዝብት አንብቤ አዘንኩኝ፤ አሳስፈላጊ አገላለጾችን ተጠቅመዋል:: ነባቂ ተኩላዎች በቅርብ ርቀት ኾነው ምእመናንን ለመንጠቅ አሰፍስፈው በሚጠብቁበት ወቅት «እምን መዝሙር በየአካባቢው ተዘመረ?» ብሎ መተቸት ከቶ ለምንድን ነው? ተኩላዎችን ማበረታታት ይመስለኛል:: ዛሬ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ልጆችዋን ብቻ ሳይሆን ሌሎችንም ወደ እውነተኛና መጀመሪያዪቱ ሃይማኖት ለማምጣት ወንጌል በመስበክ ላይ ትገኛለች::

ቅዱስ ወንጌል በተለያየ መንገድ ለዓለም ይሰበካል፤ የሚሰበክበትም አንዱ መንገድ መዝሙር በመዘመር ነው:: በስም ብቻ ክርስቲያን የነበሩ፣ የቤተ ክርስቲያናችንን መግቢያ በር የማያውቁ አንዳንድ ሰዎች በሚያስገርምና በሚያስደንቅ ሁኔታ ፊታቸውን ወደ እርሷ አዙረዋል:: የቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ቅጥር ግቢ በምእመናን አሸብርቋል:: ምክንያቱም በተለያዩ ተሽከርካሪዎች ላይ ሞንታርቦ /የድምፅ ማጉያ/ ጭነው በየሥፍራው በመዘዋወር በመዝሙር አማካይነት በሚሰበከው ወንጌል ነው::

እርግጠኛ ነኝ ከዚህ ቀደም የመዝሙር ካሴት የሚያዳምጠው ምእመን ቁጥር እብዛም ነበር:: ዛሬ ግን የዘማርያን አገልግሎታቸውን ይባርክልንና አብዛኛው ምእመን የመዝሙር አድማጭ ሆኗል:: ምናልባት ግን ያዳመጠ ሁሉ ቃሉን ይተገብራል ማለት አይደለም:: ቢያንስ እንኳን ፈሪሃ እግዚአብሔር ያድርበታል፤ ሌላውን ለእግዚአብሔር እንተወው::

እነ ኃ/ገብርኤል ዘሐና፦ በእውነት ለቤተ ክርስቲያናችን ተቆርቁራችሁ ነው የእግዚአብሔር ቅዱስ ቃል ከአንደበታቸው የሚወጣ ዘማርያንን «ሥራ አጥ ቦዘኔ ከሚባል ነው ካሴት የሚያወጣው» ለማለት የደፈራችሁት? እስኪ ያሳያችሁ፥ ለአንድ አፍታ የጻፋችሁትን ትችት አስተውሉት፤ ለተቃራኒው ወገን በር የሚከፍትና የሚያስተች ነው:: ስለዚህ «የራስህን ጉድፍ ያላወጣህ የሌላውን ጉድፍ የምታወጣ አንተ ማነህ?» ይላል የእግዚአብሔር ቃል፤ አስቡት፤ አምላካችን ይቅር ባይ ነውና ለሁላችንም ይቅርታውን ያድለን::

ሌሎቹ አስተያየት ሰጪዎች ያነሡት ነጥብ መዝሙር «ለአገልግሎት ወይስ ለቢዝነስ» የሚል ነው:: ቅዱስ መጽሐፍ «በላብህ በወዝህ ጥረህ ግረህ ብላ» ይላል:: ዘማርያኑ ቁጭ በማለት አንዳችም የሚያመጡት ነገር የለም:: በመንፈሳዊ አገልግሎት እያገለገሉም የዕለት ጉርሳቸውን ለማግኘት መሥራት ይጠበቅባቸዋል:: ማናችንም ብንኾን ገንዘብ የሚገኝበትን ሥራ እየሠራን ኑሯችንን እየኖርን ነው:: ምክንያቱም እኛም ዘማርያንም ለእግዚአብሔር እኩል ነን:: ስለዚህ ጊዜአቸውን የሚያሳልፉት በየአገልግሎቱ ስፍራ በማገልገልና መዝሙር በማውጣት ስለሆነ በሠሩት የመዝሙር ካሴት መጠቀም አለባቸው::

*«በየአብያተ ክርስቲያናቱ በራፍ በመቆም፣ በተሽከርካሪ መኪና ላይ ሞንታርቦ በመጫን፣ በቅዳሴ ሰዓትና የሠርክ ትምህርት በሚሰጥበት ወቅት መዝሙር በመክፈት ምእመናን እንዳይገለገሉ እያደረጉ ናቸው»* ለተባለው በእርግጥ በዚያ ወቅት ይህ ድርጊት ከተደረገ ስሕተት ነው:: እያንዳንዱ ሕዝበ ክርስቲያን ድርጊቱን ተባብሮ ሊያስቆም ይገባዋል:: እኔ በአለሁበት በአዋሳ ከተማ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን በቅዳሴና በሠርክ ጉባኤ ወቅት ሚኒባስ ታክሲው ሞንታርቦ እንደ ጫነ ይቆማል:: ጸሎተ ቅዳሴውና የስብከተ ወንጌል አገልግሎቱ እንዳበቃ የተጫነው ሞንታርቦ አገልግሎቱን ይጀምራል፤ ምእመኑም የመዝሙር ካሴቱን እየገዛ ወደ ቤቱ በረከት ይዞ ይገባል:: ቅዱስ ዳዊት፦ «በምድር ያላችሁ በሙሉ ለእግዚአብሔር እልል በሉ፥ ዘምሩ» እንዳለው ከዚህ ባለፈ በቅዳሴና በስብከተ ወንጌል አገልግሎት ጊዜ የመዝሙር ካሴት የሚከፍት ካለ የአጥቢያ አቢያተ ክርስቲያናቱ አስተዳደር አካላት መቆጣጠር አለባቸው:: የምንተቻችባቸው ብዙ ሌሎች ጉዳዮች አሉኮ፤ ከላይ የገለጽኳቸውን መልካም ነገሮች ወይም አገልግሎትን የሚቃወም ግን የቅድስት ቤተ ክርስቲያን ወገን አይደለም:: እነዚህን ዘማርያን ማበረታታት ይጠበቅብናል:: ለዛሬ አበቃሁ:: እናንተ የመጽሔት አዘጋጆች አገልግሎታችሁን እግዚአብሔር ይባርክላችሁ:: የእግዚአብሔር አብ ጸጋ፣ የእግዚ አብሔር ወልድ ቸርነት፣ የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ አንድነት፤ የእመቤታችን አማላጅነት፤ የጻድቃን ሰማዕታት ተራዳኢነት ከሁላችን ጋር ይሁን:: አሜን::

አብነት ገብሩ
አዋሳ

## «ጥፉ፥ ጥፉ» ያሰኛል

በሴቶች ልማድ ወቅት ሥርዐተ ቤተ ክርስቲያንን የምንከታተለውና የምንፈጽመው በደጅ ቆመን ነው:: ታድያ በተለይ በክብረ በዓላት ቀናት መግቢያ ቀዳዳ እስኪጠፋን ድረስ በድምፅ ማጉያ ታግዞ በጆሮአችን ላይ የሚያንባርቀው «አዲሱ የመዝሙር ካሴት ገበያ» ለማስቀደስና ታቦቱን ለማክበር ቀርቶ ለደቂቃ እንኳን የማያስቆም በመኾኑ ከቦታው ጥፉ፥ ጥፉ ያሰኛል:: ይህንም እናቶችና እኅቶች ከሚያሰሟቸው የእሮሮና የብስጭት ንግግሮች መረዳት ይቻላል:: ታቦቱን አቁሞ መዝሙር እየዘመሩ «የእገሌ ካሴት ነውና ግዙ» በማለት በዐውደ ምሕረቱ የንግድ ቅስቀሳ ማድረጉስ ተገቢ ነው ወይ? በዚህ ሳቢያ ይመስላል የቅጽረ ቤተ ክርስቲያን ዙሪያ የገበያ መናኸሪያ ከመኾኑ የተነሣ *«ምርጥ ዕቃ ስትፈልጉ በንግሥ ቀናት ወደ ቤተ ክርስቲያን ሂዱ»* እስከ መባል ተደርሷል:: እውነት ችግሩ የተባባሰው ቤተ ክርስቲያናችን ሥርዐት ለማስከበር አቅም ሳይኖራት ቀርቶ ነውን? በምእመናንም በኩል በቤተ ክርስቲያን አካባቢ የሚሸጡ ዕቃዎችን ከመግዛት ብንቆጠብ እኮ ሻጮቹ ትክክለኛ ቦታቸውን ይፈልጋሉ:: እስኪ ለማንኛውም እናስብበት::

አልማዝ - ጉለሌ

## ኹኔታው ከተገለጸው በላይ ነው

በ14ኛ ዓመት ቁጥር ሁለት መጋቢት/ሚያዝያ 1998ዓ.ም እትም በጀርባ ሽፋን የውስጥ ገጽ በመንገደኛውና በሌሎችም ተሳታፊዎች የቀረበው ጽሑፍ የውስጤን ስሜት የዳሰሰ በመኾኑ አስደስቶኛል:: የመዝሙራችን ይዞታና ወቅታዊ «የገበያ ሁኔታ» በተለይም በክልልና በወረዳ ከተሞች ከተገለጸውም በላይ ነውና የሚመለከተው ክፍል ቢያስብበት መልካም ነው:: መናፍቃኑም፦ -«ኦርቶዶክሶች በየመንገዱ የሚያስተዋውቁት መንፈሳዊ መዝሙር ቤት ስለሌላቸው ነው» እያሉ እስከ መሳለቅ ደርሰዋል:: በጣም ያሳዝናል:: ስለዚህም ከዘማርያኑና ከሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ጋር ተቀራርቦ በመወያየት ረገድ ያሉ አንዳንድ ጅምሮች ተጠናክረው መቀጠል ይኖርባቸዋል:: በእናንተም በኩል ቢኾን ይህን ጉልህ ችግር በተቆራረጠ መልኩ በሽፋን ገጽ ላይ በማስፈር ብቻ የተጣለባችሁን ሐላፊነትና ግዴታ በበቂ ትወጡታላችሁ ብዬ አላስብም፤ አቀራረባችሁ ትኩረታችሁን ያሳያልና::

*ላቀው አመነሸዋ፣ ሸዋዬ ከበደ /ኢ.ኢ/፣ ውብ ዓለም በለጠ /ቤሩት/፣ ዐጸደ ማርያም /ሸና/፣ ዲ/ን ተመስገን ዘዋ /ወረታ/፣ ንጉሤ መብራቱ /ጋምቤላ-ፒኝውዶ/ ፣አልማዝ ሊታ እና መሠረት ግርማ /አሶሳ/ ::*

## መፍትሔው መነታረክ ሳይሆን ማስተማር ነው

በአዲሱ የመዝሙር ገበያ ዙሪያ የተፈጠረውን ችግር ለመፍታት መፍትሔው ከዘማርያኑ ጋር እሰጥ እገባ ዓይነት ሙግት ውስጥ መግባትና እርስ በርስ በመጽሔትና ጋዜጣ መተቻቸት አይደለም:: ይልቁንም ምእመኑን ስለ ያሬዳዊ መዝሙር ምንነት፣ ሥርዐትና አዘገጃጀት በዐውደ ምሕረት የሠርክ መርሐ ግብሮችና በሰንበት ትምህርት ቤቶች ሳያሠልሱ ማስተማር የተሻለ ነው::

*ዲ.ን ዮርዳኖስ ተክሥተ-ህገረ ግራርያ*




www.eotcmk.org

©

!"   #$   %
& '   (   )   *   $++